# የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ትንተና

በ

ደመቀ ጀንበሬ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒትስ ኮሌጅ ድህረ ምረቃ ትምህርት
ቤት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ -አማርኛ ትምህርት ክፍል
ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና
ፎክሎር ድህረ ምረቃ ዘርፍ

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ኤም.ኤ.ድግሪ  ከፊል ማሟያ የተቀረበ ጥናት

ሰኔ 2011 ዓ.ም.

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒትስ ኮሌጅ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ -አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና

ፎክሎር ድህረ ምረቃ ዘርፍ

# የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ትንተና

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ኤም.ኤ.ድግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ደመቀ ጀንበሬ

አማካሪ፡- ዶ/ር ለማ ንጋቱ

ሰኔ 2011 ዓ.ም.

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ትንተና

ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒትስ ኮሌጅ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ -አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና

ፎክሎር ድህረ ምረቃ ዘርፍ

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ኤም.ኤ.ድግሪ ከፊል ማሟያ የተዘጋጀ ጥናት

በ

ደመቀ ጀንበሬ

ሰኔ 2011 ዓ.ም.

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ለኤም.ኤ.ድግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ----------------------------------------ፊርማ------------------------ቀን-----------------------

የውስጥ ፈታኝ------------------------------------ፊርማ---------------------------ቀን---------------------
-

የውጭ ፈታኝ--------------------------------------ፊርማ----------------------------ቀን------------------

## ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ማውጫ.....i

ምስጋና.....vi

አጠቃሎ.....vii

አበርክቶ.....viii

መግለጫ.....x

ሙዳየ ቃላት.....xi

ምዕራፍአንድ.....1

1. መግቢያ.....1

1.1. የጥናቱ ዳራ.....2

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.....4

1.3. የጥናቱ ዋና ዓላማ-,.....5

1.4. የምርምር ጥያቄዎች.....6

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ.....6

1.6 የጥናቱ ወሰን.....7

. 1.7 የመስክ ተሞክሮ.....8

1.8. ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎች.....11

ምዕራፍ ሁለት.....13

2. የየም ብሄረሰብ ታሪካዊ ፣መልክዓምድራዊ ና ማህበረ- ባህላዊ ዳራ.....13

2.1. የየም ብሄረሰብ ታሪካዊ ዳራ.....13

2.1.1.ስያሜ.....13

2.1.2. የየም ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ.....16

2.2. መልከዓምድራዊ ገጽታ........................................................................17
2.1.1. ቋንቋ..........................................................................................18
2.1.2. የህዝብ ብዛት..................................................................................19
2.2.3. ኢኮኖሚያዊ መሰረት...........................................................................20
2.3. ማህበረ-ባህላዊ ዳራ..............................................................................20
2.3.1. የአስተዳደር ስርዓት)............................................................................20
2.3.2. እምነት........................................................................................21
2.3.3. ጋብቻ..........................................................................................22
2.3.4. ባህላዊ ምግቦች................................................................................23
ምዕራፍ ሶስት......................................................................................24
3. ክለሳ ድርሳናት...................................................................................24
3.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔዎች...........................................................................24
3.1.1.ሀገረሰባዊ ልማድ................................................................................24
3.1.2.ለቅሶ..........................................................................................24
3.1.3.ለቀስተኛ.......................................................................................25
3.1.4.ስርዓተ ቀብር...................................................................................25
3.1.5.ሙሾ..........................................................................................26
3.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት..............................................................................26
3.2.1. መሰረተ ባህላዊ ሞዴል (Infracultural model)...................................................27
3..2.1.1. ስርዓተ ከበራ(Ritual).......................................................................28
3.2.1.2. ክዋኔ.......................................................................................30
3.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት..........................................................................34
ምዕራፍ አራት......................................................................................42
4. የጥናቱ ስነ ዘዴና ንድፍ..........................................................................42
4.1. የጥናተቱ ስነ ዘዴ...............................................................................42
4.2.የጥናቱ ዘዴ......................................................................................42

4.2.1. የመረጃ ምንጮችና የንሞና ዘዴ..........................................................44
4.2.2. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ..........................................................45
4.2.2.1. ምልከታ..........................................................45
4.2.2.2. ቃለ መጠይቅ..........................................................46
4.2.2.3. ተተኳሪ ቡድን ውይይት..........................................................47
4.2.2.4. ሰነድ ፍተሻ..........................................................47
4.3. የመረጃ አደረጃጀትና ትንተና..........................................................48
4.3.1. የመረጃ አደረጃጀት..........................................................48
4.3.2. የመረጃ ትንተና ..........................................................49
ምዕራፍ አምስት..........................................................51
5. የመረጃ ትንተና ..........................................................51
5.1. የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ትንተና..........................................................51
5.1.1.ቅድመ ሞት ክወና ስርዓቶች..........................................................53
5.1.2. ጊዜ ሞት ክወና ስርዓቶች..........................................................58
5.1.3. ድህረ ሞት ክወና ስርዓቶች..........................................................65
5.1.3.1.ቅድመ ቀብር ስርዓቶች..........................................................66
5.1.3.1.1.ቴሻ (የለቅሶ)ስርዓት ..........................................................68
5.1.3.1.1.1.የሴቶች ቴሻ(ለቅሶ) ስርዓት..........................................................73
5.1.3.1.2. የወንዶች የቴሻ ስርዓት..........................................................75
5.1.3.1.2. የዚዛ (የሙሾ)ክወና ስርዓት ..........................................................91

5.1.3.2. ጊዜ ቀብር ስርዓት……………………………………………………………111

5.1.3.3. ድህረ ቀብር ክወና ስርዓቶች ………………………………………...114

ምዕራፍ ስድስት……………………………...............................122

6. የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት…………………………………………..........122

6.1. የጥናቱ ማጠቃለያ………………………………..............................122

6.2. አስተያየት…………………………………………..................................126

ዋቢዎች………………………………………………………………………..128

አባሪ አንድ…………………………………………………........................132

አባሪ ሁለት………………………………………………………………………135

አባሪ ሶስት……………………………………………………………............138

አባሪ አራት………………………………………………………………………139

አባሪ አምስት……………………………………………………………...........142

አባሪ ስድስት……………………………………………………………………152

አባሪ ሰባት………………………………………………………………………153

## ማረጋገጫ

የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ትንተና በሚል ርዕስ  በጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒትስ ኮሌጅ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ -አማርኛ ትምህርት ክፍል የኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ኤም.ኤ.ድግሪ ማሟያነት ያዘጋጀሁት ይህ ጥናት የእኔ ስራ መሆኑን እና በጥናቱ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎች ምንጭ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡-----------------------------------------------------------

ፊርማ፡---------------------------------------------------------

የማስረከቢያ ቀን፡------------------------------------------------

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ የዚህ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚ እንድሆንና ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ እንዳካሂድ ያስቻለኝን የማምነው አምላክ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ በማስቀጠል ከማስተማር በተጨማሪ በህይወት ልምዳቸው ያካበቱትን ዕውቀት ሳይሰስቱ በማካፈልና ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ለዚህ እንዲበቃ በማማከርና በማረም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱልኝ አማካሪዬ ዶ/ር ለማ ንጋቱ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

የየም ልዩ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የቀድሞ ኃላፊ አቶ ሀብታሙ ዘውዴ ለባህል ልማት ካላቸው ጉጉት የተነሳ የፎክሎር ትምህርት በሁለተኛ ድግሪ እንድከታተል ሀሳብ ከመለገስ ጀምሮ በቅን ልቦና የስፖንሰርነት ሁኔታዎችን በማመቻቸት ያበረከቱልኝን አስተዋጽኦ የማልረሳው ነው፡፡ እንዲሁም ይህን ትምህርት ሳልቸገር እንድከታተል የወር ደመወዜ እየተከፈለኝ እንድማር ያደረገኝ በደቡብ ሬዲዮና ቴሌቭዥን ድርጅት ለወልቂጤ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የፎቶ ካሜራህን በፍጹም ቅንነት በማዋስ ስራዬን ባግባቡ እንድሰራ የተባበርከኝ አለማየሁ ዲጋ ከልብ ምስጋናዬ ወደር የለውም፡፡

ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ አስፈላጊውን መረጃ እንዳገኝ በማድረግ የተባበራችሁኝ የየም ልዩ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት ባልደረቦች አስተዋጽኦአችሁ የማይዘነጋ ነው፡፡ ትምህርቴን ከገበታው ተከታትዬ እንዳጠናቅቅ ያደረገኝ የጅማ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናው ከፍ ያለ ነው፡፡

ለስራዬ አጋዥ የሚሆኑ የተለያዩ የጥናት ጽሁፎችን ከቤተመጽሐፍት እንዳነብ በቅንነት ተቀብሎ ያስተናገደኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን እንዲሁ አመሰግናለሁ፡፡

ትምህርቴን በተገቢው ተከታትዬ እንዳጠናቅቅ የሞራል ድጋፍ በመስጠት ልጃችን መክሊት ስትታመም እንኳ እስከ ሆስፒታል ድረስ በመንከራተትና ማህበራዊ ኃላፊነትን በሙሉ ብቻሽን በመሸከም ለትምህርቴ ስኬት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተሻልና ባለቤቴ ነጻነት ንጋቱ ትልቅ ምስጋና ይገባሻል፡፡

ጥናቴን በስኬት እንዳካሂድ በቅን ልቦና ከሀሳብ ጀምሮ መረጃ በመስጠት የተባበራችሁኝ በሙሉ ከልብ አመሰግናለችኋለሁ፡፡

## አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ትንተና በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው በየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስነ ስርዓት ላይ ነው፡፡ የጥናቱ አላማ የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ላይ ገላጻዊ ትንተና በማድረግ ስርዓቱን ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ ኢትኖግራፊዊ ሲሆን አላማውን ለማሳካት በዋናነት ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ፣ የሰነድ ፍተሻ እና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ተካሂዷል፡፡ በሁለት ተፈጥሯዊ የለቅሶ መቼቶች ላይ በመገኘት መረጃው ተሰብስቧል፡፡ ጥናቱ በመሰረተ ባህል ሞዴል ንድፈ ሀሳብ የተቃኘ ነው፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረት የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት በእድሜ፣ በጾታና በማህበራዊ ደረጃ እንዲሁም በብሄረሰቡ ዘንድ የፈጣሪ ቁጣ ነው ተብለው በሚታመኑ ህመሞችና አደጋዎች በሚከሰት ሞት ምክንያት የተለያዩ የለቅሶ ክዋኔዎች መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከማህበራዊ ደረጃ አንጻርም ሚች ንጉስ፣የጎሳ መሪ፣ ጀግና፣ የዕድሜ ባለጸጋ ከሆኑ የሚከወንላቸው የለቅሶና የዚዛ (ሙሾ) ስርዓቶ የሚችን ተግባርና ማንነት የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔውን ከዕድሜ እንዲሁም ከጾታ አንጻር ሲታይ የአባ ወራ ወይም የእማ ወራ ቀድሞ መሞት ኪኖ (ቡሉኮ) የሚቀመጥበትን ቦታ እንደሚወስንና በዚዛ (ሙሾ) ክወናውም ውስን ልዩነቶች እንዳሉት ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ የለቅሶ ስርዓቱ በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን አጣምሮ የያዘ ነው፡፡ በየም ብሄረሰብ በለቅሶ ስርዓት ማንነትና ማህበራዊ ትስስርን የሚያጠናክሩበት እና የሚገነቡበት፣ እንዲሁም የማህበረሰቡን ታሪክ፣ እምነትና አመለካከት የሚገልጹበት አጋጣሚ እንደሆነ ግኝቱ ያሳያል፡፡ በብሄረሰቡ እምነት መሰረት ሞት በአካለ ስጋ ከመኖር በመንፈስ ወደ መኖር መሸጋገሪያ እንጂ የህይወት ፍጻሜ አይደለም፡፡ ነፍስ ሙት ከሆነው ስጋ ሲለይ ወደማይታወቅ ዘላለማዊ ስፍራ ሆኖ ከወገኖቹ ጋር በመንፈስ ወደሚገናኝበት ምዕራፍ የሚሸጋገርበት ነው፡፡  በለቅሶው ክዋኔ ላይ በሚቀርቡ የፎክሎር ዘውጎች የሚተላለፉ መልዕክቶች እና ትርጓሜዎች በጥናቱ ውስጥ ተተንትነዋል፡፡ የለቅሶ ስርዓት ክወናው በአስተዳደር ስርዓት መለወጥና በተለያዩ ምክንያቶች በተለይ የዚዛ ስርዓተ ክወናው የመዋሀድ፣ ፈጽሞ የመጥፋት፣ የመጨመርና የመተካት ለውጦች ተስተውሎበታል ፡፡ በነዚህ ምክንያቶች  ከለቅሶ ስርዓት ክወና ጋር የተያያዙ የታሪክና የባህል መረጃዎች መዛባታቸው አይቀሬ ነው፡፡ በመሆኑም ቅርሱን በተለያዩ ዘውጎች በመመደብ ማጥናትና እንዲሰነድና እንዲቀረስ ምሁራንና የባህሉ ባለቤቶች  ድርሻ ነው፡፡

# አበርክቶ

ከየትኛውም ደረጃ ላይ ለመድረስ መንገድ በመሆን ያላችሁን ዕውቀት ያለስስት በማካፈል ብዙ ፍሬ ለምታፈሩ መምህራን ለማይከፈለው ውለታችሁ እነሆ በረከት፡፡

ያኔ ዛሬዬን ሳላውቅ ከህይወት ገጾችሽ ሳልጠይቅሽ የተለያዩ ታሪኮችን እያዝናናሽ በማካፈል ለዛሬ ማንነቴ ስብዕናዬን ስትገነቢ ለነበርሽና እንዳለመታደል ሆኖ የምኞቴን ያህል ሳልጦርሽ በሞት ለተለየሽኝ አያቴ አስካለማሪያም ዋጂ ይህንን ስራ በመታሰቢያነት ሳበረክት ከውለታሽ አንጻር ምንም አይደለም፡፡

## መግለጫ

- በዚህ ጥናት ውስጥ በውጭ ቋንቋ የተጠቀሱ ምንጮች የጥናት ዘመናቸው እንደ ግሪጎሮሳውያን አቆጣጠር የተገለጹ ናቸው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ የተጠቀሱት ምንጮች በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የተገለጹ ሲሆን ይህን ለመለየት ዓ.ም. ከፊት ለፊታቸው ተመላክቷል፡፡
- ምንም እንኳ የምኛ ቋንቋ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ድረስ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት የላቲን የአጻጻፍ ስርዓትን በመከተል ህጻናት በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚማሩት ቢሆንም የልዩ ወረዳው የስራ ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡ በመሆኑ በዚህ ጥናት ውስጥ የመገኛ ቋንቋ ቃላትን ጭምር በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፍ ተጠቅሜአለሁ፡፡

## ሙዳዬ ቃላት

የቃላቱ ፍች የተሰጠው በጥናታዊ ጽሁፉ አውድ ላይ በመመስረት ነው ፡፡

| የየምኛ ቃላት | | የአማርኛ ፍቺ |
|---|---|---|
| ዚዛ | = | በየም ብሄረሰብ በተለያዩ ቁሳቁሶች ታጅቦ የሚከወን ሙሾ |
| ካሞ | = | ሟች እጅግ እንዲታዘንለትና ሙሾው እንዲደምቅ በጩኸት ስሜታቸውን የሚገልጹ የሟች ሴት ልጆችና እህቶች ቡድን |
| ጎኑ | = | ከሾላ/ኮርች ግንድ ተቦርቡሮ የሚዘጋጅ የአስክሬን በቅበሪያ ሳጥን |
| ካብጉኒ ካማ | = | የትልቅ ሰው ሞት የሟች መኖሪያ ቤት ላይ የሚነጠፍና መከፈኛ 12 ክንድ የሸማ ልብስ(ከቡሉኮ የሚበልጥ) |
| ቤራ | = | ለእያንዳንዱ የየም ጎሳ አባላት በቋሚነት የሚዛመዱና መንፈሳዊ ጉዳዮችን የሚያስፈጽሙ የሸክላ ስራ ባለሙያዎች |
| አው | = | የእንሰት ችግኝ |
| ደዶ | = | ነጎድጓድ |
| ሄቦ | = | ከመስከረም 17 ጀምሮ ከሳምንት በላይ የሚከበር የየም ብሄረሰብ ዘመን መለወጫ በዓል፡፡ |
| ሞጋ | = | መቃብር |
| ሙኒሞጋ | = | የስጋ ደዌ ታማሚ መቃብር |

| | | |
|---|---|---|
| ፊሎ | = | መዝለል፣ መወዛወዝ፣ ማሽብሽብ (ለዚዛ ክወና) |
| ሾሮዶ | = | ከእንሰት ኮባና ቀርከሃ የሚሰራ እንደሳጥን ለልብስ ማስቀመጫነትና ለዚዛ ክወና ከመሬት ጋር እየተጋጨ ድምጽ የሚሰጥ |
| ታላ | = | የማግ ክር |
| ኮባና | = | ለደቦ ስራና ለበዓላት በወፍራሙ የሚጋገር ቆጮ |
| አታ ከጃ | = | ለዓመት እንዲጠነቀቅ የታዘዘን ስርዓት ጠብቆ መድረና ስርዓቱን መፈጸም |
| ጌሪያ | = | በአማችነት ትስስር ለደስታም ይሁን ለሀዘን ደራሽ ቡድን |
| ጉዶ | = | ከስንደዶ የሚሰራና እንስራ የእንስራ ቅርጽ ያለው ለቦርዴ ማመላለሻነትና ለዚዛ ክወና የምት የሙዚቃ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግል ቁስ |
| ሰላባ | | ጀግና ጀግንነቱ እንዲመሰከርለት ስለመግደሉ ወይም ስለመማረኩ የሚያሳየው ምልክት |
| ጌባ | | ከጎሽና ዝሆን ቆዳ የሚዘጋጅ ለጦር መከላከያነትና በለቅሶ ዚዛ ክወና ከጦር ዘንግ ጋር እየተመታ በማጀብ እንደምት የሙዚቃ መሳሪያነት የሚያገለግል |
| አልባ | = | ያልተጣራ የቦርዶ(ባህላዊ መጠጥ) ድፍድፍ |
| ጋዛ | = | መናዘዝ ማለት ሲሆን ለተለያዩ ላልተለመዱ ክስተቶች ከአምላክ ጋር እርቅ መፈጸሚያ ተብሎ ቤራዎች(ሽከላ ሰሪዎች) የሚናገሩትና የሚገልጡት ቋንቋ |
| ጋላ | = | ስንቅ |
| ኪታ | = | ገዳይ መንፈስ |
| ኖሩ | = | በእሳት ለብ ብሎ የለሰለሰ የእንሰት ቅጠል |
| ማዕኖ | = | ከጎረቤት ተዘጋጅቶ የሚመጣ የዕዝን ምግብ |

ሻኒ = የለቅሶ ቤት ምግብ አዛዥ

ኦግዲ = የለቅሶ ቤት ምግብና መስተንግዶ ተቆጣጣሪ

አካኒ ኡሹ = የቀብር እለት ለለቀስተኞ ውሃ ማጠጫ ምግብ

ባቾ = ድንኳን መንቀያ ቀን ለመታሰቢያነት ከተለያየ የእህል ዓይነት የሚዘጋጅ ምግብ

ኒጹ = የትልቅ ሰው ሞት(የክብር)

ዱጊቴ = ሞቱ ለንጉስ የክብር

# ምዕራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

ይህ ጥናት በየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በዕድሜ አርጅተውም ሆነ ያለዕድሜ በተለያዩ ምክንያቶች ሰዎች ከወገኖቻቸው በሞት ሲለዩ አልቅሶ መቅበር በአብዛኛዎቹ ኢትዮጵያን የተለመደ ባህል ነው፡፡ ሆኖም የአለቃቀስና የቀብር ስርዓቱ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ባለው የባህልና የእምነት ልዩነቶች ምክንያት ልዩ ልዩ መልኮች አሉት፡፡ አንዳንዱ የሚቹን ልዩ ልዩ ገፅታዎች የሚያወሱ ግጥሞችን እየደረደረ ሙሾ በማውረድ ሲያለቅስ፣ ሌላው ደግሞ ያለለቅሶ በእንባ ብቻ ቀብሮ የሚመለስ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ መልኩም የለቅሶ ስርቱ የሚከወንበት ድባብ፣ የቀብር ስርዓቱም እንዲሁም የየራሱ መልክ ያለው ነው፡፡

የየም ብሔረሰብም ከሌሎቹ ኢትዮጵያውያን የሚጋራቸው የጋራ እሴቶች ቢኖሩትም የራሱ መገለጫ የሆኑ የተለያዩ ባህላዊ እሴቶች አሉት፡፡ ከነዚህ ባህላዊ እሴቶች መካከል የለቅሶ ስርዓቱ አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የለቅሶ ስርዓቱን ከቅድመ ሞት ዝግጅት ጀምሮ እስከ ግበዓተ መሬት ድረስ ያለውን አጠቃላይ ሂደት ተንትኖ የሚያሳይ ነው፡፡

ጥናቱ አምስት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ምዕራፍ አንድ፤ የጥናቱ ዳራ፣ ጥናቱን ለማካሄድ ያነሳሱ ምክንያቶች፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመስክ ተሞክሮ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች የሚሉትን ንዑሳን ክፍሎች የያዘ ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት፤ ክለሳ ድርሳናት ሲሆን በውስጡ የጽንሰ ሀሳቦች ብያኔ፣ የንድፈ ሀሳቦችና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት፣ የተጠኚው ማህበረሰብ መልከዓምድራዊና ማህበረ ባህላዊ ገጽታ የሚሉ ንዑሳን ክሎችን ይዟል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የጥናቱ ስነ ዘዴ የተመላከተበት ሲሆን የጥናቱ ዘዴ፣ የመረጃ ምንጮችች ናሙና፣ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎችን የያዘ ነው፡፡ ምዕራፍ አራት በየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑበት ክፍል ሲሆን የመጨረሻውና ምዕራፍ አምስት የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት የተመላከተበት ነው፡፡

## 1.1.የጥናቱ ዳራ

ፎክሎር በርካታ ሰዋዊ ጉዳዮችን ያጠናል፡፡ይህ ጥናት የሚያተኩረው የሀገረሰባዊ ልማድ ንዑስ ምድብ በሆነው የሞት ከበራ (Death Ritual) ላይ ሲሆን ይህም "የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ላይ ነው፡፡" ልደትና ሞትን የሰው ልጆች ሁሉ ይጋሯቸዋል፡፡ የተለያዩ ኃይማኖቶችና ማህበረሰቦች ስለሞት ያላቸው ትርጉምና ፍልስፍና የተለያየ ነው፡፡Gire,(2014,4-5) እንደገለጹት የሞትን ጽንሰ ሀሳብ በሚመለከት ያሉ የብያኔ ልዩነቶች ሰፋት አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ምን ይሆናል እስከሚለው ድረስ የሚደርስ ነው፡፡ የህንዱ እምነት ፍልስፍና አንድ ሰው ከሞተ በኋላ በሌላ አዲስ ማንነት እንደገና እንደሚመጣ ነው፡፡ ይህ እንደገና ወደ ሌላ ህይወት ውስጥ የመግባቱ ሂደት ለብዙ ጊዜያት እንደሚከሰት ነው፡፡ ስለዚህ በህንዱ እምነት ተከታዮች ዘንድ ሞት በማያቋርጥ የማንነት ሽግግር ወደ ሌላ እየተቀየሩ መኖር ነው ማለት ነው፡፡

በክርስትናው ኃይማኖት ደግሞ ሞትን በሚመለከት በ1972 ዓ.ም በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር የተዘጋጀው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገጽ 62 ላይ ሞት ለሚለው ቃል ብያኔ የሰጠው ሞት የሰው ልጅ ሞት ሁለት ዓይነት መሆኑን ነው፡፡ይህም በስጋዊም በመንፈሳዊም እይታ ሲሆን "የመንፈስ ሞት" የሚባለው አንድ ሰው የኃይማኖቱ አስተምህሮ ከሚፈቅደው ውጪ የሆኑ ልዩ ልዩ ተግባራትን ፈፅሞ ሲገኝ ከመንፈሳዊ ህይወቱ ተገልሏል፣ ነፍስ የዘራለት ፈጣሪውን አስቀይሟል፣ በመሆኑም እሱ ያለው በአካል እንጂ በመንፈሱ ሞቷል የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ የሚይዝ እንደሆነ ነው፡፡ "የስጋ ሞት" የሚባለው ደግሞ አንድ ሰው ነፍሱ ከስጋው ተለይታ "ሰው" የሚለው መጠሪያው ተቀይሮ "ሬሳ" ተብሎ ሲጠራ ነው የሚል ፍች ነው የሚሰጠው፡፡ በህክምናዊ ብየናው (clinical definition) ደግሞ እ.ኤ.አ.ከ1960ዎቹ ጀምሮ የሞት ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔ በየጊዜው እየተሻሻለ ዛሬም ድረስ እንደዘለቀ ነው፡፡ በመጀመሪያዎቹ አካባቢ ሞት የህይወት አለመኖር ነው (‹‹Death is the absence of life››)፣ ሞት ወሳኝ የሆኑ የአካል ክፍሎች (የልብ ምትና ትንፈሳ የመሳሰሉት) ስራ ማቆም ነው፡፡ ("Death is the suspension or cessation of vital processes of the body, as heartbeat and respiration.") እና ሞት በማይመለሱት (በማይነቁት) ቁልፍ ውስጥ (irreversible coma) መግባት ነው የሚሉት ተጠቃሽ መሆናቸውን Black

(1977,136) ያስገነዝባሉ፡፡ ስለሞት ያለው ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔ ወጥነት የሌለውና እስካሁንም አዳዲስ ሀሳቦች እየመነጩ ያለማቋረጥ እንደቀጠለ መሆኑን ነው Black የሚያስቀምጡት፡፡ ከአማርኛ ቋንቋ ትርጉም አንጻር ስንመለከት የአማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት (1993፣ 85) ሞት "የነፍስ ከስጋ መለየት፣ የህይወት ፍፃሜ፣ እልፈት፡፡" ሲል ያብራራዋል፡፡ በዚህ ብያኔ መሰረት ማንኛውም ፍጥረት ሞተ ሊባል የሚችለው እስትንፋሱ ዳግመኛ ላትመለስ ከስጋው ስትለይ እንደሆነ ነው፡፡

ከላይ ከተገለጹት የሞት ጽንሰ ሀሳብ ብያኔዎች የምንረዳው ስለሞት የሚሰጡ ብያኔዎች ውስብስብ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህ ምስጢራዊነት የሚመነጨው ነፍስ ከስጋ ሲለይ የሚኖረውን ሁነት በመግለጽና አንድ ሰው ሞተ ሊባል የሚችለው የትኛው ክፍሉ እስከ ምን ድረስ በሚለው ጉዳይ ነው፡፡

በየም ብሄረሰብ እምነት መሰረት ሰው የሞተው የተወለደ ዕለት ነው፡፡ ‹‹እያንዳንዱ ሰው የአሟሟት መንገዱ አስቀድሞ የተወሰነለት ነው፡፡ ሞት የስጋ ከነፍስ መለየት ሲሆን ስጋ ከወገኖቹ ፈጽሞ ሲለይ ነፍስ ግን በስውር ትኖራለች እንጂ ፈጽሞ እንደማትለይ ነው፡፡ ነፍስ ከስጋ ትለይ እንጂ የት እንደምትኖር አይታወቅም፡፡›› የሚል እምነት አላቸው፡፡ ይህ ፍልስፍና የሰው ልጅን ተያያዥ ገጾች የሚያሳይ ነው፡፡ ሞትና ህይወት የሰው ልጅ ተያያዥ ገጾች ናቸው፡፡ ህጻን ሲወለድ ያለቅሳል፡፡ ይህ ለቅሶ ወደፊት ለሚገጥመው ሞት የመጀመሪያው ለቅሶ ነው፡፡ ስለዚህ በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ህይወት የሚጀምረው በሞት ነው፡፡

ሞት ለሰው ልጅ በሙሉ የሚገጥመው የህይወት ሽግግር ስርዓተ ከበራ ነው፡፡ አንድ የማህበረሰብ አባል በተወሰኑ የእድሜና ማህበራዊ ደረጃዎች ሲደርስ፣ ከአንድ አካላዊ፣ ስነልቡናዊ፣ ማህበራዊ ወይም ባህላዊ ማህበርተኝነት ደረጃ ወደሌላ ደረጃ ሲሸጋገር የሚከወኑ የተለያዩ ስርዓቶችን የሚያሳይ ነው፡፡ Sims and Stephens (2005፡110-125) ፡፡ የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ልደት፣ ወጣትነት፣ ጋብቻ፣ ጉልምስና፣ እርጅና፣ ሞት ወዘተ. ከሚያልፍባቸው የህይወት መሸጋገሪያዎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህና ሌሎች የህይወት ሽግግር ከበራዎች ለህይወት ኃያል ትርጉም ያላቸው የመሰብሰቢያና ስሜትን መግለጫ እድልን የሚፈጥሩ ሁነቶች ናቸው፡፡ Mwandayi(2011,75) ፡፡

የሁለቱን ምሁራን ሀሳብ ስንመለከት ሞት አንድ ሰው ከነበረበት ወደ ሌላ ምዕራፍ የሚሸጋገርበት ሁነት ነው፡፡ ጽንሰ ሀሳቡ ሞት በመከሰቱ ምክንያት የሚፈጸምለትን ስርዓት የሚያመላክት እንጂ ሽግግሩ ምን ድረስ ነው፣ ሽግግሩ የመጨረሻው ይሁን አይሁን

የሚያመላክት አይደለም፡፡ ሞትን በሚመለከት ያሉ ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔዎችና የየማህበረ ሰቡ ፍልስፍናዎች የሚሽከረከሩት ሞት ፍጻሜ ነው፣ ጅማሬ ነው፣ መሸጋገሪያ ነው በሚሉ ሀሳቦች ዙሪያ ነው፡፡ ተመሳሳይ እምነት ተከታይ በሆኑ በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል ሞት ሲከሰት በሚፈጸሙ የለቅሶ ስርዓቶች እንኳ ልዩነቶች ይኖራቸዋል፡፡ Reimers (1999,148-49) እንደገለጹት የተለያዩ ባህሎችና ኃይማኖቶች የተለያየ ስርዓት ከበራ ይከውናሉ፡፡ ለምሳሌ የእስልምናው የለቅሶ ስርዓት ከካቶሊክ ክርስቲያኑ ስርዓት ይለያል፡፡ እንዲሁም በቦስኒያ ሙስሊሞች የሚፈጸመው የለቅሶ ስርዓት በኢራን ሙስሊሞች ከሚፈጸመው የለቅሶ ስርዓት ጋር ተመሳሳይነት ቢታይም ልዩነቶች ግን አሏቸው፡፡ ይህ ሀሳብ የሚያስገነዝበን ተመሳሳይ ይዘት ያለው ሀይማኖት በሚከውንበት የተለያየ ማህበረሰብ ውስጥ እንኳ ለየት ያሉ ስርዓቶች የሚንጸባረቁ መሆናቸውን ነው፡፡

የለቅሶ ስርዓት ክዋኔዎችን ማጥናት የአንድን ማህበረሰብ ማንነት፣ አስተሳሰብ፣ አኗኗር፣ ባህል፣ እና የህይወት ፍልስፍናውን የሚያሳዩ ጉዳዮችን ለማግኘት ያስችላል፡፡ በመሆኑም የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ምን ይመስላል? የሚለውን ይህ ጥናት ያሳያል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህን ጥናት ርዕስ ለመምረጥ ያነሳሱኝ ሁለት ዋና ዋና ምክንቶች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የግል ሲሆን ሁለተኛው አካዳሚያዊ ምክንያት ነው፡፡ በቀዳሚነት የማነሳው የግል ምክንያቴ ዋልታ ሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ድርጅት የየም ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓትና የወንዶች ግርዛት ስርዓትን የተመለከተ ዘጋቢ ፊልም በ2000 ዓ.ም.በማዘጋጀት ሀገሬ በተሰኘ ፕሮግራሙ ለእይታ አቅርቦ ነበር፡፡ በዚህ ፕሮግራሙ ለዘገባ ፍጆታ ሲባል ተቆራርጦ የቀረበና በዚዛ (ሙሾ) ስርዓቱ ላይ ብቻ ያተኮረ በመሆኑ የተሟላ ቅርስ ሆኖ አልቀረበም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለት ሰፋፊ ርእሰ ጉዳዮችን በማጨቅ የተዘጋጀ በመሆኑ በተለይ የለቅሶ ስርዓቱን ክወና ከማሳየት ባለፈ ትንተና አልነበረውም፡፡ ይህን ልገነዘብ የቻልኩትም የብሄረሰቡ አባል በመሆኔና ይበልጥ ደግሞ በጅማ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል በመጀመሪያ ድግሪ ትምህርቴ ‹‹የፎክሎር መግቢያ›› በሚል ከወሰድኩት አንድ ኮርስ ባገኘሁት እውቀት ነው፡፡ በዚህ እውቀት ስመለከተው የለቅሶ ስርዓቱ ፎክሎራዊ ጥናት ቢደረግበት መልካም ነው የሚል እሳቤ በውስጤ ተፈጥሮ ቆየ፡፡

ሁለተኛው የግል ምክንያቴ በ2009 ዓ.ም.የየም ልዩ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ‹‹የባህልና ቱሪዝም ልማት ምክር ቤት›› ለማቋቋም ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ከምሰራበት መስሪያ ቤት ተጋብዤ ተሳትፌ ነበር፡፡ በዚህ የውይይ ት መድረክ ላይ ትኩረት ከተደረገባቸው የባህል ጉዳዮች አንዱ የለቅሶ ስርዓቱ በተለይም የዚዛ (ሙሾ) ስርዓት ክወናው በተለያዩ ምክንያቶች እየተበረዘና እየጠፋ እንደሆነ የሚያመላክት ነበር፡፡ እኔም ከዚህ ውይይት በኃላ የሚጠበቅብኝ ሙያዊ ግዴታ ይህን ባህላዊ ቅርስ የተመለከተ ፎክሎራዊ ጥናት ማድረግ እንደሆነ በማመን ጽሁፋዊ መረጃዎችን ሳገላብጥ የኢትዮጵያ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ከዩኔስኮ ጋር በመተባበር በደቡብና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ 20 ብሄረሰቦችን የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች በመሰብሰብ ታህሳስ 2002 ዓ.ም. ባሳተመው ጽሁፍ ውስጥ ‹‹የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት››አደጋ የተጋረጠበት እንደሆነ ተመዝግቦ ማግኘቴ ለጥናቴ መነሻ ሆኖኛል፡፡

በዓለም ላይ ፎክሎር ራሱን የቻለ የጥናት መስክ የሆነው ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ ነው፡፡ በሀገራችንም ገና በጅምር ላይ ያለ እንደሆነ ይታ ወቃል፡፡በዚህም ምክንያት የበርካታ የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ፎክሎራዊ እሴቶች አልተጠኑም፡፡ በየም ብሄረሰብ የፎክሎር ሀብቶች ላይም በቁጥርም ሆነ በጥልቀት የተጠና መረጃ በጣት የሚቆጠር ነው፡፡ ዓለም ደግሞ በለውጥ ሂደት ውስጥ ነው፡፡ የባህልና የታሪክ መረጃዎች ምንጭ የሆኑ የእድሜ ባለጸጋዎች እየሞቱ በአዲስ ትውልድ መተካካቱና የአስተሳሰብ ለውጦች፣ የአጎራቻች ማህበረሰቦች ባህልና ሀይማኖቶች ተጽዕኖ እንዲሁም የቴክኖሎጂ እድገትና የምእራባውያን የባህል ወረራ ቱባውን ባህል እየበረዘውና እያጠፋው ይገኛል፡፡ ከእነዚህ በመጥፋት ላይ ካሉ ባህሎች ውስጥ የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት አንዱ እንደሆነ በመረዳቴ ለተተኪው ትውልድ መረጃውን ለመቅረስ በማሰብ ጥናቱን ለማድረግ ተነሳስቻለሁ፡፡

### 1.3. የጥናቱ ዋና ዓላማ

- የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የየምን ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት መተንተን ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡-

1. የብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ምን እንደሚመስል ይገልጻል፣
2. በዚዛ ስርዓቱ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ ቁሳዊ፣ ትውን ጥበባዊ፣ ልማዳዊና ስነቃላዊ የፎክሎር ዘሮችን ይፈክራል፣
3.የየም ብሄረሰብ በለቅሶ ስርዓቱ ስለሞት ያለውን ፍልስፍና ይተነትናል፣

## 1.4. የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

1. የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት አጠቃላይ ሂደት ምን ይመስላል?
2. በለቅሶ ስርዓት ከወናው ላይ የሚታዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ትዕምርቶች ምን ምን ጉዳዮችን ያመለክታሉ?
3. የየም ብሄረሰብ ለሞት ያለው ፍልስፍና ምን ይመስላል?

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት መካሄዱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና መጠናቱ የብሔረሰቡ አባላት የለቅሶ ስርዓታቸውን በውል እንዲያጤኑት፣ እንዲያደንቁትና ቅርሱ ለትውልድ የሚተላለፍ በትን ሚና እንዲጫወቱ መነሳሳትን ይፈጥርላቸዋል፣
- ለተለያዩ ጥናቶችም ይሁን ለሌሎች ጉዳዮች ሲባል ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ሊነበብ ስለሚችል የብሄረሰቡን ባህልና ማንነት በማስተዋወቅ ረገድ የተወሰነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፣
- ተለዋዋጭነት የፎክሎር ባህሪ እንደመሆኑ በአንድ ወቅት ይከወን የነበረ ወይም አገልግሎት ይሰጥ የነበረ  የፎክሎር ዘርፍ በጊዜ ብዛት፣ በቴክኖሎጂ እድገትና በአን ዳች አስገዳጅ ምክንያት ሲለወጥ፣ በተወሰነ መልኩ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊቀየርና ሊጠፋ ይችላል፡፡ በመሆኑም የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ በተለያዩ ምክንያቶች የመጥፋት አደጋ ቢገጥመው ይህ ጥናት መደረጉ አሁን ያለውን ባህል ማሳያ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፣

- ወደፊት በጊዜ ሂደት በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የታዩትን ለውጦች በንጽጽር ለማጥናት ለሚፈልግ አካል የመረጃ ምንጭ ሊሆን ይችላል፣
- ለተጠኚው ማህበረሰብም ሆነ ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በሚመለከት የተለያዩ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን ለመቅረጽ፣ የልማት ተግባራትን ለማቀድና ከአካባቢው ህብረተሰብ ጋር ውይይት ማድረግ የሚፈልግ አካል የማህበረሰቡን ማንነት እና አመለካከት አስቀድሞ እንዲረዳ የተወሰነ ፍንጭ ይሰጣል ተብተሎ ይታመናል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ለአንድ ጥናት ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት፣ የሚፈጀውን ጊዜና ወጪን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተተግባሪ ጥናት ማካሄድ ተገቢ ነው፡፡ ይህ ክፍል የጥናቱን ስፋት፣ ምን ምን ጉዳዮችን እንደሚዳስስ የሚያስረዳ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ወሰን በሚከተለው መልኩ ተለይቷል፡፡

የየም ብሔረሰብ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚኖር ቢሆንም ይህ ጥናት የሚካሄደው የብሔረሰቡ አባላት በዋናነት በሚኖሩበት በየም ልዩ ወረዳ ነው፡፡ የጥናቱ ስፋትም የለቅሶ ስርዓተ ክወናውን ከቅድመ ሞት ዝግጅት እስከ ድህረ ቀብር ድረስ ያለውን ሂደት የሚተነትን ነው፡፡ በልዩ ወረዳው ካሉ 31 የገጠርና 3 አነስተኛ የከተማ ቀበሌዎች ውስጥም ከስድስት ቀበሌዎች መረጃ ተሰብስቦ የተጠና ነው፡፡ እነዚህ ስድስቱ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያትም በልዩ ወረዳው ባህልና ቱሪዝም ባለሙያዎች መረጃ መሰረት የተቀሩት ቀበሌዎች ከሌሎች አጎራባች ቀበሌዎች ጋር የሚዋሰኑ በመሆናቸው ባንድም ሆነ በሌላ የባህል መወራረሶች ያሉባቸው በመሆናቸው የለቅሶ ስርዓቱ የመበረዝ ዕድሉ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል በሚል ስጋት ነው፡፡ በመሆኑም (ሸሞ መቴሎ፣ ኢዲያ፣ ኦያ ኤረቶ፣ ሰሙ አዋሾ፣ የላይኛው ከሸሊ እና አዝጊ ዘምዳ የሚባሉ ማዕከላዊ ቀበሌዎች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡ እነዚህ የተመረጡ ቀበሌያትም ቢሆኑ የባህል ንክኪያቸው የእነዚያን ያህል ከፍተኛ አይሆንም ከሚል እምነት ነው፡፡ የደረጃ ልዩነት ካልሆነ በስተቀር ያልተበረዘ ሊገኝ አይችልም፡፡ በነዚህ ቀበሌያት ላይ በማትኮር የተሰበሰቡ መረጃዎች በየም ብሄረሰብ አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓት ላይ የሚከወኑ ቁሳዊ፣ ልማዳዊ፣ ትውን ጥበባዊና ስነቃላዊ ጉዳዮችን ለመተንተንና ለመፈከር ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 1.7. የመስክ ተሞክሮ

ማንኛውም ተግባር ተከናውኖ ሲጠናቀቅ የተከናወነበት ሂደት ለቀጣዩ መንገድ ትምህርት የሚወሰድበት ነው፡፡ ይህ ጥናት በሚካሄድበት ወቅት ካጋጠሙ ጉዳዮች ውስጥ ለተሞክሮ ይሆናሉ ያልኳቸው የሚከተሉት ናቸው፡፡

ለዚህ ጥናት የሚሆነኝን መረጃ ለመሰብሰብ መስክ ከመውጣቴ አስቀድሜ በቤተ መፃሕፍት በመገኘት ከቀን 9-20/6/2011 ዓ.ም ድረስ የማጠናበትን ርዕሰ ጉዳይ እና የየም ብሔረሰብን የተመለከቱ ልዩ ልዩ መረጃዎችን አሰባስቤአለሁ፡፡ በመጋቢት 2011ዓ.ም. መጀመሪያዎቹ አካባቢ ትልመ ጥናቱን በማቅረብ በተቋቁሞ ወቅት የተሰጠኝን የማስተካከያ ሀሳብ አርሜ ለዩኒቨርሲቲው እንዳስገባሁኝ ወደ የም ልዩ ወረዳ ዋና ከተማ ሳጃ በ12/7/2011 ዓ.ም 6፡00 ሰዓት ላይ ደረስኩኝ፡፡ ከምሳ ሰዓት በኋላ ወደ ልዩ ወረዳው ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት በማቅናት ከጽ/ቤቱ ኃላፊና ሰራተኞች ጋር ሰላምታ ተለዋወጥንና የሄድኩበትን ዓላማ በማስረዳት ከጅማ ዩኒቨርሲቲ የተጻፈልኝን የትብብር ደብዳቤ አቀረብኩኝ፡፡ ለህጋዊነቱ ሲባል እንጂ ደብዳቤ እንደማያስፈልግና ጥናቱ መካሄዱ የጋራ ጥቅም ያለው መሆኑን ኃላፊው ገልጸውልኝ በማግስቱ መረጃ ወደ ምሰበስብበት ቀበሌዎች ይገፍ የምሄደውን የትብብር ደብዳቤ እንደሚጽፉልኝ ተስማምተን በዕለቱ ተለያየን፡፡ ነገር ግን ከማግስቱ ጀምሮ ለሁለት ቀናት የመብራት አገልግሎት በመጥፋቱ ኃላፊው የኔን ጉዳይ በመዘንጋት ለስራ ስምሪት ወደ ቀበሌ እንደሄዱ ተነገረኝ፡፡ ስልካቸውን ብደውልም ማግኘት ባለመቻል ለሁለት ቀናት እዚያው ቆየሁ፡፡ ነገር ግን ጊዜዬን ለመጠቀም ስል ለጽ/ቤቱ የባህል ልማት ባለሙያ አቶ ፈለቀ ውቤ የጥናቴን ዓላማ እና አንዳንድ መሰረታዊ ነጥቦችን በዝርዝር ከገለጽኩኝ በኋላ በጉዳዩ ዙሪያ መነጋገር ጀመርን፡፡ ይህን አስመልክቶ የተሻለ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ግለሰቦችን የተመለከተ ዝርዝር መረጃ ሰጡኝ፡፡ በተጨማሪም ከርእሰ ጉዳዩ ጋር የተያያዙ መረጃዎች ካሉ እንዲያውሰኝ ጠይቄአቸው በዘርፉ የተደረገ የጥናት መረጃ አለመኖሩን በመግለጽ መጽሔት ሰጡኝ፡፡ እንዲሁም በለቅሶ ስርዓት ላይ የተቀረጸ አንድ የቪዲዮ ካሴት ከመረጃ ክፍል ወጪ ተደርጎ ተሰጥቶኝ በመመልከት ለቃለ መጠይቅ መነሻ የሚሆኑኝን ተጨማሪ ሀሳቦች እያጠናቀርኩኝ ለሁለት ቀናት ሳጃ ቆየሁኝ፡፡

በሶስተኛው ቀን የጽ/ቤቱ ኃላፊ ከቀበሌ ስምሪት ተመልሰው የጻፉልኝን ደብዳቤ ይዤ በቀን 14/7/2011 ዓ.ም በጽ/ቤቱ ሞተር ሳይክል ትብብር ተደርጎልኝ ለቃለ መጠይቅ ወደ ተመረጡ ቀበሌዎች በመሄድ ከቀበሌው ስራ አስኪያጆች ጋር መረጃ ተለዋውጠን ለቃለመጠይቅ ቀጠሮ ይዤ ማምሻውን 11፡30 አካባቢ ሳጃ ገባሁኝ፡፡ ከዚያም በቀን 15/7/2011ዓ.ም በቃለ መጠይቅ መረጃ መሰብሰብ አሁዱ ብዬ ጀመርኩኝ፡፡ እንደ አጋጣሚ ሆኖ በቀን 17/7/2011 ዓ.ም እኔ ወደ ምሄድበት ቀበሌ ለራሱ ስራ ጉዳይ ሰዎችን ይዞ የሚሄድ ተሽከርካሪ ተገኘና ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት አካባቢ ወደ ሰሙናማ ቀበሌ ከ30 ኪ.ሜ. በላይ የሚሆን መንገድ እንደተጓዝን እኔ ወደምሄድበት ቀበሌ መገንጠያ ላይ ስንደርስ ተሽከርካሪው አውርዶኝ ወደተላከበት ቦታ አልፎ ሄደ፡፡ እንደአጋጣሚ ሆኖ የእንስሳት ህክምና አገልግሎት ስራ የሚሰራ ወንድም እዚያ ቀበሌ ነበረኝና ስልክ ደውዬለት መጥቶ ይዞኝ 30 ደቂቃ ያህል መንገድ ተጉዘን ቀበሌው ጋር 7፡00 ላይ ደረስን፡፡ ከአንድ ቀን በፊት ስልክ ደውዬ በጉዳዩ ዙሪያ ሀሳብ ተለዋውጠን ስለነበረ ምንም ጊዜ ሳናጠፋ ወደተጠቆሙልኝ ቁልፍ መረጃ አቀባይ አባ ዲጋ ባሻን ቤት ከቀበሌው የ25 ደቂቃ ያህል መንገድ ተጉዘን 8፡ሰዓት ላይ ደረስን፡፡

አባ ዲጋ ቤት ደጅ እንደደረስን ቤቶች የሚል ድምጽ ስናሰማ ለካ እቤት ሆነው እኛን ሲመለከቱ ኖረዋልና ወዲያውኑ አንድ ወጣት ልጅ ከቤት በመውጣት ከእጃችን ቦርሳችንን ተቀብሎ ቤት እንድንገባ አደረገን፡፡ እቤት ስንገባ  የበልግ እርሻ ስራ በማከናወን ላይ ቆይተው የቤተሰብ አባላት ተሰባስበው ምሳ በልተው አገባደው መሶብ ሳይነሳ ነበር የደረስነው፡፡ የቤተሰቡ አባላት ሽማግሌውም ጭምር ሁሉም ተነስተው ቆመው እንድንቀመጥ በአክብሮት ጋበዙንና ተቀመጥን፡፡ የበሉት ምሳ ቆጮ በተልባ ስለነበር የማንበላ መስሏቸው የቤቱ እማወራ በጣም ተጨነቁ፡፡ አንድ  አብሮአቸው እቤት የነበረ እንግዳ እኛ የበላነውን ስጧቸውና ከበሉ ይብሉ ካልበሉም ይተውት ይላቸውና  እማወራዋ ወይኔ ጉዴ እያሉ ተወቅጦ የተበጠበጠ ተልባ በቆጮ አምጥተውልን ስንበላ የተሰማቸውን የደስታ ስሜት ልገልጸው የማልችለው ነው፡፡ ከዚያም በተረጋጋ መንፈስ ትንሽ ካናገሩን በኋላ እጅግ በፈጠነ ጊዜ ውስጥ ቡና አፍልተው የገብስ ቆሎ ቆልተው አመጡልንና በላን፡፡ እናም እማወራዋ እንዲህ አሉን፡-

> *ድሮ ሁለት ሰዎች ለክስ ጉዳይ በአንድ አካባቢ ወደሚገኝ ዳኛ እየሄዱ አንደኛው ውሃ ይጠማውና በመንገዳቸው አቅጣጫ ወደነበረ ቤት ጎራ ብሎ*

*ውሃ አጠጡኝ ይላቸዋል፡፡ የቤቱ እመቤት ማድ ቤት አንዳንድ ኩራተኛ ወንዶች የማይበሉትና የሴቶች ምግብ የሚባለውን ከረጋ የቆሎ ጭማቂ የሚዘጋጀውን ‹‹ማላ›› የተሰኘ ምግብ አዘጋጅታ እየበላች ነበር፡፡ ሴትየዋ ‹‹መንም ብስል ነገር ቤት ውስጥ የለም ባዶ ውሃ ምን ብዬ ልስጦት እኔ ይሔን እየበላሁ ነው ብላ ለመንገደኛው ሰውዬ ስትናገር፣›› ‹‹ችግር የለውም እርሶ የሚበሉትን አምጡና ልብላ›› ብሎ ምግቡን ወስዶ በላ፡፡ ሌላኛው ጓደኛው ግን ‹‹እኔ እንደዚህ ዓይነት ምግብ አልበላም›› ሲል ‹‹በቃ እርሶ እዚያው ይጠብቁ›› ብላ ምግቡን እበላለው ላለው ሰውዬ አምጥታ ሰጠችው፡፡ ሰውዬውም ምግቡን ስለበላ ደስ ብሏት ውሃ አልሰጠውም ብላ ቤት የነበረ ቦርዴ(ባህላዊ መጠጥ) አምጥታ ሰጠችው፡፡ ደጋግማ ሰጠችውና ጠጥቶ ጠግቦ አመስግኖ ወደ መንገዳቸው ቀጠሉ፡፡ ጓደኛው ታዲያ ደጋግሞ ሲጠጣ የነበረው ምን ያህል ውሃ ጠምቶት ነበር ብሎ እያሰላሰለ ነበር የሄዱት፡፡ ለሌላ ጊዜም እነዚሁ ሰዎች በዚያው መንገድ ሲያልፉ ሴትየዋ መንገድ ላይ ታገኛቸውና አንደኛውን ሰውዬ ‹‹እርሶ እዚህ ይቆዩና እሳቸው የሆነ መልዕክት አላቸው ይዘው ይምጡ›› ብላ የመጀመሪው ቀን ምግቧን ሳይንቅ የበላላትን ሰውዬ ይዛ ወደ ቤቷ ሄደች፡፡ የማህበር ዝግጅት እቤቷ ነበረና ከድግሱ ምግብና መጠጥ ሰጥታው በልቶ ከጠገበ በኋላ ‹‹ባላፊው የሰጠሁህን ምግብ ሳትንቅ ስለበላህ ነው›› በማለት ‹‹በቃ ሂድ›› ብላ ሸኘችው፡፡ ሲባል ሰምቻለሁና ምግቤን በመብላታችሁ በጣም ደስ ብሎኛል በማለት ታሪክ ነገሩን፡፡*

ምግቡን ባንበላ ኖሮ ምን ሊገጥመን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ ምግባችንን እየበላን የሄድንበትን ዓላማ አስረድተን ነበርና የቤቱ አባወራ ሽማግሌ በፍቅር ተቀብለውን የሚያስፈልገውን መረጃ በቃለመጠይቅ ሰጥተውን ለተጨማሪ ግን እዚያው ቀበሌ ውስጥ ሌላ ሰው ማግኘት እንዳለብኝ ጠቆሙኝና ማምሻውን በምስጋና ተሰናብተን 12፡00 ሰዓት አካባቢ ወደ ወንድሜ ቤት ለአዳር ሄድን፡፡ በማግስቱ ከወንድሜ ጋር አባ ዲጋ ወደ ጠቆሙልኝ አባ ፊጣ ሲመል ጋር በማጠያየቅ አራት ሰዓት አካባቢ ደረስን ፡፡ አባ ፊጣ ቤት ስንደርስ ከበራፉ አንድ የ4 ዓመት ህጻን ልጅ ብቻ ነበረች፡፡ ትንሽ ደነገጥኩኝ ምክንያቱም የእለቱ ጊዜዬ ይባክናል ብዬ ስለሰጋሁ ነው፡፡ ለማንኛውም ብለን ወዴት

እንደሄዱ ህጻናን ስንጠይቃት ሌላ ቤት እንዳላቸው ነግራን ወደዚያ መራችን፡፡ ከቦታው ስንደርስ አባ ፌጣ እውጭ ላይ ታስረው ያሉ ከብቶችን እየቃኙ አገኘናቸውና ሰላምታ ተለዋውጠን የሄድኩበትን ምክንያት ገለጽኩላቸው፡፡ እቤት እንሂድ ብለውን ወደ ዋናው ቤት ይዘውን ሄድን፡፡ትንሽ ካዋሩን በኋላ መጀመሪያ መረቁን፡፡

> ያሁኑ ትውልድ እኛ የምንናገረውን አይሰማም፣ጠጥቶ ራሱን መሳት እንጂ ታሪክ አያውቅም፣ ስራም አይወድም እናንተ ይሄን ሁሉ መንገድ አቋርጣችሁ የታሪክ መረጃ ለመስማት መምጣታችሁ የሚያስደንቅ ነው፡፡ እኔ እስከ ወረዳ ድረስ በሀገር ሽማግሌነት በፊት እየተጠራው መረጃ እሰጥ ነበር፡፡ እኔ የታሪክ መረጃ የማወቀው ሽማግሌ ስለሆንኩኝ አይደለም፣ አያቴ ናት ለዚህ ያበቃችኝ፡፡ በጣም ስለምትወደኝ የምልህን አትርሳ፣ ሰው የሚልህን ስማ፣ ባልሆነ ነገር ከሰው አትጣላ፣ ስራ አትጥላ፣ የሰው ነገር አትመኝ፣ ብላ ጆሮዬን ይዛ መርቃኝና አስምላኝ ነው በየጊዜው ታሪክ ስታወራኝ ያደኩት፡፡ የምትናገረኝን ምን ያህል እንደምሰማት ከሶስት አራት ቀናት በኋላ ባለፊው የነገርኩህን ታሪክ እስኪ ዛሬ አንተ ንገረኝ እያለች እንድተርክላት ታደርግና የረሳሁትን እያረመች ነበር ስታስተምረኝ የነበረው፡፡ በማለት ተረኩልን፡፡

ትረካውን እንዲያቋርጡና ወደ ሄድኩበት ጉዳይ እንድንገባ ባደርጋቸው ጥሩ ስሜት አይኖራቸውም ነበር፡፡ ትረካውን በማድመጤ ደስ ብሏቸው ወደዋናው ጉዳይ በመግባት የጠየኳቸውን ሁሉ ተርከውልኝ አመስግኜ ስናበቃ ቡና ተፈልቶ ምሳ በልተን ጠጥተን ተሰነባብተን ተለያየን፡፡ አብዛኛዎቹ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎቹ በእንደዚህ ዓይነት መልካም መስተንግዶ ነው መረጃ ሰጥተው መረጃ የመሰብሰብ ስራዬን ጨርሼ ወደ ትንተና የገባሁት፡፡

## 1.8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

በዚህ ጥናት ክንውን ወቅት ያጋጠመኝ ከፍተኛ ችግር በብሔረሰቡ ባህል መሰረት ሞት ሲከሰት የግነዛ ስርዓቱ እስኪያልቅ ድረስ ማንም ሰው እንዲሰማው የማይፈቀድ መሆኑ ነው፡፡ ለቅሶውን በምን መልኩ እንጀምር የሚለው ምክክር የሚጀመረው እንኳ አስክሬን ከተገነዘ በኋላ በመሆኑ ሂደቱን በፎቶም ሆነ በቪዲዮ መቅረጽ አልቻልኩም፡፡ በዚህ

ምክንያት የአስክሬን ግነዛ ስርዓቱን ሂደት አጠቃላይ መረጃ በቃለመጠይቅ ነው ለማሟላት የቻልኩት፡፡

የሞት ቀጠሮው የማይታወቅና የት አካባቢ ማን እንደሚሞት የሚታወቅ መረጃ የሌለው በመሆኑ ተፈጥሮአዊ መቼት ላይ ተገኝቼ ምልከታ በማድረግ በነደፍኩት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ጥናቴን እንዳላከናውን አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሮብኛል፡፡ ሆኖም ከዚህ በፊት በልዩ ወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያዎች አማካይነት በአንድ ለቅሶ ላይ የተቀረጸና አርትኦት ያልተደረገበት የቪዲዮ መረጃ በማግኘት ፍተሻ በማድረግና ሌሎች አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓቱን የተመለከተ መረጃ ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች በመሰብሰብ ላይ እያለሁ የአንድ ወጣትና የአንድ ሽማግሌ ሞት በተለያዩ ቀበሌያት ተከስቶ ተገኝቼ በመቅረጽ ጥናቴን ማካሄድ ችያለሁ፡፡ ሌላው በተቀላጠፈ ሁኔታ በሚፈለገው ቦታ ተገኝቼ የተሟላ መረጃ እንዳልሰበስብ ለዚህ ጥናት ሲባል የተመደበ ተሽከርካሪ ባለመኖሩ የስራ ጊዜ መስተጓጉሎች እንዲፈጠሩ አድጓል፡፡ ለራሳቸው ተግባር ከሚንቀሳቀሱ የልዩ ወረዳው ተሽከርካሪዎች ጋር በመቀናጀትና የህዝብ ትራንስፖርት ጭምር በመጠቀም ሁለት እስከ ሁለትና ሶስት ሰዓት በእግርም ጭምር በመጓዝ መረጃውን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ላይ በማትኮር የተደረገ የጥናት መረጃ አለመኖሩ በተዛምዶ ያደረኩት ቅኝት አልነበረም ፡፡ ጥናቱ ቢኖር ለኔ አጋዥ ቢሆንም ሙሉ መረጃ በመሰብሰብ ያከናወንኩት በመሆኑ አለመኖሩ በጥናቴ ውጤት ላይ እምብዛም ተጽዕኖ አይኖረውም፡፡

ይህ ጥናት በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ በሚካተተው የህይወት ሽግግር ከበራ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ይህ የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ሁሉንም የፎክሎር ዘውጎች በማቀፍ የሚከወነው ነው፡፡ የእያንዳንዱ ዘውግ ሰፊና ራሱን ችሎ ሊጠና የሚል ነው፡፡ በዚህም ምክንያት እያንዳንዱን ጉዳይ ራሱን በማስቻል የዘውግ ምደባ በማካሄድ ጥልቅ ትንተና ለማድረግ ከጊዜም አንጻር ምቹ አልነበረም፡፡ በመሆኑም አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓቱን የተመለከተ ጥናት ያካሄድኩ ስለሆነ በቀጣይ ሌሎች ምሁራን በዚህ ርዕስ አቅጣጫ ለይተው ቢያጠኑ ጉድለቱ ይሞላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የየም ብሄረሰብ ታሪካዊ ፣መልከዓምድዊ ና ማህበረ -ባህላዊ ዳራ

በዚህ ክፍል በሶስት ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች ስር የሚካተቱ መረጃዎች ይዳሰሳሉ፡፡ እነዚህም የብሄረሰቡ ታሪካዊ ዳራ፣ መልከዓምድራዊ ገጽታ እና ማህበረ-ባህላዊ ገጽታዎች ናቸው፡፡

### 2.1.የየም ብሄረሰብ ታሪካዊ ዳራ

የብሄረሰቡ ታሪካዊ ዳራ መረጃ አስፈላጊነት ጥናቱ የሚካሄድበት ማህበረሰብ ማን ነው የሚለውን የተወሰነ ፍንጭ ለመስጠት እንጂ ሙሉ የታሪክ መረጃ ለመስጠት አለመሆኑን ልብ ይሏል፡፡ በመሆኑም የየም ብሄረሰብ ስያሜ፣ ታሪካዊ አመጣጥና ቋንቋን እንዲሁም መልከዓምድራዊና ማህበረ ባህላዊ መረጃዎች በዚህ ክፍል ይቃኛሉ፡፡

#### 2.1.1. ስያሜ

የየም ብሄረሰብ ስያሜን በሚመለከት በጽሁፍ ያሉ ጥቂት መረጃዎችም ቢሆኑ በአፈታሪክ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ብሄረሰቡ ሁለት የተለያዩ መጠሪያዎች ያሉት ሲሆን እነዚህም ‹‹የም››እና ‹‹ጃንጀሮ›› የሚሉት ናቸው፡፡ ወንድማገኝ ብዙአየሁ፣ አየለ ገላን፣ ንጉሴ ዘበን፣ ወርቁ ካብቱ፣ ሀብቴ ገብረሚካኤልና መኮንን ወልደየሱስ (2004፣1-2) [ወንድማገኝና ሌሎች 2004 ዓ.ም.] ‹‹የየም ብሄረሰብ ታሪክ›› በሚለው መጽሀፍ እንደገለጹት ብሄረሰቡ ራሱን ‹‹የም›› ወይም ‹‹የማ›› ብሎ ይጠራል፡፡ በሌላ በኩል ከተለያዩ ታሪካዊ ሁነቶች ጋር በተያያዘ ‹‹ጃንጀሮ›› የሚለው ስያሜ በአጎራባችና በሌሎች ህዝቦች ዘንድ እንደተሰጠው ያስገነዝባሉ፡፡ ‹‹ጃንጀሮ›› ለሚለው ስያሜ መነሻ ነው የሚባለው አንደኛው ምክንያት ጥንት ከፍተኛ ዝና የነበረው አንድ ‹‹ጅሮ›› የሚባል ሰው በጎንደር አካባቢ ይኖር ነበር ፡፡ ይህ ሰው ሶስት ልጆች እንደነበሩትና ከልጆቹም መካከል ‹‹ጃን››የሚባለው ከጎንደር ፈልሶ ወደ አሁኑ የየም ግዛት በመግባት ለመታሰቢያነት የሚሆን ሰፋፊ ቅርንጫፍ ያለው ዛፍ ተክሎ እንደነበርና በኋላም ወደስልጣን ሲመጣ አካባቢውን፣ የራሱንና የአባቱን ስም በማዋሃድ ‹‹ጃንጅሮ›› በማለት እንደሰየመ ነው፡፡

በሌላ መልኩ ከዚሁ ጋር በተያያዘ  የተጠቀሰው ‹‹የጃን›› ተክል ለአባቱ መታሰቢያነት በጎንደር በመትከል ወደ አሁኑ የም ግዛት እንደመጣና ከዚህም ጋር በማያያዝ ብሄረሰቡ ጃንጀሮ ተብሎ እንደተጠራ ነው፡፡

ሁለተኛው ምክንያት የጥንት የእናሪያ መንግስት ‹‹ዣንኹሮ›› የሚባል የነገስታት ንጉስ እንደነበረውና በዚህም መሰረት የብሄረሰቡ ስም ከንጉሱ ስም በመነሳት ‹‹ጃንጀሮ›› አንደተባለ የሚገልጽ ነው፡፡

ሶስተኛው በ19ኛው መቶ ምዕተ ዓመት በራስ ወልደጊዮርጊስ የሚመራው የምኒልክ ጦር የየምን ግዛት በተቆጣጠረበት ወቅት ብሄረሰቡ ታዛዥና ቅን ስለነበር የጦር መሪው ራስ ወልደጊዮርጊስ ከብሄረሰቡ አንድ መርጠው ለንጉስ ምኒልክ ምስጢራዊ መልዕክት እንዲያ ደርሱላቸው ያደርጉ ነበር፡፡ ከመልዕክተኛው ጋር በተያያዘ ብሄረሰቡ ‹‹የጃንሆይ ጆሮ›› የሚል ስም እንደተሰጠውና በሂደትንም ‹‹ጃንጀሮ›› ወደሚለው መጠሪያነት እንደዋለ ለማ (1999፣16)፣ ወንድማገኝ እና ሌሎች (2004፣1-4) የአፈ-ታሪክና ተመሳሳይነት ያላቸው መረጃዎችን በመጥቀስ ይገልጻሉ፡፡

ስለብሄረሰቡ ስያሜ ከሌሎቹ የተለየ የሚመስል አፈ-ታሪካዊ መረጃን በመጥቀስ ሂሩት ወልደማሪያም (1993 እ.ኤ.አ.) የደርግ መንግስት (የመንግስቱ ኃይለማሪያም ማርክሲሳዊ አስተዳደር) ‹‹ጃንጀሮ›› የሚለውን መጠሪያ በመቀየር ብሄረሰቡን ‹‹የምሳ›› ቋንቋውን ‹‹የምስኛ›› በሚል መጠሪያ እንደቀየረና ‹‹የምስኛ›› የሚለው የቋንቋው መጠሪያ አሉታዊ ስሜት በማሳደሩ ‹‹የም›› ወደሚል ማጠሩን ገልጸዋል፡፡ የሂሩት መረጃ ግን የደርግ ዘመን አስተዳደራዊ የጽሁፍ መረጃዎችን ማግኘት የሚቻል ሆኖ ሳለ ይህን ያልተመለከቱ ይመስ ላል፡፡ ‹‹ጃንጀሮ›› የሚለውን የብሄረሰቡን ስያሜ ‹‹የም›› ወደሚለው መጠሪያ የመንግስቱ ኃይለማሪያም አስተዳደር እንዳልቀየረውና ይልቅስ በወቅቱ የነበረው የብሄረሰቡ አስተዳ ደራዊ መዋቅር ስም ‹‹ጃንጀሮ ወረዳ›› ይባል እንደነበረ  የአካባ ቢው የታሪክ አዋቂዎችና የባህል ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ዮሐንስ ወልደማሪያም (1936፣127) ‹‹የአለም ታሪክ ከጅኦግራፊ ጋር›› በሚለው መጽሀፋቸ ው የእናሪያ ህዝብ ሁሉ የካም ዘር እንደሆነና የሚኖርበት አካባቢና አቅጣጫን ጭምር አመላክተው፡፡ ‹‹ቀድሞ ተጠቅልሎ ባንድ ንጉስ ይገዛ ነበር፡፡ እንደገበዝ አክሱም ሊቀ ካህናቱ ››የኹንጅሮ›› ንጉስ ነበር፡፡ ባረብኛ ኹን ማለት ባለግርማ፣ የሚያንቀጠቅጥ ማለት

ነው፡፡ ጅሮ ማለት ድሮ ማለት ይመስላል ፡፡ስለዚ ‹‹ዥንጅሮ›› ማለት የድሮ ባለግርማ ንጉስ ማለት ይሆናል፡፡ እርግጡ ግን አልታወቀም›› በማለት ስልስያሜው ይገልጻሉ፡፡

ምትኩ ነጋሽ (2005፣13) የተክለጻዲቅ መኩሪያን መረጃ በመጠቆም ‹‹በእናሪያ የሚኖሩ ህዝቦች ከእስራኤል ጋር ተዋልዶ የተቀላቀሉ ልዩ ልዩ ታሪክ እኔ በጻፍኩት መጽሐፍ ውስጥ አልተካተተም፡፡ ‹‹የጃንጀሮ›› ታሪክ በውጭ የታሪክ መጽሐፍት ላይ በሰፊው የተጻፈ ስለሆነ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ አልተካተተም በማለት የብሄረሰቡን ስያሜ የተመለከተ መረጃ ማመላከታቸውን ያስገነዝባል፡፡ በሌላ በኩል ‹‹የም›› የሚለው የብሄረሰቡ ሌላኛው ስያሜም ከሶስት ጉዳዮች ጋር እንደሚያያዝ ነው፡፡

የመጀመሪያው በቀደምት የየም ታሪክ ውስጥ በጉልህ የሚጠቀሱትና በአንድ ወቅት ከየመን ፈልሰው የመጡ ሰዎች እንደነበሩና እነዚህ ሰዎች ከፍተኛ ቁጥር ባይኖራቸውም በብሄረሰቡ ባህልና ፖለቲካ ላይ ጽኑ ጫና እንዳደረጉ ይነገራል ፡፡ እነዚህ ሰዎች ምናልባትም ከፍተኛ የአረብ እስላም ጫና ካለበት ከሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢ የገቡ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ‹‹የም›› ተብሎ እንደተሰየመ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ በየም ፖለቲካ ውስጥ በአንድ ወቅት ከ‹‹ጋማ›› ስርወ መንግስት ነገስታት መካከል ‹‹ታቶ የምኖ››የሚባል ንጉስ እንደነበረና ንጉሱ በወቅቱ በአካባቢው ፖለቲካ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የነበረው በመሆኑ ብሄረሰቡ ‹‹የም›› ተብሎ እንደተጠራ ነው፡፡

ሶስተኛው ደግሞ በጣም ጥንት ምናልባትም በ660 ቅድመ ክርስቶስ ልደት አካባቢ የየም ብሄረሰብ ወደ አሁኑ መኖሪያቸው የነሱ ዘር አካል የሆነ ‹‹የሙ›› የሚባል ንጉስ በአሁኗ የእስራኤል ግዛት ይኖር ነበር፤ አይሁዶችን ሲገዛ እንደነበርና ከዚህ የንጉሱ ስም በመነሳት ብሄረሰቡ ‹‹የም›› ተብሎ እንደተጠራ የታሪክ አዋቂዎች እንደሚተርኩ ወንድማገኝና ሌሎች (2004፣3) ሶስቱንም ምክንያቶች ገልጸዋል፡፡ ለማ (1999፣17) ግን አምስቱን መረጃ አቀባይ የብሄረሰቡ ሽማግሌዎችን በመጥቀስ ብሄረሰቡ ከየመን ፈልሶ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ‹‹የም›› የሚለው ስያሜው የተሰጠው መሆኑን ነው የጠቀሱት፡፡

የሆነ ሆኖ ብሄረሰቡ ራሱን ‹‹የም››ብሎ ይጥራ እንጂ ጥቂትም ቢሆኑ በቀደምቶቹ የውጭም ሆኑ የሀገራችን የታሪክ ጽሁፎች ውስጥ በብዛት ተጠቅሶ ያለው ‹‹ጃንጀሮ››የሚለው ስያሜ

## 2.1.2. የየም ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ

በተለያዩ መረጃዎች መሰረት የየም ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር በሶስት መልኩ ይተረካል፡፡

ለማ (1999፣18) የምና ባህሉ (1987ዓ.ም.)ን በመጥቀስ እንደገለጸው ‹‹ከተጻፉት መረጃዎች በተገኘው መሰረት የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀዳሚዎቹ ነዋሪዎች የተባለላቸውን የአካባቢውን ተወላጅ ጎሳዎች የሚመለከት መሆኑን ሲገልጹ ወንድማገኝና ሌሎች (በ2004 ዓ.ም.ገጽ15) የብሄረሰቡን አመጣጥ በተመለከተ የተለያዩ የታሪክ ምሁራን በተለያየ መልኩ ገልጸውታል በሚል ነው ሀተታቸውን የሚጀምሩት፡፡ የዚህ ታሪክ መጽሀፍ ምንጮችም የብሄረሰቡ ታሪክ አዋቂ ሽማግሌዎችና ጥቂት የሀገር ውስጥና የውጭ ጽሁፎች ናቸው፡፡ በመጽሐፍቹ የተገለጹ መረጃዎች ሁለት የተለያየ ሀሳብ የያዙ ናቸው፡፡ እነሱም አንደኛው አብዛኞዎቹ የብሄረሰቡ አመጣጥ ከየመን ወይም ከደቡብ አረቢያ ባልታወቀ ጊዜ ነው የሚል ነው፡፡ሁለተኛው ሀሳብ ብሄረሰቡ ባለበት አካባቢ ነባር የሆነና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የራሱን ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ስርዓት (መዋቅር) ለዘመናት ዘርግቶ የኖረ እንደሆነ የሚገልጽ ነው፡፡

የመጀመሪያዎቹ በደቡብ አረቢያ ወይም በየመን አድርገው የመጡ የሚባሉ የብሄረሰቡ መሪ የሆኑት ሼህ ድንቡል ከሶስት ወንድሞቻቸው፣ ከእናታቸው፣ ከወታደሮቻቸው፣ ከአማካሪዎቻቸውና ከአብሮ ተጓዦቻቸው ጋር እንደሆነ ነው፡፡ ሁለተኛው ‹‹ባለወልድ›› በተባሉ የሀይማኖት አስተማሪና የፖለቲካ መሪ የተመራና ሶስት ወንድሞቻቸውን፣ አማካሪዎቻቸውንና ወታደሮቻቸውን የያዘው ሌላኛው ቡድን በጉራጌ አድርጎ የጊቤን ወንዝ ከተሻገረ በኋላ ወደ አሁኑ የየም ግዛት እንደገባ ነው፡፡

የብሄረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ የሚጠቁሙ መረጃዎች እንደሚያያሳዩት ከሀይማኖት አንጻር የአይሁድና እስልምና እምነት ተካታይ የሆኑ ቡድኖች ናቸው በተለያዩ ጊዜያት በአካባቢው የገቡት፡፡ ከቋንቋ አንጻር አረብኛ ሴማዊ ሲሆን የምኛ ኦሞአዊ ነው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ታሪክ ላይ ባለመሆኑ ስነልሳናዊና ጥልቅ ታሪካዊ ጥናቱን ለስነ ልሳንና ታሪክ ጥናት ምሁራን እተዋለሁ፡፡

አለቃ ታዬ(፲፱፻፲፬ [1914 ዓ.ም.፣37] ) ‹‹የእናሪያ እዝብ ሁሉ የካም ዘር ነው፡፡ ነገደ ዮቅጣን መጥተው የነገደ ኩሳን መንግስት በወሰዱ ጊዜ በኢትዮጵያ ደቡብ ዳር ለዳር (...) የሚኖር ህዝብ ነው››፡፡ በማለት ከቀድሞ ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከዚያም እስከ ዘመነ ክርስትና ድረስ ተያይዞ እንደመጣና አንድ እናሪያ ተብሎ ከንጉሰ ነገስት በታች አንድ ንጉስ ይሾምበት፣ ይነግስበት እንደነበረ አስረድተዋል፡፡ ይህም ሊታወቅ የቻለው ስለቀዳማዊ ምኒልክ በሚናገረው ‹‹ዙዋይ›. በተሰኘው ታሪክ እንደሆነ በመጠቆም የእናሪያ ግዛት ንጉስ እንደገበዝ አክሱም ሊቀ ካህናት የጃንጀሮ ንጉስ እንደነበረ ገልጸዋል፡፡ ይህን ሀሳብ ዮሀንስ ወልደማሪያም (1936፣127-130) በተመሳሳይ መረጃ ገልጸውታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተበታትነው በሚገኙ ጥቂት የብሄረሰቡ መረጃዎች መሰረት የሞች ቢያንስ ከ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአሁኗ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ጠንካራና ታዋቂ መንግስት መስርተው ይኖሩ እንደነበር፣ ለዚህም ተክለጻድቅ መኩሪያ (1966፣163) ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ይኩኖ አምላክ እስከ አጼ ልብነ ድልግል››በሚለው የታሪክ መጽሀፍ ውስጥ ‹‹ጃንጀሮዎች›› የፈረስ ግብር ማስገባታቸውን ለአብነት መጥቀሱን ለማ (1999፣18-19) የጌታቸው(1995 እ.ኤ.አ) ጥቁም መረጃን ይጠቅሳሉ፡፡ የብሄረሰቡ አባላት ከተጠቀሰው ዘመን ቀደም ብለው እንደገቡ መገመት እንደማያዳግትና ነገር ግን በትክክል ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን ጊዜ የሚያመላክት የአፈታሪክም ሆነ የጽሁፍ መረጃ አለማግኘታቸውን ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን በአበዛኛው ከአፈታሪኩም ሆነ የጽሁፍ መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው የብሄረሰቡ አባላት አሁን ባሉበት አካባቢ ቀደም ብለው ከሌላ አካባቢ የገቡ መሆናቸውን ነው፡፡

## 2.2. መልከዓምድራዊ ገጽታ

የየም ብሄረሰብ በዋናነት የሚኖረው በየም ልዩ ወረዳ ውስጥ ነው፡፡ ልዩ ወረዳው

በደቡብ ኢትዮጵያ አቅጣጫ የሚገኝ ሲሆን ከአዲስ አበባ በ239 ኪ.ሜ. እንዲሁም ከሀዋሳ በቡታጅራ በኩል በ333 ኪ.ሜ.ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በስተደቡብ የኦሮሚያ ክልልና ሀዲያ ዞን፣ በስተሰሜን ኦሮሚያ ክልል፣ በስተምስራቅ ጉራጌ ዞንና ሀዲያ ዞን፣ እንዲሁም በስተምዕራብ ኦሮሚያ ክልል ያዋስኑታል፡፡ የቆዳ ስፋቱም 742.5 ስኩዬር ኪሎ ሜትር ነው፡፡ የብሄረሰቡ አባላት በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን ባሉ አብዛኛዎቹ ወረዳዎች በብዛት ይኖራሉ ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በጉራጌና ሀዲያ ዞኖች እንዲሁም በሌሎችም የሀገሪቱ

አካባቢዎች  እንደሚኖሩ ነው፡፡ ልዩ ወረዳው በ31 የገጠርና 4 የከተማ ማዘጋጃ ቤት ቀበሌዎች የተደራጀ ነው፡፡ ዋና ከተማው ሳጃ ሲሆን ከአዲስ አበባ ጅማ የሚወሰወደው ዋና የአስፋልት መንገድ አቋርጦት ያልፈዋል፡፡

የየም ልዩ ወረዳ መልከዓምድራዊ አቀማመጡ ተራራማና ኮረብታማ ሲሆን ከባህር ወለል በላይ 930 እስከ 2939 ሜትር ከፍታ ያላቸው አካባቢዎችን ይሸፍናል፡፡ ይህም 20 በመቶው ተራራማ፣ 3 በመቶ ሜዳማ፣ 12 በመቶ ተዳፋታማ ሲሆን ቀሪው 65 በመቶው ኮረብታማ፣ ሰንሰለታማና ወጣገባማ የመሬት ገጽታን የያዘ ነው፡፡ የአፈሩ ዓይነትም 60 በመቶው ቀይ አፈር፣ 25 በመቶው ቡናማ ሲሆን ቀሪው 15 በመቶው ጥቁር አፈር ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ 16 በመቶው ደጋ፣ 73 በመቶ ወይናደጋና 11 በመቶ ቆላማ ቦታዎችን የሚይዝ ሲሆን ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ801-1400 ሚሊ ሜትር ይደርሳል፡፡ ዓመታዊ አማካይ የሙቀት መጠኑም ከ12-30 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ መካከል ነው፡፡ ‹‹ቱባ መጽሔት››፣ ቁ.26፣ መስከረም 2010 ዓ.ም.)

### 2.2.1. ቋንቋ

በ‹‹የምኛ›› ቋንቋ ቤተሰባዊ ምድብ ላይም የተለያዩ አጥኝዎች የተለያየ ትንታኔ ሲያስቀምጡ ይስተዋላል፡፡ ደመቀ ግዛቸው እና ፈቀደ መኑታ (2013፣14 እ.ኤ.አ) የየም ቋንቋ ምንጩ ከምዕራብ ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደብ ነው፡፡ የኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብ የሆኑ ከዳውሮ፣ ኮንታ፣ ወላይታ፣ ካፍቾ፣ ሸኮ፣ በንች እና የኩሽቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ከሆነው ኦሮምኛ ጋር የቃላት ተመሳስሎ እንዳለው ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ሳይንሳዊ ምክንት አላመላከቱም፡፡ ወንድማገኝና ሌሎች (2004፣7 ዓ.ም) G.W.B.Hanting Ford (1995.)ን በመጥቀስ የብሂረሰቡን ቋንቋ ኩሻዊ ከሆነው ሲዳማ የቋንቋ ቤተሰብ ክፍል የሚመደበው የየም ቋንቋ በስነ-ምዕላድም ሆነ በስነ ድምጽ ከሌሎች የሲዳማ ቋንቋዎች የተለየና የራሱ የሆነ አመዳደብ እንዳለው መግለጹን ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በተለየ መልኩ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የ1974 ዓ.ም ሪፖርት የየም ቋንቋ ባህሪ ከኦሞአዊ ይልቅ ከናይሎቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ጋር ተዛማጅነት ያለው መሆኑን ያብራራሉ፡፡

Hirut (1993) ደግሞ ቋንቋው ምዕራብ ኦሞአዊ መሆኑንና ጊሞጃን ከሚባለው ንዑስ የቋንቋ ቤተሰብ ይመደባል በማለት ይህ ንዑስ የቋንቋ ክፍል ከየም ቋንቋ በተጨማሪ ጊሚራ እና ኦሜቶ የተሰኙትን ቋንቋዎች እንደሚያካትት ገልጸዋል፡፡

አብዛኛዎቹ የቋንቋ አጥኝዎች የምኛ ምዕራብ ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ የሚመድቡ ቢሆንም ስለምድቡ አሳማኝ የስነልሳን ትንታኔ በማቅረብ አይደለም፡፡ በኦሞቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ተመድበው የሚገኙ ቋንቋዎችም በአንድ አካባቢ በተለይም በኦሞና የኦሞ ገባር በሆኑ ወንዞች ዙሪያ የቋንቋው ተናጋሪዎች በመገኘታቸው ነው በማለት አንዳንድ የቋንቋ አጥኝዎች እንደሚያስቀምጡ ወንድማገኝና ሌሎች (2004፣7-8 ዓ.) ያስገነዝባሉ፡፡

በአብዛኛው  የጥናት ውጤቶች በጋራ የሚጠቅሱት የምኛ ቋንቋ በኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ እንደሚመደብ ሲሆን ይህ ግን ታሪካዊና ስነልሳናዊ ጥናት የሚያሻው ነው፡፡

### 2.2.2. የህዝብ ብዛት

የየም ህዝብ በልዩ ወረዳው ካለው ይልቅ ከአስተዳደራዊ ክልሉ ውጭ ያለው ቁጥሩ እን ደሚልቅ ይነገራል፡፡ ለማ (1999፣22 ዓ.ም) የጌታቸው (1995፣እ.ኤ.አ)ን መረጃ በመጥቀስ እንዳመለከቱት የብሄረሰቡ አባላት በስነምህዳር ችግርና በመሬት ጥበት ምክንያት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ለስደት ስለተዳረጉ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የሚኖሩት ከወረዳው ውጪ እንደሆነ ነው፡፡ በ1976 ዓ.ም በተካሄደው የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት በየምና ባህሉ መጽሔት (1987 ዓ.ም.) የወረዳው ህዝብ ብዛት 340,949 እንደሆነ መገለጹንና በተመሳሳይ ወቅት የተካሄደውን የፌዴራል ህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ በጌታቸው (1995. እ.ኤ.አ.) በሀገሪቱ 115,906 የብሄረሰቡ አባላት እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም ደርብ (2004፣እ.ኤ.አ) በ1994 ዓ.ም. የፌደራል የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃን ዋቢ በማድረግ የብሄረሰቡ መረጃ በጎሳ ደረጃ ወደ 267,570 እንደሚደርስ መግለጹንና እሱም ቢሆን በተመሳይ ወቅት ከተካሄደው ህዝብና ቤት ቆጠራ ቢሮ ያገኘው መረጃ በወረዳው ያለው የብሄረሰቡ ቁጥር 64,852 መሆኑን የገለጸበትን የተለያዩ አሃዛዊ መረጃዎችን ማግኘቱን ለማ (1999፣21) ያስገነዝባሉ፡፡ ከደቡብ ክልል መንግስት ስነ-ህዝብ ቢሮ የተገኘው የ1996 ዓ.ም መረጃ ደግሞ የብሄረሰቡ ቁጥር 87,009 መሆኑን እንደሚያስረዳ ይጠቁሟል፡፡ ለማ የአሃዞ ቹን መለያየት በተመለከተ ከመረጃ አቀባዮች ባገኘው መረጃ እንደገለጸው የብሄረሰቡ

አባላት በአጎራባች የኦሮሚያ ወረዳዎች በብዛት ስለሚኖሩ ቁጥራቸውን በትክክል ለማወቅ ያስቸግራል የሚል ነው፡፡

በ1999ዓ.ም. በተካሄደው ብሄራዊ የህዝብና ቤት ቆጠራ መረጃ መሰረት ደግሞ የልዩ ወረዳው ህዝብ ብዛት 80,524 እንደሆነ ነው፡፡ ብሄረሰቡ በተባሉት ስነምህዳርም ሆነ በመሬት ጥበት አሊያም በሌላ ምክንያት በሰፈራ መልክ ወደ ሌላ አካባቢ የተሰደደበት ጊዜን የሚያመላክት መረጃ ግን አላገኘሁም፡፡ የሀገራችን የህዝብ ቁጥር ዕድገት በየዓመቱ የሚጨምር ሆኖ ሳለ የህዝቡ ቁጥር በነበረበት እንኳ ከመቆየት ይልቅ በከፍተኛ ቁጥር የሚቀንስ አሃዝ የማሳየቱን ምክንያት በትክክል ለማወቅ ጥናት የሚያሻው ይመስላል፡፡

### 2.2.3. ኢኮኖሚያዊ መሰረት

አብዛኛው ማለትም ከ89.6 በመቶ በላይ የሚሆነው የየም ልዩ ወረዳ ህዝብ የሚተዳደረው በግብርና ሲሆን እንሰት ዋነኛ የምግብ ምንጭ ነው፡፡ ገብስ፣ በቆሎ፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ አተር፣ ባቄላና የመሳሰሉ የተለያዩ የአገዳና የብርዕ ሰብሎች፣ እንዲሁም የተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎች በሰፊው ይመረታሉ፡፡ ከእንስሳት ደግሞ ከቀንድ ከብቶ ላም፣ በግ፣ ፍየል፣ ከጋማ ከብቶች ፈረስ፣ በቅሎና አህያ እንዲሁም ከአዕዋፋት ዶሮን በማርባት፣ ከእደ ጥበብም የሸክላ፣ የቆዳ፣ የብረት፣ የሸማና ከእንሰት ተረፈ ምርቶች የሚዘጋጁ የተለያዩ ቁሶችን አምርተው በመሸጥ በተጨማሪነት ኑሮአቸውን ይደጉማሉ፡፡ (ቱባ መጽሔት፣ቁ.26፣ መስከረም 2010 ዓ.ም.) ወንድማገኝና ሌሎች (2004፣195) ዓ.ም፡፡

## 2.3. ማህበረ-ባህላዊ ዳራ

ይህ ክፍል በተወሰነ መልኩ የብሄረሰቡን ባህላዊ የአስተዳደርና ማህበራዊ የኑሮ መሰረቱን የሚመለከቱ መረጃዎችን የሚዳስስ ነው፡፡

### 2.3.1. የአስተዳደር ስርዓት

የየም ብሄረሰብ በተለያዩ ጊዜያት የራሱ የሆነ የዘመናዊ አስተዳደር ጽንሰ ሀሳብን የተከተለ ፖለቲካዊና ማህበራዊ የአስተዳደር ስርዓትና መዋቅር እንደነበረው ይገለፃል፡፡ ይህም በአመዛኙ በዘር ሀረግ አመጣጥና የሀይል ሚዛን በሚያጋድለው የበላይ ጎሳ አማካይነት

እየተዋቀረ ብሄረሰቡ ይተዳደር እንደነበረ ነው፡፡ የየም ንጉስ ‹‹ታቶ›› የሚል ስያሜ ሲኖረው በዋነኛነት የጋማ፣ የጌመሎና የሞዋ ጎሳ ስርወ መንግስት ነገስታት አስተዳድ ረውታል፡፡ በአስተዳደራዊ መዋቅሩ ወደ 380 የሚደርሱ ጎሳዎች እንደነበሩና ከነዚህም መካከል የ224 ጎሳዎች ስያሜ እስካሁን ድረስ ተመዝግቦ እንደሚገኝ ወንድማገኝና ሌሎች (2004፣27-28 ዓ.ም) ገልጸዋል ፡፡

ዮሐንስ ወልደማሪያም (1936፣127) ከቀድሞ ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከዚያም በኃላ እስከ ዘመነ ክርስትና አንድ እናሪያ ተብሎ ከንጉስ ነገስት በታች አንድ ንጉስ ይሾምበትና ይነግስበት እንደነበር በመግለጽ የብሄረሰቡን ጥንታዊ የአስተዳደር ስርዓት ያስገነዝባል፡፡ የብሄረሰቡ ሉአላዊ አስተዳደር እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ በአፄ ምኒልክ ፊርሶ የኢትዮጵያ አንድ አካል እንዲሆን መደረጉን ወንድማገኝና ሌሎች (2004ዓ.ም ገጽ69 ) ሲያስገነዝቡ ከአፄ ኃይለስላሴ እስከ ደርግ መንግስት ድረስ በወረዳ አስተዳደርነት ደረጃ ያሉት ባለስልጣናት የሌላ ብሄረሰብ ቢሆኑም በሌሎች የስልጣን ተዋረዶች የብሄረሰቡ አባላት በማስተዳሰደር ላይ መሆናቸውን ለማ (1999 ዓ.ም ገጽ20) ገልጿል፡፡

### 2.3.2. እምነት

ዮሀንስ ወልደማሪያም (1936 ዓ.ም ገጽ 127-128) እና አለቃ ታዬ (1914 ዓ.ም ገጽ 37-40) የኢናሪያ እዝብ በአጼ አግብዓ ጺዮን ዘመን በ1270 ዓ.ም. በአቡነ ተክለኃማኖት ስብከት አምኖ ተቀብሎ ክርስቲያን ሆኖ እንደነበርና በኃላ ግን በክርስትና እምነት ላይ በተፈጸመው የወረራ ጥቃት ሞትና ውድመት እንደደረሰበት ገልጸዋል፡፡ ከሞት የተረፈውም የሚያስተ ምረው ሲያጣ እንደገና ተመልሶ አረማዊ በመሆን የክርስትና ሃይማኖትን አጥፍቶ በዘንዶና በዛር ማምለክ ውስጥ እንደገባ ነው፡፡ ክርስትና ከጠፋ ወዲህ የኢናሪያ ህዝብ በዘንዶና በዛር ወደማምለክ እንደገባ የሚያስረዳ ከዚያ ወዲህ የሚነግስ የጃንጀሮ ንጉስ ለዘንዶ ይገብራል ንጉሱም ባለብዙ ሚስት ነው በማለት ብሄረሰቡ ቀደም ባሉት ጊዜያት ይከተል የነበረውን እምነት አመላክተዋል፡፡

ለማ (1999 ዓ.ም ገጽ 22) የታሪክ አዋቂ መረጃ አቀባዮችን በመጥቀስ እንደገለጹት ጊዜውን መጥቀስ ባይቻልም የየም ብሄረሰብ የክርስትናን እምነት የተቀበለው ‹‹ የሞዋ››ጎሳ ከጎንደር ፈልሶ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ነው፡፡ በ16ኛው መ.ክ.ዘ.የግራኝ አህመድ ሰራዊት አካባቢውን ሲወር ቤተክርስቲያናት ተቃጥለዋል፡፡ አማኞቹም ተሰደዋል፣ ተጨፍጭፈዋል፡፡

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የብሄረሰቡ አባላት በአዞ፣ በወንዝ፣ በተራራ ወዘተ. ሲያመልኩ ቢቆዩም በአጼ ምኒ ልክ ዘመን የፊታውራሪ ገብረመድህን ጦር ወደ አካባቢው ሲመጣ በ1889 ዓ.ም.ታቦታትን ይዞ እንደመጣና የክርስትናን ሀይማኖት እንደገና እንዳስፋፋ ይነገራል በማለት ለማ ገልጸዋል፡፡ ለዚህም በ1890 ዓ.ም የተተከለው የፎፋ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን ለአብነት ይጠቀሳል በማለት፡፡ ከክርስትና እምነት ጎን ብሄረሰቡ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በአዞና በቃልቻ ማመን የተለመደ እንደነበር ለማ በጥናት መረጃቸው አመልክ ተዋል፡፡ በ1999ዓ.ም በብሄራዊ መረጃና ስታስቲክስ ኤጀንሲ የተካሄደው ህዝብና ቤት ቆጣራ መረጃ እንደሚያመለክተው ከልዩ ወረዳው ህዝብ 80 በመቶው የኦርቶዶክስ፣ 5 በመቶው የፕሮቴስታንት ክርስትና እና 15 በመቶ የሚሆኑት የእስልምና እምነት ተከታዮች እንደሆኑ ነው፡፡

### 2.3.3. ጋብቻ

በሰው ልጅ ህይወት መሸጋገሪያ ሁነቶች አንዱ ጋብቻ ነው፡፡በየም ብሄረሰብ ከተመሳሳይ ጎሳ ጋርና የዝምድና ትስስር ካላቸው ጋር በጋብቻ መጣመር አይፈቀድም፡፡ ወንድማገኝና ሌሎች (2004 ዓ.ም ገጽ 159-174)፣ ምትኩ (2005 ዓ.ም ገጽ18-22) በብሄረሰቡ ዘንድ አምስት ዓይነት የጋብቻ መመስረቻ መንገዶች አሉ፡፡ እነሱም፡-1.‹‹ዛታ ጊሩ››(በቤተሰብ ስምምነት የሚመሰረት ጋብቻ)፣ 2.‹‹ራራ ጊሩ›› (በድንገት የሚመሰረት ጋብቻ) 3.‹‹ቦአ ጊሩ›› (በጠለፋ የሚ መሰረት ጋብቻ) 4.‹‹ዞካ ጊሩ››(በድለላ/በአገናኝ የሚመሰረት ጋብቻ) እና 5.‹‹ሹዋ ጊሩ›› (በውዴታ/በመፈቃቀር የሚመሰረት ጋብቻ) ናቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የተወሰኑት ብቻ እንደሚፈጸሙና በከተሞችና ቀለም ቀመሱ ማህበረሰብ ዘንድ በተጋቢዎች መፈቃቀር የሚመሰረተው ጋብቻ (ሹዋ ጊሩ) እተለመደ መምጣቱን ነው ከላይ የተጠቀሱ የመረጃ ምንጮች የሚያመለክቱት፡፡

እንደ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ አባ ፊጣ ሲመልና አባ ዲጋ ባሻን መረጃ መሰረት በየም ብሄረሰብ ጥንት በሰርግ ማግባትም ሆነ የሰርግ ዘፈን አልነበረም፡፡ እንደመረጃ ሰጪዎቹ ገለጻ ጋብቻ ይመሰረት የነበረው በማጠያየቅ የልጅቷን ቤተሰብ ማንነት  በመለየት ነው ከስምምነት ሲደረስ የተወሰኑ ሰዎች ይዘዋት የሚመጡት፡፡ ‹‹ሙሽራዋ ቤት ከመጣች በኋላ ወጣቶች እየመጡ ክራርና ጋማ የሚባል ጨዋታ እየተጫወቱ ሙሽራዎች እንዳይደበሩ

ያደርጋሉ እንጂ ሌላ የሰርግ ዘፈን አልነበረም፡፡ ዛሬ የምናያቸው የሰርግ ዘፈኖች የኛ አይደሉም፡፡›› በማለት ነው ያስረዱት፡፡

### 2.3.4. ባህላዊ ምግቦች

የየም ብሄረሰብ ባህላዊ ምግቦች አብዛኛዎቹ የእንሰት ውጤቶች ናቸው፡፡ እንሰት ለየም ብሄረሰብ ሁሉ ነገሩ ነው፡፡ እንሰትን ለምግብነት፣ ከተረፈ ምርቱ ደምሞ ለመኝታ፣ ለመቀመ ጫ፣ ለልብስ ማስቀመጫ ሳጥንነት፣ ለተለያዩ ነገሮች ማሰሪያነት (ለአጥርና ለቤት ማገር ማሰሪያነት፣ ተገምዶ ደግሞ ለእንስሳትና እቃ ማሰሪያነት) እንዲሁም ለእንስሳት መኖነት ይገለገላል፡፡ ቅጠሉ በደስታም ይሁን በሀዘን ጊዜ ለምግባ ማቅረቢያነት፣ ለመቀመ ጫነትና ለጥላነት፣ ሌሎች ምግቦችን ጠቅልሎ ለማብሰል ይጠቅማል፡፡ ከእንሰት ምርት ከአስር በላይ ባህላዊ የምግብ ዓይነቶች በየም ብሄረሰብ ይሰናዳሉ፡፡

ከሚዘጋጁ የምግብ ዓይነቶች ውስጥ ዋነኛውና ተዘውታሪው ቆጮ ሲሆን ማባያው ሽላቆ(ጥረው የባቄላ ክክ ከጎመን ጋር ተቀላቅሎ የበሰለ)፣ አላስቶ አፐዮ(በተለያዩ ማጣፈጫ ቅመሞች ተሚሽቶ በመጠኑ የበሰለ የባቄላ ክክ) እና ስጋ ናቸው፡፡ የትልቅ ሰው ሞት ሲከሰት ለለቀስተኞች፣ ለደቦ ስራና ለበዓላት በርከት ያሉ ሰዎችን ለማስተናገድ ታስቦ የሚዘጋጀው ኮባና(የድፎ ዳቦን ያህል መጠን ያለው) ይባላል፡፡ ይህ ምግብ በመጠን እንጂ ይዘቱም ማባያውም ከቆጮ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

በተለይ ለቅሶ ሲከሰት እንሰት ያለው አገልግሎት ከፍተኛ ነው፡፡ ቆጮውና ኮባናው ለመስተንግዶ፣ ቅጠሉ ተቆርጦ ከጸሀይና ዝናብ መጠለያነት እንዲሁም በአንድ ላይ በርከት ተደርጎና ተቀጣጥሎ ሲታሰር ለለቀስተኞች መቀመጫነት የሚያገለግል ነው፡፡ ከዚህ ዘርፈ ብዙ የእንሰት አገልግሎት የተነሳበየም በብሄረሰቡ ዘንድ በመኖሪያ ቤቱ ጓሮ የእንሰት ማሳ የሌለው ሰው እርቃኑን እንደለ ይቆጠራል፡፡

የየም ብሄረሰብ ባህላዊ መጠጡም ቦርዴ ሲሆን ዳጉሳ፣ ገብስ፣ ቀይ ጤፍና ብቅል፣ ለዚህ መጠጥ ዝግጅት ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ግብዓቶች ተፈጭተው ይጠመቅና የተወሰኑ ቀናት ተቀምጦ ሲፈላ በማጣሪያ(ዎሙ) ተጣሮቶ ይጠታል፡፡ ሼኡ ቁ.3 .(2003 ዓ.ም).እና ቁልፍ መረጃ አቀባይ አቶ ገዛኸኝ ዘርፉ፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

# 3. ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ክፍል የሚቃኙት ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔዎች፣ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራና ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጽሁፎች እንዲሁም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው ማህበረሰብ መረጃ ዎች ናቸው፡፡

## 3.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔዎች

በዚህ ክፍል በጥናቱ የሚንጸባረቁና ከመነሻው እስከ መጨረሻው ድረስ ሊቀጥሉ የሚችሉ አበይት ጽንሰ ሀሳቦች ብያኔዎች ይዳሰሳሉ፡፡

### 3.1.1 ሀገረሰባዊ ልማድ

ልማድ የሚለው ቃል ጥቅልና ሰፊ ጽንሰ ሀሳብን የሚይዝ ነው፡፡ቃሉም በዚህ ዘውግ ስር ያሉትን ርእሰ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆን አብዛኛውን የፎክሎር ዓይነቶች የሚገልጽ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ዘውግ ስር የሚመደቡ የፎክሎር አይነቶችን የጋራ ባህሪት በመለየት ግልጽ በሆነ መንገድ ለመበየን አስቸጋሪ መሆኑን ሰለሞን (2007፣52) ያመለክታሉ፡፡

በሀገረሰባዊ ልማድ ዘውግ ስር የሚመደቡ አብይና ንዑሳን አካዳሚያዊ ምደባዎች የፎክሎ ሮቹን ተደጋጋሚነትና በፎክ ቡድኑ የህይወት አጋጣሚ የሚከሰቱና የሚከወኑ ልማዶች ላይ መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ይህ ማለት ልማድ በተደጋጋሚ የሚገጥሙ፣ የሚቀርቡና የሚከወኑ ጥበቦች ጥቅል መጠሪያ መሆኑን Dorson(1972፡3-4) ይገልጻሉ፡፡ ጥበቦቹም ማኅበረሰቡ፣ የፎክ ቡድኑ ወይም የቤተሰብ አባል ከእምነት፣ከበዓል ቀኖች፣ከምርት ማምረት ከእርግዝና፣ ከውልደት፣ ከግርዛት፣ ከጋብቻ፣ ከሞት፣ ወይም ከሌሎች ሁነቶች ጋር በማያያዝ የሚከውኗቸው ናቸው በማለት ነው የሚያብራሩት፡፡

### 3.1.2. ለቅሶ

ለቅሶ የተለያየ ስሜት መግለጫ ነው፡፡ ሰው ለሀዘንም ለደስታም ሊያለቅስ ይችላል፡፡ ስሜቱ ግን ይለያያል፡፡ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣17) ለቅሶን "ሀዘን፡፡ ሙሾ፣ ዋይ

ዋይታ፡፡ መጮህ፣ ማንባት፡፡ የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ፡፡" ሲል ይበይነዋል፡፡ ልዩነቱ በሞት ምክንያት የሚደረገው ለቅሶ ስርዓት ከበራዊና ሰው የሀዘን ስሜቱን ለመግለጽ ማናቸውንም አይነት ተግባራት በሰዓቱ የሚፈፅም መሆኑን ነው፡፡ ለሞት የሚደረግ ለቅሶ ድምጹቱም የተለየ ነው፡፡ ይህም ማለት ለቅሶ እንድ ሰው ወይም ማህበረሰብ አካላዊ እንቅስቃሴው ጋር ተጨባጭ ቁሶችን ከድምጽ ጋር በማስማማት የሚያሰማው የሀዘን ድምጽ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ነገር ግን ‹‹እንደየማህበረሰቡ ባህል የለቅሶ ስርዓቱ የተለያየ ነው›› በማለት Gire, (2014,11) ያስረዳሉ፡፡

### 3.1.3. ለቀስተኛ

ለቀስተኛ የለቅሶው ታዳሚዎችን የሚመለከት ነው፡፡ ሰዎች ወገናቸው በሞት ሲለይ ስሜታቸው በሀዘን ይጎዳል፡፡ ስነልቦናዊም አካላዊም አቅም ያጣሉ፣ ለዚህም ወዳጅ ዘመዶቻቸው ሀዘናቸውን እንዲጋሩላቸውና የሞተ ወገናቸውን አስክሬን ወደማረፊያ ቦታው እንዲወስዱ ለቅሶ ያሰማሉ፡፡

ለቅሶውን የሰሙ ወዳጅ ዘመዶችም ከስፍራው በመድረስ ለቅሶውን በማጀብ የሀዘኑ ተካፋ ይሆናሉ፡፡ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣17) ‹‹ለቀስተኛ›› ለሚለው ቃል የሬሳ አጃቢ፣ ለቅሶ የሚያደርስ ፣ የሚያስተዛዝን በማለት ጽንሰ ሀሳባዊ ብኔ ይሰጠዋል፡፡

Worden (2009)ን በመጥቀስ Gire (2014,10-11) እንደገለጹት ሀዘን አንድ ሰው ለጠፋ ወገን የውስጥ ስሜቱን የሚገልጽበት(ምላሽ የሚሰጥበት) ሲሆን ሀዘንተኛነት የወዳጅ ሞትን ተከትሎ የሚገለጽ ስሜት እንደሆነ ነው፡፡ ለቅሶ ደግሞ ሀዘን የሚገለጽበት ሂደት ሲሆን ሰዎች ወዳጃቸው በመሞቱ ምክንያት ባህላዊ ተቀባይነት ባለው መልኩ የውስጥ ሀዘን ስሜታቸውን የሚገልጹበት መንገድ ነው በማለት ይበይናሉ፡፡ ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሀዘን፣ ሀዘንተኛነት፣ ለቅሶና ለቀስተኞች ሰዎች ለተለያቸው ወዳጃቸው በማህበረሰባቸው ባህል ተቀባይነት ባለው ስርዓት መሰረት የሀዘን ስሜታቸውን የሚገልጹበት መንገድ መሆኑን ነው፡፡

### 3.1.4. ስርዓተ ቀብር

በማንኛውም ማህበረሰብ የትኛውም ባህል በዘፈቀደ አይፈጸምም፤ ከጅምሩ እስከፍጻሜው የራሱ የሆነ ስርዓት ተከትሎ እንጂ፡፡ ‹‹ስርዓት›› አንድ ነገር የሚሰራበት ወይም የሚከወ ንበት ደንብ ህግ፣ ወግ፣ ባህል ሲሆን ስርዓተ ቀብር በቀብር ጊዜ የሚከናወን ስነስርዓት

መሆኑን የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣ 137) ፍቺ ይሰጣል፡፡ እንደየማህበረሰቡ ባህል የለቅሶ ስርዓቱ የተለያየ ቢሆንም የሚመሳሰሉ ጉዳዮች አሉት፡፡ ለምሳሌ፡- የሞት ማርዳት (መንገር)፣ የግንዘት ስርዓቶችን ማከናወን፣ ኃይማኖታዊ/እምነታዊ ስርአቶችን መፈጸም፣ ለመቅበር ወይም በሌላ ዓይነት መንገድ ለመፈጸም የሚደረግ ስርዓታዊ ጉዞ እና ለቅሶ በሁሉም ማህበረሰብ የሚፈጸምና በተመሳስሎ ሊጠቀሱ የሚችሉ መሆናቸውን Encyclopedia(vol.7,1998:483) ይገልጻል፡፡" ሞት ሲከሰት አስክሬን የሚቀበረው መወይም ወደዘላለማዊ ማረፊያው የሚወሰደው እንደየ ማህበረሰቡ ባህል፣ወግና ስርዓት መሰረት እንደሆነ ጽሁፉ የሚያስረዳን ነጥብ አለው፡፡

### 3.1.5. ሙሾ

በተለያዩ ማህበረሰቦች የህዘን ስሜት የሚገለጽበትና አስክሬን ከሟች ቤት የሚሸኝበት መንገድ በተለያየ ክንውኖች ነው፡፡ ከነዚህም መካከል በተለያዩ ማህበረሰቦች የተለያየ ስያሜ የሚሰጠው ሙሾ ነው፡፡ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣68) ሙሾ ‹‹ሰው በሞተ ጊዜ በአውራጅና በተቀባይ አማካይነት በግጥምና በዜማ እየታጀበ የሚካሄድ ለቅሶ ነው›› በማለት ብያኔ ይሰጠዋል፡፡ ይህ ብያኔ ስነቃላዊ ጉዳዮችን ብቻ የተመለከተ ይመስላል፡፡ ነገር ግን ሙሾ በቁሳዊና ልማዳዊ ባህሎችም ጭምር የሚታጀብ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ የሚታዩት ቁሳዊም ሆነ ስነቃላዊ ናቸው፡፡

## 3.2. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

ይህ ጥናት ከአራቱ አበይት የፎክሎር ዘውጎች አንዱ በሆነው ሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ተካቶ በሚጠናው "የለቅሶ ስርዓት" ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ የለቅሶ ስርዓት አፈጻጸሙ የተለያየ ቢሆንም በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ ማህበረሰቦች ዘንድ ሰው ሲሞት አልቅሶ መቅበር የተለመደ ተግባር ነው፡፡ የለቅሶ ስርዓቱ ታዳሚዎች ስሜታቸውን በተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎችና ተግባራት ነው የሚገልጹት፡፡ ዘሪሁን(1992፣ 22) "በአንዱ የለቅሶ ስነስርዓት ሙሾ እየተደረደረ ደረት ይደለቃል፣ ይዘለላል፡፡ በሌላው ደግሞ የሟች ዘመዶች ፊታቸውን ይቧጥጣሉ፣ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፡፡ በቀረው ደግሞ ከበሮ ይዞ በመጨፈር የለቅሶ ክዋኔ ይደረጋል፡፡ በሆታና በድልቂያ ሙታቸውን የሚሰናበቱም አሉ፡፡" በማለት ያብራራሉ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች የምንረዳው የለቅሶ ስርዓት በተለያዩ የፎክሎር ዘሮች ታጅቦ የሚከወን መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሞት ወይም ለለቅሶ የሚከወኑ ስርዓቶች በርካታና ጥልቅ ሀሳቦችን የያዙ እንዲሁም ማህበረሰቡ ለስርዓተ ሞት(ለቅሶ) ክወና የሚሰጠው ቦታ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡

ሞት ሲከሰት ወዳጅ ዘመድ ያዝናል፣ የሀዘን ስሜት ከሚገለጥባቸው መንገዶች ደግሞ አንዱ ለቅሶ ነው፡፡ የለቅሶ ስርዓተ ክወና ደግሞ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ የሚለያይ ነው፡፡
ምንም እንኳ ሞት ያለቀጠሮ ድንገት የሚከሰት ሁነት ቢሆንም እንደየማህበረሰቡ ባህላዊ ወይም ኃይማኖታዊ ስርዓት መሰረት ስርዓተ ቀብሩ የሚፈጸመው በታቀደና ቅደም ተከተላ ዊ ስርዓት ባለው መልኩ ነው፡፡ በመሆኑም ይኼን ስርዓት ለማከናወን በየማህበረሰቡ የሚዘጋጅ ስርዓት ከበራ አለ ማለት ነው፡፡ ከበራው ደግሞ የሚፈጸመው በክዋኔ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከበራን እና ክዋኔን መሰረት በማድረግ መሰረተባህላዊ ትንተና በፎክሎር ጥናት(Infracultural Model in Folklore analysis) በሚል ጽንሰ ሀሳባዊ የትወራ ማዕቀፍ የሚቃኝ ነው፡፡

### 3.2.1. መሰረተ ባህላዊ ሞዴል (Infracultural model)

ይህ ሞዴል በአንድ በተወሰነ የባህል አውድ ላይ የሚከወኑ ቃላትንና ክንውኖችን(words and action) ትርጉም ለማብራራት ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ ይህ ማለት በአንድ ባህል አውድ ላይ የሚከወኑ ቃላትና ክንውኖች ፍች በተጠኚው ማህበረሰብ የእይታ መነጽር መሆኑን Alembi (2002,22 ) እና (2008) ያስረዳሉ፡፡ ይህ ሞዴል ‹‹The Construction of the *Abanyole* Perceptions on Death Through Oral Funeral Poetry›› በሚል ባካሄዱት መመረቂያ እና ‹‹THE ABANYOLE DIRGE›› በሚል ርዕስ ለጥናት መጽሔት በኬኒያ የአባኞል ማህበረሰብ የሙሾ ስርዓትን በተመለከተ ለማጥናት Alembi ያመነጩት ነው፡፡ ይህ ጽንሰ ሀሳባዊ የትንተና ማዕቀፍ የሚከተሉት መሰረታዊ ነጥቦች ላይ የሚያተኩር መሆኑን ይገልጻሉ፡-

- በቤተኛነት የባህሉን የጥበብ ተግባራትንና የማህበረሰቡን ተጨባጭ እውነታዎች ለመተንተንና ለመተርጎም ነው፡፡ ቤተኛ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ በማድረግ የማህበረሰቡ ሁነት አካል ለመሆን ቁርጠኛ የሆነ ሰው ነው፡፡

ስነቃሎችን በባህላዊ አውዳቸው ለመተርጎም ነው፡፡ ምክንያቱም ስነቃሎች ስረ መሰረታቸው በከዋኞቱ ባህልና ልማድ ላይ እንደሆነ በኢትኖግራፊያዊ ጥናትም ተቀባይነት ያለው መሆኑ ይገለጻል፡፡ ከዋኞቹ የሚከውኗቸው ስነልሳናዊ ጉዳዮች ከአውዳቸው ጋር የተቆራኙ ነው፡፡ ይህ ማለት ከዋኞችና ታዳሚዎች የሚጋሩት ተመሳሳይ ኮድ አላቸው፡፡ ከዚህ ኮድ ውጭ ሆኖ ትንታኔያዊ ትርጉም መስጠት መልዕክቱ ላይ የተሳሳተ አረዳድ እንዲኖረን ያደርጋል፡፡

- ትረካዎችን ከቅርጻዊ ባህሪያቸው ባሻገር አወቃቀራዊ ትስስራቸውን መመርመር፣
- በማህበረሰቡና በሁነቱ ዙሪያ ያሉ መሰረታዊ ጉዳዮችን ለመረዳት ጥልቅ በሆነ ተሳትፎአዊ ምልልስ(dialogue) ለማድረግ፣
- የክወናውን አስፈላጊነትና የሚሰጠው ትርጉም መተንተን ፡፡ ምክንያቱም ለስነቃላዊ ቅንጣቶች (texts) ፍች የሚበየነው በከዋኙና ታዳሚው ባህልና ልማድ ነው፡፡
- ከዋኙ፣ታዳሚውና ፎክሎረኛው ሆነው በጋራ በክወናው መግባታቸው  የሚፈለገውን ትርጉም ያስገኛል፡፡ ይህ ትወራዊ ቅኝት ለአፍሪካ ፎክሎር ጥናት ጠንካራ መሰረት የሚኖረው ነው፡፡ ምክንያቱም  አንድ ነጠላ ሁነት  እንኳ ጥልቅ የሆነ መልዕት የሚያስተላልፉ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡ ይህ ጥናትም በዚህ ማዕቀፍ ተቃኝቶ የለቅሶ ዚዛ ስርዓት ክወናን ይፈክራል፡፡ በዚህ ንድፈ ሀሳባዊ የትንተና ማዕቀፍ ውስጥ የሚነሳው ሌላው አንኳር ነጥብ ስርዓት ከበራ እና ክዋኔ ነው፡፡

### 3.2. 1.1. ስርዓት ከበራ (Ritual)

ስርዓት ከበራ (Ritual) አንድ ማህበረሰብ ያለውን ባህል፣ ወግና ኃይማኖት መነሻ በማደረግ ካላቸው ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኃይማኖታዊ ዋጋ አንጻር በመለየት በከፍተኛ ቅደም ተከተላዊ ስርዓትና በተደጋጋሚነት የሚከውናቸው ሁነቶች ናቸው፡፡ ከበራዎች ተደጋጋሚ፣ የተለመዱና ምክንያታዊ ተግባራት ሲሆኑ በተደራጀ አኳኃን የሚመሩ ቡድናዊ ክዋኔዎች ናቸው ሲሉ Sims and Stephens (2005,94) ያብራራሉ፡፡

አንድ የማህበረሰብ አባል በተወሰኑ የእድሜ ደረጃዎች ከአንድ አካላዊ ወይም ባህላዊ ማህበርተንነት ደረጃ ወደ ሌላ የሚሸጋገርበትን የደስታም ይሁን የሀዘን የህይወት መሸጋገሪያ ስርዓት ከበራዎችን የሚመለከት ነው፡፡ የመሸጋገሪያ ከበራ በሰዎች ህይወት

ውስጥ ወሳኝ የሽግግር ምዕራፍ ሲሆን ልደት፣ ጉርምስና፣ ጋብቻ፣ ሞት ወዘተ የመሳሰሉት ለአብነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን Sims and Stephens (2005,110) ያስገነዝ ባሉ፡፡

ከበራ ቴክኒካዊ በሆነ መልኩ ሲታይ በከፍተኛ ደረጃ ወካይ(ተምሳሌታዊ) በሆኑ ክወናዎች የተወሰኑ የህይወት ጉዳዮች ወይም ልምዶች ትርጉም፣ ጥልቅና ምጡቅ ሀሳቦች የሚገለጹበት ነው፡፡ ከበራዎች ለመሰብሰብና ስ ሜትን ለመግለጽ ዕድል የሚፈጥሩና ለህይወት ሁነቶች ትርጉም መስጫ መሳሪያ ናቸው፡፡ማህበረሰቡ እንዲገኝ እድል ይሰጠዋል፣ እንዲመለከተውና ለቀጣይነቱም እንዲተረጉመው ያደርጋል፡፡ ከበራ የተወሰኑ የጋራ ማንነቶችን የሚያጠናክር እንደሆነ Mwandayi (2011 ,54) ይገልጻሉ፡፡

በተመሳሳይ Reimers (*1999,)* ‹‹ስርዓተ ከበራዎች ያለፈውን፣ ከነባሩና ከወደፊ ጋር በማገናኘት መሸጋገሪያ የሚሆኑ ሲሆኑ የግልና የጋራ ማንነትን የሚገነቡ ናቸው›› በማለት ያብራራሉ፡፡ ከበራ አንዱ የልማድ ዘውግ ነው፡፡ ቤተሰባዊ፣ ማህበረሰባዊ፣ መንፈሳዊና ዓለማዊ ድግሶች እንዲሁም ሌሎች በርካታ የተቀናጁ ክወናዎችን የሚመለከት ነው፡፡

ከበራዎች ተደጋጋሚና የተደራጁ፣ ተግባራዊ ውክልናዎችን በውስጣቸው ያቀፉ መጀመሪና ፍጻሜአቸው የሚታወቅ የአንድ ሁነት ክወናዎች ናቸው፡፡ ከበራዎች ጥልቅ የሆነ ውክልናዊ ሀሳብን የያዙ ለየት ያሉና አውድ ላይ መሰረት ያደረጉ፣ አንድ የቡድን አባላት በተግባር በመከወን እውቅና የሚሰጡበትና የሚያስተዋውቁበት ጥልቅ የሆነ ሀሳብ የያዙ ባህል፣ ልማድና የእምነት ተግባራት የሚከወኑበት መድረክ መሆኑን Myerhoff(1977,200)ን በመጥቀስ Sims, and Stephens (2005,95) ያስገነዝባሉ፡፡

ከእነዚህ ጥቁም ሀሳቦች የምንረዳው ከበራ ከዋኙና ታዳሚው ስለአከዋወኑና ምክንያታዊ መከሰቻው የሚያውቁት፣ በትውልድ መካከል ቀጣይነት ያለው ግንኙነት እንዲኖር እድል የሚፈጥር፣ ማንነት የሚጠናከርበት፣ ማንኛውም ባህላዊ ስርዓት የሚከወንበትና የጋራ ተግባ ቦታዊ ህግ ያለው ጥልቅ መልዕክቶች በተለያዩ ቁሳዊና ስነቃላዊ ጥበቦች የሚቀቀርቡበት የተደራጀ መድረክ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ ድንገት ሊከሰት ለሚችለው ሞትም ሆነ ሌሎች ከበራዎች የጋራ ባህሪ አላቸው፡፡ እነሱም፡- ተደጋጋሚነት፣ ቅንጅት፣ ውክልናዊ ሀሳቦችን መያዛቸው፣ ቡድናዊነት፣ መጀመሪያና መጨሻቸው የሚታወቅ መሆኑ፣ የጋራ ማንነትን የሚያጠናክሩ መሆናቸው የሚጠቀሱ መሆናቸውን Mwandayi (201,54) እና Sims, and Stephens 2005,95) ያስነዝባሉ፡

### 3.2.1.2. ክዋኔ (Performance)

ክዋኔ በፎክሎር ጥናት ውስጥ ዋና ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡Finnegan, (1992: 86) ‹‹የትኛውም ተግባር ክዋኔ እንዳለው ይታሰባል›› በማለት ሲገልጹ Bauman (1986፣3) ደግሞ ክዋኔ የተግባቦት ወይም የአነጋገር ስልት እንደሆነ ያብራሩታል ፡፡

እነዚህ ጥቅሶች የሚያስረዱን ከዋኙ ክወናውን በሚያቀርብበት ባህል ልማዳዊ ህግ መሰረት የሚጠበቅበትን ጥበብ እያሟላ ታዳሚው ደግሞ የሚጠበቀውን ትውፊታዊ ውበት እያገኘ እርሰ በእርስ የሚፈጥሩት ተግባቦት ነው፡፡ እንዲሁም ክዋኔ ታዳሚው የከዋኙን ባህላዊ ክህሎት ገምግሞ የሚመጣበት እና ልምድ የሚቀያየሩበት ነው፡፡ ለክወናው መፍዘዝም ሆነ መድመቅ የታዳሚው ሚና ወሳኝ መሆኑን ነው፡፡ ሌላው Sims, and Stephens (2005፣ 128) ክወና ተውህቦ ያለው፣ የተቀናጀ የመነጋገሪያ ስልት የሆነ፣ የተጣጣመ ወይም የጠመጠነ አካላዊ እንቅስቃሴ ያለው፣ ተደጋጋሚና በከዋኞቹ ዘንድ በጊዜና በቦታ የተወሰነ ፣ በግለሰብና በቡድን ማንነት የተገነባ ባህሪን የያዘ መሆኑን ምንነቱንና ባህሪውን በአንድ ላይ ያብራራሉ፡፡

Finnegan (1992፣ 91) Bauman (1975፣ 290)ን በመጥቀስ ክዋኔን መሰረት አድርጎ የሚያጠና የፎክሎር ተመራማሪ የክዋኔ አጋጣሚ፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ ቴክስት፣ አውድ፣ መቼት እና ቅርፅ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባው ያስገነዝባሉ፡፡ ሰለሞን (2007፣46-47) አሀድ(text)፣ ገጽታ (texture)፣ አውድ (context) እና ክወና (performance) የፎክሎር ዓላባውያን ናቸው በማለት ይዘረዝራቸዋል፡፡ ይህ ጥናት በለቅሶ ሙሾ (ዚዛ) ስርዓት ክዋኔ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ እያንዳንዳቸውን በዝርዝር እንመልከት፡፡

#### 1. የክዋኔ አጋጣሚ

አንድ የፎክሎር ዘውግ ሲከወን የሚከወንበት ምክንያታዊ ቦታ፣ጊዜና ሃሰብ አለው፡፡ለምሳሌ ለሙሾ ክወና ሞትና የለቅሶ ስርዓት ይኖር ዘንድ ግድ ነው፡፡ ሙሾው በዚህ ጊዜና ሰዓት ተቀናጅቶ የሚቀርብ ሲሆን ሙሾ አውራጁም ሆነ ታዳሚው እውናዊ በሆነ ስሜት ውስጥ ተገኝተው የሀዘን ስሜታቸውን የሚገልጹት ይሆናል፡፡

ክወና ይከናወን ዘንድ በታዳሚዎች(ተሳታፊዎች) የሚታወቅ መቼት ይከሰት ዘንድ ግድ መሆኑን Sims,and Stephens (2005,128) ‹‹In order for a performance to “happen,” a recognized setting must exist.›› በማለት ይገልጻሉ፡፡

## 2. ከዋኝ

ከዋኝ የአንድ ባህል ባለቤት የሆነና ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት ስርዓቱን የሚፈጽመው ቡድንና ግለሰብን የሚመለከት ነው፡፡ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣ 380) ከወነ የሚለውን ቃል "አዘጋጀ፣ አሰናዳ፣ አስጌጠ፣ አሳመረ፣ ፈፀመ፣ ጨረሰ" ሲል ፍቺ ይሰጣል፡፡ ይህ ፍች የከዋኙን ድርጊት የሚያመለክት ሲሆን ከዋኝ ክወናውን በማዘጋት፣ በመተግበር፣ ክወናውን በመጀመርና በማስጀመር፣ እንዲሁም ከማሳመርም አኳያ ጉልህ ሚና ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ከዋኝና ታዳሚ በክወና ወቅት የሚፈለገው መልዕክት እንዲተላለፍ የሚያደርጉ መሆናቸውን ሰለሞን (2007፣51) ሲገልጹ Finnegan (1992፣ 90) ደግሞ ከዋኝ ለክዋኔው ሀሳብ በማቅረብ፣ ከክዋኔው አስቀድሞ ወይም በክዋኔው ወቅት ለአውዱ የሚስማሙ ጉዳዮችን የሚደርስ (composer) መሆኑን በመግለጽ የከዋኝን ሚና ያስረዳሉ ፡፡

## 3.ታዳሚ

ታዳሚዎች ክወናው በሚከወንበት አካባቢ ተገኝተው ለከዋኙ ድርጊት አንዳች ምላሽ የሚሰጡ ናቸው፡፡ Finnegan (1977፣216) “Audience is really parts of the performance itself” በማለት ታዳሚ የክዋኔው አንድ አካል መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

በየትኛውም ክዋኔ ውስጥ የታዳሚዎች ሚና ወሳኝ ነው፡፡ በክዋኔው ወቅት ታዳሚ ክዋኔውን በድምፅ፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ፣ በጭብጨባ፣ በከበሮ፣ በድልቂያ፣ በማጀብ ምላሽ ይሰጣል፡፡ አንድ ክዋኔ በሚከወንበት ጊዜ ክዋኔው በሚካሄድበት መቼት እንደ ተሳታፊዎች ባህሪያት ነው ምላሽ የሚሰጠው፡፡ መቼቱ በተሳታፊዎች መካከል ያለው ግንኙነት እንደ ተሳታፊዎቹ ዕድሜ፣ ፆታና ማህበራዊ ደረጃ ይወሰናል፡፡

ከዚህ ሃሳብ እንደምንረዳው ክዋኔ በጣም ሰፊ የሆነ ጽንሰ ሃሳብን የሚይዝ መሆኑን ነው፡፡በለቅሶ ስርዓት ክወናም ለቀስተኛም እንደየማህበረሰቡ ባህል መሰረት ከአለባበስ ጀምሮ የየማህበረሰቡን ባህላዊ ስርዓት ድባብ ያለው ሆኖ መገኘትን የሚጠይቅ ነው፡፡

## 4.ቅንጣት

በፎክሎራዊ ትርጓሜው በርካታ ነገሮችን አስተሳስሮ የያዘ ወይም ክወናው እንዲካሄድ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ነው፡፡ለምሳሌ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ሰው ሲሞት

የሚከወነው የለቅሶ ስርዓት አጠቃላይ ገፅታ  በተለያየ መልኩ ሊታይ እና ሊጠና የሚችል ነው ማለት እንችላለን፡፡

## 5. አውድ

በክወናዊ ጥናት አውድ መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳብ እንደሆነ Hufford(1995 ፣531-32) ሲገልጹ Dan Ben-Amos(1993፣ 209፣212)ደግሞ አውድ ፎክሎር የሚተረጎምበት መሰረታዊ ነገር መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ Sims, and Stephens (2005,138) እና Dan Ben-Amos (1993:215) እንዳብራሩት የክዋኔ አውዶች ማለትም ተጨባጭ እና ማህበራዊ አውዶች በጥናቱ የሚተኮሩ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ተጨባጭ አውድ በክዋኔ ወቅት የሚታዩትን አካላዊ እንቅስቃሴ፣ የድምጽ ቅላጼ፣ ዜማ አወጣጥ፣ የፊት ገጽታ መለዋወጥ፣ ሽታ፣ የክወናውን ቦታ፣ ጊዜ ወዘተ የሚይዝ ሲሆን፣ ማህበራዊው አውድ ደግሞ በክዋኔው ላይ የሚታደሙትን ተሳታፊዎች ሁለንተናዊና ማህበራዊ ገጽታ ይመለከታል፡፡ እነዚህም የታዳሚዎችን ማንነት፣ ኃይማኖት፣ ባህል፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ ስራ፣... ወዘተ የሚመለከት ነው ፡፡

## 6. መቼት

አንድ ከበራ የሚከወንበትን ቦታና ጊዜን የሚመለከት ነው፡፡ Bauman (1992፣ 46) አንድ ክዋኔ የሚከወንበት ጊዜ የሚታወቅ፣ ክዋኔውን ለመከወን ቅድመ ዝግጅት የሚደረግበትና ክዋኔው መጀመሪያው እና መጨረሻው የሚታወቅ ወይም መነሻ እና መድረሻ ያለው መሆኑን በማመላከት በክዋኔው ውስጥ ጊዜ እና ቦታ ያላቸውን ጉልህ ሚና ዘርዝረዋል፡፡

## 7. ገጽታ ወይም ላህይ

የትኛውም የፎክሎር ዘር የሚቀርብበት የራሱ የሆነ ቃና ወይም ድምጸት አለው፡፡ ይህ ድምጸት የሚፈጠረው ማህበረሰቡ አምኖ በተቀበለው አኳኋን ነው፡፡ ለምሳሌ የለቅሶ ስርዓት እንደየማህበረሰቡ እምነትና ልማድ የራሱ የሆነ ገጽታ ያለው በመሆኑ በምንም መንገድ በሌላ ዘውግ ቅርጽ ሊቀርብ አይችልም፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ሲል የተመላከቱት የክዋኔ ባህሪያት በአንድ ከበራ (Ritual) ውስጥ ክዋኔው ህያው ሆኖ እንዲጓዝ የሚያስችሉ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህ የክዋኔ

ባህሪያት የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው "የለቅሶ ስርዓት›› ውስጥ እንደምን እንደቀረቡ በትንታኔ ለማሳየት ይሞከራል፡፡

### 2.3. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንዑስ ክፍል ይህ ጥናት ከሚያተኩርበት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የኤም.ኤ መመረቂያና ጥናታዊ ጽሁፎች ተቃኝተዋል፡፡ የነዚህ ጽሁፎች መዳሰስ ፋይዳው ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ያላቸውን ተዛምዶና ልዩነት በመጠቆም ይህ ጥናት የሚሞላውን ክፍተት ለማመላከት ነው፡፡ ጥናታዊ ጽሁፎቹ የተቃኙበት ቅደምተከተል የጥናት ዓመታቸውን መሰረት በማድረግ ከሩቅ ወደ ቅርብ ሲሆን በዚህ ቅደም ተከተል ያየሁበት ምክንያት ከኋላ የታዩትን ክፍተቶች ተከትለው የመጡት ጥናቶች እንዴት እንደሞሉት ለማንሳትና በእነዚህ ያልታዩትን በኔ ጥናት ለመሙላት ነው፡፡በተመሳሳይ ዓ.ም. የተጠኑት የአጥኚዎችን ስም  ፊደል ገበታ ቅደም ተከተል መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡

Abbink (1992) FUNERAL AS RITUAL: AS ANALYSIS OF ME'EN OF MORTUARY RITES (SOUTH WEST ETHIOPIA) በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ የመኒኢትን ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት መግለጽና መፈከር ነው፡፡ የጥናቱ ትወራዊ ማዕቀፍ ‹‹በፈጠራዊነት ላይ የተመሰረተ ተግባቦታዊ ባህሪ›› (Communicative behavior framed by premises of fictionality) በሚል ንድፈ ሀሳብ የተቃኘ ነው፡፡ በመረጃ ትንተናው ክፍል ‹‹ቀብር››የሚል ርዕስ በመስጠት ነው የመኒኢትን ማህበረሰብ አጠቃላይ ስርዓተ ቀብር ክዋኔን የተነተነው፡፡ትንተናው በዋነኛነት ያተኮረው ውክልናዊ (ትዕምርታዊ) ልማዶች ክዋኔዎች (symbolic customs) ላይ ነው፡፡
ይህም ትወራዊ ማዕቀፉ የነዚህ ውክልናዎች ተግባቦታዊ ጉዳይን የሚመለከት በመሆኑ ነው፡፡ አጥኚው በጥቅሉ የመኢኒት ብሄረሰብን የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ከትወራዊ ማዕቀፉ ቅኝት አኳያ  አራት ዋና ዋና ትርጉም ነው የሰጡት፡፡

ይህ ጥናት ከአላማው አንጻር የብሄረሰቡን የቀብር ስርዓት እጅግ ግልጽ ስዕላዊ ገለጻ በማድረግ ፍከራዊ ትንተና አካሂደዋል ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን  የለቅሶ ወይም የቀብር ስርዓቱን ሂደት በምዕራፍ ለይተው አላሳዩም፡፡ የቀብር ስርዓት ሞት በመከሰቱ ከሚፈጸሙ ስርዓቶች አንዱ ሆኖ ሳለ አጥኚው ሙሉ ትኩረቱ የቀብር ስርዓቱ ላይ ብቻ ነው፡፡ይህ ደካማ ጎኑ ነው፡፡

ሌላው አባንኪ በማህበረሰቡ ፎክሎራዊ ጥናት በማድረግ የመጀመሪያው እንደሆነ የገለጹ ቢሆንም በተዛማጅ ጥናት ቅኝቱ የተመለከተው አጠቃላይ በለቅሶ ስርዓት (Rituals) ላይ ያተኩሩ ሆነው ከኢትዮጵያ ውጭ የተደረጉ ጥናቶችን ብቻ መመልከቱ ለምን የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡ የAbbink ጥናት ዓላማ የመኢኒትን ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ትዕምርታዊ ጉዳዮችን በተግባቦታዊ ማዕቀፍ በመግለጽ መፈከር ነው፡፡ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ጉዳዮችን በገለጻ የሚፈክር በመሆኑ በዓላማና ግኝቱ ያመሳስለናል፡፡ የተጠኚው ማህበረሰብና የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ እንዲሁም የለቅሶ ስርዓቱን ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ቀብር ድረስ ያሉ ሂደቶችን ከማስቃኘት አኳያ ልዩነቶቻችን ናቸው፡፡ ምክንያቱም የAbbink ጥናት ሙሉ ትኩረት ትዕምርታዊ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡

Alembi (2008.) THE ABANYOLE DIRGE: " ESCORTING" THE DEAD WITH SONG DANCE በሚል ርዕስ በኬኒያ የአበኞል ማህበረሰብ የለቅሶ ሙሾ ስርዓት ላይ የሚከወነውን የዳንስና የሀገረሰባዊ መዝሙር ክወና ጥናት ሌላው የቃኘሁት ጽሁፍ ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረት የአበኞል ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ መዝሙሮች ላይ ነው፡፡ ጥናቱ የተነተነው በገለጻዊ ፍከራ ሲሆን ለዚህም መሰረተ ባህላዊ ሞዴል (Infracultural model) የሚል ጽንሰሀሳባዊ የትንተና ማዕቀፍን ነው የተጠቀመው፡፡ ለዚህ ሞዴል የተጠቀሙት ትወራ ደግሞ ህዝብን ያማከለ (people centred) የሚል ነው፡፡ ለጥናቱ መረጃ የሰበሰቡት በተሳትፎአዊ ምልከታ፣ በቃለመጠይቅና ማህበረሰባዊ ውይይቶችን በማድረግ ነው፡፡ ከጥናቱ ዓላማ አንጻር በለቅሶ ሙሾ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ዳንስና ዘፈኖችን ተንትነዋል፡፡

ከጥናቱ ዓላማ አንጻር ግቡን መቷል የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ Alembi የአባኞል ማህበረሰብ የለቅሶ ሙሾ ስርዓትን የተመለከቱ ቢሆንም የፍከራ ትንተናው ያተኮረው በትውን ጥበብ ላይ ነው፡፡ በዚህም በተጠኚው ማህበረሰብ፣ በአጠቃላይ ዓላማና ግኝቱ የምንለያይ ሲሆን በርዕሰ ጉዳይና በትንተና ዘዴ ያመሳስለናል፡፡

ህይወት (2003ዓ.ም.) ‹‹የመኢኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ›› በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማ የብሄረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን በገላጭ ትንተና ማሳየት ነው፡፡ በተፈጥሮአዊ መቼት ምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተሰበሰቡ የድምጽ፣ የቪዲዮና የፎቶግራፍ መረጃዎችን የተነተኑት ዕድሜ፣ ማህበራዊ የስልጣን ደረጃንና የአሟሟት ሁኔታን መሰረት ያደረገ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ለይተው በማሳየት ነው፡፡ ተጠኚው ማህበረሰብ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ለሁነቶች የሚሰጠውን ስያሜ

መሰረት አድርጋ መተንተኗ ከፎክሎር ጥናት አኳያ ተገቢ ነው፡፡ በለቅሶ ስርዓቱ ክወና ላይ የሚቀርቡ ትዕይንቶችን ትርጉምና ተግባር እንዲሁም የስርዓቱን ማህበራዊ ፋይዳ በገለጻ አብራርተዋል፡፡

ህይወት የለቅሶ ስርዓቱን ክወና እንደሚገልጹ የጠቆሙ ቢሆንም የጥናቱን ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ በግልጽ አላመላከቱም፡፡ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ስነቃሎችን በጥናቱ ለይተው አለማመላከታቸው እንዲሁም ጥናቱ ትኩረት ያደረገው የ‹‹ኔይሬን›› ባህላዊ እምነት ተከታዮች ላይ መሆኑና የሌሎች ማህበረሰብ ክፍሎችን የለቅሶ ስርዓት ያልዳሰሱበትን ምክንያት አለመግለጿ በድክመት ሊገለጽ የሚችል ነው፡፡

ሌላው Abbink( 1992) ህይወት ባካሄደችው ማህበረሰብ ላይ በገላጭ ፍከራ ዘዴ የለቅሶ ስርዓቱን ሂደት ስዕላዊ በሆነ ትንተና አሳይተዋል፡፡ አባይንክ የቀብር ስርዓቱን ሂደትና በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ትዕምርታዊ ጉዳዮችን ነው የተመለከቱት፡፡ ህይወት የብሄረ ሰቡን አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓት ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ቀብር ድረስ ያሉ ሂደቶችን ቢያሳዩም ስነቃሎችን ለይተው ካለመተንተናቸውም በተጨማሪ ከአባይንክ የተሻለ ጥናት አድርገዋል ማለት አይቻልም፡፡ የህይወት ጥናት ከኔ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይና በአብዛ ኛዎቹ ነጥቦች ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን በሚከተለው ትወራዊ ማዕቀፍና በመረጃ መተንተኛ ስነዘዴ እንደዲሁም በግኝቱ ይለያል፡፡

ዘላለም (2004 ዓ.ም.) ‹‹የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ በበና ጸማይ ወረዳ››በሚል ርዕስ በበና ጸማይ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ ትኩረት በማድረግ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔውን ማሳየትና በእያንዳንዱ ስርዓት ክዋኔ ጀርባ ያለውን ትርጉም መግለጽ ነው፡፡

መረጃውን የሰበሰበው በታላሚ ንሞና ዘዴ ተፈጥሮአዊ መቼት ላይ ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ፣ በቃለ መጠይቅና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማካሄድ ነው፡፡ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብን በመከተል ጥናቱን አካሂዷል፡፡ ጥናቱን ለማጠናከር ንድፈ ሀሳባዊና ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት በማድረግ ከቅድመ ሞት እስከ ድህረ ሞት ድረስ ያሉ ስርዓቶችን ሂደት በዝርዝር አሳይቷል፡፡ የዘላለም ጥናት ውጤት በበና ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ የሚያስተላልፈው መልዕክት የማህበረሰቡን ምንጭ (አመጣጥ)፣ አሰፋፈርና የኑሮ ዘይቤውን እንዲሁም ለህይወት ያለውን እይታ የሚገልጽበት መሆኑን ነው ያሳየው፡፡

የዘላለም ጥናት በሚከተለው የጥናት ዘዴ፣ አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓቱን ከመግለጽና ከዓላማ አንጻር የሚያመሳስለን ነገር ቢኖረንም በተጠኚው ማህበረሰብ ባህልና በግኝቱ እንለያ ያለን፡፡

ውቤ (2005ዓ.ም.) ‹‹የቤንች ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ›› በሚል ርእስ የብሄረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ክዋኔውን መግለጽን ዓላማ በማድረግ የለቅሶ ስርዓቱን ከቃል ግጥሞቹ ጋር በማቆራኘት የሚተነትን ጥናት አካሂደዋል፡፡ ጥናቱ ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብን በመከተል የክዋኔ ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን በታላሚ ንሞና ዘዴ በተፈጥሮአዊ መቼት ላይ ኢተሳትፏዊ ምልከታ በማድረግ፣ በቃለ መጠይቅና በተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃውን ሰብስቧል፡፡

የጥናቱ ውጤት ብሄረሰቡ በለቅሶ ስርዓት ክወና ተሳትፎ በማድረግ ታሪኩን የሚያጸናበት፣ የስልጣን ሽግግር የሚያደርግበት፣ የጎሳ የዘር ግንድ የሚገለጽበትና ባህላዊ እምነቱን የሚያ ስጠብቅበት ስርዓት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በብሄረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ላይ የሚከወኑ ስነቃሎ ችን፣ ቁሳዊ ባህሎችንና ትዕምርቶችን በመተርጎም ስዕላዊ ገለጻ ማድረጉ ከፎክሎር ጥናት አኳያ ሲታይ በጥንካሬ የሚገለጽ ነው፡፡

አየሁሽ (2005 ዓ.ም.) ‹‹የወላይታ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ›› ላይ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማ በብሄረሰቡ ዘንድ የሚከወነውን የለቅሶ ስርዓት ገጽታ በመግለጽ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ለሚታዩ ትዕምርቶች ማህበረሰቡ የሚሰጠውን ትርጉም መመርመር ነው፡፡ ለጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በአንድ ቀበሌ ውስጥ በተከሰተ ተፈጥሮአዊ መቼት ላይ በመገኘት ምልከታ በማድረግ፣ በቃለ መጠይቅና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማድረግ ነው፡፡

አየሁሽ በትንተናቸው የብሄረሰቡን የለቅሶ ስርዓት በስፋት በመዘርዘር የትዕምርቶችን ትርጉም በስፋት አሳይተዋል፡፡ ነገር ግን በርካታ የቃል ግጥሞችን ያሰፈረች ቢሆንም ከክዋኔው ጋር በማያያዝ አልተነተኑም፡፡ ሌላው የጥናቷ ወሰን ከወላይታ ዞን የትኛው ወረዳና የትኛው ቀበሌ እንዳተኮረ ያሉት ነገር የለም፡፡ እነዚህ ነጥቦች እንደድክመት ያስተዋልኳቸው ናቸው፡፡ የአየሁሽ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይ፣ ከሰነድ ፍተሻ በስተቀር በሌሎች መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና የፎክሎር ዘውጎችን ከመዳሰስ አኳያ የሚመሳሰል ሲሆን በንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍና በጥናቱ ስነዘዴ እንለያያለን፡፡

ደስታ (2006ዓ.ም.)፡- ‹‹የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ›› በሚል ርእስ ለኤም.ኤ ድግሪ ማሟያነት ያቀረቡት ጥናት ሌላኛው የተቃኘው ጽሁፍ  ነው፡፡ የጥናቱ አላማ የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ላይ ገላጭ ትንተና በማድረግ ስርዓቱን ማሳየት ነው፡፡ ደስታ በሶስት ተፈጥሮአዊ መቼቶች ላይ በመገኘት መረጃዎችን ሰብስበዋል፡፡ የተጠቀሙት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴም ምልከታ፣ቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይቶች ናቸው፡፡ በክወና ንድፈ ሀሳብ ትወራ ማዕቀፍ  ገላጭ ዘዴን በመጠቀም የተሰበሰበውን መረጃዎች ተንትነዋል፡፡

ደስታ በመረጃ ትንተና ክፍሉ የዲዚ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔን በተመለከተ የባላባት፣ የአዛውንቶች፣ የጎልማሶችና የወጣቶች እንዲሁም የህጻናት የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ በሚል በአራት ክፍሎች በመመደብ  ለእያንዳንዳቸውም ቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞትና ድህረ ሞት ለሚፈጸሙ ስርዓቶች ገለጻ ሰጥተዋል፡፡ የለቅሶ ስርዓት ከሚፈጸምላቸ አራቱ ውስጥ ለባላባቶች የሚደረገው የለቅሶ ስርዓት ሰፋ ያለና በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው መሆኑን ደስታ በትንተናቸው በስፋት አመልክተዋል፡፡ በእያንዳንዱ የለቅሶ ስርዓት ላይ የሚታዩ ቁሳዊ ባህሎች የብሄረሰቡን የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአኗኗር ሁኔታዎችን የሚገልጹ መሆናቸውን እንዲሁም በክዋኔው ላይ ከሚቀርቡ ስነ ቃሎች መካከል ውዳሴዎችና የሙሾ ግጥሞች የሚጠቀሱ ሲሆን ግጥሞቹ የሟቹ (ቿ)ን ማንነት፣ እምነት፣ የዘር ግንድ አመጣጥ ወዘተ የሚገልፁ ናቸው በሚል ተንትነዋል፡፡ የሰማኒያ ቀንና የተስካር ስርዓት እንደሚከወን በትንተናው ጠቁመዋል፡፡ ይህ ስርዓት ከክርትና እምነት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ይህን አንድ ላይ አጭቆ ለሁሉም የብሄረሰቡ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት አንዱ አካል አድርጎ ማቅረቡ እንደድክመት የሚገለጽ ነው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ ደስታ እንደፎክሎረኛ የዲዚን ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ትውን ጥበባዊ ክወናዎችን፣ ሀገረሰባዊ ልማዶችን፣ ቁሳዊ ውክልናዎችን በለቅሶው ላይ የሚከወኑ የሙሾ ስነቃሎችን ምስል ከሳች በሆነ መልኩ ገልጸዋል ማለት ይቻላል፡፡

ፍፁም (2006 ዓ.ም)፡- የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር የማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ የፍጹም ጥናት ዋና ዓላማው የብሔረሰቡን ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ከሞት እስከ ግብዓተ መሬት ፍፃሜ ድረስ ያለውን የአከዋወን ሂደት ማሳየትና መተንተን ነው፡፡ ይህንን እና ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ አጥኚው በሁለት ተፈጥሯዊ መቼቶች ላይ

በመገኘት ምልከታ አድርገዋል፡፡ እንዲሁም ስለብሔረሰቡ ባህል ጥልቅ መረጃ አላቸው ተብለው ከታመነባቸው የብሔረሰቡ አባላት ቃለ-መጠይቅ በማድረግና የተተኳሪ ቡድን ውይይት በማካሔድ መረጃዎችን ሰብስበዋል፡፡ የፍጹም ጥናት ትወራዊ ማዕቀፍ በከበራና ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡

የተሰበሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓትን "ለህፃናት የሚደረግ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት" እና "ለአዋቂዎች የሚደረግ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት" በሚል በሁለት ዋና ዋና ምድቦች ከፍለው ተንትነዋል፡፡ በመቀጠል በሁለቱም ምድብ ስር ደግሞ ቅድመ ሞት እና ጊዜ ሞት እንዲሁም ቅድመ ቀብር፣ ጊዜ ቀብር እና ድህረ ቀብር በሚሉ ንኡሳን እርከኖች ከፋፍለው ነው ትንተናውን ያቀረቡት፡፡ እድሜ፣ ፆታ እና ማህበራዊ ደረጃ በብሔረሰቡ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ወቅት የሚፈጥሯቸው የተወሰኑ ልዩነቶች እንዳሉም በትንተናው አሳይተዋል ፡፡

ሌላው ከመቀበሪያ ቦታ ጋር በተያያዘ የሸካቾ ብሔረሰብ አዋቂዎች ቀብር የሚፈፀመው በሟች መኖሪያ ቤት አቅራቢያ በሚገኝ የሟች ማሳ ውስጥና በአንድ አካባቢ የሚገኙ ሰዎች በጋራ ተስማምተው ኮረብታማ ስፍራ ላይ በሚያሰናዱት ስፍራ ነው፡፡ በሁለቱም መካነ መቃብሮች ቀብር በሚፈፀምበት ወቅት በርከት ያሉ ዛፎችን በመቃብሩ ዙሪያ መትከል የተለመደ ተግባር ነው፡፡

ለህጻናት በቅድመ፣ ጊዜ ሞትና ድህረ ሞት የሚከናወኑ በርካታ ተግባራትን ግልጽ አድርጎ በጽሁፍ ማስቀመጥ ችሏል፡፡ ነገር ግን ይህ ለህጻናት የሚደረገው የለቅሶና ዛፍ ላይ የመቅበር ስርዓት አሁንም ድረስ ይከወን አይከወን ያመለከቱት ነገር የለም፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክወናው ከመለወጥ፤ ከመበረዝና፣ ከመጥፋት አደጋ ጋር ተያይዞ ያለውን አሁናዊ ገጽታ የጠቆሙት ነገር የለም፡፡ ስርዓቱ በተሟላ መልኩ እየተከወነ ከሆነም ለመቆየቱ እንደምክንያት ሊጠቀስ የሚችል ነገር ቢኖረው መልካም ነበር የሚል አስተያየት አለኝ፡፡ ሌላው ሊነሳ የሚችለው የመንጃ ጎሳ አባላት ከሸካቾ ብሄረሰብ ጎሳዎች አንዱ እንደሆኑ በመግለጽ ማህበራዊ መገለል የሚደረግባቸው ቢሆንም ለሙሾ ድርደራ የሚመረጡ መሆናቸውን ፍጹም በትንተናቸው ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን የጎሳው አባላት የለቅሶ ስርዓት ከሌላው ጎሳ የሚለይ መሆን አለመሆኑንም ያሉት ነገር የለም፡፡ ምክንያቱም የጥናቱ ዓላማ የሸካቾን ብሄረሰብ ጎሳዎችን አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓት መግለጽ እንደሆነ ስለሚታመን ነው፡፡ እንዲሁም ጋሻ፣ ጦርና ከበሮ በለቅሶ ስርዓት ክወና

ላይ የሚቀርቡ ቁሶች ናቸው፡፡ ነገር ግን  በጥቂቱም ቢሆን ‹‹ሞትን ለመውጋት›› በሚል ለጦር ከሰጠው ገለጻ በስተቀር እንደፎክሎረኛ ስለሌሎቹ ቁሶች ያሉት ነገር የለም፡፡ በተጨማሪም የስርዓቶችን አፈጻጸም ሂደት እንጂ በስፋት የተመለከቱት ስነቃሎችን፣ ቁሳዊ ባህሎችን ትውን ጥበባዊ ጉዳዮችን በወጉ ለይተው አለማሳየታቸው በድክመት ሊጠቀስ የሚችል ነው፡፡

አበራች (2010 ዓ.ም.) ‹‹የቦሮ -ሽናሻ የለቅሶ ስርዓት ክወና የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና›› በሚል ርዕስ የዲስኩር ትንተና ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የቦሮ-ሺናሻን የለቅሶ ስርዓት ክወና የቋንቋ አጠቃቀም መተንተን ሲሆን የለቅሶ ስርዓቱ የቋንቋ አጠቃቀም መተንተን፣ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚገለጹ ትዕምርቶች ቋንቋ ውክልናን መፈከር፣ ከሟች ዕድሜ፣ ጾታ፣ ማህበራዊ ደረጃና የአሟሟት ሁኔታ ጋር በተያያዘ ያሉ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነቶችን መተንተን የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን የያዘ ነው፡፡ ጥናቱን ያካሄደችው በከበራና ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብ ላይ በመመርኮዝ ነው፡፡ በዚህ ማዕቀፍ ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ላይ በማትኮር ገላጭ የምርምር ዘዴን ተጠቅመዋል፡፡ የጥናቱ አካባቢ ወሰን እና መረጃ አቀባዮች የተለዩት በአመቺ እና በታላሚ የንሞና ዘዴ ሲሆን መረጃዎቹን የሰበሰቡት ተፈጥሮአዊ መቼት ላይ በመገኘት በተሳትፏዊ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ነው፡፡

አበራች በመረጃ ትንተና ክፍላቸው በተጠኚው ማህበረሰብ ዘንድ የሚፈጸመውን የለቅሶ ስርዓተ ክወና ዝርዝር መረጃ የሚሰጥ ትንተና አካሂደዋል፡፡ የትንተና አደረጃጀቱ የሟችን ማህበራዊ ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ጾታና የአሟሟት ሁኔታን መሰረት ያደረገ ሲሆን በእያንዳንዳቸው የሚከወኑ ስርዓቶችን ቅድመ፣ ጊዜና ድህረ የሚሉ የተግባር ጊዜ ሂደት  ቅደምተከተሎችን በመለየት ነው የተነተኑት፡፡ የእያንዳንዱን ክወና ምክንያታዊ መፈጸሚያ ተንትነው አሳይተዋል፡፡

የአበራች ጥናት ከዓላማው አንጻር ሲታይ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ስነቃላዊ፣ ቁሳዊ፣ ልማዳዊና ትውን ጥበባዊ ጉዳዮችን በስፋት ከማሳየትና ከመንገር በዘለለ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ጥቅም ላይ የሚውለው ቋንቋ (ዲስኩር) ከመደበኛው ቋንቋ የተለየበትን ምክንያት፣ ጥቅሙንና ከማህበረሰቡ ጋር ያለውን ቁርኝት በሚፈክር መልኩ በስፋት አለማሳየታቸው በድክመት የሚጠቀስ ነው፡፡ ሌላው በትንተናው በኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚፈጸመው የ40 ቀን እና የተከሳር ስርዓት የሁሉም የተጠኚው ማህበረሰብ የለቅሶ

ስርዓት ተደርጎ ነው የተተነተነው፡፡ ይህ ደግሞ ባህላዊነቱን መጠበቅ አለመጠበቁንና የእስልምና እምነት ተከታዮችንና ሌሎችን ለምን የጥናቱ አካል እንዳላደረገች ያለችው ነገር አለመኖሩም እንደድክመት ይጠቀሳል፡፡

ይህ ጥናት ሞት በመከሰቱ የሚከወኑ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን ከማሳየትና በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚያመሳስሉን ነጥቦች ሲኖረን ልዩነታችን  የአበራች ጥናት ዋና ዓላማና ግኝቱ የቦሮ-ሽናሻን የለቅሶ ስርዓት ክወና የቋንቋ  አጠቃቀም በገላጭ ዘዴ መተንተን  ሲሆን የኔ ጥናት ዋና ዓላማ የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓትን በኢትኖግራፊያዊ ዘዴ በመግለጽ መፈከር ነው፡፡

ከዚህ በላይ የተቃኙት ዘጠኝ ጥናታዊ ጽሁፎች በሞት ክስተት ስርዓተ ክዋኔ ላይ የተደረጉ ጥናቶች መሆናቸው ከኔ ጥናት ጋር ያዛምደናል፡፡ ሌላው በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴና መሳሪያ እንዲሁም ፎክሎራዊ የሆነ ጥናት ከማካሄድ አኳያ ያመሳስሉናል፡፡ ከቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎች መካከል በቦሮ-ሽናሻ ላይ የተሰራው የአበራች ብርሃኑ ጥናት በለቅሶ ስርዓቱ ላይ የሚከወኑ ስርዓቶች የቋንቋ አጠቃቀም (ዲስኩር) ላይ ያተኮረ በመሆኑ  በዓላማ እንለያለን፡፡ ነገር ግን አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓቱን ሂደት ከማሳየት አኳያ የሚያመሳስሉን ጉዳዮች አሉን፡፡ በተመሳሳይ የደስታ ወ/መስቀል፣ የፍጹም ብርሃኑ፣ የህይወት አበሩ፣ የአየሁሽ ቶማ፣ የውቤ ታደገና የዘላለም ፋንቱ ጥናቶች የየተጠኚ ማህበረሰቦችን አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ  ያሳዩ በመሆናቸው የምንመሳሰል ቢሆንም በንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍና በጥናቱ ዘዴ እንለያለን፡፡ የኔ ጥናት ኢንፍራካልቸራል ሞዴል በፎክሎር ትንተና የሚለውን ጽንሰሀሳባዊ ንድፈሀሳብን እና ኢትኖግራፊያዊ የአጠናን ዘዴን የሚከተል ሲሆን ተጠቃሾቹ ጥናቶች ክዋኔ ተኮር ንድፈ ሀሳብና ገላጭ የትንተና ዘዴን የሚከተሉ ናቸው፡፡

በኢንግሊዝኛ ቋንቋ ከተጠኑት የተቃኙ ጥናቶች መካከል በመኢኒት ብሄረሰብ ላይ በ(Abbink) የተጠናው ጥናት በርዕሰ ጉዳይ፣ለክዋኔው የትርጉም(Interepretation)ትንተና በማካሄድ እንመሳሰላለን፡፡ ሌላው በኬኒያ አባኞል ማህበረሰብ ላይ የተካሄደው የ(Alembi) ጥናትም ከኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ጥናቱ የሚካደው በለቅሶ ሙሾ ስርዓት ላይ መሆኑ፣ በንድፈ ሀሳብና በትንተና ዘዴው ነው፡፡ ነገር ግን በጥናቱ ዓላማ እንለያየለን፡፡ እንዲሁም ጥናቱ ከሀገራችን ውጭ ባለ ማህበረሰብ ላይ በውጭ ቋንቋ የተጠና መሆኑ ያለያየናል፡፡ ባጠቃላይ ልዩነቶቻችን እንደተጠበቁ ሆነው በቅኝቱ በድክመት የተመላከቱ ድክመቶችን ለመቅረፍ ይህ ጥናት ይጥራል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. የጥናቱ ስነ ዘዴና ንድፍ

ይህ ክፍል አጠቃላይ ጥናቱ የተካሄደበትን ዘዴና ሂደቱን የሚገልጽ ክፍል፡፡

### 4.1. የጥናቱ ስነ ዘዴ

የጥናትና ምርምር ስነ ዘዴ የጥናትና ምርምሩን ዓይነት፣አካሄድና የንሞና ዘዴን የሚወስንና ጥናትና ምርምሩ የሚካሄደበትን ቅደም ተከተላዊ ሁኔታን የሚያሳይ መስታወት ነው፡፡ ይህ ጥናት በአይነታዊ ስነ ዘዴ (Qualitative Method) የሚካሄድ ነው፡፡

ዓይነታዊ ምርምር ለዚህ ጥናት ተመራጭነቱ ከሚሰበሰበው መረጃ ባህሪ አንጻር ሲሆን ዓይነታዊ ስነ ዘዴ ተራኪና፣ ክፍት በመሆኑ በተፈጥሮአዊ መቼት የሚታየውን ሁነት ለመግለጽ፣ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለመተንተንና ለመፈከር ለአጥኚው ነጻነት የሚሰጥ እና አጥኚው በምርምር ሁነቱ ላይ አጠቃላይ የሆነ እይታ እንዲኖር የሚያደርግ በመሆኑ ነው፡፡ Give (2008,77) ለጥናቱ ውጤታማነት ካለው ጠቀሜታ አንጻር ዓይነታዊ ስነዘዴ ተመራጭ መሆኑን በመግለጽ ምክንያቱ ደግሞ ዓይነታዊ ስነ ዘዴ ተራኪና፣ ክፍት(ነጻ) በመሆኑ እንደሆነ ምክንያቱም ጭምር ይገልጻሉ፡፡

### 4.2. የጥናቱ ዘዴ

የጥናትና ምርም ዘዴ ጥናቱን ለማካሄድ ተግባር ላይ የሚውሉ ቅደም ተከተሎች (ስልቶች) ወይም ምርምሩ የሚካሄድበትን ዘዴ ለመገንባት የሚያስችሉ መሳሪያዎችና ተግባራትን የሚመለከት ነው። ይህ ጥናት በኢትኖግራፊያዊ ዘዴ የተካሄደ ነው፡፡ ኢትናግራፊ አንዱ ከመስክ ዓነታዊ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው።Sangasuban (2011,568) Fettermanን (1998) በመጥቀስ እንዳብራሩት ኢትኖግራፊያዊ ዘዴ የአንድን ቡድን ወይም ባህል የሚገልጽ ሳይንስ ነው ፡፡ በተመሳሳይ ሀሳብ በፎክሎር ጥናት ኢትኖግራፊ አንድን ማህበረሰብ (ቡድኖችን) ለማወቅ የሚካሄድ የመስክ ጥናት መሆኑን በመጥቀስ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ ምልከታን የመግለጽና የመተንተን ሂደት

መሆኑን Sims and Stephens (2005,202) ይገልጻሉ፡፡ Sangasuban (2011,568) Walcottን (1999) በመጥቀስ እንደገለጹት ለጥናትና ምርምር የሚመረጡ በርካታ ዘዴዎች ቢኖሩም ኢትኖግራፊያዊ ዘዴ በሚከተሉት ጠቀሜታዎቹ ተመራጭ ነው፡፡ እነዚህም በግለሰብ ወይም በቡድን ሊካሄድ የሚችል መሆኑ፣ በየትኛውም ቦታ ሊካሄድ የሚችል መሆኑ፣ ሌሎች እንዲተባበሩ ከመለማመጥ ይልቅ ተሳትፎን የሚጋብዝ መሆኑ፣ ለተጨማሪ ምርምር የሚሆን በቂና ጥልቀት ያለው መረጃ የሚገኝበት መሆኑ፣ ለጥናቱ ውጤታማነት ብቻም ሳይሆን አደጋን የመጋፈጥ ልምድን የሚያጎለብት መሆኑ፣ ሌላ ቋንቋን የመልመድ አጋጣሚን የሚፈጥር መሆኑ፣ ሙያ ከግል (ማህበራዊ) ህይወት ጋር እንዲተሳሰር የሚያደርግ መሆኑ፣ እንዲሁም አጥኚው ቤተኛ ሆኖ እውነታን እንዲቃኝ በማድረጉ፣ በቃል የሚገለጸውንና የማይገለጸውን የሰዎችን እውነተኛ ባህሪ በተፈጥሮአዊ መቼት ለማወቅ የሚረዳ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኢትኖግራፊያዊ የጥናት ዘዴ በዋናነት የመስክ ስራ ላይ መሰረት የሚያደርግ፣ ከባህላዊ ሀብቶች መካከል የማህበረ-ባህላዊ አውድ፣ ሂደትና ምንነት ጥናት ላይ የሚያተኩር፣ ነጻና ምርምራዊ ጫና የማይደረግበት፣ እለታዊና ቀጣይነት ያለው ቀረጻና ማስታወሻ የመያዝ ስራ የሚከናወንወበትና መረጃዎችን በዓይነታዊ የሚተነትን መሆኑን Whitehead (2004,5) ይገልጻሉ፡፡

በነዚህ ምክንያቶች ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት በተፈጥሯዊ መቼት ላይ በመገኘትና በቤተኛነት በመሳተፍ እውነታን በመቃኘት፣ በቃል የሚገለጸውንና የማይገለጸውን የከዋኞችን እውነተኛ ባህሪ ለማጥናት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ያለውን የለቅሶ ስርዓት ክዋኔን ሂደት መረጃ ለመቃኘት ስል መርጫለሁ፡፡ እንዲሁም የተጠኚውን ማህበረሰብ ቋንቋ የምችል በመሆኑ ሌሎች እንዲተባበሩ ከመለማመጥ ይልቅ በመስክ ላይ በመቆየት ለጥናቱ ትክክለኛና የተሟላ መረጃ በመሰብሰብ በተጠኚው ማህበረሰብ ባህል እይታ መሰረት ለመግለጽና ለመተንተን ይህን ዘዴ መርጫለሁ፡፡

የጥናቱ ሞዴል መሰረተ ባህል (Infracultural model) ሲሆን ይህ ንድፈ ሃሳብ የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱ ክዋኔ ተኮር በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ሞዴል በአንድ በተወሰነ የባህል አውድ ላይ የሚከወኑ ቃላትንና ክንውኖች (words and action) በራሳቸው በባህሉ ባለቤቶች ትርጉም ለማብራራት ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ በአንድ ባህል አውድ ላይ የሚከወኑ ቃላትና ክንውኖች ፍች በተጠኚው ማህበረሰብ የእይታ መነጽር የሚተነተን

መሆኑን Alembi (2002,22) እና (2008) ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም ይህ ንድፈ ሃሳብ ክዋኔውን፣ የሚከወንበትን አጋጣሚ፣ ታዳሚን፣ የክዋኔ ቦታና ማህበራዊ አውዶችን፣ መልዕክት፣ አቀራረብ የሚመለከት ነው፡፡

በመሆኑም የመረጃዎቹ ትንተና በባህሉ ባለቤቶች ትርጉም እንዲሰጥ፣ በድርጊትና በቃላት የሚቀርቡትን ሀሳቦች ብቻ ሳይሆን ድርጊቶቹ ከቀረቡባቸው አኳኋኖች፣ቃላቱ ከተነገሩባቸው ድምጾች ጋር የተያያዙ ትርጉሞችን ለማካተት ስለሚያግዝ ለዚህ ጥናት ሞዴሉ ተመርጧል፡፡

## 4.2.1. የመረጃ ምንጮችችና የንሞና ዘዴ

ይህ ክፍል የተጠኚዎች ማንነት፣የመረጃ አቀባዮች አመራረጥና የንሞና ዘዴን የሚመለከት ነው፡፡ተጠኚዎቹ የየም ብሄረሰብ ሲሆኑ በልዩ ወረዳው ላይ በማትኮር የተካሄደ ጥናት ነው፡፡

ጥናቱ በልዩ ወረዳው ካሉ 31 የገጠርና 3 አነስተኛ የከተማ ቀበሌዎች ውስጥ በስድስት ቀበሌዎች ላይ ትኩረት በማረግ ተካሂዷል፡፡እነዚህ ስድስቱ ቀበሌዎች የተመረጡበት ምክንያትም የተቀሩት ቀበሌያት ከአጎራባች ክልሎችና ዞኖች ጋር የሚዋሰኑ በመሆናቸው ባንድም ሆነ በሌላ የባህል መወራረሶች ያሉባቸው በመሆናቸው የለቅሶ ስርዓቱ የመበረዝ ዕድሉ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል በሚል ስጋት ነው፡፡ በሌላ በኩል ከጊዜና ከወጪ አንጻርም ሁሉንም ቦታዎች ለማዳረስ የማይቻል በመሆኑ ነው፡፡በመሆኑም (ሸሞ መቴሎ፣ኢዲያ፣ደሪ ኤረቶ፣ ሰሙ አዋሾ፣የላይኛው ከሸሊ እና አዝጊ ዘምዳ የሚባሉ 6 ማዕከላዊ ቀበሌያት ላይ ጥናቱ ዒላማ አድርጓል፡፡

ለጥናቱ ተገቢ መረጃ አቀባዮችን ለመመልመል የተመረጠው የንሞና ዘዴም ታላሚ የንሞና ስልት (Purposive sampling technique) ነው፡፡ምክንያቱ ደግሞ የጥናቱ መረጃ የብሄረሰቡን ባህልና ታሪክ ጠንቅቀው ያውቃሉ ተብለው ከሚመረጡ የብሄረሰቡ አባላት የሚሰበሰብ በመሆኑ ነው፡፡ መረጃዎች የተሰበሰቡት ሙሉ በሙሉ ከመስክ ሲሆን ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የንድፈ ሀሳብና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት በቤተመፃህፍት ተካሂዷል፡፡ መረጃዎቹ የተሰበሰቡት ከመጋቢት እስከ ሚያዝያ 2011 ዓ.ም ባሉት ሁለት ወራት ውስጥ ሲሆን መረጃ አቀባዮቹ ስለብሄረሰቡ ታሪክና ባህል ጠንቅቀው ያውቃሉ ከሚባሉ ከሁለቱም ፆታዎች የተመረጡ በተለያየ የእድሜ ክልል የሚገኙ የብሔረሰቡ

አባላት ናቸው፡፡ ከስድስቱ ቀበሌያት ከእያንዳንዳቸው አንድ ወንድና ሴት በድምሩ አስር ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ተመርጠው ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የጾታ ስብጥሩ በዚህ መልኩ የሆነበት ምክንያት በብሄረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የጋራና የተናጥል ክወና ያላቸው በመሆኑ ሁሉን አቀፍ መረጃ ለመሰብሰብ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ በተጨማሪም ተጠኚው ማህበረሰብ ማን ምን ዓይነት እውቀት እንዳለው ያውቃልና  መረጃ ለመሰብሰብ ከተመረጡት ቀበሌያት ውጭ ያሉ ሶስት የብሄረሰቡ አባላትም ባላቸው ዕውቀትና የተለያዩ የታሪክና የባህል መረጃዎችን በማጠናቀር እውቅናቸው በመረጃ ሰጪዎቹ ጥቆማ መሰረት የመረጃ ምንጭ ሆነዋል፡፡ ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች በእድሜ በአማካይ ዝቅተኛው 50 ሲሆን ከፍተኛው 90 ነው፡፡ እንዲሁም በቡድን ተኮር ውይይት ለመሳተፍ ከተመረጡ አስር ሰዎች መካከል ሶስቱ ሴቶች ሲሆኑ የተቀሩት ወንዶች ናቸው፡፡ ከነዚህም በዕድሜ ዝቅተኛው 30 ሲሆን ከፍተኛው 70 ነው፡፡

## 4.2.2. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

እንደየጥናቶቹ ዓይነት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ወይም ቴክኒኮች የተለያዩ ናቸው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ምርጫው የሚወሰነው ለጥናቱ ተገቢ መረጃ በማስገኘት አቅሙ ነው፡፡ በኢትኖግራፊያዊ የጥናት ዘዴ በመረጃ መሰብሰቢያነት ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና መዛግብት ፍተሻ ተገቢዎች እንደሆኑ ናቸው በማለት Sangasuban (2011,568) Angrosino, (2007)ን በመጥቀስ ሲያስረዱ ለማ (2002፣140) ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይትና ሰነድ ፍተሻ ለፎክሎረኛ ዋነኛቹ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እንደሆኑ ያስገነዝባሉ፡፡ በመሆኑም እነዚህ አራቱ ዘዴዎች ለዚህ ጥናት ዓይነታዊ መረጃን ለመሰብሰብ ወሳኝ በመሆናቸው  ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 4.2.2.1. ምልከታ

ምልከታ ጥናትና ምርምሩ ወደሚካሄድበት (ወደሚከወንበት) ቦታ በመሄድ ከሚጠናው ጉዳይ ጋር የተያያዙ ክንውኖችንና አካባቢያዊ የተፈጥሮ ገጽታዎችን በንቃትና በአስተውሎት በአዕምሮ ውስጥ መመዝገብን የሚመለከት ነው፡፡ Finnegan (2005,87) በምልከታ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥያቄዎች፣ ቴክስቱ ወይም ሁነቱ በተፈጥሮአዊ መቼቱ እንዴትና መቼ እንደሚከወን፣ እንዴት እንደሚቀናጅና እንደሚዘጋጅ፣ ማን እንዳለበት፣ ባህሪው እንዴት

እንደሚንጸባረቅና የሚጠበቀው ምን እንደሆነ፣ጥቃቅን የክወና ቅንጣቶችን ጭምር ከዋኞቹ እንዴት እንደሚያፈልቁ፣ የታዳሚዎቹ ሚና ምን እንደሚመስል እና ስርዓቱ ከእለት ተእለት የህይወት ሂደት በተለየ መልኩ እንዴት እንደሚቀነበብ መቃኘት መሆኑን ያስገ ነዝባሉ::

ይህ ጥናት በተፈጥሮአዊ መቼቱ ላይ በመገኘትና ከፊል ተሳትፎ በማድረግ ከቅድመ ለቅሶ ጀምሮ ድህረ ቀብር ድረስ ያሉ ስርዓቶችን በመቃኘት በቪዲዮና ፎቶ ካሜራዎች በመቅረጽ፣ በምልከታው ውቅት ትዝብትን የሚፈጥሩና ሊረሱ የሚችሉ ሁነቶችን በማ ስታ ወሻ በመመዝገብ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ የከፊል ተሳትፎው ምክንያትም በክወናው ላይ ሙሉ ተሳትፎ የማደርግ ከሆነ በአትኩሮት የሚያዙ መረጃዎች እንዳያመልጡ በማሰብ ነው፡፡

## 4.2.2.2. ቃለ-መጠይቅ

ያለው (2009 ዓ.ም.) እና ለማ (2002.ዓ.ም ገጽ41) እንደሚያስረዱት ቃለ መጠይቅ መረጃ ሰብሳቢውና አቀባዩ ፊት ለፊት ተገናኝተው በጥያቄና መልስ መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡ ራሱን ችሎ ወይም ከምልከታ በኋላ አጋዥ መረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በዚህ ጥናትም በምልከታ ወቅት ያልተንተጸባረቁ ምክንያታዊና ታሪካዊ መረጃዎችን ለማኘት፣ በምልከታ ጊዜ ጥያቄና ጥርጣሬ ለፈጠሩ ጉዳዮች መልስ ለማግኘት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ቃለ-መጠይቅ አገልግሎት ላይ የዋለው ስለ ብሄረሰቡ አጠቃላይ ታሪክና የለቅሶ ስርዓቱን ጠንቅቀው ያውቃሉ ተብለው በአግባቡ ከተመረጡ መረጃ አቀባዮች መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ስለየም ብሔረሰብ ባህል ጥልቅ መረጃ አላቸው ተብለው ከሚታመንባቸው ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ነጻ ቃለ-መጠይቅ በማዘጋጀት በመቅረጸ ድምጽ በመቅዳትና ፎቶግራፍ በማንሳት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ነጻ ቃለ መጠይቅ የተመረጠው አጥኚው ጥቂት ጥያቄዎችን ብቻ አስቀድሞ በማዘጋጀት ቃለመጠይቅ ከጀመረ በኋላ ከምልልሱ በርካታ ጥያቄዎችን የሚያመነጭበት እና የሚጠይ ቅበት በመሆኑ ለአጥኚው እና ለመረጃ ሰጪው ሰፊ ነጻነት በመስጠት ጥሩ የሆነ መግባባት የሚፈጠርበት በመሆኑ ነው ያለው (2009 ዓ.ም.)፡፡

### 4.2.2.3. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

በቃለ መጠይቅም ሆነ በምልከታ ያልተሟሉ መረጃዎችን፣ እርስበርስ የሚፋለሱትን ሃሳቦች በአግባቡ በመለየት ትክክለኛውን መረጃ ለማጣራት የተተኳሪ ቡድን ውይይት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ለዚህም በየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ዙሪያ በቂ እውቀት አላቸው ተብለው የታመኑ ሰዎች ለቡድን ውይይቱ ተመርጠዋል፡፡ ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተጠቀምኩት በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ወቅት የተገኙ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥና አዳዲስ መረጃዎችን ለማገኘት የመወያያ ጥያቄዎች በማዘጋጀት የተቀናጀ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ያለው (2009 ዓ.ም) በተተኳሪ ቡድን ውይይት እስከ 12 ሰዎችን ማሳተፍ እንደሚቻል ሲገልጹ Kruegor (1994,79) አባላቱ ከ8-10 ቢሆኑ የተሻለ እንደሚሆን ያስረዳሉ፡፡ ለዚህ ጥናት ከስድስቱም ቀበሌያት የተውጣጡ አምስት ወንዶች፣ አራት ሴቶች እንዲሁም አንድ የባህል ልማት ባለሙያን አካቶ በድምሩ 10 ሰዎች በሁለት ቡድን ተመድበው ሁለት ጊዜ ውይይቱ ተካሂደዷል፡፡

ይህ ዘዴ ከቃለ መጠይቅ የሚለየው በርካታ ሰዎች በአንድ ጊዜ መሳተፋቸው ነው፡፡ በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የኔ ሚና የነበረው ጻር ሆኖ በመከታተል ለተወያዮች ጥያቄ መስጠት፣ውይይቱ ከጭብጡ እንዳያፈነግጥና በአንድ ግለሰብ ቁጥጥር ውስጥ እንዳይሆን መቆጣጠር፣ ሁሉም ተሳታፊዎች በውይይቱ እኩል እድል እንዲያገኙ በማድረግ፣ ተቃራኒ ሀሳቦች ሲቀርቡ አለመጫን፣ ተወያዮች ያልገባቸውን መንፈስ ማብራራት፣ የውይይቱን አቅጣጫ መቆጣጠርና የመሳሰሉ ተግባራትን ማከናወን ነበር ፡፡

### 4.2.2.4. ሰነድ ፍተሻ

ሰነድ ፍተሻ ለምርምር ተብሎም ይሁን ለሌላ ተግባር የተከማቸን መረጃ ለጥናት መጠቀምን የሚመለከት ነው፡፡ Sangasuban (2011,568) ፡፡ የጥናቱን ርዕስ የተመለከቱ በተለያዩ ቤተ መጽሐፍትና በሌሎችም መረጃ ማከማቻዎች የሚገኙ የጽሁፍ፣የድምጽና የምስል ሰነዶች ተፈትሸው የትንተናው አካል የሚሆኑበት ነው፡፡ በዚህም መሰረት በየም ልዩ ወረዳ ባህል፣ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት አማካይነት በለቅሶ ስርዓት ላይ በማትኮር ተቀርጸው የተሰነዱ አንድ የቪዲዮ፣ በብሄረቡ ታሪክ መጽሀፍና ሼኡ ቁጥር አንድ በተሰኙ

መጽሄት ላይ የሰፈሩ የለቅሶ ስርዓትን የተመለከቱ መረጃዎች የትናተናው አካል ተደርገዋል፡፡የተመለከትኳቸው መረጃዎች ምንም ዓይነት የእርማት ተግባር ያልተደረገባቸውና ጥሬ መረጃዎች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ለ2 ወራት ያህል ከብሔረሰቡ ጋር ባደረኩት የመስክ ላይ ቆይታ የብሄረሰቡን የለቅሶ ስርዓት የድምጽ 1.26 GB፣ የቪዲዮ 23.10 GB እና 249 ፎቶ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

## 4.3. የመረጃ አደረጃጀትና ትንተና

ይህ ክፍል ከመስክ የተሰበሰበውን መረጃ በተገቢው መንገድ በመልክ በመልኩ መመደብንና ትንተናው የሚካድበትን መንገድ የሚመለከት ነው፡፡

### 4.3.1. የመረጃ አደረጃጀት

መረጃን ማደራጀት ከመስክ  የተሰበሰበውን መረጃ በተገቢው መንገድ በመልክ በመልኩ መመደብን የሚመለከት ነው፡፡

ያለው (2009 ዓ.ም 240) የመረጃ አደረጃጀትን በሚመለከት ‹‹…ትንተናውን ለማካሄድ እንዲቻል መረጃው ለትንተና በሚያመች መልኩ ተደራጅቶ፣ ተቀናጅቶና ትርጉም በሚሰጥ መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡››ይላሉ፡፡ የመጀመሪያው ተግባር መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት ክፍተት የታየባቸውን ነጥቦች መለየት ነበር፡፡ በዚህ ተግባር ለተተኳሪ ቡድን ውይይት ከተለዩት አምስት ሴቶች ውስጥ ሁለቱ በቀጠሮው እለት አለመገኘታቸው ተለይቷል፡፡ ነገር ግን አብላጫዎቹ ስለተገኙ ውይይቱን በማካሄድ የተሟላ መረጃ ማግኘት ስለተቻለ ዳግም መቅጠር ባለማስፈለጉ የሁለቶቹ ተሳትፎ መቅርቱ ተረጋግጧል፡፡ እንዚሁም በቁልፍ መረጃ አቀባይነት ከተለዩት መካከል አንድ ግለሰብ በህመም ምክንያት መረጃ ለመስጠት አልቻሉም፡፡ሆኖም በሌሎቹ ቁልፍ መረጃ አቀባዮችና በቡድን ተኮር ውይይት ለጥናቱ የተሟላ መረጃ መሰብሰብ መቻሉ ታውቋል፡፡ቀጣዩ ተግባር በመቅረጸ ድምጽና በቪዲዮ ካሜራ የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ወደ ጽሁፍ መቀየር ነበር፡፡ ወደ ጽሁፍ ስቀይርም የመረጃ ሰጪዎቹ የድምጽ ቃና፣ የአካል እንቅስቃሴና አውዳዊ ገጽታዎችን በሚጠቁም መልኩ በቅንፍ በጽሁፍ በማስፈር ያልተሟሉ መረጃዎችን በማስወገድና የተሟሉትን ደግሞ በቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞትና ድህረ ሞት የሚፈጸሙ

ስርዓቶች በሚሌ ክፍሎችና ፎክሎራዊ ዘውጎች በመለየት በመልክ በመልካቸው በማደራጀት ነው ወደ ትንተና የገባሁት፡፡

### 4.3.2. የመረጃ ትንተና

በሁለት ተፈጥሯዊ የለቅሶ መቼት/natural setting/ ላይ በመገኘት ምልከታ በማድረግ፣ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ፣ በቡድን ተኮር ውይይትና በመዛግብት ፍተሻ የለቅሶ ስርዓት ክወናን የተመለከቱ መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ፡፡ መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኃላ ከመገኛ ቋንቋው ወደ አማርኛ ለመተርጎም እኔ ቋንቋውን የምችል ቢሆንም ግልጽ ያልሆኑና ለመተርጎም አሻሚ የሆኑትን ከመረጃ አቀባዮቹ በመጠየቅ ከመስክ መልስ በፊት መረጃዎቹን የማስተርጎም ስራ ተከናውኗል፡፡

ለማ (1999 ዓ.ም 5) Fineን (1984,150) ዋቢ በማድረገረ እንዳመለከቱት የመደበኛ አቻዊነት እና የፍጹም አቻዊነት የትርጉም ስልቶች ለፎክሎር ትርጉም የተለየ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ከእነዚህ የትርጉም ስልቶች ለዚህ ጥናት የሚስማማው የመደበኛ አቻዊነት የትርጉም ስልት በመሆኑ መረጃዎቹ የተተረጉሙት በዚህ የትርጉም ስልት ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ የትርጉም ስልት ትኩረት የሚሰጠው በቅርጽም ሆነ በይዘት የመገኛ ቋንቋውን መልእክት ለመረዳት ነው፡፡ ስለሆነም የመገኛ ቋንቋው ጽንሰ ሀሰብ፣ ከመመለሻ ቋንቋው ጽንሰ ሀሰብ ጋር እንዲመሳሰል ወይም እንዲስማማ ጥረት እየተደረገ የትርጉም ስራው ተከናውኗል፡፡

በዚህ የትርጉም ስራ ሁለት ግለሰቦች አጋዥ የሆኑኝ ሲሆን እነዚህ ግለሰቦች የብሄረሰቡን ባህል ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፣ መገኛ ቋንቋውን እና መመለሻ ቋንቋውንም በደንብ በመቻላቸው እገዛቸው የጎላ ነበር፡፡ በዚህ መንገድ መረጃዎቹ ወደ አማርኛ ጽሁፍ ተቀይረዋል፡፡ የትርጉም ስራው ውስጥ የተካተቱት ሁለቱ ቋንቋዎች ከተለያየ ባህልና አካባቢ በመሆናቸው ግድፈቶች ሲያጋጥሙ ማብራሪያዎችን /explanatory notes/ በመጠቀም የአማርኛ አቻ ላልተገኘላቸው የየምኛ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦች በየሚገኙባቸው ቦታዎች ፊት ለፊት ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል ፡

የተሰበሰቡ መረጃዎችን በዚህ መልኩ በመለየት በማመቻቸት ለትንተና ካዘጋጀሁ በኋላ ባህሉ በሚሰጣቸው ስርዓታዊ መጠሪያዎች መሰረት ነው የለቅሶ ስርዓቱን ሂደታዊ ክወና

በመከተል መረጃዎች የተተነተኑት፡፡ ይህ ማለት ቀደም ሲል በጠቀስኳቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች መረጃዎችን እያደጋገፍኩና እያስማማሁ ተጠቅሜለሁ፡፡መረጃዎቹ በሚሰበሰቡበት ወቅትም ሆነ ከተሰበሰቡ በኋላ የእያንዳንዱ ክዋኔ ትዕምርትም ሆነ ትርጉም ከክዋኔው እና በባህሉ እይታ በመሰረተ ባህል ሞዴል (Infracultural Model) ንድፈ ሃሳባዊ ማዕቀፍ የማህበረሰቡን ባህላዊ ትርጉም መነሻ በማድረግ፣ ክወናው በገለጻ፣ባህሉ በፍከራ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. የመረጃ ትንተና

### 5.1. የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና

ይህ ጥናት የሚያተኩረው በየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ፣ በመዛግብት ፍተሻና በቡድን ውይይት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

የሰው ልጅ በተለያዩ ምክንያቶች መሞቱ አይቀሬ ነው፡፡ ሞት የተፈጥሮ ህግ ነው፡፡ ጥፋት ሰራም አልሰራም መሞቱ አይቀሬ ነው፡፡ በየም ብሄረሰብ ዘንድ ሞት ‹‹ኪቱ›› የሚል መጠርያ ያለው ሲሆን የሚገድለውም ሀኦ (እግዚአብሄር) ሳይሆን ኪታ (መላከ ሞት) የሚባል ነው፡፡ በብሄረሰቡ አመለካከት ‹‹ኮንተኒ ምኖቱ ክትኒ›› (አንድ ሰው የሞተው የተወለደ እለት ነው) የሚል ፍልስፍና አለ፡፡ እያንዳንዱ ሰው የሚሞተውም ሲወለድ በተወሰነለት የአሟሟት ጊዜና መንገድ ነው፡፡ በተወሰነው የአሟሟት ጊዜና መንገድ ኪታ(የሞት መላክ) እንደሚገድለው ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አቶ ኃይለማሪያም ዱዱ እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *ሞት በመጀመሪያ ሲመጣ የነበረው በግልጽ እንደነበረ ነው የሰማሁት፡፡ የሚገድለውም ኪታ ነው የሚባለው፡፡ ይህ ኪታ ሰዎች ሲወለዱ የመሞቻ ጊዜአቸውንና የአሟሟት ሁኔታቸውን ጭምር እየመጣ ይናገር ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን በኬንቲሞ[1] (በባህላዊ አዋላጅ) አንዲት እናት ወንድ ልጅ ስትወልድ ኪታው (ገዳዩ) ይመጣና (ለኬንቲሞዋ) ይህ ልጅ ሚስት እንዳገባ በማግስቱ ነው የሚሞተው ይላታል፡፡ ኬንቲሞዋም ‹‹ለዚህ ልጅ ሚስት እንዳትድሩለት ሚስት ባገባ ማግስት እንደሚሞት ነው ኪታ የነገረኝ›› ብላ ለእናትየው ትናገራለች፡፡በዚህ ምክንያ ልጁ ሚስት ሳያገባ ለዓመታት ቆየ፡፡ የልጁ እናትና አባት የሆነ ይሁን ኪታ (ገዳዩ) ከመጣ እኛ ባንተ ፈንታ እንሞታለን ብለው ይስማሙና ልጃቸውን ይድሩታል፡፡ ልጁ*

---

[1] ኬንቲሞ፡- በየም ብሄረሰብ ዘንድ ልጅ ከተጸነሰ ጊዜ ጀምሮ እስኪወለድ ድረስ ተፈጥሮ በሰጣቸው ዕውቀት ጽንሱን እየዳሰሱም ጭምር ደህንነቱን የሚከታተሉ ባህላዊ አዋላጆች፡፡

*በተዳረ ማግስት ኪታው ለመግደል ሲመጣ ሙሽራው ልጅ ‹‹እንግዲህ ኪታው መጥቷል ባንተ ፈንታ እንሞታለን ብላችሁ ነበር›› ብሎ ለወላጆቹ ሲነግራቸው ለመሞት ቃል የገቡለት ወላጆች ‹‹እረ ለኛም እኮ ነፍሳችን ነው›› ብለው እምቢ ይሉታል፡፡ በዚህ ጊዜ ማታ የመጣችው ሙሽሪት የኪታውን ፊት ቀና ብላ ሳታይ ‹‹እኔ ማታ መጥቼ በማግስቱ እሱን ከምገድል እኔን ግደል እኔ ነኝ የምሞተው›› ብላ ሙሽራውን ለመግደል የመጣው ኪታ ትለምናለች፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሽሮችን ሳይገድል በይቅርታ በማለፍ ‹‹በግልጽ ለመግደል መምጣታችን ነው እንዲህ ያደረገው›› በማለት ከዚህ ዕለት ጀምሮ ሞት በድብቅ መግደል እንደጀመረ ነው ሲነገር የሰማሁት፡፡ (ቃለ መጠይቅ በ25/7/2011 ዓ.ም.)*

አቶ ሳህለ ዘበንም በ15/7/2011ዓ.ም በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ‹‹የየም ብሄረሰብ ሰውን የሚገድለው ኪታ ነው በማለት ነው የሚያምነው›› ሲሉ፣ በ3/8/ 2011ዓ.ም አቶ ወልደማሪ ያም ያዳ ‹‹ ኮንተኒ ዎኖቱ ኪትኒ›› (የተወለድን ዕለት ነው የሞትነው)፣ ‹‹የሚገድ ለውም ኪታ ነው›› በማለት ገዳይን በሚመለከት በተመሳሳይ ሀሳብ ሲገልጹ እንዲሁ አባ ዲጋ ባሻን ደግሞ በ17/7/2011 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ‹‹የሞች ከጥንት ጀምሮ፣ ዛሬ ደግሞ በመጽሀፍ ቅዱስ እንደምንሰማው የተወለድን ዕለት ነው የሞትነው፡፡ይህ የምናወራው እኛ እኮ የሞትን ነን፡፡ እስክንለያይ ድረስ ቀኑን አላወቅነውም እንጂ፡፡›› በማለት በተመሳሳይ ሀሳብ አጠናክረዋል፡፡

ከላይ የተገለጸው መረጃ የሚያስረዳን በየም ብሄረሰብ አመለካከት ሰው ነፍሱ ከስጋው ባትለይም ተንቀሳቃሽ ሙት ነው፡፡ ሰውን የሚገድለው ደግሞ ኪታ (መላከ ሞት) እንጂ ሀኦ(ፈጣሪ) እንዳልሆነ ይታመናል፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጅ የአሟሟት መንገዱም ሆነ ሟች መሆኑ አስቀድሞ የተወሰነለት መሆኑን የሚጠቁም አመለካከት ነው፡፡

በብሄረሰቡ ፍልስፍና መሰረት ህይወት የሚጀምረው በሞት ነው፡፡ ይህ ፍልስፍና የሰው ልጅን ተያያዥ ገጾች የሚያሳይ ነው፡፡ ሞትና ህይወት የሰውን ልጅ ጅማሬና ፍጻሜን የሚገልጹ ገጾች ናቸው፡፡ ህጻን ሲወለድ ያለቅሳል፡፡ ይህ ለቅሶ ወደፊት ለሚገጥመው ሞት የመጀመሪያው ለቅሶ ነው፡፡ ስለዚህ በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ህይወት የሚጀምረው በሞት መሆኑን መረጃው ያስረዳል፡፡

በዚህም ይመስላል የሞች አስቀድሞ በተወሰነው መንገድ ድንገት ሞት ቢከሰት ብለው ለመቀበሪያቸው አስፈላጊ ነገሮችን አዘጋጅተው የሚጠባበቁት፡፡ በመሆኑም በብሄረሰቡ ዘንድ ለሞት የሚፈጸመውን ስርዓት ለማየት በሚከወኑት ድርጊቶች መነሻነት ቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞትና ድህረ ሞት በሚሉ ዋና ዋና ምድቦች ለይተን እንቃኛለን፡፡ በነዚህ ምድቦች በማህበራዊ ደራጃ፣ በዕድሜና ጾታም ልዩነቶች ምክንያት የሚከወኑ ተግባራት እንዲሁም በብሄረሰቡ ዘንድ እንደ ልዩ ክስተት በሚታመኑ አደጋዎች በሚከሰት ሞት የሚፈጸሙ ስርዓቶችንም እያይዘን በየክፍላቸው የምንመለከት ይሆናል፡፡

### 5.1.1. ቅድመ ሞት ክወና ስርዓቶች

ቀጠሮው አይታወቅም እንጂ ሰው ሁሉ ሟች መሆኑ እሙን ነው፡፡ በ10/08/2011 ዓ.ም.በተካሄደው የተተኳሪ ቡድን ውይይት ለማወቅ እንደተቻለው የየም ብሄረሰብ አባላት ሞት በድንገተኛ አደጋም ሆነ በእርጅና ቢከሰት ቤተሰብ ወይም ጎረቤት እንደይቸገር አስቀድመው በርካታ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ፡፡ ቤት ሲሰራ እንኳ ድንገት ሞት ቢከሰት ለቀስተኞችን መያዝ በሚችል መልኩ ነው ግቢው ሰፋ ተደርጎ የሚዘጋጀው፡፡ የቤቱ በረንዳ እስከ በራፉ መውጪያ ድረስ አጥር ማጠር ግድ ነው፡፡አጥሩ ለቅሶ ቢከሰት ጦር ማስደገፊያ ነው ተብሎ ነው በውስጥ ታዋቂነት የሚታጠረው፡፡ በየም ብሄረሰብ ልዩ ቦታ የሚሰጠው የመኖሪያ ቤት አጥር ከድንበርተኛን መለያ ሳይሆን ከዋናው መኖሪያ ቤት መውጫ በር በኩል በስተቀኝ ሁለት እስከ ሶስት ሜትር ድረስ ጀምሮ ርዝመቱ እንደየበለቤቱ ደረጃ የሚለያይና እስከ ግቢ መውጫ ድረስ የሚታጠር ነው፡፡ምክንያቱም ቤቱ አጥር የሌለውና ባግባቡ ያልታጠረ ከሆኑ ድንገት ሞት ቢከሰት ይህ ሰው ቀድሞውንም የሞት ነው መቀበር ብቻ እንጂ የቀረው ተብሎ በለቀስተኞች ስለሚዘለፍ አጥር ማጠር በብሄረሰቡ ዘንድ ግድ ነው፡፡

ሞት አይቀርምና በማንኛውም አጋጣሚ ቢከሰት በቀላሉ ጥቅም ላይ ለማዋል ሲል የየም ብሄረሰብ የተለያዩ ቁሶችን አስቀድሞ በማዘጋጀት ነው ሞትን የሚጠባበቀው፡፡ በብሄረሰቡ የመቀበሪያ ሳጥን ዝግጅት የሚጀምረው ከዛፍ ችግኝ ተከላ ነው፡፡ ከየሞች የእንሰት ማሳ የኮርችና የሾላ ዛፍ አይታጣም፡፡ እነዚህ ዛፎች ለሁለት ዓላማ በእንሰት ማሳ ውስጥ እንደሚተክሉ ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አቶ አየለ ገላን ያብራሩታል፡፡

*ኮርችና ሾላ ከእንሰት ጋር የሚተከልበት አንዱ ምክንያት ኮርቹና ሾላውን ጎኑ(የሬሳ ሳጥን) ለመቅረጽ ይመቻል፣ለስላሳ ስለሆነ ይፈጥናል፣ ምስጥም አይበላውም፡፡ሁለተኛው ሾላና ኮርች በደረቅና እርጥበታማ ወቅቶች የውሃ ቅብብሎሹ በቂ ሆኖ እንሰቱ እንዳይሞት የሚያደርግ በመሆኑ እነዚህ ዛፎች ከእንሰት ተለይተው አይታዩም፡፡ ከነዚህ ዛፎች በሁለት መልኩ የአስክሬን ሳጥን ይዘጋጃል፡፡ አንደኛው ጎኑ ወይም ብድሩ የሚል መጠሪያ ያለው ነው፡፡ ይህ ጎኑ የሚገጣጠም ሳይሆን የኮርቹ ወይም ሾላው ዛፍ ከተቆረጠ በኋላ ለክዳን የሚሆን ከላዩ ላይ ተሰንጥቆ ይወጣና ውስጡ በመጥረቢያ ተቦርቡሮ የሚዘጋጅ ነው፡፡ ይህን ጎኑ እድሜአቸው እየገፋ ሲሄድ በልካቸው ጠርበው በማዘጋጀት ውስጥ ገብተው ተኝተው በማየትም ጭምር ነው አሰናድተው በማስቀመጥ ሞት እስኪመጣ የሚጠብቁት፡፡*

*በአሁኑ ሰዓት ግን ጎኑ ወይም ብዷሩ (ከግንድ ተቦርቡሮ የሚዘጋጅ የአስክሬን ሳጥን) የማዘጋጀት ልምዱ መቅረቱንና በብዛት የሚዘወተረው ዞዳ (በባህላዊ መንድ የሚዘጋጀ የአስክሬን ሳጥን የሚሆን ጣውላ) መሆኑን በመግለጽ ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ ያጠናቀሩት ሌላው ቁልፍ መረጃ አቀባይ አባ ዲጋ ባሻን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡*

*የአስክሬን መቀበሪያ ሳጥን ከየትም አይወሰድም፡፡እያንዳንዱ ሰው ራሱን ችሎ አዘጋጅቶ ነው የሚቀመጠው ፡፡ዛሬ ዛሬ ግን ይከብዳል ተብሎ የተላገ ጣውላ ተፈልጎ ከአናጺ ይገዛል እንጂ ሁሉም ሰው በየቤቱ ከኮርችና ከሾላ ለአስክሬን ሳጥን የሚሆን ዞዳ ጠርቦ አዘጋጅቶ ነው ያለው፡፡ በእያንዳንዱ ቤት ብትሄድ የከብቶች ቤት ውስጥ ተደርድሮ ታገኛለህ፡፡ ኮርችና ሾላ በየጓሮአችን እየተከልን ነው የምንቀመጠው፡፡ኮርችና ሾላ ለአስክሬን ሳጥን የተመረጡበት ምክንያት ለመጥረብ ለስላሳ በመሆኑ፣ ኮርች ምስጥ ስለማይበላው እና ሾላው ደግሞ ከደረቀ በኋላ መሬት ውስጥ ከገባ ቶሎ ስለማይበሰብስ ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ በ*17/7/2011*ዓ.ም ሰሙ አዋሾ፡፡*

ከላይ ከተገለጹ መረጃዎች መረዳት የሚቻለው ለሞት ከሚደረገው ቅድመ ዝግጅት ባለፈ ኮርችና ሾላ ለአስክሬን ሳጥንነት የመመረጣቸው ምክንያት ኮርች ምስጥ የማይበላው በመሆኑ ሲሆን ሾላው ደግሞ ቶሎ የማይበሰብስ በመሆኑ እንደሆነ ነው፡፡ ኮርችና ሾላ

በብሄረሰቡ ዘንድ የልምላሜና የቀጣይነት ተምሳሌት ነው፡፡ ሁለቱ ዘዛፎች በእንሰት ማሳ ውስጥ የሚተከሉበት ምክንት የሁለቱ ዛፎች በጋና ክረምት ቅጠላቸው የሚረግፈው በመፈራረቅ ነው፡፡ እነዚህ ዛፎች በእንሰት ማሳ ውስጥ ካሉ በየትናውም ወቅት ማሳው ለምለም ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ሽማግሌዎች በሚመርቁበት ወቅት ቴኔ ችሬፋዎ (ሾላህ ይለምልም)፣ ኮቾኔ ችሬፋዎ (ኮርችህ ይለምልም) ማለትን ፈጽሞ አይዘነጉም፡፡ እነዚህ ዛፎች ምልክትነታቸው የህይወት ወይም የትውልድ ቀጣይነትን ትዕምርታዊ መልዕክት የሚስተላልፉ ናቸው፡፡



ፎቶ1. ለአስክሬን ሳጥን ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ዞዳ(ባህላዊ ጣውላ)  ሰሙ አዋሾ ቀበሌ፡፡

ወገን በሞት ሲለይ የለቅሶ ስርዓቱ ከማህበረሰብ ማህበረሰብና ከባህል ባህል እንደሚለያይ ሀሉ ለእያንዳንዱ ተግባር የሚሰጠው ዋጋም እንዲሁ ይለያያል፡፡ በየም ብሄረሰብ ከፈን የትልቅነት፣ የክብርና የኑሮ መገለጫ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ በቅድመ ሞት ዝግጅት ውስጥ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ኪኖ (የከፈን ልብስ) ነው፡፡ ሞት ከተከሰተ በኋላ ከፈን ፍለጋ መሯሯጥ በብሄረሰቡ ዘንድ የበታችነት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡  በመሆኑም እያንዳንዱ የየም ብሄረሰብ አባወራ ይህን የከፈን ልብስ ገዝቶ ቤቱ በማስቀመጥ ነው ሞትን የሚጠባበቀው፡፡ ይህ ኪኖ (የከፈን ልብስ) ሁለት ዓይነት አገልግሎት አለው፡፡ አንደኛው የቤቱ አባወራ ወይም እማወራ ሲሞቱ አስክሬናቸው የሚከፈንበት ሲሆን ሁለተኛው አገልግሎቱ በለቅሶው ዕለት ከቀብር በፊት አባወራው የሞተ እንደሆነ የሚች ቤት ጣሪያ ላይ በውጭ በኩል ከጉልላቱ እስከ መግቢያ በር ድረስ በቁመቱ ተዘርግቶ ይነጠፋል፡፡ ሚች እማወራዋ ከሆነች

ግን  አጥር ላይ ተዘረግቶ ይነጠፍና ለቅሶው ይካሄዳል፡፡ ሌላው በአካባቢው ወዳጅ ዘመድ የሆነ ትልቅ ሰው ሲሞት በውሰት እየተወሰደ በሟች ቤት ላይ በተጨማሪነት በመነጠፍ የሚያገለግል ነው፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች አባ ዲጋ ባሻን፣ አቶ ሳህሌ ዘበን፣ አባ ፊጣ ሲመል እና አቶ ወልደማሪያም ያዳ በሰጡት ተመሳሳይ መረጃ መሰረት በየም ብሄረሰብ ዘንድ ኪኖ (የከፈን ልብስ) በአካባቢው ሸማኔዎች የሚሰራ ነው፡፡

ኪኖ በቀለም ደረጃ ነጭ አብዛኛውን መጠን የሚይዝ ሲሆን ቀጥሎ ያለውን ደረጃ የሚይዘው ቀይ ቀለም ነው፡፡ ከነዚህ ውጭ ቢጫ፣ አረንጓዴ፣ ቡኒ፣ ሎሚ፣ ወይንጠጅ ቀለሞሞች ነው የሚሰራው፡፡ ይህ ኪኖ ለዘወትር ልብስነት የሚውል ሳይሆን ሞት ሲከሰት በቤት ጣሪያ ላይ ተዘርግቶ የሚቀመጥና ለከፈን ብቻ የሚያገለግል ነው፡፡ የከፈን ልብሱ ከአካባቢው ሸማኔዎች በትዕዛዝ ተሰርቶ ወይም ከገበያ ተገዝቶ ከዚህ በታች በፎቶ በተመላከተው ሾሮዶ በሚባል የብሄረሰቡ ባህላዊ የልብስ ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ ነው በየቤቱ የሚቀመጠው፡፡



ፎቶ 2. ኪኖ (የከፈን ልብስ)

የከፈን ልብሱ ግን ለማንኛውም ሰው ሞት ጥቅም ላይ አይውልም፡፡ ከዕድሜ አንጻር ህጻናት፣ ታዳጊዎችና ወጣቶች የሚከፈኑት በጋቢ ሲሆን በቤት ጣሪያ ላይም አይነጠፍላቸውም፡፡ ነገር ግን ለወጣቶች ሞት ኪኖ (የከፈን ልብሱ) አስክሬን ተለብሶ ወደቀብር ቦታ ሊወሰድ ይችላል እንጂ መከፈን ግዴታ አይደለም፡፡ ለሁሉም አዋቂዎች ግን ያለጾታና ማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ከፈኑ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ኪኖ የሚባለው የከፈን ልብስ በሰፊ የነጭ መደብና ጥለቱ በቀይ ቢጫና አረንጓዴ የተሰራ ሸማ ንው፡፡ ነጭ በብሄረሰቡ ዘንድ የውስጥ ንጽህናን የሚወክል ሲሆን ቀዩ የአዳኝነትና የጦር ጀግንነት ተምሳሌት ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ በብሄረሰቡ እምነት መሰረት ኪኖ የንጽህና የክብርና የታላቅነት ምልክት ነው፡፡

የአስክሬን መገነዣ ታላ (የፈትል ክር ወይም ማግ) አስቀድሞ ከሚዘጋጁ ቁሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ የዚህን ፈትል አገልግሎት በተመለከተ  አባ ዲጋ ባሻን ‹‹ታላ (ማግ) አስክሬኑ ከታጠበ በኋላ እጅና እግሩ እንዳይኮማተር የሚታሰርበት ነው፡፡ እንዲሁም የሟች ቤተሰብ የሆኑና ሀዘንተኛ መሆናቸውን ለማመላከት ከለቅሶ ቀን ጀምሮ የሀዘን ቀን እስኪያበቃ ድረስ በአንገታቸው እንደማተብ ለማሰርም ይህ ማግ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው፡፡›› በማለት ያስረዳሉ፡፡

ሁለት የአገልግሎት አላማን ይዞ የሚሰራው ሾሮዶ (ባህላዊ ሳጥን) የየም ብሄረሰብ ለለቅሶ ክወና ማጀቢያነት ይውል ዘንድ አስቀድመው ከሚያዘጋጁት ቁስ መካከል ነው፡፡ ሾሮዶ ከእንሰት ኮባና ቃጫ እንዲሁም በቀጫጭኑ ተሰነጣጥቆ በላመ ቀርከሀ በተለያየ መጠንና ቅርጽ ተሰፍቶ የሚዘጋጅ ሲሆን ክዳን ያለው እንደሳጥን ለልብስ ማስቀመጫነትና በዚዛ (ሙሾ) ክወና ላይ በምት የሙዚቃ መሳሪያነት የሚያገለግል ነው፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ወ/ሮ አስናቀች ፊጣ እንደሚሉት ለዚዛ ማጀቢያነት የሚዘጋጀው ሾሮዶ  ክብ ቅርጽ ያለው ሲሆን መጠኑ እስከ አንድ ሜትር የሚደርስ ነው፡፡ ይህን ሾሮዶ የሚሰሩት ሴቶች ሲሆኑ በዚዛው ላይም የሚከወነው በሴቶች ነው፡፡ ለነዚህ ሁለቱ አገልግሎቶች ሲባል ሾሮዶ ተገዝቶ ወይም በትዕዛዝ ተሰርቶ በእያንዳንዱ ቤት ይቀመጣል፡፡ (ቃለ መጠይቅ 26/7/2011ዓ.ም ሰሙ አዋሾ ቀበሌ፡፡)



ፎቶ 3. ለዚዛ ክወና ማጀቢያነትና ለልብስ ማስቀመጫነት የሚያገለግል ሾሮዶ

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ ሞት ሲከሰት የተሌየ አገልግሎት የሚሰጡ ቁሶች ሞት መከሰቻ ጊዜና መንገዱ ስለማታወቅ ከተከሰተ በኋላ ፍለጋ ከመሯሯጥ አስቀድመው የሚዘጋጁ ናቸው፡፡ ይህም ‹‹ሰው የተወለደ ዕለት ነው የሞተው ነፍሱ ከስጋው የምትለይበትን ቀን እንጂ ያላወቀው›› የሚለውን የብሂረሰቡን አስተሳሰብ የሚያመላክት ዝግጅት ነው፡፡ ሰው በህይወት ዘመኑ ተንቀሳቃሽ ሬሳ መሆኑን ለማመላከት የአስክሬን መከፈኛ ቁሶች ጭምር ነፍስ ከስጋው እስከምትለይ ድረስ አብረውት እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩ ሞት መጠባበቂያ ቁሶችች በማንኛውም ጊዜ ሞት ቢከሰት አገልግ ሎት ላይ የሚውሉ ናቸው፡፡ ከዕድሜ አንጻር የአስክሬን መገነዣ ታላ (ማግ) እና ዞዳ ዝግጅት ሁሉንም ጾታ፣ ዕድሜና ማህበራዊ ደረጃን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን ኪኖ፣ የሾሮዶ እና ጎኑ ዝግጅት የሚደረገው ግን የአባወራ ወይም የእማወራ ሞት ሲከሰት ብቻ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው፡፡ (የተተኳሪ ቡድን ውይይት በቀን 10/8/2011 ዓ.ም.) ፡፡

## 5.1.2. ጊዜ ሞት ክወና ስርዓቶች

ጊዜ ሞት ዝግጅት ሞት ተከስቶ ከመለቀሱ በፊት በሟች ቤተሰቦችና በአካባው ማህበረሰብ የሚደረጉ ዝግጅቶችን የሚመለከት ነው፡፡ በየም ብሂረሰብ ባህል መሰረት ሞት ሲከሰት የሚደረጉ ዝግጅቶች ስፋትና ድምቀት እንደየሟቹ ማህበራዊ ደረጃና ዕድሜ ይወሰናል፡፡

ከማህበራዊ ደረጃ አንጻር በተለይ ለንጉስ፣ ለጎሳ መሪና ለጀግና ሞት የሚፈጸሙ ዝግጅቶችና የለቅሶ ስርዓታቸው ከሌሎቹ የተወሰኑ ልዩነቶች የሚታዩባቸው ናቸው፡፡ እንደ ቁልፍ መረጃ አቀባይ አቶ ሳህሌ፣ አቶ ገዛኸኝ እና አባ ፊጣ ገለጻ በማህበረሰቡ ውስጥ ካለው ክብርና ስልጣን አንጻር የንጉስ ሞት ታላቅ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ አንድ ቀን ሞት እንደሚከሰት ታምኖ በዝግጅት የሚጠበቅ ቢሆንም፣ ሲከሰት ከመለቀሱ በፊት በርካታ ቅድመ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከተግባራቱ የመጀመሪያው የግንዘት ስርዓት ነው፡፡ በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ሞት ከተከሰተ የግንዘት ስርዓት ሳይከናወን የለቅሶ ድምጽ ማሰማት ክልክል ነው፡፡ በማህበራዊ ደረጃቸው በጊዜ ሞት ወቅት የሚፈጸሙ ተግባራትን ቀጥለን በደረጃቸው እንመለከታለን፡፡

የንጉስ ሞት በምትኩ ሌላ የማንገስ ስርዓት እስኪጠናቀቅ ድረስ ይፋ አይደረግም፡፡ ነገር ግን የሚፈጸመው የግንዘት ስርዓት በሁሉም የብሄረሰቡ አባላት ዘንድ ተመሳሳይ መሆኑን በመገለጽ ቀደም ባሉ ጊዜያት አስክሬን ይገንዙ የነበሩት ቤራዎች (የሸክላ ስራ ሙያተኞች መሆናቸውን ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አባ ፊጣ ሲመል እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> *እያንዳንዱ የየም ብሄረሰብ ጎሳ የየራሱ ገናዥ ቤራ (የሸክላ ስራ ሙያተኞች) አለው፡፡ ቤራው ሞት ሳይከሰትም በፊት ተዛምዶ የሚኖር ነው፡፡ ይህ ዛሬ በኦርቶዶክስ ክርስትና የነፍስ አባት እንደሚባለው ለተዛመደው ሰው አገልጋይ ነው፡፡ በዓላት ሲቃረቡም ሆነ ሲቸገር ቀጠሮ በማስያዝ የተለያዩ የሸክላ ውጤቶችን ይዞ በመምጣት ቦርዴ ተጠምቆለት፣ እርጎ ተጠራቅሞ፣ ምግብ ተዘጋጅቶለት በልቶ ጠጥቶ ቅቤም ይዞ ይሄድ ነበር፡፡ እንደዚህ ተዛምደው ያሉ ቤራዎች ሞት ሲከሰት ተጠርተው ይመጡና ምግብ ተዘጋጅቶላቸው በልተው አስክሬኑን አጥበው ገንዘው ያስቀምጡና ሄደው መቃብር ቆፍረው ወስደው ይቀብሩ ነበር፡፡ በድሮ ጊዜ ዘርማንዘር ያልቃል ተብሎ ስለሚታመን አስክሬን ሌላ ሰው አይነካም፡፡ ሟች በተለያዩ ተላላፊ በሽታዎችና የአምላክ ቁጣ ነው በሚባሉ አደጋዎች ሊሞት ስለሚችል አውሬ አድርጎ ነው ሰው አስክሬን የሚሸሸው፡፡ (ቃ.መ. በ16/7/2011ዓ.ም ሶሙአዋሾ)*
> 
> ፡፡

ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በጥንት ጊዜ በብሄረሰቡ ዘንድ አስክሬን መገነዝ፣መቃብር የመቆፈርና አስክሬን ተሸክሞ ወስዶ የመቅበር ተግባር ይፈጸም የነበረው በቤራዎች (የሸክላ ስራ ሙያተኞች) ብቻ እንደነበረ ነው፡፡ ይህ የሆነበት በተለያዩ ምክንያቶች እንደሆነ ነው በተተኳሪ ቡድን ውይይት ለማወቅ የተቻለው፡፡ ከምክንያቶቹም የመጀመሪያው ሰው የሚሞተው በተለያዩ ተላላፊ በሽታዎችና በፈጣሪ ቁጣ ነው ተብሎ ስለሚታመን አስክሬን ማንም አይነካም፡፡ ይህም ሞት ይከሰታል ከሚል ፍርሀት የተነሳ እንደሆነ ነው፡፡ ቤራዎች ደግሞ ታማኝና ንጹህ የሰውን የማይፈልጉ፣ በላባቸው ሰርተው የሚኖሩና ፈጣሪ የሚሰማቸው ናቸው የሚል እምነት  በብሄረሰቡ ዘንድ ስላለ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት በጥንት ጊዜ የብሄረሰቡ አኗኗርም በጣም በተበታተነ መልኩ ስለነበርና የመሬቱ አቀማመጥም ወጣ ገባ በመሆኑ ከአንድ ሰው በላይ አስክሬን ተሸክሞ ወደ ቀብር ቦታ መውሰድ የሚያስችል መንገድ ባለመኖሩ እንደሆነ ነው፡፡ የአስክሬን አገናነዝ ስርዓቱንም አባ ፊጣ ሲያስረዱ፡-

> *የአገናነዝ ስርዓቱ ሬሳው ከታጠበ በኋላ እንዳይኮማተር እያንዳንዱን የአካል ክፍል እጥፋት እያሹ ቀጥ አድርገው ነው የሚገንዙት፡፡ ለሟች ቤተሰቦችም ሆነ ለአካባቢው እንዲሁም ለሟች ራሱ ሰላምና በረከት ይሆን ዘንድ የአስክሬኑ ዓይን ስር፣ አናቱና ደረቱ ላይ ቅቤ ይቀባ ነበር፡፡ የእጅ አውራ ጣቶች በነጭ የማግ ክር አንድ ላይ ተያይዘው ይታሰራሉ፣ እንደዚሁ የእግርም አውራ ጣቶች በአንድ ላይ ይታሰራሉ፡፡ ተረከዝ፣ ጉልበትና ትከሻም እንዳይጣመም በደንብ አድርገው አስረው ይገንዙታል፡፡ይህ በእንዲህ ታስሮ ካለቀ በኋላ ነው በልብስ የሚጠቀለለው፡፡ ጥጥ ያለው ሰው ከሆነ በአስክሬኑ በተለያዩ ቀዳዳዎች በኩል ሽታ እንዳይወጣ ሲባል በጥጥ ይወተፋል፡፡ ምክንያቱም ነፍስ ከተለየ በተለያዩ ቀዳዳዎች በኩል ሊሸት ይችላል፡፡ ከዚህ በኋላ ኮማ (ቁርበት) ከስር ይነጠፍና ምናልባት ከአስክሬኑ የሚወጣ ፈሳሽ ካለ ወደ ወጭ እንዳይወጣና እንዲመጥ ተብሎ ቁርበቱ ላይ ጥጥ ይደረጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ጥጥ በሾርዶ ተጠቅጥቆ ነው የሚቀመጠው፡፡*

በራዎች አስክሬን የሚገንዙበትን ምክንያትም አቶ አየለ ገላንና አባ ፊጣ እንደሚከተለው አጠናክረው ያስረዳሉ፡-

*በተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ሰው ሊሞት ይችላል፤ ሟች የተለያዩ ኃጢያቶችንም ሰርቶ ሊሆን ይችላል፡፡ የሌላ ሰው በሽታ ወደ ቤራ (ፉጋ) አይተላለፍም፣ የፉጋ ቤተሰቦች በማህበረሰቡ ውስጥ በማህበራዊ ደረጃ የተገለሉ ቢሆኑም በመንፈሳዊ ኃይል ግን በጣም የበላይ ናቸው ተብለው ነው የሚታመኑት፡፡ በጫወታ መካከል የፉጋን ቤተሰብ ህጻን የሌላ ቤተሰብ ህጻን ቢመታውና ቢደማ እንኳ በጣም ትልቅ መቅሰፍት ይወርዳል ተብሎ ስለሚሰጋ ቶሎ ነው እርቅ የሚደረገው፡፡*

*ሌላው ፉጋዎች አንጋሽ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ በሙያ በዕውቀትና በጥበብ የበላይ ናቸው፡፡ እነዚህ በመንፈሳዊ ነገር የበላይ እና በቀላሉ አንድ ነገር ማግኘት የሚችሉ ሰዎች በማህበራዊ ደረጃ ግን የበታችና ከሌላው ማህበረሰብ የተገለሉ ናቸው፡፡ (ቃ.መ. በ16/7/2011 ዓ.ም ሶሙአዋሾ እና በ30/7/2011 ዓ.ም ሳጃ ቀበሌ,ዖት)፡፡*

ከላይ ከተገለጸው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው ከየም ብሄረሰብ አባላት ቤራ ከሚባሉ ጎሳዎች በስተቀር ሌሎቹ ሞትን ከመፍራታቸው የተነሳ የሟችን አስከሬን እንደማይነኩ ነው፡፡ ምክንቶቹ ደግሞ ሟች የሞተበት ምክንያት ወደኔ ሊተላለፍ ይችላል ብለው ከመስጋታቸው የተነሳ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ሰው ተንቀሳቃሽ ሙት እንደሆነ ያምናሉ፤ ይህን ማወቃቸውና ለዚህም ተዘጋጅተው መቀመጣቸው ለፍርሀታቸው ምንጭ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም ሰው የሚፈራው የሚያውቀውን ነገር ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ሞቱ ሊተላለፍብኝ ይችላል ከሚል ስጋት አስከሬን አይነካም፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጅ የጋራ ባህሪ ነው፡፡ Gire (2011,6) እንደሚሉት ሁላችንም ከምንጋራቸው ጥቂት የጋራ ስምምነቶች መካከል አንዱ፣ አንድ ቀን ሞት የሚያገኘን መሆኑ ነው፡፡ ይህ እውነታ ሰው ሞትን እንዲፈራና የወገኑን ሞት እንዲያስብ እንዳደረገ ነው የሚልጹት፡፡ Gire ለ30 ዓመታት በዘርፉ የተደረገ የምርምር ውጤትን በመጥቀስ እንደገለጹት፣ የሰው ልጅ ራሱን ለመጠበቅ ባለው የፍላጎት ፍትጊያና ሞት የማይቀርና መቼ እንደሚከሰት የማይታወቅ መሆኑ ሞትን እንዲሰጋና እንዲፈራ አድርጎታል፡፡

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የበላይም የበታችም ይኖራል፡፡ መካከለኛም መኖሩ የማይቀር ነው፡፡ ሁሉም ነገር ለአንድ ጎሳ ወይም ለአንድ ሰው ተሟልቶ አለመሰጠቱ በሰዎች መካከል ተፈላላጊነት እንዲኖር ነው፡፡ በስልጣን፣ በገንዘብና በጉልበት የበላይ የሆነው የመጨረሻ

ዝቅተኛ ናቸው ብሎ ለሚያስባቸው ጎንበስ ብሎ የሚታዘዝበት ጊዜ አለ፡፡ ይህ ጊዜ ዝቅተኛ የሚባለው የበላይ የሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማህበራዊ ግንኙነቱን ተመጣጣኝ (Social balance) ለማድረግ ነው፡፡ የየም ማህበረሰብ ስሪቱ በዚህ ነው፡፡ ምክንያቱም በጋብቻ እንኳ መተሳሰር የማይፈቀደው፣ በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች በጋራ የማይሳተፈውና የመጨረሻ የተገለለው ቤራ(የፉጋ ቤተሰብ) በመንፈሳዊ ኃይሉ ከንጉስ ሁሉ በላይና ቀጥታ ከፈጣሪ ቀጥሎ ያለ ሰው ተደርጎ የሚቆጠር ነው፡፡ ንጉስ ነው የሚባልው ግን በመንፈሳዊ ተሰጥኦው በጣም ዝቅተኛ ቦታ ተሰጥቶት ቤራው ነው ገንዞ የሚቀብረው፡፡ ፉጋው አስክሬን ገንዞ፣ መቃብር ቆፍሮ የሬሳ ሳጥን ሰርቶ ወስዶ ቀብሮ ከተመለሰ በኋላ ከንጉስ ቤተሰብ እንኳ ከፊሉን ወይንም ሙሉውን ሀብት ይወስድ እንደነበረ መረጃ አቀባዮቹ ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ፈጣሪ ነው በዚህ ተሰጥኦ እንዲሰሩ የሚያደርገው ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

በቅድመ ሞትና ጊዜ ሞት፣ ለማጎችና ጀግኖች እንዲሁም ለእድሜ ባለጸጋዎች የሚፈጸሙ ስርዓቶች ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ሲሆን በድህረ ሞት ወይም በቅድመ ቀብር ስርዓታቸው በሚከወነው የለቅሶና የዚዛ ስርዓቱ ላይ ነው የተወሰነ ልዩነት የሚንጸባተቀው፡፡ ልዩነቱ እ ንደሚኞቹ ማንነት በሚደረደሩ የለቅሶና የዚዛ ቃል ግጥሞች ምክንያት እንደሆነ ነው ቁልፍ መረጃ አቀባይ አባ ሶሪ አባ ጀቢር፣ ወ/አለሚቱ ኩምሳና አቶ ወልደማሪያም ያዳ የገለጹት፡፡ (ቃ፣መ በ03/08/2011ዓ.ም፣ በ04/08/2011 እና በ03/08/2011ዓ.ም)፡፡

‹‹ማግ›› የሚባሉት በተለየ ማህበራዊ ደረጃቸውና ችሎታቸው ለየጎሳው በንጉሱ የሚሾሙ ናቸው፡፡ አቶ ወልደማሪያም እንደሚሉት ማጎች የለቅሶና የዚዛ ክብር ደረጃ አላቸው፡፡ ዛሬ በአንድ መንግስት አስተዳደር ሊቀመንበር እንደሚሾመው ሁሉ ማጎችም በየጎሳው በንጉሱ አስተዳደር የተሾሙ ናቸው፡፡ ማጎች የንጉሱ ወኪሎች ናቸው፡፡ ኬማዎችን (ኬላዎችን) ከፍተው የዛራ[2] ስርዓት የሚያስፈጽሙት ማጎች ናቸው፡፡ አስክሬናቸው የሚቀበረው በየጎሳቸው መቃብር ቦታ ነው ፡፡ ነገር ግን እንደንጉሱ አስክሬናቸው በድብቅ አይቀበርም፡፡ የለቅሶና የዚዛ ስርዓታቸውም እንደማንኛውም ክብር እንደሚሰጠው የብሄረሰቡ ጎሳ ነው የሚፈጸመው፡፡

[2] ዛራ፡- የንጻትና የእርቅ ስርዓት

ከማህበራዊ ደረጃ አንጻር ሌላው በየም ብሄረሰብ ዘንድ ልዩ የክብር ቦታ የሚሰጣቸው ጀግኖች ናቸው፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ ጀግና የሚባለው ከአጎራባች አካባቢዎች ጋር በሚደረጉ ጦርነቶች ተሳትፎ በማድረግ ጠላትን የገደለና የማረከ እና በአዳኝነቱ  ታዋቂ የሆነ ሰው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የጀግና ሞት በልዩ ሁኔታ የለቅሶውና የዚዛ ክወናው ስርዓቱ ደማቅ ነው፡፡

የጊዜ ሞት ዝግጅቶች ሳይጠናቀቁ  የማጎች፣ የጀግኖችም ሆነ የተራ ሽማግሌ  ሞት ይፋ አይደረግም፡፡ ነገር ግን ከግንዘት ስርዓቱ በስተቀር ለለቅሶ ስርዓቱ የሚደረገው ዝግጅት በኢኮኖሚ አቅምና ማህበራዊ ትስስር ምክንያት የድምቀት መጠን ደረጃው ይለያያል፡፡ ለዝግጅት ተብሎ ሳይለቀስ የሚቆይበት ጊዜ ግን የሟችን እድሜና የአሟሟት ሁኔታ እንደሚወስን ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ሟች ተላላፊ ነው ተብሎ በማህበረሰቡ ዘንድ በሚፈራውና ባኡ (ሆድ በሚያሳብጥ) እና በስጋ ደዌ በሽታ ታሞ የሞተ ከሆነ ለቅድመ ዝግጅት ተብሎ አይቆይም፡፡ ቀደም ባለው ጊዜ አስክሬን የሚገንዙት ቤራዎች (የሸክላ ሰራተኞች) አሁንም ድረስ በአንዳንድ የማህበረሰቡ አባላት ዘንድ ፍርሀቱ ስላልጠፋ በእንደዚህ ዓይነት በሽታ የሞተን ሰው የሚገንዙት እነሱ ናቸው፡፡ የቡድን ተኮር ውይይት መረጃ እንደሚያስረዳው ከዚህ ውጪ በየም ብሄረሰብ ባህል መሰረት ትልቅ ሰው እንደሞተ ወዲያው አይለቀስም፡፡ ሟች የዕድሜ ደረጃው ከፍ ያለ ሰው ከሆነ ቅድመ ዝግጅቶች ይደረጋሉ፡፡ ለመቀበሪያ ሳጥን የሚሆን ዞዳ፣ ኪኖ (መከፈኛ ልብስ) አስቀድሞ የሚዘጋጅ ቢሆንም ምናልባት የነበሩ ቁሶችን በቅርብ ለተከሰተ የዘመድ  ሞት መቀበሪያነት አውሎት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ምክንያ ያልተዘጋጀ ነገር ካለ በግዥ ወይም ከጎረቤት መጥቶ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ኮባና(በወፍራሙ የተጋገረና መጠነኛ ቆጮ በስሎ ይከማቻል፡፡ ማባያው ባቄላም ይቀቀላል፡፡ ለንፍሮ የሚሆን ስንዴም ተዘጋጅቶ ይነፈራል፡፡ በዚህ መልኩ መስተንግዶው ባግባቡ ተሰናድቶ መጠናቀቁ፣ ወደየዘመዱ መልዕክት መላኩ፣ የአካባቢው ንፅህና ሁኔታ፣ የቤቱ አጥር፣ አጠቃላይ በዙሪያው ያሉ ነገሮች በደንብ መሰናዳታቸው ይረጋገጣል፡፡ እነዚህ ነገሮች ቀድመው ሳይዘጋጁ የተለቀሰ እንደሆነ የአካባቢው ህብረተሰብ ለምን ይሄን አላደረጉም?፣ ለምን ይሄ እንዲህ ሆነ? እያለ  ይወቅሳል፡፡ ያለበቂ ዝግጅት ለቀሶ ይፋ ከተደረገ መሳቂያም ያደርጋል፡፡ አዋቂ አስተዋይ የላቸወም ወይ? ያስብላል ፡፡

የደጅ አጥር በትክክለኛ ፍልጥ ያልታጠረ ከሆነ እንደገና ተስተካክሎ ይታጠራል፡፡ ሟች ታዋቂና ትልቅ ሰው ከሆነ የዚዛ ስርዓት ስለሚያስፈልግ ለዚዛው ምቹ የሆነ ቦታ የማዘጋጀት

ስራ ይሰራል፡፡ ይህ ያልሆነ እንደሆነ ለቀስተኞች ‹‹እሳቸው ድሮውንም በቁማቸው ሞተዋል የቀራቸው መቀበሩ ብቻ ነው›› በማለት ይዘልፋሉ፡፡ ይህ የጊዜ ሞት ዝግጅት እስኪጠናቀቅ ድረስ ለቤተዘመድ ካልሆነ በስተቀር ሞት መከሰቱ ይፋ ሳይደረግ እስከ ሶስት ቀን ሊቆይ ይችላል ፡፡

የመርዶ መልዕክተኛም በጥንቃቄ ነው የሚለየው፡፡ ሩቅ ለሚኖሩ የሟች ልጆች ወይም ቤተዘመድ ዘንድ የሚላከው መልዕተኛ በዕድሜም ጠና ያለ፣ አስተዋይ፣ መርዶውን በቀጥታ በመንገር የማያስደነግጥ፣ በጥበብ ማስረዳት የሚችል መሆን አለበት፡፡ ሟች በህይወት እንዳሉ ነገር ግን ህመም የጸናባቸው ስለሆነ መጥተው ቢያዩ መልካም መሆኑን በመንገር ነው መልዕክት የሚያደርሰው፡፡ መልዕክተኛው ሞት መሆኑን ለጎረቤት በመግለጽ ይዘዋቸው እንዲመጡ ይነግራል፡፡ የሟች ዘመድ ጎረቤቶችም ‹‹ብቻችሁን እንዴት እንሰዳለን እኛም አብረን ሄደን አይተን እንምጣ›› በማለት ነው ይዘዋቸው የሚሄዱት፡፡

ለቅሶው ባህሉን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን ይጠበቃል፡፡ ለዚዛ የሚሆን ቀንድ የሚያመጡ የዚዛ ስርዓቱን በደንብ የሚያውቁ አካባቢዎች አሉ፤ ወደነሱና ወደ አማችም ይላካል፡፡ አማች ደግሞ ዝም ብሎ አይመጣም፤ ለለቅሶ ባህሉ ዚዛ (ሙሾ) ክወና ቡድኖችን አስተባብሮ ነው ይዞ የሚመጣው፡፡ በፈረስም ጭምር ስለሚለቀስ ይህንንም አመቻችቶ ነው የሚመጣው፡፡ (ቡ.ተ.ው.በ10/8/2011 ዓ.ም.ሳጀ)፡፡

በብሄረሰቡ ማህበራዊ ትስስር መሰረት የሟች ጎረቤቶችም ለጊዜ ሞት ዝግጅቱ ድርሻ አላቸው፡፡በአንድ አካባቢ ሞት ሲከሰት ለለቀስተኛ እንግዶችም ሆነ ለሟች ቤተሰቦች ጎረቤቶች ወይም የአካባቢው ማህበረሰብ ምግብ ያዘጋጃሉ፡፡ እንግዶችን የሚቀበሉበትን ሁኔታ በተመለከተ ሟች ታዋቂ ሰው ከሆነ ‹‹ከባድ ዘመድ ነው ያለው ምን እናድርግ›› ብለው በመምከር ለመስተንግዶ የሚሆን ምግብ በቤታቸውም ያዘጋጃሉ፡፡ በአንድ አካባቢ ለቅሶ ሲከሰት ከሟች ቤተሰብ ይልቅ ጎረቤት እንደሚጨነቅ ነው የቡድን ተኮር ውይይት መረጃ የሚያስረዳው ፡፡

በቀብር ዕለት ለቀስተኛ የሚስተናገደው የቤቱን መስተንግዶ ብቻ አይደለም፡፡ ጎረቤትም ለለቅሶ ከሚመጡት መካከል የተለየ ቅርበት ያላቸውንና የራሱ ዘመድ የሆኑትን ወደ ቤቱ ወስዶ አብልቶ አጠጥቶ ነው የሚሸኘው፡፡ ስለዚህ የራሱንም ዝግጅት ያደርጋል ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ለቅሶ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ ቶሽኒ ዋራ (ድንኳን)

የሚነቀልበት ቀን ድረስ የተለያዩ የስራ ድርሻዎች አሉት፡፡ እነዚህ የስራ ድርሻዎች በማህበረሰቡ ውስጠ ደንብ የተወሰኑ ናቸው፡፡ በእነዚህ ውስጠ ደንቦች መሰረት ከውይይት አንስቶ የሚከወኑ ነገሮችን በየተራው ይከውናል፡፡ የከብቶችን ደህንነት በጠበቅና ሌሎች ቀደም ሲል የሚች ቤተሰቦች የሚያከናውኗቸው ተግባራት በሙሉ በለቅሶ ወቅት የሚሸፈኑት በአካባቢው ማህበረሰብ ነው፡፡ ምግብ፣ የማገዶ እንጨትና ውሃ ማቅረብ፣ የሚመጣውን ለቀስተኛ ከመቀበል ጀምሮ እስከ ማስተናገድ ድረስ ያለው ተግባር የሚሸፈነው በአካባቢው ማህበረሰብ ነው፡፡ ቶሻ /ድንኳን/ እስከሚነቀል ድረስም በለቅሶ ቤቱ በየተራ በማደር ሀዘንተኞችን ያጫውታሉ፡፡ ሀዘንተኛን ለማጫወትና ለማፅናናት በቀንም ተራ በተራ ጎረቤቶች ይመጣሉ፡፡ መጨረሻም ቶሻውን(ድንኳን) የሚነቅሉትም ጎረቤቶች ናቸው ፡፡

በጥቅሉ ሲታይ በየም ብሄረሰብ ማህበራዊ ትስስሩ ከፍተኛ ነው፡፡ አንድ ቤት ሞት ሲከሰት የሟች ቤተሰብ በለቅሶ ሀዘናቸውን ከመግለጽ ውጪ ለቀስተኛን ማስተናገድና ሟችን ወደ ግባተ መሬቱ ለመሸኘት ከፍተኛ ሚና ያለው የአካባቢው ማህበረሰብ ነው፡፡ ሰው ሞቶበት ቤተሰብ እደጁ ወጥቶ የለቅሶ ጩኸት የሚያሰማው ሀዘኑን ሊገልጥ ብቻ ሳይሆን ድረሱልኝና ሀዘኔን ተካፈሉ ለሚል የእርዳታ ጥሪም ጭምር ነው፡፡

አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁ በሟች ቤተሰብና በጎረቤቶች ሲረጋገጥ የአዋቂ ሞት ሲሆን ሊነጋ ሲል 11፡30 እስከ 12፡00 ባለው ጊዜ ውስጥ በጩኸት ይፋ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን የህጻናትና ታዳጊ ወጣቶች ሞት ከሆነ የሀዘን ስሜቱ ከፍተኛ በመሆኑ ሞቱ ከቀትር መኋላ ተከስቶ ለቀብር ይመሻል ተብሎ ካልቀረ በስተቀር የግነዛ ስርዓቱ እንዳለቀ ወዲያው ይለቀሳል እንጂ ለቅድመ ዝግጅት ሲባል አይቆይም፡፡

ከጾታ አንጻር እንደ አቶ ገዛኸኝ ገላጻ በየም ብሄረሰብ ዘንድ የእድሜ ባለጸጋ የሆኑ ሴቶች ሲሞቱ በጊዜ ሞት የሚፈጸሙ ስርዓቶች ከወንዶቹ ጋር ተመሳሳነት ያላቸው ናቸው፡፡

### 5.1.3. ድህረ ሞት ክወና ስርዓቶች

በድህረ ሞት ስርዓቱ የሚታዩት የጊዜ ሞት ተግባራት ከተጠናቀቁበት ሰዓት አንስቶ ከቅድመ ቀብር እስከ ጊዜ ቀብር ድረስ የሚከናወኑ ተግባራትን የሚመለከት ነው፡፡

### 5.1.3.1.ቅድመ ቀብር ስርዓቶች

እንደየሚቱ ማህበራዊ ደረጃ እድሜና የአሟሟት ሁኔታ በቅድመ ቀብር የሚፈጸሙ ስርዓቶች የተለያዩ ናቸው፡፡ እንደ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ገለጻ የንጉሱ ሞት ሲሆን ተተኪ የማንገስ ስርዓቱ እየተካሄደ ለለቅሶ የሚመጡ እንግዶች የሚበሉት መስተንግዶ እየተዘጋጀ ነው የሚቆየው፡፡ ኮባና (በወፍራሙ የተጋገረ ቆጮ)፣ ሽላቆ (የባቂላ ክክና አበሻ ጎመን ተቀላቅሎ የበሰለ)፣ የባቄላ አሹቅ፣ ስጋ እና ከመጠጥ ደግሞ ቦርዴ (ባህላዊ መጠጥ) ይዘጋጃል፡፡ ሌላ የማንገስ ስርዓቱም ሆነ የመስተንግዶ ዝግጅቱ እንደተጠናቀቀ ለቅሶው ይፋ ይደረጋል፡፡ እንደቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ አቶ አየለ ገላን፣ ሳህሌ ዘበንና በቀለ ጆቢር ገለጻ በዚህ ጥናት የብሄረሰቡ የአስተዳደር ስርዓት ታሪክ በተዳሰሰበት ክፍል እንደተገለጸው የየም ብሄረሰብ የአስተዳደር ስርዓት ሙሉ በሙሉ ወደ ማዕከላዊ መንግስት ስር እስከተጠቃለለበት ከ1966 ዓ.ም ጊዜ ድረስ የጋማ፣ የገሜሎና የሞዋ ጎሳ ነገስታት በቅደም ተከተላቸው አስተዳድረዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ለንጉስ ቤተሰብ ወገኖች የሚደረገው የለቅሶና የዚዛ ስርዓት በታሪካዊነት እየተነሳ እንደሚከወን ነው የተናገሩት፡፡ ነገር ግን ስርዓቱ እንዴት ይፈጸም ነበር የሚለውን በቃለ መጠይቅ ታሪካዊ መረጃ ለመዳሰስ ተችሏል፡፡ ከነዚህ ነገስታት በማስተዳደር ላይ የነበሩት ሲሞቱ በተለያዩ ስርዓቶች ግብዓተ መሬታቸው ይፈጸም ነበር፡፡

> ንጉስ ቢሞትም እንዳለ ተደርጎ ተደብቆ ነው የቤት አገልጋዮችና ቤራዎች መቃብር ቆፍረው ወስደው የሚቀብሩት፡፡ ንጉስ እንደሞተ ወዲያው ለህዝብ ይፋ ተደርጎ የማይለቀስበት ምክንያት በምትኩ ሌላ ሳይተካ ከተነገረ ንጉስ የሌለበት ሀገር ሆኖ ህዝብ ሊረበሽ ስለሚችል ከሳምንት በኋላ ሌላ ንጉስ ሲተካ ነው የሚነገረው፡፡ የንግስና ስርዓቱ በዘር ሀረግ የሚካሄድ ስለሆነ የሚተካው የንጉሱ ታላቅ ልጅ ነው፡፡ በንግስና ስርዓቱም የማስፈጸም ትልቅ ሚና ያላቸው ቤራዎች ናቸው፡፡ ስርዓቱም ራሱን የቻለ ረጅም ሂደት ስላለው እስከ ሳምንት ሊቆይ ይችላል፡፡ በዚህ ቆይታ አስክሬኑ ስለሚሸት ፈሳሽ ሊመጥ የሚችል ከእንሰት ኮባ ውስጥ ተሸልቅቆ በሚወጣ ‹‹ጋሳ›› ላይ አስክሬኑን ዘቅዝቆ በማቆም በአፍና በአፍንጫው ፈሳሽ ተንጠባጥቦ እንዲያልቅ ይደረጋል፡፡ ፈሳሹ ካለቀ በኋላ የግነዛ ስርአት ይፈጸማል፡፡ በዚህም አስክሬኑ ሳይሸት እስከ ሳምንት ሊቆይ ይችላል፡፡ ፈሳሹ የተንጠባጠበበት ‹‹ጋሳ›› ጓሮ ባለ እንሰት ስር

ይቀመጥና ይህን እንሰት ቤራዎች ፍቀው ይጠቀሙታል፡፡ የግነዛ ስርዓቱ እንደላቀ በምትኩ ሌላ ንጉስ ከተሰየመ በኋላ ነው አስተሴሮች (የኅሳ ተወካዮች) ለህዝብ ይፋ የሚያደርጉት፡፡ ድሮ ኡሙሪ[3] ከሚባል ተክል የሚዘጋጅ የሙዚቃ መሳሪያ እየተነፋ ነው የንጉስ መሞት በየአካባቢው የሚነገረው፡፡ ከዚያም ከህጻን ጀምሮ ሁሉም ሰው ንጉሳችን ሞተ ብሎ ጸጉሩን በመላጨት ከሳምንት እስከ ወርም ያዝናል፡፡ በንጉሱ ግዛት ያለ ባላባት፣ የሁሉም ግዛት ኅሳ መሪዎች እንዲሁም መሄድ የሚችል ሁሉ እስከ ቤተመንግስት ድረስ በመሄድ ሀዘናቸውን ሲገልጹ ሌሎች በየግዛታቸው ኡሙሪ ተነፍቶ አንድ ቦታ ተሰባስበው ነው የሚያለቅሱት፡፡ ከየአቅጣቸው ለለቅሶ የሚመጡት የነብርና የአንበሳ ቆዳ ለብሰው፣ የአጋዘንና የድኩላ ቀንድ ተሸክመው፣ ጋሻና ጦር በመያዝ ነው፡፡ ተራው ሰው ሲሞት የአክብሮ ሲሆን ንጺ (አረፈ) ሲባል ለንጉስ ግን ኬምኒ ዱጊቴ[4] ነው የሚባለው፡፡በየም ብሄረሰብ ዘንድ ንጉሱ ኬምኒ (ዓይናችን) ስለሚባሉ ሞታቸውም ኬምኒ ኬሮ (የዓይን መፍወሰስ) ነው የሚባለው፡፡

እንደ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎች ገለጻ ሌላ የማንገስ ስርዓቱም ሆነ የመስተንግዶ ዝግጅቱ እንደተጠናቀቀ ለቅሶው ይፋ ይደረጋል፡፡ ከተለያዩ የንጉሱ ግዛቶች የሚመጡ እንግዶች እየበሉ እየጠጡ ነው የለቅሶ ስርዓቱን በዚዛ ክወና የሚፈጽሙት፡፡

በለቅሶው የሚደረደሩ ቃል ግጥሞችም የሚከተሉትን ይመስላሉ፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| ታቶኒሶ ታቶኒሶ | ንጉሳችን፣ ንጉሳችን |
| አፍኒሶ፣ አፍኒሶ | አይናችን፣ አይናችን |

[3] ኡሙሪ፡-እስከ አንድ ሜትር ተኩል የሚደር በሁለቱም አቅጣጫ ቀዳዳ ያለው በድሮ ጊዜ በወንዶች ግርዛት ስነስርዓትና ለንጉስ ሞት ማርጂያነት የሚነፋ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

[4] ዱጊቴ- ንጉስ ሲሞት ሌላው ማህበረሰብ እንደሞቱ የሚገልጽበት ቃል ነው፡፡

| | |
|---|---|
| አውኒሶ አውኒሶ | ጸሀያችን፣ ጸሀያችን |
| አስኒሶ ስኒሶ | ጨረቃችን፣ ጨረቃችን |
| ገዴውኒ አባኖ፣ ኦሮማኒ አባኖ | የዝግባው አባት፣ የኦሮማው (የዛፍ ዓይነት) አባት |
| ዳኒ አባኖ ታቶኒሴ ቢዳሮኒሴ | የመሬት ባለቤቱ፣ ንጉሳችን፣ ምልክታችን |
| እኖታን ሻቴተዎሶ | ከኛ ተለዩብን ወይ |
| ዳምኒሶ፣ ዳምኒሶ ኮኒ የኛ | ጌታችን፣ ጌታችን ዘመዶችዎ መጥተዋል |
| ጋይማ ጋሮ የኛ ዳምኒሶ | ታላቅ ታናሹ መጥተዋል ጌታችን |
| ኤቶኒ የኛ ዳምኒሶ | አንበሶችዎ መጡ ጌታችን |
| ሜውኒ የኛ ዳምኒሶ | ነብሮችዎ መጡ ጌታችን… በማለት እየተለቀሰ |

ለሳምንት ያህል ይታዘናል፣ ገበያም አይኬድም፣ ጥሩ ልብስም አይለበስም፡፡ ለንጉስ ሞት የም የተባለ የለቅሶ ስርዓቱ ላይ ይሳተፋል፡፡ የለቅሶ ግጥሞቹ ሲቃኙ ከመደበኛው የንግግር ቋንቋ በተለየ መለኩ በጣም አክብሮት የሚበዛባቸው ናቸው፡፡ ለቅሶውም ለህዝብ ታውጆ እንዲለቀስ የሚደረግ መሆኑ ስርዓቱ ለክብራቸው ሲባል የሚፈጸም እንጂ እንደሌሎቹ ለማህበራዊ ግንኙነታቸውና ለዝምድናቸው ተብሎ አለመሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ከላይ የተገለጹ የለቅሶ ቃላቶቹ ስሜት እንኳ እጅግ አክብሮትና ፍርሀት የሚንጸባረቅባቸው ናቸው፡፡

### 5.1.3.1.1. የቴሻ/ለቅሶ/ ስርዓት

እንደቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ ገለጻ በየም ብሄረሰብ ዘንድ በአንድ ቤት ውስጥ ሞት ተከስቶ መለቀስ ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ ድንኳን እስከሚነቀልበት ቀን ድረስ የሚከውነው የለቅሶ ስርዓት ‹‹ቴሻ››[5] ይባላል፡፡ በየም ብሄረሰብ ዘንድ እድሜ፣ ማህበራዊ ደረጃ፣ ጾታና የአሟሟት ሁኔታ ለሟች የሚደረገውን የለቅሶ ስርዓት ይወስናል፡፡ ቴዎድሮስ (2008 ዓ.ም 153) Milesን (1991,202) በመጥቀስ እንደገለጹት ‹‹በኒቼ እምነት መሰረት አንድ ሰው

[5] ቴሻ፡- በየም ብሄረሰብ ዘንድ ሞት ተከስቶ ከቀብር ዕለት ጀምሮ የሟች ቤተዘመዶች ከበራፍ ቆመው ከውጭ የሚመጡ ለቀስተኞችን በስልተዊ የለቅሶ ክወና የሚፈጸሙት የለቅሶ ስርዓት፡፡

በህይወት አልነው ዩኒቨርስ ውስጥ ለመገኘቱ ምክንያት የሆነውን ታላቅ ተግባር በማከናወን ወይም የጀግንነት፣ የተጋዳሊነትን ግዳጅ በመፈጸም በጥበብ ኖሮ በጥበብ ማለፍ ከቻለ ሞቱ ጊዜውን የጠበቀ ነው፡፡››

ይህ ጥቅስ የሚያስረዳን በኒቼ እምነት መሰረት ትክክለኛ ወይም ጊዜውን የጠበቀ ሞት አርጅቶ ብዙ አይቶ የዕድሜ ባለጸጋ ሆኖ መሞት ሳይሆን ተጋድሎን ወይም ታላቅ ተግባርን ፈጽሞ መሞት ነው፡፡ በወጣትነትም ሆነ በሽምግልና ዕድሜ ይሙት ተጋድሎን በድል መወጣት ነው ዋናው ቁልፍ ጉዳይ እንጂ እድሜው ምንም ዓይደለም፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ አቶ ገዛኸኝ ዘርፉ፣ አቶ ሳህሌ ዘበን፣ አባ ዲጋ ባሻን እና አባ ፊጣ ሲመል በሰጡኝ መረጃ መሰረት፣ በየም ብሄረሰብ ዘንድ አንድ ሰው ፈጽሞ እንደሞተ የሚቆጠረው ዘር ያልተካ ሲሆን ነው፡፡ ለእንዲህ ዓይነቱ ሞት የለቅሶና ሀዘን ስሜቱ ሀያል ነው፡፡

ከማህበራዊ ደረጃ አንጻር ለተራ ሽማግሌ ሞት የሚከወነውን ስርዓት ስንመለከት ለሽማግሌዎች ሞት የሚኖረው ለቅሶና ሀዘን ወግ ነውና እንደነገሩ ተለቅሶ ይታዘናል፡፡ ለቅሶውም ቢሆን የዘር ሀረግና የሟች የህይወት ታሪክ የሚነገርበት ነው፡፡ ቀደም ሲል በጊዜ ሞት ተግባራት ለመጠቆም እንደተሞከረው አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት እንደተጠናቀቀ ለኪኖ (ለከፈን) የተቀመጠውን ርዝመቱ 12 ክንድ ቡሉኮ ሁለት ሰው ይዞ ይወጣና የቤቱ ጣሪያ ከጉልላቱ እስከ በሩ ድረስ ቁልቁል ተዘርግቶ ይነጠፋል፣ ከሟች የክት ልብሶች መካከል ኮፊያና ካፖርቱ ወይም ኮትና ሱሪው ከሳር ክዳን ቤቱ ጉልላት ላይ ይሰቀላል፡፡ ከዚህ በኋላ የሟች ቤተሰቦች ሟች አዘውትሮ የሚጠቀምባቸውን የተለያዩ ቁሶችን ይዘው ንጋት ላይ እደጅ ወጥተው በጩኸት የሞት ለቅሶ ያሰማሉ፡፡የአካባቢው ሰው ጩኸት እንደሰማ በሩጫ ከውጭ መኩል እየጮኸ ይመጣና በቴሻ ስርዓት በማልቀስ ሀዘኑን ይገልጻል፡፡ ከዚህ በኋላ ከየአቅጣጫው ለቀስተኞች በቡድን በቡድን እየሆኑ ይተማሉ፡፡ ወንዶች የጦር ዘንጋቸውን ይዘው ሴቶች ነጫጭ ነጠላቸውን ጥለቱን ወደላይ ዘቅዝቀው ለብሰው፣ የቅርብ ዝምድና እና የጠበቀ ትውውቅ ያላቸው ዝግ ባለ ድምጽ እያለቀሱ ሲያሶመስሙ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የግል ጨዋታ ይዘው እያወሩ ወደ ለቅሶ ቤቱ የሚመጡበት ስሜትና ትዕይንት የተለያየ ንባብ ያለው ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ስሜት ለቅሶ ቤቱ አቅራቢያ ሲደርሱ ሴቶች ነጠላቸውን አውልቀው ከወገባቸው በታች አገልድመው በማሰር ለቴሻ ይዘጋጃሉ፤ ወንዶችም እንደዚሁ ጋቢ የለበሱ ሽማግሌዎች አብሮ ካሉ እነሱም ጋቢያቸውን አውልቀው ከወገብ በታች ይደገድጉና ወደ ለቅሶው ይገባሉ፡፡ በዚህ

ዝግጅት ጊዜ አብረዋቸው የመጡ  የቅርብ ዝምድና ያላቸው ደጅ እንደደረሱ አብረው የመጡትን አይጠብቁም፡፡ በፍጥነት ፊትለክ ብለው ይወጡና ወጣት ከሆኑ ጭንቅላታቸውን በሁለቱም እጃቸው በመያዝ እየጮሁ በማልቀስ እደጅ የቆሙ የሟች ቤተሰቦችን አቅፈው በማልቀስ መጨረሻ ላይ እዚያው ከለቀስተኛ ቤተሰቦች ጋር  ተቀላቅለው ይቆማሉ፡፡ ከኋላ የነበሩት ለቀስተኞ ደግሞ ሴቶችን በመስቀደም የሟችን ስም እየጠሩ፣ ተግባሩን እያወሱ የሀዘን ስሜትን የሚቀሰቅሱ ቃላትን እያመነጩ፥ በቴሻ ስርዓት ወደ ለቅሶ ይገባሉ፡፡ ሴቶቹ ቀድመው በቴሻ ስርዓታቸው ፊታቸውን ወደ ሟች ቤተሰቦች አድርገው ሁለቱንም እጃቸውን ከውስጥ ወደ ውጭ እየዘረጉ በለቅሶ ቃላት ስሜታቸውን እየገለጹ ወደ ቀኝ ወደ ግራ ሄድ መለስ፣ ሄድ መለስ በማለት ራስን በማይጎዳ አኳኋን በሁለቱም እጆቻቸው ሁሉም ባንድነት እንደመውደቅ ብለው መሬት ነክተው ይነሱና ወደ ሟች ቤተሰቦች በመሄድ ተራ በተራ አቅፈው ካጽናኑ በኋላ ሴቶች ነጠላቸውን ፈተው ጥለቱን ወደላይ መልሰው ለብሰው ዝምድና ያላቸው ከሟች ቤተሰብ አጠገብ ሌሎች ደግሞ አስቀድመው የመጡ ለቀስተኞ ወደቆሙበት  ወይም ወደተቀመጡበት ሄደው ይቀላቀላሉ፡፡

‹‹የሽማግሌ ሞት በየመሀሉ ለቅሶ መቀላቀሉ ነው እንጂ ተራ (ጊዜውን የጠበቀ) ያለው ሞት ስለሆነ ሰርግ ነው›› የሚሉት አባ ዲጋ ባሻንና አባ ፊጣ ሲመል በተለይ የዚዛ ክወናውን ሰው እንደጨዋታ በመሳተፍም በመመልከትም የሚታደመው መሆኑን ነው የገለጹት፡፡ የቀብር ጉዞው በዚዛ ታጅቦ  ነው መቀበሪያ ቦታ የሚደርሰው፡፡ ለቀብር ጉዞ ዝግጅት የሚጀመረው ከ6 እስከ 7 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ጉዞው እስከሚጀመር ድረስ በየመሀሉ ከሚመጡት ለቀስተኞች ጋር እየተለቀሰ፣እንደገና ዚዛው እየተከወነ መቃብር ተቆፍሮ ዝግጁ መሆኑ መልዕክት ሲሰማ ኪኖው (ቡሉኮው) ከቤቱ ላይ ይወርዳል፡፡ በዚህ ጊዜ የቀብር ሰዓት መድረሱንና ወደ ቀብር ጉዞ ሊጀመር መሆኑን ሁሉም ለቀስተኛ በመረዳት ዝግጁ ይሆናል፡፡ ከቤቱ ላይ የወረደው ኪኖ ቤት ይገባና  በሁለቱም ጫፍ በኩል ከነጥለቱ አንድ ሜትር የሚሆን ተቆርጦ ቀሪው ጥለት የሌለው ቀደም ሲል በጋቢ ተገንዞ የተቀመጠው አስክሬን ተጠቅሎ ይታሰራል፡፡ ከነጥለቱ ተቆርጦ የቀረው ደግሞ ካሮ(ቁራጭ) ለማስታወሻነት ተብሎ ሟች አራት ሴት ልጆች ያሉት ከሆነ አራት ቦታ ተካፍሎ ይሰጣቸዋል፡፡ሁለት ከሆኑ ግን ከሁለቱም ጫፍ የተቆረጠው አንድ አንድ ይሰጣቸዋል፡፡ ሴት ልጆች የሌሉ እንደሆነ ደግሞ ለእህቶቹ ነው የሚሰጠው፡፡ ይህ ካሮው የሚሰጠው ወዲያው እንደተቆረጠ አስክሬኑ ከቤት ሳይወጣ ሲሆን በዚህ ጊዜ ለቅሶው ደጅ ላይ እንደ

አዲስ የደመቀ ይሆናል፡፡ ሴቶቹ ካሮውን ይዘው እየዘለሉ በከፍተኛ ጩኸት ያለቅሳሉ፡፡ቁልፍ መረጃ አቀባይ አቶ ወልደማሪያም ያዳ ‹‹ካሮው››ን አስመልክቶ እንዳሉት

> *በየም ብሄረሰብ ዘንድ ቤተሰብ ሲሞት ጥቁር የሀዘን ልብስ የመልበስ ልምድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጣ እንጂ ድሮ ሀዘን የሚገለጸው ጸጉር በመላጨትና ሴቶች ደግሞ ከአስክሬን ከፈን ተቆርጠ የሚሰጠውን ካሮ በመልበስ ነው፡፡ እንዲሁም ከኪኖው ክር ይመዘዝና ከሌሎች ለቀስተኞች የሟች ቤተሰብ መሆናቸውን ለመለየትና ለሀዘንተኛነታቸው ምልክት ይሆን ዘንድ ከዕለቱ ጀምሮ ቶሻ (ድንኳን) እስከሚነቀልበት ቀን ድረስ በአንገታቸው ላይ ይታሰርላቸዋል፡፡ ጸጉር የሚላጨውም ከቀብር ማግስት ጀምሮ ባሉቀናት ውስጥ ነው፡፡ (ቃ.መ.* 03/08/ 2011 *ዓ.ም*፡፡)

ከላይ ከተገለጸው መረጃ መረዳት የሚቻለው ዘመድ ሞቶ አንገት ላይ የሚታሰው የፈትል ክር የሀዘኑ ባለቤት የመሆን ምልክት ሲሆን ዝምድናን ማስተዋወቂያም ነው፡፡ እንደ ቁልፍ መረጃ ሰጪዎቹ ገለጻ ለቅሶ ለየም ብሄረሰብ ትልቅ ክብር ነው ያለው፡፡ ለዚህም የሩቅም የቅርብም እንዲሁም የሚተዋወቅ ሁሉ ተሰባስቦ የሚገናኝበት አጋጣሚ ነው፡፡ በመሆኑም የሟች ልጆች ወይም የቅርብ ዘመድ መሆናቸውን ለቀስተኞች እንዲተዋወቁ እድል የሚፈጥረው ይሄን ክር በማሰራቸው ነው፡፡ ሌላው በየም ብሄረሰብ ባህል መሰረት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ጸጉር ያሳድጋሉ፡፡ ወገን ሲሞት ይህን ጸጉር መላጨታቸው በሚገባ ማዘንን የሚገልጽ ነው፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ ወገን ከወገን ሲለይ  ይታዘናል፡፡ በተለይ ሴቶች ለአባትና ለእናታቸው ሞት ንጹህ ልብስ ራሱ አይለብሱም፣ ራሳቸውን ጥለው የሚያዝኑት፡፡ በተደጋጋሚ ነው የሚላጩት፡፡ ባግባቡ ጸጉሯን ተላጭታ ያላዘነች እንደሆነ ጨካኝነቷ ጉድ ያስብላታል፡፡

እንደ ብሄረሰቡ ባህል ካሮ የሚሰጣቸው ለሴቶች ብቻ ነው፡፡ የሟች ሴት ልጆች ወይም እህቶች ናቸው የሚለብሱት፡፡ ካሮ የቅርብ ዝምድና ምልክት ነው፡፡ ወንድ ልጆች ግን የሀዘን ጦር ነው ይዞ የሚያለቅሰው፡፡ ወንዶች ሟች በመንፈስ እንዳለ እንዲታወስ የሚሰሩት ብዙ ስራ አለ ተብሎ ስለሚታመን ካሮ አይሰጣቸውም፡፡ ሴቶች ግን አግብተው የሚሄዱ ወይም ያገቡ ሊሆኑ ስለሚችሉ  ሟችን የሚያስታውሱት በካሮ ነው፡፡

የቀብሩ ዕለት ያልተገኘ የሩቅም ሆነ የቅርብ ዘመድ እንዲሁም በተለያዩ ጉዳዮች የሚተዋወቅ የማህበረሰቡ አባል ድንኳን ሳይነቀል ለቅሶ ቤት ሲመጣ በቴሻ ስርዓት ነው ሀዘኑንን የሚገልጸው፡፡ ሀዘንተኞችም የሚመጣውን ለቀስተኛ በሙሉ ቆመው ነው እያለቀሱ የሚቀበሉት፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ወ/ሮ አስናቀች ፊጣ እንደሚሉት በቴሻ ስርዓት ማልቀስና እንዲሁ ማልቀስ ትልቅ ልዩነት አለው፡፡ ‹‹የሟችን ስም ጠርቶ በማወደስ በተለያዩ አካላዊ እንቅስቃሴዎች በቁጭት ሲለቀስ ቤተዘመድም ሆነ ሌላው ሰው ያለቅሳል፡፡ በዚህም ለቀስተኞች በጣም አዝኖለታል፣ ሞትን መውጋት ብቻ ነው ያቃተው ይላሉ፡፡ ሟችንም ምን ዓይነት ጥሩ ሰው ነበረ፤ ሰውን ምን ያህል የሚወድ ነው ይሉለታል፡፡

በአንድ አካባቢ ሞት ሲከሰት የሟች ዘመድ አዝማድ ፣ በአንድ ማህበራዊ መዋቅር ውስጥ የጋራ መተዳደሪያ ደንብ ያላቸው ማህበረሰቦችና በተለያዩ ምክንያቶች የሚተዋወቁ የብሄረሰቡ አባላት ለቴሻ (ለለቅሶ) `መድረስ ማህበራዊ ግዴታ ነው፡፡

> *የሟች ወገን ዘመድ ሞቶበት ለቅሶ ያልደረሰ ሰው ካለ እንዴት ለቅሶዬን አልደረሰም? አስረግሟል ወይ? በማለት እሱ ነው የገደለብኝ እስከማለት ይደረሳል፡፡ እንዲሁም ለቅሶ በተከሰተ ዕለት ለግል ጉዳዩ ወይም ገቢያ የሄደ የአካባቢው ማህበረሰብ አባል የቴሻው ማብቂያ ዕለት ተጠርቶ ይጠየቅና በማህበረሰቡ የሚጣልበትን ቅጣት ይቀጣል፡፡ በገንዘብም ሊቀጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን ጥፋቱ ሁለትና ሶስት ከሆነ ከማንኛውም ማህበራዊ ተሳትፎ ከአካባቢው ማህበረሰብ የመገለል ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፡፡ ግለሰቡ ጥፋቱን አምኖ ይቅርታ በመጠየቀ ከካሰ ነው ወደ ማህበረሰቡ የሚቀላቀለው፡፡(ቃ.መ ወ/ሮ አስ ናቀች ፊጣ* 26/7/2011*ዓ.ምሰሙ አዋሾ ቀበሌ፣ አቶ ሳህሌ ዘበን 15/7/ 2011 ዓ.ም ሳኛ፡፡)*

በየም ብሄረሰብ የለቅሶ (ቴሻ) ስርዓቱ ለህጻናትና የፈጣሪ ቁጣ ነው በሚባሉ ክስተቶች ከሚሞቱት ካልሆነ በስተቀር ለሁሉም እድሜ፣ ጾታና ማህበራዊ ደረጃ ተመሳሳይ ሲሆን በለቅሶው የሚደረደረው ስነ ቃል ግን እንደየሟቹ እድሜና ማህበራዊ ማንነትና ደረጃ የሚለያይ ነው፡፡ እንደዚሁም ለሁሉም አዋቂዎች ዚዛ (ሙሾ) የሚከወን ሲሆን ክወናው ግን እንደ ቴሻ ስርዓቱ ሁሉ በጾታና በማህበራዊ ደረጃ ይለያያል፡፡

ለሴት አዛውንቶች የሚፈጸመው የለቅሶ ስርዓትም እንደወንድ አዛውንቶች በቴሻ ስርዓት ነው የሚከወነው፡፡ እንደ አቶ ገዛኸኝ ገለጻ ቀደም ሲል ለሴቶች የዚዛ ስርዓት የማይከወን ቢሆንም ከጊዜ በኋላ ለማንኛውም ሰው እንደሚከወነው ሁሉ ቀንድ ተይዞ ዚዛ እየተካሄደ ነው፡፡ ነገር ግን አባወራው እያለ ቀድማ የሞተች እንደሆነ ኪኖ (ከፈን/ቡሉኮ) የሚነጠፈው የቤቱ ጣሪያ ላይ ሳይሆን አጥር ላይ ነው፡፡ አባወራው ቀድሞ የሞተ እንደሆነ ግን ኪኖው የሚነጠፈው የቤቱ ጣሪያ ላይ ነው፡፡ እንደዚሁ እናት ልጇ ቤት እየተጦረች የሞተች እንደሆነም ኪኖው የልጇ ቤት ላይ አይነጠፍም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ አባወራውን ይገድላል ተብሎ ስለሚታምን ነው፡፡ አልፎ አልፎ ዚዛም የማይፈቅዱ አካባቢዎች አሉ፡፡ (ቃ.መ.16/7/20 11)፡፡



ፎቶ 5. የአባወራ ሞት ቴሻ(ለቅሶ) ስርዓት ክወና፡፡

### 5.1.3.1.1.1 የሴቶች ቴሻ(ለቅሶ) ክወና ስርዓት

በየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ውስጥ ሴቶች የራሳቸው የሆነ የቴሻ (ለቅሶ) ክወና ስርዓት አላቸው፡፡ የቴሻ ክወናቸው እንደሚያሳየው ሴቶች ስልታዊ የአካል እንቅስቃሴ ያደርጋሉ እንጂ ሁሉም በዘፈቀደ ቴሻውን አይከውንም፡፡ በቴሻ ክወናው ሶሶ[6] (አሳዛኝ የአለቃቀስ ድምጽ ቅላጼ አወጣጥ) በሴቶች ላይ የድምጸት ገጽታው የተለየ ነው፡፡ በለቅሶው እንባ ባይኖራቸው እንኳ በአለቃቀስ ድምጻቸው መውጣትና መውረድ እና በሚደረድሩት

[6] ሶሶ፡- አሳዛኝ የለቅሶ ድምጽ ቅላጼ

የማስለቀሻ ቃላት ታጅቦ የለቀስተኞችን ስሜት የመቀስቀስ ሀይሉ ከፍተኛ ነው፡፡ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ በቡድንም ሆነ በግል ሲከውኑ የተለየ ገጽታ አላቸው፡፡ ወገብ ላይ የነጠላ አስተሳሰር፣ የእጅ አዘረጋግና የእግር አነሳስ፣ ወደፊት ወደኋላ፣ ወደቀኝ ወደግራ ሄድ መለስ በማለት ሙሉ አካል መሬት ሳይነካ በጎን እንደመውደቅ ብለው በሁለቱም እጅ መዳፍ መሬት ነክተው በመነሳት ሄደው የሀዘንተኞችን ትከሻ በመንካት የሚፈጽሙት ስርዓት ክወና የመጀመሪያና መጨረሻ ስርዓቱ ቀመራዊ ነው፡፡ የክወና ሂደቱን በተመለከተ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ወ/ሮ ወለተየሱስ ምሬ እና ወ/ሮ አስናቀች ፌጣ በተመሳሳይ ሀሳብ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> ለቴሻ በምንሄድበት ጊዜ ከፊት የሚቀድሙት ትልልቅ ሴቶች ናቸው፡፡ በሰልፍ ወይም ባንድነት እጅብ ብለን በመሄድ ለቅሶ ቤቱ አካባቢ ስንደረስ ሟች ወንድ ከሆነ አበኒዮይ አቤኒዮይ (ምነው፣ ምነው)፣ የችፋው ኒኛ፣ የችፋውኒኛ (እኔን፣ እኔን)፣ ይ፣ ይ፣ይ፣ ው፣ ው፣ ው፣ እያልን በጩኸት እያለቀስን ነው የምንሄደው፡፡ የቀብሩ ዕለት የምንሄድ ከሆነ የአካሄዳችን ስሜት የሆነ ነገር ለማስጣል የምንሄድ ነው የሚመስለው፡፡ ወደ ቴሻው ለመሄድ ከቤት ስንወጣ የነጠላችንን ጥለት ወደላይ ገልብጠን ለብሰን ነው የምንሄደው፡፡ የቴሻው(ለቅሶ ቤቱ) በራፍ ልንደርስ አካባቢ ግን እናወልቅና ጥለቱን ወደታች ገልብጠን ከወገባችን በታች አስረን ወደ ቴሻው በሶሶ (ሰው ሞቶ የሚለቀስበት የለቅሶ ድምጸትና ቃና) እንገባለን፡፡ አሰላለፋችን እድሜን ያገናዘበ ሲሆን ትላልቅ እናቶች ይቀድሙና አንድ ጊዜ ሄድ መለስ፣ ሄድ መለስ እያሉ ወደ ሀዘንተኛው ደርሰው አንደገና ወደ እኛ ሲመለሱ ነው በጋራ እጅብ ብለን በፊት መሪዋ አማካይነት እጃችንን ከእግራችን እንቅስቃሴ ጋር እያስማማን ከውስጥ ወደ ውጭ በሚዘረጋ መልኩ እጃችንን እያንቀሳቀስን፣ እያለቀስን በአንድ አቅጫ ሶስቴ ሄድ መለስ በማለት ቶሎ ለመነሳት በሚያስችል አኳኋን ወድቀን መሬት በመንካት እንነሳና የሀዘንተኞችን ትከሻ ተራ በተራ በማቀፍ እናበቃለን፡፡

ከላይ በተገለጸው ዓይነት ክወና የለቅሶ ስርዓቱን መፈጸም በየምኛ ‹‹ጌብቤ ቴሾ››[7] እንደሚባል ነው መረጃ ሰጪዋ የገለጹልኝ፡፡ ቴሻውን ሲያከናውኑ ስርዓቱ የመጀመሪያ የመሀልና የማጠናቀቂያ ተግባር በጊዜ የተመጠነ ነው፡፡ ሁሉም ቦታ ቦታውን ያውቃልና ክወናው የሚለመድበትን ሂደት ወ/ሮ አለሚቱ ኩምሳ እንደመከተለው ያስረዳሉ፡፡

*የቴሻ ስርዓት ክወናውን እኛ ሴቶች የምንለምደው ከእናቶቻችን ነው፡፡ ጌብቤ ቴሾ የሚባል ስርዓት አለው፡፡ይሄን ስርዓት እናቶቻችን እንዲህ ነው የምታደርጉት በማለት አንዳንዴ ማድ ቤት ደጃፍ እንዲሁም ማታ ማታ ስራ ሲያልቅ ክወናውን ያሳዩናል፡፡ወጣቶችም እንጨት ሰበራ ወደ ጫካ ስንሄድና ውሃ ለመቅዳት ስንሄድ እንለማመዳለን፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቴሻ ስርዓቱን በድንብ ያልቻሉ ወጣቶች ከአዋቂዎች ጋር ሲሄዱ ከኋላ ሆነው ነው ታላላቆቻቸው በሚመሩት መሰረት የሚከውኑት፡፡ (በ22/8/2011 ዓ.ም.ኢ.ዲ.የ)*

## 5.1.3 .1.1.2. የወንዶች የቴሻ ስርዓት

የወንዶች የቴሻ ስርዓትም እንደሴቶቹ የራሱ የሆነ ገጽታ ያለው ነው፡፡ በቡድን ሆነው ለቅሶ ቤቱ ሲሄዱ በእድሜ ደረጃቸው ታላላቆች ከፊት ሆነው እየመሩ ሲሄዱ ከያዙት የጦር ዘንግ ጋር ሲታዩ ሽማግሌዎች ጋቢ መልበሳቸው እንጂ ለውጊያ የሚሄዱ ነው የሚመስለው፡፡ ለቅሶቤቱ ደጅ ሲቃረቡም ጋቢ የለበሱ ሽማግሌዎች ካሉ ሌሎቹ ከኋላ ሆነው እየጠበቁ ጋቢያቸውን አውልቀው ከወገብ በታች ደግድገው ከሰሩ በኋላ ቡድኑን እየመሩ ወጣቶች ከኋላ ሆነው ከሟቹ ማንነት ጋር ግንኙነት ያላቸው የለቅሶ ቃላትን እየደረደሩ በሶምሶማ አይነት እንቅስቃሴ እደጅ ይደርሳሉ፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አባ ፊጣ ሲመል እንደሚሉት የወንዶች የቴሻ ስርዓት አሁንም ድረስ ያለ ቢሆንም ቀደም ሲል ይከወን የነበረ አሁን ግን የቀረ ክወና እንዳለ በመግለጽ ሂደቱን ያስረዳሉ፡፡

*የለቅሶ ጩኸት ሲሰማ በአካባቢው ያለው ማህበረሰብ ቶሎ ነው የሚደርሰው፡፡ በድሮ ጊዜ የለቅሶ ጩኸት እንደተሰማ በስራ ልብስ እየተሮጠ ይኬድና በደረት ወድቆ ማልቀስ ነበር፡፡ እኔ ራሴ በደረት ወድቄ አለቅስ ነበር፡፡ ይሀ ወድቆ ማልቀስ ለሟች ያለንን ፍቅርና በመሞቱ የተሰማንን*

---

[7] ጌብቤ ቴሾ ፡- በየም ብሄረሰብ ሴቶች በስልታዊ የአካል እንቅስቃሴ የሚያከናውኑት የለቅሶ ስርዓት ፡፡

*ቁጭት መግለጫ ስሜት ነው፡፡ አሁን ይሄ ቀርቷል፡፡ ወንዶች ለቴሻ ሲሄዱ ጦር ይዘው ነው የሚሄዱት፡፡ ሽማግሌዎች ጋቢ ለብሰው፣ ጎልማሶችና ወጣቶች ከስራ ልብሳቸው በስተቀር ማንኛውንም ዓይነት ልብስ ለብሰው ነው በአንድላይ የሚሄዱት፡፡ ከለቅሶ ቤቱ ደጅ እንደደረሱም ሽማግሌዎችን በማስቀደም ሌሎች በእድሚያቸው ይሆኑና ሽማግሌዎች ጋቢአቸውን አገልድመው ወገባቸውን በማሰር ለቅሶውን ይመራሉ፡፡ ሁሉም የጦር ዘንጋቸውን እያወራጩ፣ ጭንቅላታቸውን በቁጭት እየነቀነቁ፣ ወደ ሀዘንተኛቹ ሄድ መለስ እያሉ አዳኝ ከሆነ ወደ አደን የሄደበትን ቦታ እየጠሩ፣ ከብት አርቢ ከሆነ የሚያሰማራባቸው አካባቢዎች እንዲሁም ደረባውን እየጠሩ፣ የሟች የዘር ሀረግ ወጥቶ የሚገባበትን ቦታ ሁሉ እየጠሩ ነው እያለቀሱ ሀዘንተኞችን የሚያስለ ቅሱት፡፡ ለምሳሌ በዚህ ሰዓት ከሚደረደሩ ማልቀሻ ቃላት መካከል የሚከተ ሉት ይገኛሉ፡፡*



ፎቶ 4. ወንዶች ቴሻ (የለቅሶ) ስርዓት ሲከውኑ፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | የአማርኛ አቻው |
|---|---|
| ቄውዋ ቴጋና ኬስዋ | አንተ እገሌ ልጥራህና ውጣ |
| ካቡዋ ፣ካቡዋ… | ተነስልኝ፣ ተነስልኝ.. |
| ጉዳማዋ፣አራማዋ፣ካሳማዋ.. | ጉዳማሳ፣ አራማሳ፣ ካሳማሳ(የደረባ ስሞች) |
| ካቡዋ ካቢን አምኒዋ | እባክህ ተነስና እንሂድ |
| ያንዋ ካቢን አምኒዋ | መጥቻለሁ ተነስና እንሂድ |
| ጉዙዋ አፋዕቴቶሶ? | ንቃ እንጂ አንቀላፍተሀል ወይ? |
| አዞዞ አኔ ግዕተፌዋ አቴሶ | ሌላ ቀን አታኮርፍም ነበር ምን ሆነሀል |
| አቴሶ ካቡዋ | ምነካህ ተነስ እንጂ |
| ካሳዬፋን ማኮንዋ | ቀና በልና ልንገርህ |
| ኬሳ ኡጳዋ አፌኖሶ ? | ውጣና ላግኝህ የለህም ወይ? |

እያልን ወዲያ ወዲህ በማለት ጭንቅላታችንን ነቅነቅ በማድረግ የጦር ዘንጉን አወራጭተን በመስበቅ የሟችን ስም እየጠራን ስናለቅስ ለቀስተኞች ስሜታቸው ተቀስቅሶ ለቅሶው በከፍተኛ ሁኔታ ነው የሚሞቀው፡፡ በተለይ የአንዳንዱ የአለቃቀስ ስሜት ከነጦሩ እንቅስቃሴ ሲታይ ሞት ቢገኝ የሚወጋ ነው የሚመስለው፡፡

ከበላይ የተደረደረውን የለቅሶ ግጥም ስንመለከት ሟች ከብት አርቢ መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡ ስንኞቱ በሙሉ ከከብት እርባታ ስራ ጋር በተያያ የሚንቀሳቀስባቸውን አካባቢዎች፣ ከሰዎች ጋር የሚያደርጋቸውን ግንኙነቶች፣ ቀናነቱን የሚያወሱ ናቸው፡፡ ሟችን በስሙ በመጥራት መልስ የሚሰጥ በማስመሰል የሚያናግሩ ናቸው፡፡ እነዚህ የለቅሶ ግጥም ስንኞች የሟችን እንቅስቃሴና ተግባር በምናባቸው እንዲመለከቱና ለቅሶው መሪር እንዲሆን የሚያደርጉ ናቸው፡፡

ሟች በመልካምነቱ የሚታወቅ ትልቅ ሰው ከሆነ፡-

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
| --- | --- |
| አውኤን ኒኤን ኮኢኛ- | ከዛሬ ጀምሮ ሁሉም ነገር በእርሶ አበቃ |
| አቤንዮይ፣ አቤንዮይ | ምን እናድርግ ምን እናድርግ? |
| ዙታሾዋ፣ ዙቲቦዋ አቤኒዮይ | ሰብሳቢ አለቃችን፣ ሰብሳቢያችን ምን ይሻለናል? |
| አይን አማንሪ፣አይን አማንሪ | የት ነው የምንሄደው የት ነው የምንሄደው? |
| አውኤዋ አውጌሻዋ አባኒሶ | ወይኔ ትልቁ ጎሻችን[8] አባታችን |
| ማንጉ ሜያሲን ፉኦኒኛ | ከክፉ ፍላጻ ያድኑኝ |
| ታን ኮሩንኛ | ዋስ ይሁኑኝ |
| ማንጊና ዎዋ ንኪቱ ዮናኛ | ሲካፉኝ እርሶ ጋር ነው የምመጣው |
| ኮርራቱ ፉኦኒኛ | ዋስ ሁነው ነው የሚያድኑኝ |
| ማንግፋን ያናና | ከፍቶኝ መጥቻለሁ |
| ኬሩክ አፌኒዋይ | ከቤት የሉም ወይ …፡፡ |

እየተባለ ነው መልካምነቱ ለወገን ደራሽነቱ እየተወደሰ የሚለቀሰው፡፡

‹‹ከዛሬ ጀምሮ ሁሉም ነገር በእርሶ አበቃ››፣ ‹‹ሰብሳቢ አለቃችን››፣ ‹‹ሰብሳቢያችን የት ነው የምንሄደው››፣ ‹‹ወይኔ ትልቁ ጎሻችን››፣ ‹‹አባታችን ከክፉ ነገር ያድኑኝ››፣ ‹‹ዋስ ሁነው ያድኑኝ››፣ ‹‹ሲከፋኝ እርሶ ጋር ነው የምመጣው››፣ ‹‹ከፍቶኝ መጥቻለሁ ከቤት የሉም ወይ›› የሚሉ ስንኞች የሟችን መልካምነት በቀላሉ ለመረዳት የሚያስችሉ የተግባርና የባህሪይ ጠቋሚዎች ናቸው፡፡ ይህም ርህራኄውን ለማስታወስ ‹‹ችግሮት ለሄደ መፍትሄ የሚያበጅ ሰው መሆኑን እንዲሁም ‹‹ጎሽ ለልጁ ስትል ተወጋች›› እንደሚባለው ሟች

[8] ጎሻችን:-‹‹ጎሽ ለልጁ ስትል ተወጋች›› እንደሚባለው ሟች ለወገኑ ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰው እንደነበረ በተለዋጭ ዘይቤ የተገለጸ ሀሳብ ነው፡፡

ለወገኑ ሲል ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ መሆኑን ለመግለጽ ‹‹በጎሽ›› በመመሰል ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ የሚገልጡ ናቸው፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
| --- | --- |
| ቤዝታሶ፣ ቤዝታሶ | ጀግናዬ፣ ጀግናዬ |
| ኤቶታሶ፣ ኤቶታሶ | አንበሳዬ አንበሳዬ |
| አምባንሶ ኡጴሪ፣አምባንሶ ኡጴሪ | ምን አገኘህ፣ ምን አገኘህ |
| ዛሮ ዴሳውና ፣ኮሻ ኮሻ ዴሳውና | እንሽላሊት ያስፈራራን፣ ኮሽታ ያስፈራራን |
| ቡራኒ ኦዳውና፣ ቡራኒ ኦዳውና | በሉኝና ልስማ፣ በሉኝና ልስማ |
| ካማድርኖን፣ አደድርኖን፣ ዲፕሳኖን | ካማድር፣ አዳድር፣ ዲፕሳ[9] |
| ካቢን አምኒዋ፣ካምቤልዋ፣ | ተነሳና እንሂድ ካምቤል[10] ነው |
| አውኔዋ ዞሞታሶ፣ ቴጋና ኬስዋ፣ | ወይኔ ጓደኛዬ፣ ልጥራህና ውጣ |
| አኘን አምኒዋ ኦታና አማናሶ፣ ኦፒቶሶ | ደከመህ ወይ ከማን ጋር ልሂድ |
| ጋቹኔ ጋንደፋንዋ፣ | በሬዎችህ ገደል ይውደቁ |
| ፋዝኔ ጋው ጊሪፋንዋ | ፈረስህ ገደል ይግባና |
| ዞሞኔ ኦፒፋዎዋ፣ | ጓደኛህ ይድከምና |

ከላይ የተገለጹት የለቅሶ ቃል ግጥሞች የሟች ቤተሰብ ለጀግና ሞት በቴሻ (ለቅሶ) ላይ የደረደሩት የቃል ግጥሞች ናቸው፡፡ በሁለተኛው መስመር ላይ ‹‹አንበሳዬ›› የሚለው ቃል በጀግንነቱ የበላይ መሆኑን እንዲሁም በአራተኛው መስመር ላይ ‹‹እንሽላሊት ያስፈራራን፣ ኮሽታ ያስፈራራን›› የሚለው ሀሳብ ጀግናችን ሞተሀልና ከአሁን በኋላ ጥቃቅን ነገር ነው

---

[9] ካማድር፣ አዳድር፣ ዲፕሳ ፡- የጠላት መከላኬያ ኬላ ስሞች ናቸው፡፡

[10] ካምቤል፡- የጠላት መከላኬያ ኬላ ስም ነው፡፡

የሚያስፈራራን ምን ይሻለናል በማለት ለጀግና ሞት የተደረደሩ ስነቃሎች ናቸው፡፡ ሚች በተለያዩ ጦርነቶች ተሳትፎ የነበረው ከሆነ የውጊያ ቦታዎቹ፣ ጀግንነቱ፣ ጓደኝነቱ እየተጠራና እየተወደሰ ነው የሚለቀሰው፡፡ ለምሳሌ፡- ከዚህ በታች የተገለጹ ለለቅሶው የሚመጣ የሟች የቅርብ ጓደኛ በለቅሶው የደረድራቸው ስነቃሎች ናቸው፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አውኔዋ፣ አውነዋ፣ አውኔዋ | ወይኔ፣ ወይኔ፣ ወይኔ |
| አምባንሶ አግሪ አማባንሶ ኡጼሪ | ምን ሆነህል፣ ምን አገኘህ |
| አኜን ኔቦክ አምኒዋ | ና ለውጊያ እንሂድ |
| ካማድርኖን፣ አደድርኖን፣ ዲፕሳኖን | ካማድርኖን፣ አደድርኖ፣ ዲፕሳኖን(የቦታ ስም) |
| ካቢን አምኒዋ ካምቤልዋ | ተነሳና እንሂድ ካምቤል(የቦታ ስም) ነው |
| አውኔዋ ዞሞታሶ ቴጋና ከስዋ | ወይኔ ጓደኛዬ ልጥራህና ውጣ |
| አኜን አምኒዋ ኦታና አማናሶ | ናና እንሂድ ከማን ጋር ልሂድ |
| ጋቹኔ ኦቾፒፋንዋ | በሬዎችህ ይዳከሙ |
| ዞሞኔ ፒፋዎዋ | ጓደኞችህ ይዳካሙ |
| ቤዝኒሶ ያዲዋ፣ ያዲዋ | ጀግናችን ያዲ ነው፣ ያዲ ነው(የቦታ ስም) |
| ዲፕሳዋ፣ ካምቤልዋ | ዲፕሳ ነው፣ ካምቤል ነው (የቦታ ስሞች) |
| ካቡዋ፣ ካቡዋ፣ ኦፒቶሶ | እረ ተነስ፣ እረ ተነስ ደከመህ ወይ? |
| ካቡዋ፣ ኦፒቶሶ ዞሞታሶ | ተነስ እንጂ ጓደኛዬ ደክሞሀል ወይ? |
| ዞሞኔሳ ጎዳ ኦፒፋንዋ | የጓደኛህ አቅም ይዳከም |
| ዞሞኔሳ ታላ ካተፋንዋ | የጓደኛህ ቋንጃ ይቆረጥና |
| የረፋይዋ ካቡዋ | አይዞህ ተነስ እንጂ |

| | |
|---|---|
| ዛጻሶ ዎልጉዋ፣ ዛጻኔሶ ኦጳ ያንዋ | ጦርህን መልስ፣ ጦርህን ይገፍ መጥታቻለሁ |
| ዛጻኔሶ ኦጳ ያዲፋንዋ | ጦርህን ይገፍ እየመጣሁ ነው፡፡ |
| አኔ ካሰፈኒ ዛጻሶ ኦጳ ያድፋንዋ ዎልጉዋ | አብረን የምንጫወተውን ጦር ይገፍ መጥቻለሁ |
| ኬሳ አን ኔቦሲ ዎልጉዋ | ወጥተህ ይሄን ጦር መልስ |
| ዛጻሶ ዎልጉዋ | ዘንጉን መልስ ፡፡ |

ወይኔ ምን ሆነህል፣ ምን አገኘህ፣ ና ለውጊያ እንሂድ፣ በማለት ድንገት እንኳ ሲጠራ ቶሎ ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን ለማስታወስ ‹‹ጓደኛዬ ልጥራህና ውጣ››፣ምነው ዛሬ ዝም አልክ፣ ጀግናችን ተነስ እንጂ በማለት ጦር ይዘው የሚያለቅሱትን ለቀስተኞችን ጠላት በማስመሰል ተነስና ይህን ጦር መልስ በማለት የሚማጸንና የቤተዘመድን ስሜት የሚኮረኩሩ የተግባር ቃላት ጥቅም ላይ የዋሉበት የለቅሶ ግጥም ነው፡፡

ካማድር፣ አዳድር፣ ዲፕሳ፣ ካምቤል፣ ያዲ የሚሉ ቃላት የጦር ምሽግ ቦታ ስሞች ሲሆኑ ለጀግንነቱ ትውስታነት የተጠቀሱ ናቸው ፡፡

### ሚች ጀግንነቱ እንደለ ሆኖ የዕድሜ ባለጸጋ ከሆነ፡-

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| ኦይ አባኒሶ ቤዚሶ | ወይኔ አባታችን ጀግናችን |
| ገዴውኒሶ ካሹምኒሶ | ወይኔ ዝግባችን ዋርካችን |
| ዎላባሶ ኬጹኒኛ | ኬላዎችን ይቆጣጠሩልን |
| ሽምርዋ ሽምርዋ | ሽምር ነው ሽምር ነው(የቦታ ስም)፡፡ እየተባለ |

ጀግንነቱና ዝናው ይወደሳል፡፡

በዚህ የለቅሶ ግጥም የተደረደሩ ቃላት ሚች ጀግና ብቻ ሳይሆኑ ወገን ሰብሳቢና አስተማማኝ መከታ እንደነበሩ የሚገልጹ ናቸው፡፡ በየም ብሂረሰብ ዘንድ ዝግባ የጥንካሬ ተምሳሌት ሲሆን ዋርካ ደግሞ የበላይነትንና ሰብሳቢነትን የሚወክል ነው፡፡ በመሆም

የሟችን ማንነት ለማስተዋወቅ በለቅሶ ቃል ድርደራ ውስጥ ወይኔ ጀግናችን በማለት ጀግንነታቸውን በማስቀደም ለጥንካሬአቸው ደግሞ ‹‹ወይኔ ዝግባችን›› በማለት እንዲሁም ለወገን መጠለያና ከለላ መሆናቸውን ደግሞ ‹‹ዋርካችን›› የት እንሄዳለን በማለት ባንድ በኩል የሟችን ዝና የሚያወድሱበት በሌላ በኩል ደግሞ ከለላቸውን በሞት በመነጠቃቸው መቆጨታቸውን ለመግለጽ የተደረደረ የለቅሶ ግጥም ነው፡፡

የለቅሰሶው መጠን ጠንከር የሚለው ሟች  የልብ ጓደኛ ወይም ጠንካራ ዝምድና ያለው ከሆነ ስሜትን የሚነካ ቃል እየጠቀሰ ከማልቀስ በተጨማሪ ቀደም ሲል ቢሆን ጦሩን አቁሞ ወደ በራፍ እንዲሁም ወደ ውጭ እየተመላለሰ በደረቱ ወድቆ እየተነሳ እንደሚያለቅስለት ነው ከተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃ  መረዳት የተቻለው፡፡ በጀግና ሞት ለቅሶ ላይ የሚደረደሩ ስቃሎች ባብዛኛው በሚባል መልኩ በጀግንነቱ ላይ ያተኮሩ እንደሚሆኑ ነው ቁልፍ መረጃ አቀባዮቹ የገለጹት፡፡

ከዕድሜ አንጻር ለወጣቶች ሞት ታላቅ ለቅሶና መሪር ሀዘን ነው ሚኖረው፡፡ የለቅሶ ስነቃሉም የሟች ወጣቱን ብህሪና ተግባር የሚያወሱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ገና ከወጣትነቱ የጀግንነት ወኔ ያለው ወጣት የሞት እንደሆነ ለወላጆቹና በአካባቢው ምን ዓይነት ልጅ እንደነበረ መልካምነቱና ተስፋው ነው እየተወሳ  የሚለቀሰው፡፡ ለአብነት ከዚህ በታች የተመላከተውን የቴሻ(ለቅሶ) ግጥም መመልከት ይቻላል፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አውኔዋ ቤዝኒሶ | ወይኔ ጀግናችን ወይኔ ጀግናችን |
| ባኢኒሶ ኦንሶ አርጋሱኒ | ሸክማችንን ማን ነው የሚያግዝልን |
| ከውኔሴ ከሊቶሶ አባኔኬሶ | በለጋነትህ የተቀጠፍከው አባትህንሳ |
| እማማኖ ኦኒክ ኦቲሶ | እናትህን ለማን አደራ ሰጠህ |
| ኪታ ታራባሶ ዳጌና አምሶ | ምነው ሞት ተራውን ዘነጋ |
| አቤኔሶ አቤኔሶ | ምነው፣ ምነው፣ ምነው |
| ካቢራ ስንስታ ዜማ | ከፊት ለፊት ቅደምልን |

ኬጺራ እኖትን ፉኦዋ                ከለላ ሆነህ አድነን ፡፡ እየተባለ እጅግ በመረረ ስሜት ይለቀሳል፡፡

ከላይ የተመላከተው የለቅሶ ግጥም ሟች የጀግንነት ወኔና በወጣትነቱ ባካባቢው ለተከሰቱ ችግሮች ደጀንነቱን በማሳየትና አለሁላችሁ በማለት ቤተሰብ ብቻም ሳይሆን የአካባቢው ማህበረሰብ ጭምር በብዙ ነገር ተስፋ ያደረገው ልጅ መሆኑን የሚገልጹ ስንኞችን የያዘ ነው፡፡ እንዲሁም የሞት ጽዋው ያለጊዜው እንደ ደረሰው ሞትንም ጭምር የሚወቅሱ ናቸው፡፡

ወጣትነት ወላጅ፣ ማህበረሰብም ይሁን ሀገር ለብዙ ነገር ተስፋ የሚያደርግበት ነው፡፡ በየም ብሄረሰብ ዘንድም ወጣትነት መመኪያና ተስፋ ነው፡፡ ይህ ተስፋ መንገድ ላይ ሲቀር ለወላጆችና ለአካባቢው ማህበረሰብ እጅግ መሪር ሀዘን ነው የሚፈጠረው ፡፡ በመሆኑም የለቅሶው መጠን ከፍተኛ ነው፡፡ የአለቃቀስ ስርዓቱንም ስንመለከት ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሀዘናቸውን የሚገልጹት በቴሻ የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ የቅርብ ዝምድና ያላቸው ወደ ለቅሶ ቤቱ ደጅ ሊደርሱ ሲቃረቡ በጩኸት እየሮጡ መሄድ፣ እደጅ ሲደርሱ ደግሞ  በደረት መውደቅ፣ በቁጭት የሚይዙትንና የሚጨብጡትን ሲያጡ፣ ደረት መድቃት፣ ልጆች የሆኑት ደግሞ ጭንቅላታቸውን በሁለቱም እጆቻቸው በመያዝ በቁጭት እየነቀነቁ  ማልቀስ፣ የሟች ወላጆች ዘለው ወደ እቅፋቸው ሲገቡ ሲታይ ሁሉንም ለቀስተኛ ማለት በሚያስችል መልኩ ወደ መራራ ሀዘን ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርግ ነው (ምልከታ 18/8/2011 ዓ.ም አዝጊ ዘምዳ ቀበሌ)፡፡

አቶ ሳህሌ፣ አቶገዛኸኝ፣ አባ ፊጣና አቶ ወልደማሪያም ለወጣቶች ሞት እጅግ የተለየ መሪር ሀዘን እንደሚሆን ነው በተመሳሳይ ሀሳብ የገለጹት፡፡ ወጣቶች ሲሞቱ በጣም ምርር ያለ ለቅሶና ሀዘን የሚሆንበት ምክንያት  ቤት ሰርቶ ለትዳር እየተዘጋጀ የነበረ እንደሆነ፣ በአካባቢው ጥል ተነስቶ ጠላትን ደብድቦ በማስፈራራት እኔ አለሁ በማለት ደጀንነቱን ያሳይ የነበረ እንደሆነ ለአካባቢውና ለወላጆቹ ያለው ተስፋ መንገድ ላይ በመቅረቱ  ነው፡፡ ለቅሶውም የሟች የዘር ሀረግ ማንነትና የስራ ጥናካሬ በቴሻው እየተጠቀሰ ነው የሚለቀሰ ው፡፡ በለቅሶው  የሟች አባት እንደሚከተለው  እያለ ነው የሚያለቅሰው ፡፡

በመገኛ ቋንቋ                በአማርኛ

| | |
|---|---|
| ናታሶ፣ ናታሶ[11] | ወይኔ ልጄ፣ ወይኔ ልጄ |
| አባታሶ፣ አባታሶ ኢ.ታ | ምነው አባቴ፣ አባቴ ብትል |
| አዋጊንሶ፣ አዋጊነሶ ታ ዘምባታ | እኔ እንዳልቀድም ምን አደረኩህ |
| ኦንሶ ታን ማምሱኒ | ማነው የሚጠይቀኝ |
| ካቢፋ ዎሌን ኦዶንዋ | ተነስተህ አናግረኝና ልስማህ፡፡ |

በብሄረሰቡ አመለካከት መሰረት አባት እያለ ልጅ ቀድሞ ሲሞት ተራውን ያልጠበቀ ሞት ነው የሚባለው፡፡ ልጅ አባቴ አባቴ፣ እናቴ እናቴ ብሎ ቢያለቅስ ይሻላል ነው የሚባለው፡፡ ወላጅ እያለ ወጣት ልጅ ቀድሞ የሚሞተው በወላጆች የተፈጸመ የሆነ ጥፋት ይኖራል ስለሚባልም የወጣት ልጅ መሞት ለወላጆች እጅግ ከባድ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ አባት በለቅሶው ‹‹ወይኔ ልጄ ምናለበት እኔ ቀድሜ ሞቼ አንተ አባቴ አባቴ ብለህ ብታለቅስ፣ አንተ ቀደምክ ማን ይጠይቀኛል በማለት ተስፋ አስቆራጭ ቃላትን እየደረደረ ሲያለቅስ እናቲቱም እንደዚሁ ባህሪውንና ተግባሩን፣ በልጇ ላይ የነበራትን ተስፋ እያነሳች ታለቅሳለች፡፡ ለቴሻ የሚመጡ ወዳጅ ዘመዶች የሚከተሉትን ዓይነት የለቅሶ ግጥም ቃላትን እየደረደሩ በማልቀስ ሌሎችን ያስለቅሳሉ፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አምሶ አግሪ፣አምሶ አግሪ - | ምን ሆነህል፣ ምን ሆነህል? |
| አውኔዋ ቤዝኒሶ | -ወይኔ ጀግናችን |
| አቤነሶ አበኔሶ | ወይኔ ወይኔ |
| ካቢራ ስኒስታ ዜማ | ተነስተህ ከፊታችን ቅደም |
| ከጺራ እኖትን ፉኦዋ | ተከላክለህ እኛን አድነን |

[11] ናታሶ፣ ናታሶ ፡- በየምኛ ወንድ ልጄ፣ ወንድ ልጄ ማለት ነው፡፡

*የቹዋ፣ የቹዋ፣ የቹዋ　　　　　　　አሻም፣ አሻም፣ አሻም*

*በማለትና ለታዳጊዎች የሚኖረው የለቅሶና የሀዘን ስሜት እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ የግንዛ ስርዓቱ ለሌሎች እንደሚፈጸመው በተመሳሳይ መልኩ የሚፈጸም ሲሆን የተለየ የቀብር ስርዓት የሌለ መሆኑን ነው አቶ ሳህሌ ዘበን እንደሚከተለው ያስረዱት፡፡*

> *በጥንት ቤራዎች ብቻ አስክሬን ገንዘው መቃብር ቆፍረው ብቻቸውን ነው ወሰወደው የሚቀብሩበት፡፡ የሚከፈነው ግን በጋቢ ነው፡፡ ዛሬ ደግሞ ወላጆች አስክሬን አጥበው እንደሌሎቹ የአስክሬን አገናነዝ ሂደት ገንዘው ነው የቀብር ስርዓቱ በወዳጅ ዘመዶችና በአካባቢው ማህበረሰብ ለቅሶ ታጅቦ ወደ ቀብር ቦታ የሚሄደው፡፡*

ለየም ብሄረሰብ ታዳጊነት እንደወጣትነ ሁሉ ተሰፋና መመኪያ ነው፡፡ በመሆኑም ታዳጊ ልጆቻቸውን በሞት የተነጠቁ ወላጆች ራሳቸውን መቆጣጠር በማይችሉት የለቅሶ ስሜት ውስጥ ነው የሚገቡት፡፡ ራሳቸውን እስከመሳትም ይደርሳሉ፡፡ የሟችን ልብስ ይዜው ለቀስተኞች በሚያዩት አኳኋን ወደ ላይ ከፍ አድርገው በመያዝ መዝለል፣ ደረት መድቃት፣ መውደቅ መነሳት፣ ፊት መቧጠጥ፣ ሀዘናቸው እጅግ እየበዛ ሲሄድ የእንባ መድረቅ፣ የድምጽ መታፈን በታዳጊዎችና ወጣቶች ሞት በወላጆችና በቅርብ ዘመዶች ዘንድ የሚኖር የሀዘን ስሜት ነው፡፡ አቶ ገዛኸኝ የለቅሶ ስሜቱን በተመለከተ እንደሚከተለው አስረድተዋል፡፡

> *ለታዳጊ ህጻናትና ወጣቶች የሚኖረው ለቅሶ እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡ ሀዘኑም በተለይ ለቤተሰብ እጅግ መሪር ነው፣ ገና በለጋው የተቀጨ ተብሎ ከፍተኛ ጩኸት ያለው ለቅሶ ነው የሚለቀሰው፡፡ የለቅሶ ስርዓቱ በቱሻ የሚከወን ሲሆን ሟች ታሪክ ሳይሰራ ተራውን ባልጠበቀ ሞት ያለዕድሜ በመንገድ ላይ የተቀጠፈ በመሆኑ ዚዛ አይከወንም፣ ኪኖም (የመከፈኛ ልብስ) የቤት ጣሪያ ላይ ወይም አጥር ላይ አይነጠፍም፡፡ መሞቱ ተረጋግጦ አስክሬኑ ከተገነዘ በኋላ*
>
> *ሞት የተከሰተው ከቀትር በኋላ ካልሆነ በስቀር በዕለቱ ይቀበራል እንጂ ዘመድ እስኪመጣ ድረስ ተብሎ አይጠበቅም፡፡ የለቅሶ ስነቃሉም የሟች ቤተሰቦች ሟች ወንድ ከሆነ ናታሶ፣ ናታሶ (ልጄ ልጄ)፣ ሴት ከሆነች ደግሞ (ናናሴ ናናሴ) እያሉ ነው በስማቸውም ጭምር እየጠሩ የሚያለቅሱት፡፡ እናት*

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| ማራ ሁሻ ታ ኡግናስታን ፉእተፋንዋ | በልቼ የጠጣሁት እኔ በመንገድ ላይ ልቅር፣ |
| ታር ስንፋንዋ፣ | ሞቱ የኔ ይሁን ፡፡ |
| ታ ትሽፋዋ | እኔ ድብን ልበልልህ |

እያለች  ወድቃ እተነሳች፣ ደረቷን እየደቃች  ስታለቅስ አባት ደግሞ

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አዋጋናሶ አዋጋናሶ | ምን አድርጌህ ነው ምን አድርጌህ ነው |
| ሜያ ታን ኦጸንዋ፣ | ገዳዩ እኔን ይዞኝ ይሂድ |
| ሚያሶ ኦንሶ ኬምንሪ | ከፕቶችን ማን ያግዳቸዋል፡፡ እያለ የጦሩን ዘንግ |

በቀኝ እጁ  ይዞ በቁጭት ነጠር ነጠር እያለ ያለቅሳል፡፡ ለቴሻ የሚመጡ ወዳጅ ዘመዶችም ኡ….. ኡ…..ኡ…. እያሉ በጩኸት ነው ለቅሶ ቤቱ ደጅ  የሚደርሱት፡፡ በለቅሶአቸውም ድሮ የሞቱ የሟች አያቶችንና ዘመዶችን ስም እየጠሩ፡-

| | |
|---|---|
| ካሮ ኮኢዮይ፣ | ከፊኑ አለቀ ወይ |
| ካሮ ኪኒዮይ፣ | ከፊኑ ቆሸሸ ወይ |
| አካ ኪታታዋ | ውሃ እንዳትቀዳላቸው |
| ጌያ ኦጳ ኢማታታዋ | እሳት እንዳታቀብላቸው |
| ፉሬራ ፉኦ ኦፕሰኒዮይ | ዋጅታችሁ ማትረፍ አቃታችሁ ወይ |
| ታኪ ያፋ አቼራ ፉእቴታ | ምነው እኔ ጋር መጥተህ ተደብቀህ ብትተርፍ |
| ቡራኒ ኮሪራ ኮትበኒያ | ነግረውኝ ዋስ ሆኘ ባተረፍኩት፡፡ |

እያሉ የተለያዩ የሀዘን ስሜትን የሚያባብሱ ቃላትን እየተናገሩ ነው የሚያለቅሱት፡፡

ይሄኛው የለቅሶ ግጥም ወቀሳ ያለበት ነው፡፡ የሚወቅሱትም ቀድሞ የሞቱ አያት ቅድመ አያቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ከላይ በተደረደሩ ስንኞች በአማርኛ አቻ ትርጉም የተመላከቱትን ብናይ ከፈኑ አለቀ ወይ

ከፈኑ ቆሸሸ ወይ

ውሃ እንዳትቀዳላቸው

እሳት እንዳታቀብላቸው፡፡ የሚሉ ስንኞች ለቀድሞ የልጁ አያት ቅድመ አያቶች የተገጠመ ነው፡፡ መልዕክቱም ታዳጊውን ለምን ጠራችሁት ከፈናችሁ አለቀ ወይ፣ ከፈናችሁ አረጀ ወይ፣ ለመቀየር አስባችሁ ከሆነ አይሆንላችሁም በማለት የሚወቅሱ ሲሆን ሟች ህጻኑን ደግሞ ለነሱ ውሃ እንዳይቀዳላቸው፣ እሳት እንዳያቀብላቸው የንዴት ምክር የሚሰጥ ስነቃል ነው፡፡ ከእነዚህ የግጥም ስንኞች ልንረዳ የምንችለው በአንድ ቤተሰብ ውስጥ በቀድሞ ሟቾችና በህይወት ባሉት መካከል በስጋ ቢለዩም በመንፈስ ግን ግንኙነት እንዳለ ነው፡፡ ገዳዩ የሙት መንፈስ እንደሆነና በሆነ ምክንያት መግደልም ማዳንም ይችላል የሚል አንድምታ ያለው ነው፡፡ እንዲሁም የመጨረሻዎቹ ፡-

ዋጅታችሁ ማትረፍ አቃታችሁ ወይ

ምነው እኔ ጋር ተደብቀህ ብትተርፍ

ነግረውኝ ዋስ ሆኘ ባተረፍኩት፡፡

የሚሉ ሶስቱ ስንኞች ደግሞ የሟች ታዳጊ ህጻኑን ወላጆች የሚወቅሱ ናቸው፡፡ ለህጻኑ መሞት የፈጸሙት ጥፋት እንዳለ ሲጠራጠርና ለጥፋታቸው መፍትሂ ማፈላለግ ሲችሉ ችላ ብለው ነው ህጻኑ የሞተው የሚል ስሜት በውስጡ ሲፈጠር የተደረደረ ሀሳብ ነው፡፡በዚህ ጥፋት ምክንያት ነው የቀድሞ ሟቾች ልጁን የጠሩት የሚል የጀርባ መልዕክት ያለው ነው፡፡

ለታዳጊዎች የሚፈጸመው የቀብር ሂደት ስርዓት የራሱ መልክ አለው፡፡ በለቅሶ እንጂ ዚዛ እየተከወነለት ወደ ቀብር ቦታ አይሄድም፡፡

በየም ብሄረሰብ ጨቅላ ህጻን ሲሞት መጠነኛ የሆነ ለቅሶና ሀዘን ነው የሚኖረው፡፡ እንዲያው ይደበቃል እንጂ ሞተ ተብሎ አይነገርም፡፡ ለማጽናናትም አይኬድም፡፡ መቅበ ሪያ ቦታውም በወላጆቹ እንሰት ማሳ ውስጥ ባለ ዛፍ ስር ተቆፍሮ ነው በትንሽ ሳጥን የሚቀበረው፡፡ ይህ ህጻን ለምስክርነት ሳይበቃ፣ አንድ ነገር ሳይበላ ሰጥቶ የወሰደው ሀኦ(አምላክ) ስለሆነ ነው ተብሎ ነው የማይለቀሰው፡፡ ለጨቅላ ህጻን በምሬት ከተለቀሰ ታላቅ ለቅሶ ከደጃፋችን ሊነሳ ይችላል፣መጥፎ ነገር ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ነው የሚከለከለው፡፡ ከጨቅላነት ያለፈ ህጻን ከሆነም ብዙ የማስለቀሻ ቃላት ድርደራ ሳይኖር እንደነገሩ በሶሶ ( የቃላት ድርደራ ሳይኖር በለሆሳስ በሆነ የለቅሶ ቅላጼ) ብቻ ነው የሚለቀሰው፡፡ እናትየው ግን በሶሶ ውስጥ፡-

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| ጋዳናሴ ጋዳናሴ | ቆንጆዬ፣ ቆንጆዬ |
| ሙኩናሴ ሙኩናሴ፣ | ድብርት ማጥፍያዬ፡፡ |

እያለች ታለቅሳለች፡፡ ክስተቱን የሰሙ ቅርብ ጎሬቤቶችና ቤተሰብ ለኦቾ[12] በመገኘት ‹‹አምላክ የራሱን ወስዷል ላንቺ የሚሆን የሚያድግ ልጅ ይስጥሽ›› እያሉ ያጽናናሉ››፡፡

ከአማሟት ሁኔታ ጋር በተያያዘ በየም ብሄረሰብ እምነት መሰረት የአምላክ ቁጣ ነው ተብሎ በሚታመኑ ህመሞችና አደጋዎች ለሚሞት ሰው በተለየ ስርዓት ነው የአስክሬን ግብዓተ መሬት የሚፈጸመው፡፡

በመብረቅ አደጋ ሰው ከሞተ እንደሌሎቹ የየም ብሔረሰብ አባላት የለቅሶ ስርዓት አይፈፀምለትም፡፡ መብረቅ ከእግዚአብሄር ቁጣ ጋር የተያያዘ ነው ተብሎ የሚታመን መሆኑን ነው አቶ ገዛኸኝና አቶ ኃይለማሪያም በተመሳሳይ ሀሳብ የሚናገሩት፡-

[12] ኦቾ ፡- ወገኑን በሞት የተነጠቀን ወዳጅ ዘመድ ያለ ለቅሶ ማጽናናት፡፡

*መብረቁ ከሰማይ ቤት ተወርውሮ የመጣ እሳት ነው ስለሚባል በኛ ብሄረሰብ እምነት መሰረት መብረቅ ቤት ሲመታ ከተጮኸ እሳቱ በጣም ይስፋፋና በዚያ አካባቢ ያለውን ሁሉ ሊያጠፋ ይችላል ስለሚባል ‹‹ጋማ››[13] (በስርዓቱ አውድ መሰረት መልካም ነው እንደማለት ነው) ይባላል እንጂ አይጮህም፡፡ መብረቁ የመታው ዛፍ ስር፣ ቤት ውስጥ፣ የእንስት ማሳ ውስጥ ወይም ውጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰውየውን ወይም ከብቱን፣ ቤቱን መብረቁ መትቶ ቢሆንም ጋማ (መለካም ነው)፣ ዴዶሴ ጋማ (ነገድንዱ መልካም ነው)፣ ጌየሴ ጋማ (ባንተ መጄን) ሲባል ነው እየነደደ ያለው እሳት ሊረጋጋ የሚችለው፡፡ ይህ ሳይደረግ ጩኸትና ለቅሶ ቢቀጥል እሳቱ እየጨመረ ነው የሚሄደው፡፡ ‹‹ጋማ›› ማለት አንተ ያመጣኸው መልካም ነው፣ አንተ ያመጣሄውን አብርድልን ማለት ነው፡፡ ይህ ስርዓት የሚፈፀመው በ‹‹ጋዛ›› ስርዓት ነው፡፡ የጋዛ[14] ስርዓት የሚፈፀመው ደግሞ በቤራዎች (የሸክላ ስራ ሙያተኞች) ሲሆን ስርዓቱን ከፈፀመ በኃላ አደጋው ከደረሰባቸው ወገኖች ንብረት ይወስዳል፡፡ የሞተውን ሰውም ሆነ እንስሳ ቤራው ነው ወስዶ የሚቀብረው፡፡ በጥንት ጊዜ አስክሬን በየጎሳው ይቀበር ስለነበረ የጋዛ ስርዓቱ ከተፈፀመ በኃላ በጎሳው መቃብር ቦታ ቤራው ወስዶ ሊቀብር ይችላል፡፡ ይህ የመብረቅ አደጋ ሲከሰት ዛሬም ቢሆን የእርቅ ስርዓቱን ቤራዎች የሚፈፅሙበት ሁኔታ አለ፡፡ ከሀይማኖት ጋር በተያዘም የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዩች ቄስ በማስመጣት ፀበል አስረጭተው ከዛሬ ጀምሮ ወደ ሌላ እንዳይተላለፍ በማለት የእርቅ ስርዓት የሚያስፈፅሙ አሉ ፡፡*

በየትኛውም የፈጣሪ ቁጣ ነው ተብለው በሚፈሩ አደጋዎችና በሽታዎች እነሱ ናቸው ተገኝተው እርቅ የሚፈፅሙት፡፡ ይህ ስርዓት ለባላም አማልዕክት ታርዶ የሚሰዋ ጥጃ /በሬ ጋር ጌንር (የእሳት) ተብሎ በሌሊቱ ሰው ከመኘታው ሳይነሳና አስክሬን ሳይቀበር ነው ታርዶ የሚሰዋው፡፡ ይህ

[13] ጋማ ፡- በየም ብሄረሰብ ባህል መሰረት መብረቅ ሰው ላይ ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ሲያደርስ በሆነ ምክንያት ለቁጣ የመጣ ነው ተብሎ ስለሚታመን ማልቀስ ወይም መጮህ ክክል ነው ፡፡ ስለዚህ ‹‹ጋማ›› ማለት ካንተ ዘንድ (ከአምላክ) የሆነው መልካም ነው፣ ባንተ መጄን እንደማለት፡፡

[14] ጋዛ ፡- በየምኛ መናዘዝ ማለትሲሆን የመብረቅ አደጋ፣ መንቲያ ሲወለድ በሚፈጸመው ስርዓት ላይ ‹‹ጋማ›› እየተባለ የሚፈጸመው ኑዛዜና እርቅ ነው፡፡

መስዋዕት ‹‹ባትካል›› ይባላል፡፡ ከዚህ በኃላ በመብረቅ አደጋ የሞተው ሰው በጥቁር ጥለት ልብስ ነው ተገንዞ የሚቀበረው ፡፡ በጋዛ ስርዓቱ ላይ የተለያዩ ቁሶች ይዘጋጃሉ፡፡ ቁንዶ በርበሬ፣ ወጅሚያ /አንጮቴ መሳይ ፍሬ ያለው ሀረጋማ ተክል/፣ ፎትማ /ልጥ/፣ ቱቡ/የሀረግ አይነት/፣ አብዲራ/በመስቀል ቅርፅ የተሰራ ብረት ጋር ተይዞ የጋዛ ስርዓት ይከናወናል፡፡ በስርዓቱ ላይ ከሚባሉ ስነቃሎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

| **በመገኛ ቋንቋ** | | **በአማርኛ** |
|---|---|---|
| አዝማች፡- ጋማ | | መልካም ነው |
| ዶኖካሞ ጋማ | ጋማ | ኖካሞ (የሰማዩ ወይም የተራራ አምላክ) መጄን |
| ጌያ እማሴ ጋማ | ጋማ | እሳቱን የሰጠን መጄን |
| ዳካሞ | ጋማ | ዳካሞ (የምድር ውስጥ አምላክ) መጄን |
| ጋርካሞ | ጋማ | ጋርካሞ (የጋር ተራራ አምላክ) መጄን |
| ዳክ ማዳውና ጋማ | | ለምሰሶው መጄን |
| ኤቶና ጋማ | | ከአንበሳው መጄን |
| መውና ጋማ | | ከነብሩ መጄን |
| ግሬንሴ ጋማ | | ተደስተናል መጄን |
| ግሲሴ ጋማ | | ያስደሰተን መጄን |

እየተባለ ቤራዎች በጋዛ (በማናዘዝ) ስርዓቱ ይፈፅማሉ ፡፡

ይህ በመብረቅ አደጋ የተከሰተ ሞት ስርዓተ ክዋኔ በውስጡ በርካታ ጉዳዮችን የያዘ ስለሆነ ሌላ ጥናት የሚሻ ነው፡፡ በዚህ ለመጠቆም የተፈለገው  በዚህ አደጋ ሞት ግብዓተ መሬቱ እንዴት ይፈጸማል የሚለውን ለመጠቆም ነው ፡፡

ሌላው ከአሟሟት ሁኔታ ጋር በተያያዘ ከአስክሬን ግነዛ ጀምሮ እስከ ግብዓተ መሬት ድረስ ያለውን ተግባር ቤራዎች (የሸክላ ስራ ሙያተኞች) የሚፈጽሙት የስጋ ደዌ ህሙማን ሲሞቱ ነው፡፡ በስጋ ደዌ ህሙማን ሞት ሌሎች ሰዎች የሚሳተፉት በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ብቻ ነው ፡፡ በ10/9/2011ዓ.ም በተካሄደ የተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃ መሰረት በየም ብሄረሰብ ዘንድ የስጋ ደዌ በሽታ የአምላክ ቁጣ ነው ተብሎ ስለሚታመን የዚህ በሽታ ታማሚዎች ሲሞቱ ገንዞ የመቅበሩ ሙሉ ሀላፊነት የቤራዎች ነው፡፡ የመቀበሪያ ቦታቸውም የተለየ ነው ፡፡ ሙኒ ሞጋ[15] (የስጋ ደዌ ታማሚ መቃብር) ተብሎ በተለየ ቦታ ነው የሚቀበረው፡፡ የቀብር ስርዓቱም ቤተዘመድና ሌሎች ለቀስተኞች እደጅ እያሉ ቤራዎች አስክሬኑን ወስደው ሊቀብሩ ይችላሉ፡፡ አሊያም ዘመድ አብሮ እያለ ሊቀብሩ ይችላሉ፡፡ የስጋ ደዌ ታማሚ ሆኖ የሞተ ሰው ንብረት ሁሉ የቤራዎች ነው፡፡

ሟች ምንም ያህል ሀብታም ቢሆንም ንብረቱ ለልጆች ወይም ለሌላ አይሰጥም፡፡ ልጆች በልተው የሚያድጉበት እንሰት ከጓሮ ካስቀረ እንኳን መታደል ነው እንደሆነ ነው መረጃ ሰጪዎቹ የሚገልጹት፡፡ ለምን አታስቀርም ተብሎ አይነገርም፡፡ እንዲያውም የሟች ዘመዶች ይዛችሁ ተነሱና ላለው ሰላም ይውረድ እኛ ሰርተን፣ ነግደን እንበላለን እንደሚሉ ነው፡፡ የሟች መኖሪያ ቤት ቤራዎች ካልወሰዱ እንዲሁ ተጥሎ አርጅቶ ሊፈርስ ይችላል

### 5.1.3.1.2. የዚዛ (ሙሾ) ክወና ስርዓት

በተለያዩ ማህበረሰቦች የሀዘን ስሜት የሚገለጽበትና አስክሬን ወደ ማረፊያው የሚሸኝበት መንገድ የተለያየ ነው፡፡ በየም ብሄረሰብ አዋቂዎች በተለይም በዕድሜ የገፉ ሰዎች ሲሞቱ ከለቅሶ ባለፈ ዚዛ (ሙሾ) ይከወንላቸዋል፡፡ የዚዛ ክወናው ግን እንደየማንነታቸውና ማህበ ራዊ ደረጃቸው ይለያያል፡፡ ቴዎድሮስ (2008፣153) ሞት የነገሮች መቁረጫ አሊያም መፈጸሚያ ብቻ አለመሆኑንና ይልቁንም እንደየባህሉ፣ እንደየዘመኑ፣ እንደየግለሰቡ ርዕዮተ ዓለም ሊፈከርና ሊተረጎም የሚችል ዝንቅ ትዕምርት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ በየም ብሄረሰብም ትላልቅ ሰዎች በሞት ሲለዩ ሟች የሚሸኝበትና የብሄረሰቡ የተለያዩ እሴቶች መተዋወቂያና ማስተላለፊያ ከሆኑ አጋጣሚዎች መካከል አንዱ የዚዛ ክወና ነው፡፡ ዚዛ

[15] ሙኒ ሞጋ፡- በዚህ ጥናት አውድ መሰረት የስጋ ደዌ ታማሚ መቃብር ማለት ነው፡

ሀዘንተኞችን ለማጽናናትና ለማበረታታት በተለያዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮች ታጅቦ የሚከወን ከየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ገጽታዎች ውስጥ አንዱ ክፍል ነው፡፡ በዚዛው ክወና ላይ ወንዶችም ሴቶችም ይሳተፋሉ፡፡ የዚዛ ክወናው መሪ፣ አውጪ፣ ተቀባይና ታዳሚ ያለው ነው፡፡ ጋሻ፣ ጦር፣ የአጋዘንና የድኩላ ቀንድ፣ የአንበሳና የነብር ቆዳ፣ ሾሮዶ (ከእንሰት ተረፈ ምርት የሚሰራ የልብስ ማስቀመጫ ሳጥን)፣ የዚዛ ክወናውን የሚያጅቡ ቁሶች ናቸው፡፡

ክወናው የሚካሄደው ለቅሶው በተጀመረ ከሰዓታት በኋላ ሲሆን የሚጀመረውም ካላ (የቀንድ ቡድን ሲድርስ ነው፡፡ይህ የቀንድ ቡድን እንደደረሰ በመሪው አማካይነት የቴሻ ስርዓቱን ካከናወነ በኋላ ትንሽ አረፍ በማለት ውሃ ማጠጫ የሚሆን ምግብ ቀምሶ ይመለስና የዚዛ ክወና ውስጥ ይገባል፡፡ ክወናው የራሱ የሆነ አዝማችና የአካል እንቅስቃሴ (ውዝዋዜ) ስርዓት ያለው ነው፡፡

ክወናውን ሁለት ሴቶች ነጠላቸውን ከወገባቸው በማሰር ከሟች በራፍ በኩል ከሀዘንተኞች ፊት ሆነው የሾሮዶው ክዳን እንዳይወልቅና እጃቸውንም እንዳያሳምም መጨርቅ በማሰር ወደ ቀኝ ወደ ግራ፣ ወደ ፊት ወደ ኋላ ነጠር ነጠር እያሉ ሾሮዶውን ከመሬት ጋር በተመሳሳይ ጊዜ እያጋጩ በባለሁልት ምት የሙዚቃ ቅኝት ድም፣ ድም፣ ድም ድም በሚል ድምጽ ሲያጅቡ ጋሻ የያዙ ወንዶች ደግሞ ፊታቸውን ሾሮዶ ወደሚመቱ ሴቶች በማድረግ በጦር ዘንጋቸው ጋሻቸውን በሾሮዶው ምት ልክ እያጋጩ እንደየዚዛ ቅኝቱ የዜማ ባህሪ ወደፊት ወደ ኋላ ሂድ መለስ እያሉ ወይም በክብ መስመር በመዞር ይከውናሉ፡፡ በትከሻቸው ወይም በጭንቅላታቸው ቀንድ የተሸከሙት፣ የነብርና የአንበሳ ቆዳ ከአንገታቸው እስከ ወገባቸው የለበሱት ወንዶች ቡድንም በፊት መሪው አማካይነት በሰልፍ በመሆን መጀመሪያ የሶምሶማ ዓይነት እንቅስቃሴ እያደረገ የሟችን መኖሪያ ቤት ዞሮ በመመለስ ከተመረጠው የዚዛ ክወና ዜማ ቅኝት ጋር በመዝለል ይከውናል፡፡ ይህ የዚዛ ቡድን ክወናውን ሲጀምር ለቀስተኞች ባብዛኛው ሴቶች በአንድ መስመር የተወሰኑት ደግሞ በወንዶች መስመር ገብተው እንደየዚዛው አዝማች ባህሪ በክብ በመዞር አሊም በሁለት ምድብ ሆነው በመደዳ ተሰልፈው ፊት ለፊት እየተያዩ በመጠነኛ ዝላይ ይከውናሉ፡፡ በዚህ የዚዛ ክወና የሟች ቤተሰቦችም ጭምር ተሳታፊ ናቸው፡፡



ፎቶ 5. የዚዛ (ሙሾ) ክወና

በዚዛ ክወና ለቀስተኞች በሁለት መልኩ ነው ተሳትፎ የሚያደርጉት፡፡ አንደኛው ሙሉ በሙሉ በዚዛ ክወናው በመግባት ሲሆን ሁለተኛው በክወናው የተመሰጡና ለየብቻቸው ሆነው በዋናው ቡድን እንቅስቃሴና ዜማ ቅኝት በመመራት ዳር ቆመው በመንቀሳቀስ ተሳትፎ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ዚዛው ሲከወን ዙሪያውን ከበው የሚመለከቱ ለቀስተኞችም በርካታ ናቸው፡፡ እንዲሁም ቆሞ ለመመልከት አቅም የሌላቸውና ድካም ያለባቸው እይታን በማይከልል በቤቱ ዙሪያ ባሉ የእንሰት ጥላዎች ውስጥ ተቀምጠው ይመለከታሉ፡፡



ፎቶ 6. ዚዛ(ሙሾ) ከዋኝና ታዳሚ

በክወናው አቧራው ሲቦን፣ የደከመው ሲወጣ፣ አዳዲሶች ሲቀላቀሉ  እጅግ እየደራ ይሄድና ለቅሶ ቦታ መሆኑ ቀርቶ ወደ ፍጹም ጭፈራነት ይቀየራል፡፡ በዚህ ጊዜ ካሞ (የሟች ሴት ልጆች ወይም እህቶች) በለቅሶ ጩሄት ዚዛውን በመበተን ወደ ሀዘን ድባብ ይቀይሩታል፡፡ ካሞ የሚባሉት ትዳር ይዘው የሚኖሩ የሟች ሴት ልጆች ወይም እህቶች ጋር የለቅሶ ስርዓቱን የሚያደምቅ ቡድን ሲሆን ለቅሶ ሲከሰት በአምችና ቡድናቸው ተደራጅተው ወደ ለቅሶ ቤት በመምጣት በጩኸት ለቅሶውን የሚያደምቁ ናቸው፡፡ እነዚህ ካሞዎች ሲመጡ ስሜታቸው እጅግ የሚያስፈራ ነው፡፡ ማንም ሊያስቆም የሚችል ዓይነት አይደሉም፡፡ ሁለቱንም እጃቸውን እያወራጩ ኡ፣ ፣ኡ ኡ፣ ኡ፣ ኡ…እያሉ የሟች ቤት ደጅ እንደደረሱ የሟችን ሳር ቤት ቦጭቀው በመጣል፣ የእንሰት ችግኞችን በመነቃቀል፡የትልልቅ እንሰቶችን ቅጠል በመቆራረጥና እቤት ውስጥም ጭምር በመግባት እህል አውጥተው በመበታተን የለቅሶውን ድባብ እጅግ ኃይለኛ ስሜት እንዲኖረው የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ይህ ስሜት የሚንጸባረቀው ከዛሬ ጀምሮ ሁሉም አበቃ፣ መልካሙ አባታችን ወይም ወገናችን እንኳ

ሞቷል ንብረት ምን ያደርጋል በሚል ነው፡፡ እነዚህ ካሞዎች ከሟች ቤት በራፍ አካባቢ በመደዳ ሆነው  የዚዛ ክወናውን ዜማ ይው… ይ…ይው… ይ… ይው…ይ… በማለት አንድነት ባለው የድምጽ ቃና በመጮህ የሚያጅቡም ናቸው፡፡  የዚዛው ክወናው ቆይታ ጊዜ በለቅሶው ዕለት መከወን ከተጀመረበት ሰዓት አንስቶ እስከ መቃብር ቦታ አቅራቢያ ድረስ ነው፡፡ (ምልከታ 21/8/2011 ዓ.ም ኢ.ዲ.ያ)፡፡

*የክወና ስርዓቱን በሚመለከት አቶ ወልደማሪያም ያዳ እንደሚከተለው ጨምረው አጠናክረዋል፡፡*

> *የዚዛ ስርዓቱ በትክክል እንዲከወን ከፊት ለፊት ሆኖ የሚመራ ሰው አለ፡፡ በክወናው ሴቶች ወደዛ ሲሉ ወንዶች ደግሞ የጦር ዘንጋቸውን ይዘው ወዲህ ሲሉ መሪው ወደ ኋላ ዞር እያለ እየተመለከተ ሁለቱንም ይመራል፡፡ ዝም ተብሎ አይደለም፡፡ ዚዛውን ለማድመቅ አሁን አይታይም እንጂ ድሮ የጋን አፍ በቁርበት ታስሮ ከቤቱ በራፍ ተቀምጦ እንደከበሮ ይመታል፡፡ ከስንደዶ የሚሰራና እንስራ የሚመስል ድሮ ቆላ ጥጥ በሚመረትበት ጊዜ ቦርዴ (ባህላዊ መጠጥ) ተይዞ የሚኬድበት ጉዶ የተሰኘ ቁስ ፣ እንዲሁም ሾሮዶ ከመሬት ጋር እየተጋጨ ድም፣ ድም፣ ድም፣ ድም የሚል ድምጽ ሲያወጣ ከዚሆን ጥርስ የሚሰራ ‹‹ኪሶ›› የሚባል በቁጥር አስከ አምስት የሚደርስ የእጅ አምባር ደግሞ ሴቶች በእጃቸው አድርገው እርስ በርሱ እያጋጩት ሷ፣ ሷ፣ ሷ፣ ሷ የሚል ድምጽ ያሰማል፡፡ እንዲሁም አሁን ቀረ እንጂ ድሮ በቅል ትንሽ ፍሬ እህል ተጨምሮበት ሴቶች ሲያንሸዋሸውት ወንዶች በጦሩ ዘንግ መሬት እየመቱ ድምጽ ሲያወጣ ሁሉንም ባንድነት ነው ድምጻቸውን አስማምተው  በማሰማት  ዚዛውን  የሚያጅቡት፡፡  (ቃ.መ.*03/08/2011ዓ.ም ኢ.ዲ.ያ ቀበሌ)፡፡

ከመረጃው መረዳት የሚቻለው የየም ብሄረሰብ ሞትን የሚሸኝበት መንገድ በተለያየ መልኩ ሊገለጽ የሚችል መሆኑ ነው፡፡ ይለቀሳል ይጨፈራል፣ ደስታና ሀዘን የሰው ልጅ የምድር ላይ ቆይታ ሁለቱ ገጾች ናቸው፡፡ የየም ብሄረሰብ እነዚህን ሁለቱን ገጾች ጊዜውን የጠበቀ ሞት ነው ለሚለው ወገኑ ይተውናል፡፡ እያለቀሰም እየተደሰተም መልዕክት ያስተላልፋል ፡፡ ሌላው በየም ብሄረሰብ እምነት መሰረት ሟች ስጋው ከወገኖቹ  ቢለይም ነፍስ ግን በመንፈስ ከአካባቢው አይለይም፡፡ በመሆኑም በብሄረሰቡ ዘንድ ለትልልቅ ሰዎች ሞት

የሚደረጉ የተለያዩ የለቅሶ ክዋኔዎች እንደበረከት ምንጭ ተደርገው የሚታሰቡ ናቸው፡፡ በለቅሶ ላይ የሚገኝ ለቀስተኛ የሟች ቤተዘመድን ከማክበር ባለፈ ለቅሶና ዚዛ (ሙሾውን) ከልቡ የከወነ የሟች መንፈስ ስለሚመለከት በረከት እንደሚገኝም ይታመናል፡፡



ፎቶ 7. ‹‹አሴ›› የተሰኘው የዚዛ ቅኝት ሴቶች ሾሮዶና መሬቱን እንዲሁም ወንዶች የጦር ዘንግና ጋሻቸውን እያጋጩ በሚፈጥሩት የምት ሙዚቃ፣ የአጋዘንና ድኩላ ቀንድ በተሸከሙና የነብር ቆዳ በደረቡ ወንዶች ታጅቦ ሲከወን፡፡

ቁልፍ መረጃ አቀባዬ አቶ አየለ ገላንና ሳህለ ዘበን፣ ዚዛ (ሙሾ) የሚካሄድበትን ምክንያትና አኳኋን እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

> *ቀደም ሲል የነበረውን ታሪክ ስንመለከት የየም ብሄረሰብ 24 ትልልቅ ኑጋሽ ጎሳ ነበሩት፡፡ ሃያ አራቱም የየራሳቸው ግዛት ነበራቸው ፡፡ በተለያየ ምክንያት ወደዚህ መጥተው የተሰባሰቡ በመሆኑ የት እንደነበሩ (የሩቅ ቅድመ አያታቸው የነበሩበትን ግዛት፣ የትና ምን እንደሰራ የብሄረሰቡ አዛውንቶች ከመሞታቸው በፊት ታሪካቸውን፣ የክብር ደረጃቸውንና የትውልድ ሀረጋቸውን በጣም ለሚወዱት ልጃቸው፣ ልጅ ከሌላቸው በአካባቢው ላይ በጣም ታማኝ ለሚሉት ሰው ተናግረው ነው የሚያርፉት፡፡ አንዳንዱ ደግሞ የተወሰነ ቤተሰብ በመሰብሰብ ሁሉንም ነገር ተናግሮ*

*ከጨረሰ በኋላ ሞተ የሚባልም አለ፡፡ ይሄ ነው ትልቅ ሰው ሲሞት ታሪኩ በግጥም መልክ እየተነሳ ዚዛ እየተከወነ የሚች ቤተሰብ እንዲጽናና የሚደረገው፡፡ በተለይ በዚዛ ክወናው በብዛት የሚወሱት በሚች የዘር ሀረግ ቀድሞ የሞቱ ሰዎች ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ እየተላለፈ የመጣ የልዩነት መግለጫ የለቅሶ ስርዓት ነው፡፡ (ቃ.መ. በ16/7/2011ዓ.ም እና 15/7/2011ዓ.ም፣ሳጃ)፡፡*

ከላይ ከተገለጸው መረጃ መረዳት የሚቻለው በየም ብሄረሰብ የሚከወነው የዚዛ (ሙሾ) ስርዓት አንደኛ ዓላማው ለሀዘን ማረሳሻነት ወይም ማጽናኛነት ሲሆን ሁለተኛው የሚች የዘር ሀረግ አመጣጥ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃው ባጠቃላይ የሚችና የብሄረሰቡ ታሪክ ለትውልድ የሚተዋወቅበትና የሚተላለፍበት አጋጣሚ ነው፡፡ በዚዛው የሚች አባት፣ አያትና ቅድመ አያት ስም እየተጠራ ተግባራቸውና፣ ዝናቸው እየተወሳ ነው የሚከወነው፡፡ በዚዛ ክወና መልካም የሰራ መልካምነቱ፣ ጀግና ጀግንነቱ፣ ይወደሳል፡፡ ሞትም የሚወቀስበት መድረክ ነው፡፡ ስለዚህ አንደኛ የዚዛ ስርዓት የብሄረሰቡ ታሪክና ማንነት የሚገነባበት፣ የቀድሞዎቹ የሚዘከሩበትና አዲስ ትውልድ እየተተካ የሚቀጥልበት ነው፡፡ ሁለተኛ ለቅሶና በዜማ የታጀበ ዳንኪራ (ዚዛው) ትዕምርታዊነት ያለው ነው፡፡ ይህም ህይወት ለጊዜው ያበቃለት ቢመስልም እንደገና ወደ ሌላ የሚሸጋገርበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም በየም ብሄረሰብ አስተሳሰብ መሰረት ሞት የህይወት ፍጻሜ አለመሆኑን ነው፡፡ የማህበረሰቡ ታሪክና ማንነት በአንድ ሰው ሞት የማይቋጭ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ በዚዛ ክወናው የብሄረሰቡና የቀድሞ ሚቾች ታሪክ፣ መልካምነት፣ ኢኮኖሚያቸውና ጀግንነት ይወደሳል፣ በዚህም ምክንያት የማህበረሰቡ ቀጣይነት የሚጸናበት ነው፡፡

ሌላው የዚዛ ክወና የሚቾችን እድሜ የሚገልጽ ነው፡፡ ጥሩምባው እየተነፋ፣ የከበሮ ድምጽ የሚያሰሙት የምት ሙዚቃ መሳሪያዎች ድምጻቸው ከርቀት ስለሚሰማ ባካባቢው ትልቅ ሰው መሞቱን የሚገልጹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ዚዛ ለህጻናትና ወጣቶች የማይከወን በመሆኑ፡፡ ጦር፣ የአጋዘንና የድኩላ ቀንዶች፣ የነብርና አንበሳ ቆዳ ለሚች የጀግንነት የግዳይነትና የምርኮ ምልክት ሆነው ክወናውን የሚያጅቡ ናቸው፡፡

ባጠቃላይ የዚዛ ክወና በብሄረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው ነው፡፡ ስርዓቱ ሚችን መሸኛ ብቻ ሳይሆን ስለ ህይወትና ሞት ጠቃሚ መልዕክቶች የሚተላለፉበት ነው፡፡ ይህም ሞት የመሸጋገሪያ ስርዓት መሆኑንና በዚህ ስርዓት ማህበረሰቡ ከአካለ ስጋ

በመንፈስ ወደ መኖር  የሚሸንበት ነው፡፡ ሌላው በዚዛ ክወናው ጀግንነት፣ መልካምነትና የኑሮ ደረጃና የሚወደስበት በመሆኑ ማህበረሰቡ በዚህ አጋጣሚ ስንፍናን የሚያወግዝበትና ጥንካሬን የሚያበረታታበት ነው፡፡

አቶ ሳህለ እንደሚገልጹት የዚዛ ክወና በሚቾች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎች ምክንያት የድምቀት መጠኑ ይለያያል፡፡ ሚች ብዙ ልጆችና አማች ያሉት ወይንም ዘመደ ብዙ ከሆነ ዚዛው ይሞቅለታል፡፡ በኢኮኖሚ ደረጃም የተሻለ መሆን ለድምቀቱ ሚና አለው፡፡

የዚዛ ክወና  ቅኝት ዜማ በሚቾቹ ማህበራዊ ደረጃና ጾታን መሰረት በማድረግ ከሚደረደሩ ግጥሞች ልዩነት በስተቀር አብዛኛዎች ተመሳሳይ ይዘት ኖሯቸው የዜማ ልዩነት የሚታይባቸው ናቸው፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የዚዛ አዝማች ዓይነቶቹ ስምንት ሲሆኑ ኢያንዳንዳቸውን ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡ ከአንድ እስከ ስምንት የተገለጹትና በየስንኞቹ የተሰጡ ቁጥሮች የቅኝቶቹ ቅደም ተከተል ሳይሆን እያንዳንዱን ለይቼ ለማመላከት ስል እኔ የሰጠሁት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

### ቅኝት1. ‹‹አኼያ››

| | |
|---|---|
| በመገኛ ቋንቋ፡- | አኼያ ዬያ አሂ…አሂ ዬሃ…ዬሃ |
| በአማርኛ ፡- | አኼያ ዬያ አሂ…አሂ ዬሃ…ዬሃ |
| በመገኛ ቋንቋ፡- | ኤኪባሪ…አሂ አሂ የሃ ዬሃ |
| በአማርኛ ፡- | እነዲህ ቢያደርግ አሂ ዬሃ…ዬሃ |
| በመገኛ ቋንቋ፡- | ቴሱናይ አሳኖይ አሂ አሂ የሃ ዬሃ |
| በአማርኛ ፡- | የመጀመሪያም አዲስም አይደለም አሂ አሂ የሃ ዬሃ |
| በመገኛ ቋንቋ፡- | ኮችባሪ ካላ ኮችባሪ አሂ አሂ የሃ ዬሃ |
| በአማርኛ ፡- | ይምራ ቀንዱ ይምራ አሂ አሂ የሃ ዬሃ |
| በመገኛ ቋንቋ፡- | ዞሞባሶ ቡሴዲፌ አሂ አሂ የሃ ዬሃ |

በአማርኛ ፡-          ጓደኛቹ እየመከሩ ነው አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-          ዞሞባሳ ጎዳ ሻካና አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-          የጓደኛው አቅም ይድከምና አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-          ሚያ ኢሽኮሶን ኡሽባሪ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-          ከብቶች ኢሽኮን ቢጠጡ  አሂ  አሂ  የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-          ኤቶ ዛዋሶ ቡኚኛ    አሂ ፣አሂ ፣ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-          አንበሳው ሆራውን[16] አደፈረሰ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

ከላይ በተገለጸው የዚዛ ቅኝት አዝማቹ እየተደጋገመ በስንኞቹ ደግሞ የሚቹን ማንነት መሰረት ያደረጉ ግጥሞች እየተደረደሩ የሚከወን ሲሆን ያለ ጾታና ማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ዚዛ ለሚከወንላቸው ሁሉ ይዜማል፡፡ የዚህን ዚዛ ግጥም ስንመለከት ‹‹አሂ ያ›› የሚለው ቃል የቅኝቱ አዝማች ሲሆን ዜማው የተመሰረተበትና ስንኞቹ አዝማቹን መሰረት አድርገው የሚገጠሙ እንጂ የዚህ ቃል ትርጉም ምን እንደሆነ ነው ከመረጃ አቀባዮች ፍንጭ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ በዚህ ቅኝት የተገጠሙ የተወሰኑትን ጠቅሰን ብንመለከት ሶስተኛው መስመር ላይ ሞት በሚቹ እንዳልተጀመረና አዲስ አለመሆኑን ለማመላከት ‹‹ጅማሬም አይደለም አዲስም አይደለም›› የሚል ስንኝ እናገኛለን፡፡ በዚህ ስንኝ ሀሳብ መሰረት ሰው አርጅቶ መሞቱ ወግ ነው፡፡ ሞት በእርሶ አልተጀመረም፣ ያለና የሚታወቅ፣ ድሮ የተወሰነ ነው፡፡ እንደ እርሶ ያለውን ሞት ማሞገስ እንጂ ለቅሶ ማብዛት አስፈላጊ አይደለም የሚል አንድምታ ያለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሚች መልካም ሰው በመሆናቸው፣ የብዙዎች አባት በመሆናቸው ባይሞቱ መልካም ነበር፣ ለሳቸው ሲል ሞት ለምን ሰውን መግደል ጀምረ በሚል ደግሞ ሞትን የመውቀስ አንድምታ ያለው ስንኝም ሃያ አራተኛው መስመር ላይ እናገኛበለን፡፡ይህ ስንኝ ‹‹እሳቸውን የገደለ ሞት ባፍጢሙ ይውደቅ›› ከሚል አውድ

---

[16] ሆራውን ፡- ‹‹ዛዋ›› በየምኛ ሆራ ማለት ሲሆን ከብቶች በረሀ ተወስደው የሚጠጡት ጨዋማ ውሃ ነው፡፡

የተገጠመ እንደሆነ በ04/09/2011 ዓ.ም በተካሄደ የተተኳሪ ቡድን ውይይት ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዚህ ቅኝት የሚከወነው ውዝዋዜ የከዋኞት ግራ እግር ሙሉ በሙሉ ከመሬት ሳይነሳ ከጉልበት ሰበር በማድረግ የቀኝ እግር በመጠኑ ይነሳና ከትከሻም ጭምር በማስማማት በሌሎች ቁሶች ምት ታጅቦ የሚተወን ነው፡፡ የከዋኞች ፊት ሙሉ በሙሉ ወደጎንም፣ ፊት ለፊትም የሚተያይ ሳይሆን በፊት መሪው አማካይነት በክብ የሚዞርበት ነው፡፡( ምልከታ በ21/8/2011 ዓ.ም)



ፎቶ 6. የ‹‹አኸያ›› ዚዛ ክወና

## ቅኝት 2. አርፋኝሳ /ሜያ/

ይህ ቅኝት ጥንታዊ የሚባል ሲሆን አዝማቹ ‹‹ዬሃሃ›› የሚል ነው፡፡ይህ አዝማች ከመነሻ እስከ መጨረሻ በአውራጁም ተቀባዩም የሚዜም ነው፡፡ የሚችን ማንነትና ተግባር ከተለያ ተፈጥሮዎችና ተግባራት ጋር በማነጻጸር የሚዜም የዚዛ (ሙሾ) ቅኝት ዓይነት ነው፡፡በዚዛው ክወና የማይሳተፉ የሚች ቤተሰቦችንም የሚተቹ ግጥሞችም ይደረደሩበታል፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አውራጅ፡- ዎሪፋ ኪታሴ ጋውኔ | ገዳዩ ኪታ በየገደሉ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ቤዛ ቤትዋ ቤዚሶ | ገድለህ ተሰደድ አንተ ጀግና |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡-ዌውኖ ፋዛ ታኞኔ | የአቶ እገሌ ፈረስ እንደተለጎመ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡-ዛዋሲ አባኒ ዎናፌወ ኦጺ | የሆራውን ጌታ መብረቅ መታው |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ካሲ አውኒክ ፋሲሬ | ለወፍ አውራ አስመርምሮ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ኮናኪ ማናሶ ሜሲሬ | የኮናን[17] ሸክላ ሰብሮ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ካሹምኒ ማከቶ ዋሪሬ | እንደዋርካ ሰፍቶ |

[17] የኮንን ሸክላ ሰብሮ= ኮን ማለት በየም ልዩ ወረዳ የሚገኝ የቦታ ስም፡፡

ከላይ የተደረደረው የለቅሶ ቃል ግጥም በጥቅሉ ሲቃኝ የሚያወድሱ፣ የሚያሞግሱና፣ የሚያበረታቱ፣ የሚወቅስ፣ የሚሸረድዱ ስንኞችን የያዘ ነው፡፡ ረገዳው በሁለት መደዳ በመሆን ፊት ለፊት እየተያዩ በመዚቃ መሳሪያዎቹ በመታጀብ ወደፊት ወደ ኋላ ሂድ መለስ ሂድ መለስ እየተባለ የሚከወን ነው፡፡ ወደ ኋላ መመለሻውም ፊት ሳይዞር ወደፊት በሄዱት መንገድ የሚመለሱበት ነው፡፡

## ቅኝት 3. አሴ፡-

ይህ ቅኝት በሁለት ጎራ ሆነው ፊት ለፊት እየተያዩ ቀረብ ራቅ እያሉ የሚከውኑት ሲሆን በሁሉም ዚዛ አይነቶች የሚቀርቡ ቁሶች የማይቀሩ ናቸው፡፡ሟች በህይወት እያለ የሚከውናቸው ተግባራት እየተጠቀሱ እሱን አጥተናል የሰራቸውን ስራዎች እሳት ይፍጀው ተብሎ የሚዜም ነው፡፡ በይዘት ደረጃ ከቅኝት 2 ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ልዩነቱ በዜማ ላይ ነው፡፡ ግጥሞቹ ከዚህ በታች የተመላከቱት ናቸው፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| ከጀሬ ከስናይሶ ጌያ ኮእሳው | አድኖ የወጣውን እሳት ይፍጀው |
| ነበሬ ከስናይሶ ጌያ ኮእሳው | ተዋግቶ የወጣውን |
| ቴጋ ኬንቲሶ ጌያ ኮእሳው | ከፍ ያለ ቤትዎን |
| ፊሽቴ ገሮሶ ጌያ ኮእሳው | መዋያ ቦታዎን እሳት |
| ሳሳካዎኖን ጌያ ኮእሳው | ማዘውተሪያዎን |
| ተሬ ከስናይሶ ዎጃ ኮእሳው | ተቀብሎ የወጣውን ጭልፊት ይፍጀው |
| ባነሬ ከስናይሶ ዎጃ ኮእሳው | ተካፍሎ የወጣውን ጭልፊት ይፍጀው |
| ታጋ ኬባስታ ጌያ ኮእሳው | ሰፊ ቤቱን እሳት ይፍጀው |
| ኤተና ዳባሶን ጌያ ኮእሳው | የውጊያ ሜዳው እሳት ይፍጀው |
| ከጀሬ ከስቴይሶ ጌያ ኮእሳው | ወግተው የወጡትን እሳት ይፍጀው |

| | |
|---|---|
| ታጋ ፊታሮ ጌያ ኮእሳው | ሰፊውን ፊታር እሳት ይፍጀው |
| ታጋ ዋቤዖ ጌያ ኮእሳው | ሰፊውን ዋቤ እሳት ይፍጀው |
| ዖላጎዖ ጌያ ኮእሳው | ዖላጎን[18] እሳት ይፍጀው |
| ኤትኒ ፋዝንቲሶ ጌያ ኮእሳው | የውጊያ ፈረስዖን እሳት ይፍጀው |
| ታሬራ ከስቲ ገብንቲሶ ጌያ ኮእሳው | አንግበው የወጡትን ጋሻ እሳት ይፍጀው |
| ዖላጎ ከማሶ ጌያስ ኮእሳው | የወላጎን ምሽግ እሳት ይፍጀው |
| ኤዞ ከማሶን ጌያስ ኮእሳው | የኤዞን[19] ምሽግ እሳት ይፍጀው |
| ጋርኪ ቱናሶን ጌያስ ኮእሳው | የጋርን[20] ምሽግ እሳት ይፍጀው |

### ቅኝት 4. አውማኬኒ

ይህ ቅኝት ከቅኝት1. ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሲሆን የዝላይ ደረጃው በመጠኑ ከፍ የሚል ነው፡፡ ግጥሞቹም ቢሆኑ የዜማ ልዩነት እንጂ ተመሳሰይነት ያላቸው ናቸው፡፡ አዝማቹ ‹‹አውማኬኒ›› የሚለው ሲሆን አውራጁም ጭምር እየደገፈው በተቀባዮች ምላሽ እስከ መጨረሻው የሚዜም ነው፡፡ ይህ ቅኝት ዜዛ ለሚከወንላቸው በሙሉ ያለጾታና ማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ይከወናል፡፡ ነገር ግን የሚደረደሩ ቃላት የሚችን ማንነት መሰረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የዚህ ቅኝት ግጥም ስንኞች አደራደር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| | በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|---|
| አውራጅ፡- | ኤቶኖቴ ሜውኖቴ | አቶ አንበሳው አቶ ነብሮ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ቴሱናይ አሳኖይ | ጅማሬም አዲስም አይደለም |

[18] ዖላጎ :- የምሽግ ቦታ ስም

[19] የኤዞን :-የምሽግ ቦታ ስም

[20] የጋርን = የምሽግ ቦታ ስም

| | | |
|---|---|---|
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ፉዛ ታኞኔ ፌሽባሪ | ፈረስዎ እንደተለጎመ ይዋል |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ኤኪዮይ ኤኪዮይ | ወይኔ እንዲህ አደረገዎት ወይ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ሶሞባሶ ዋሴድፌ | ጓደኖቹ እያለቀሱ ነው |
| ተቀባይ- | አማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ዞሞባሳ ከእሲዋ | በጓደኞቹ ጉልበት ስር |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ሲባሲክ ዎርፉዎኛ | በአፍጢሙ ይውደቅ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ዎሪ ኪታ ሲባሲክ ዎርፉዎኛ | ገዳዩ ኬታ ባፍጠሙ ይውደቅ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ኤቶኖቴ ሜወኖቴ | አንበሳውና ነብሩ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | አይ ኮሪፌ ኮቶኛ | ወይኔ ዋስ ሆነው ያስፈቱ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | አይ ቶኔይሶ ቶቶኛ | ወይኔ የሚወስዱትን ይውሰዱ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | አይ አኔንትሮ በይቶኛ | የወደፊቱን ይተው |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ኤቶ ዛዋሶ ቡኚኛ | አንበሳው ሆራውን አደፍርሿል |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |

ከላይ የተገለጸው ቅኝት አዝማች ለማንኛውም ትልቅ ሰው ያለ ጾታ ልዩነት የሚከወን መሆኑን ነው የቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረጃ የሚያመለክተው፡፡ ግጥሞቹ የሟቹን ማንነትና የዘር ሀረግ እንዲሁም ጥበብና ጀግንነቱን የሚያወድሱ ናቸው፡፡ ከተደረደሩ ግጥሞች መካከል በአንደኛው፣ ሁለተኛውና ሶስተኛው መስመር ላይ የተገለጸውን ሀሳብ ለአብነት ብንመለከት ሚችነበጥንካሬዎ አንበሳ ነበሩ፣ እንደነብር ብልሀተኛ ነበሩ እንዲህ አደረገዎት ወይ? በማለት ሞት ለማንም የማይቀርና የመጀመሪያም የመጨረሻ አለመሆኑን በሚገልጽ መልኩ ተደርድሮ ይገኛል፡፡

## ቅኝት 5. ማግኖቲና ማግኖ

ይህ ቅኝት የየም ብሄረሰብ በንጉስ ይተዳደር በነበረበት ጊዜ በየግዛቱ በንጉሱ ለሚሾሙና ማግ ለሚባሉ የጎሳ መሪዎች የሚከወን የዚዛ ቅኝት ነው፡፡ ይህ የዚዛ ዓይነት አዝማቹ በሟቹ የስልጣን ስም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከሟቹ ጎሳ ጋር የተያያዙ ገድላትና መንፈሳዊ ተግባራቸው ጭምር ነው እየተወሳ በዚዛው ግጥሞቹ የሚደረደሩት፡፡ ቅኝቱ ለወንዶች የሚከወን ሲሆን የማጎች ባለቤቶች ሲሞቱ ለሌሎች ሴቶች የሚዜሙ ቅኝቶች ይከወኑላቸው፡፡

| | በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|---|
| አውራጅ፡- | ማግኖቲና ማግኖ | ማግኖ ብዙ ናቸው ማግኖ |
| ተቀባይ- | ማግኖቲና ማግኖ | ማግኖ ብዙ ናቸው ማግኖ |
| አውራጅ፡- | ቲር አውኖቴ ማግኖቴ | የብዙዎች መሪ ማግኖ |
| ተቀባይ- | ማግኖቲና ማግኖ | ማግኖ ብዙ ናቸው ማግኖ |
| አውራጅ፡- | አውኒ አውኖቴ ማግኖ | የትልልቆቹ አውራ ማግኖ |
| ተቀባይ- | ማግኖቲና ማግኖ | ማግኖ ብዙ ናቸው ማግኖ |

ቀደም ሲል ማጎች ሲሞቱ ባላቸው የክብር ደረጃ በዚህ አዝማች ግጥሞች እየተገጠመላቸው ዚዛ ይከወንላቸው ነበር፡፡ይህ ቅኝት በብዛት የሚዘወተር አለመሆኑን ነው ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረዳት የተቻለው፡፡ ምክንያቱም ቀደም ሲል በነበረው ማህበራዊ መሰረት የተሰየሙት እንጂ ማጎች በአሁኑ ሰዓት በማህበረሰቡ ውስጥ ሚና የሌላቸው ስለሆነ ነው፡፡

## ቅኝት 6. ጋኛኖቲኛ

ይህ ቅኝት የተለያየ ማህበራዊ ኃላፊነት ላላቸው ወንዶች የሚከወን ነው፡፡ ለምሳሌ የጦር መሪዎች፣ የፈረስ ጦር መሪዎች፣ የሰላም ጉዳይ መሪዎችና የመሳሰሉ ኃላፊነት ያላቸው ሰዎች በብሄረሰቡ ቋንቋ ጋኛ[21] ነው የሚባሉት፡፡ ለዚህም ነው ጋኛኖቲና የሚል ዜማ የተፈጠረው፡፡ ጋኛኖ ቲኛ ማለት ጋኛዎች (ተተኪ ኃላፊዎች) ብዙ ናቸው የሚል ጽንሰ ሀሳባዊ ፍች ያለው ነው፡፡ ‹‹ጋኛኖቲኛ›› የሚለው ሀረግ እስከ መጨረሻው በተቀባይ የሚዜ ም ሲሆን የቅኝቱ ዜማ ግጥሞች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አዝማች፡- ጋኛኖቲኛ | ጋኛኖቲኛ |
| ስንኝ፡- አውኔን ጋኛንቲ ኬሲኛ | ከዛሬ ጀምሮ ስልጣንዎ ቀርቷል |
| አዝማች፡ ጋኛኖቲኛ | ጋኛኖቲኛ |
| ስንኝ፡-ሚያ እጉኖይ ጌልሙስ ኡሽባሪ | ከብቶች ያለስጋት ወንዙን ይጠጣሉ |
| አዝማች፡ጋኛኖቲኛ | ኛኖቲኛ |
| ስንኝ፡- አውኔን ጋኛንቲ ከሲኛ | ከዛሬ ጀምሮ ስልጣንዎ ወጥቷል |
| አዝማች፡ ጋኛኖቲኛ | ጋኛኖቲኛ |

ቅኝቱ የሚች ተግባር ማብቃቱን በሚገልጽ አዝማች የተገነባ ቢሆንም በሌሎች ቅኝቶች የሚደረደሩ ግጥሞችም የሚችን ተግባርና ማህበራዊ ደረጃን መሰረት በማድረግ እንደሚገ ጠሙ በተተኳሪ ቡድንው ውይይት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በልዩ ወረዳው ባህል፣ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት ተቀርጾ ከተቀመጠ መረጃ ለማረጋገጥ እንደቻልኩት በዚህ ቅኝት የዚዛ ክወናው ዝላይ መጠኑና ስሜቱ እጅግ ከፍ ያለ ነው፡፡

---

[21] ጋኛ፡- በማህበረሰቡ ውስጥ ከጎሳ መሪዎች ቀጥሎ በተለያየ ዘርፍ ስልጣን ያላቸው የስልታን ክብር ስም፡፡

## ቅኝት ሰባት.ዳምኖቲና ዳምኖ ፡-

ለሞዋ ጎሳ ነገስታትና ቤተሰቦች የሚከወን የዚዛ ቅኝት ነው፡፡ በታሪክ እንደሚወሳው የሞዋ ጎሳ የየምን ብሄረሰብ ያስተዳደረ የመጨረሻው ጎሳ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ወንዱ የሞዋ ጎሳ አባል ዳም (ጌቶች) በሚል የክብር ስም የሚጠራ ሲሆን ሴቷ ደግሞ ዳምታ በሚል የክብር ስም ነው የምትጠራው፡፡ ከዚህ የክብር ደረጃ የተነሳ ነው የዚህ ጎሳ አባላት ሲሞቱ ዳምኖቲና ዳምኖ ተብሎ የዚዛ ዜማ አዝማች የተፈጠረላቸው፡፡

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |
| አውራጅ፡-ኤኪዮ ዳምታሮ | እንዲህ አደረገዎት ወይ ጌታዬ |
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |
| አውራጅ፡-አይ ኤካኖይ ዳምታሮ | ወይኔ እንዲህ ነው ወይ ጌታዬ |
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |
| አውራጅ፡-ኤቶ ዛዋሶ ቡኂኛ ዳምታሮ | አንበሳው ሆራው አደፈረሰው ጌታዬ |
| አውራጅ፡-ዳምታሮ ዳምታኛ | ጌታዬ ጌታዬ |
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |
| አውራጅ፡-አይ ፋዛ ታኞኔ ፌሽባሪ | ፈረሱ እንደተለጎመ ይዋል |
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |

የመጨረሻው የምን በንግስና ያስተዳደረው የሞዋ ጎሳ ነበር፡፡ በመሆኑም የዚህ ጎሳ ነገስታት ሲሞቱ የሚከወን የዚዛ አዝማች ቅኝት ሲሆን አሁንም ድረስ ከጎሳው አባላት ወንድ ሲሞት፣ ‹‹ዳምኖቲና ዳምኖ›› ሴት ስትሞት ደግሞ ‹‹ማኖቲና ማኖ›› የሚሉ ቅኝቶች ናቸው የሚዜሙት፡፡ በተጨማሪነት ሌሎች ቅኝት 1፣ 2፣ 3፣ እና 4ም ይዜማሉ፡፡

## ቅኝት 8. ማኖቲና ማኖ፡-

ለሴቶች ብቻ የሚከወን ነው፡፡ በጾታ ልዩነት ምክንያት የአዝማቹ ቃልና ዜማው ተለየ እንጂ ከቅኝት 7. ጋር ተመሳሳይ የዚዛ ክወና ምት ያለው ነው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ ቅኝት አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት እና አራት ዜማዎች ለሁሉም የብሄረሰቡ አባላት የሚከወኑ ሲሆን የሚደረደሩ ግጥሞች ግን የሚቾችን ማንነትና ተግባርን መሰረት በማድረግ ነው የሚደረደሩት፡፡ ቅኝት አምስት፣ ስድስትና ሰባት የዚዛ ዜማ ዓይቶች በሚቾች ማህበራዊ የኃላፊነት ደረጃ በሚሰጡ የክብር ስሞች ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ቅኝት ስምንት ግን በጾታ ምክንያት አዝማቹ ተለየ እንጂ በይዘት ደረጃ ከ ቅኝት ሰባት ጋር ተማሳሳይነት ያለው ነው፡፡ ሌላው ቅኝት ሰባት ንጉስ ሲሞት የሚዜም ሆኖ ለንጉስ ክብር ሲባል በከፍተኛ አክብሮት የሚደረደሩ ስነቃሎቹ ቢቀሩም የሞዋ ጎሳ አባላት ሲሞቱ አሁንም ድረስ ከሌሎቹ ቅኝቶች ጋር እየተፈራረቀ እንደሚዜም ነው ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች መረዳት የተቻለው፡፡ ሌላው የዚዛ ግጥሞች ከአውድ ውጭ የሚገኙ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ቅኝት 5፣7 እና 8ን እንዲህም አይነት ዜማ አለ ከማለት ውጭ በመዛግብት ፍተሻም ሆነ በሌሎች መረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች በርከት ያሉ ግጥሞችን ለመሰብሰብ አልቻልኩም፡፡ በተፈጥሮአዊ መቼት ላይ በተገኘሁባቸው የለቅሶ ስርዓቶች ላይም ማግኘት የቻልኩት የሌሎች ቅኝቶችን ግጥም ነው፡፡

በምልከታ ለመቃኘት እንደቻልኩት የዚዛ ዜማ ቅኝቶች አዝማቻቸው ስንኞቻቸው ሳይቀር በአንድ ትዕይንት እንኳ እየተደጋገሙ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአንዱ የዜማ ቅኝት ውስጥ የተደረደሩ ግጥሞች በሌላ ዜማ ቅኝት ውስጥም የመገኘት አጋጣሚያቸው ሰፊ እንደሆነ ለመታዘብ ችያለሁ፡፡ ቁልፍ መረጃ አቀባይ አባ ፊጣ ሲመልና አቶ ወልደማሪያም ያዳ እንደገለጹት በአሁኑ ጊዜ ያለው የዚዛ ክወና የተቀላቀለ እንደሆነ ነው፡፡ የሚችን ማንነት ባግባቡ ተረድቶ ያለመከወን አዝማሚያ እየተስተዋለ መሆኑንና በተለይ ድሮ የማይታወቅ በአሁኑ ጊዜ ግን በለቅሶ ቤት መጠጥ እየተለመደ በመሆኑ የዚዛ ስርዓቱ እየተበረዘ ወደ መጥፋት አደጋ ላይ መሆኑን መረጃ ሰጪዎቹ ይናገራሉ፡፡

ሌላው አሁን አሁን ለማንኛውም አዛውንት ተይዞ የሚለቀሰው የኢጋዘንና ድኩላ ቀንድ፣ የነብርና የአንበሳ ቆዳ ተይዞ የሚከወነው በጀግና ሞት ዚዛ ላይ ብቻ ነበር፡፡ ቀንድ ተሸክሞ የዚዛ ቡድን እንኳ አንደዛሬ ከአማችነት ጋር ተያይዞ በቡድን የሚመጣ ሳይሆን ሚች በጀግንነቱ ባተረፈው እውቅና እያንዳንዱ ሰው ከየቤቱ የነብር ቆዳውንና ቀንዱን ይዞ በመምጣት የቴሻና የዚዛ ስርዓቱ እንደሚፈጸም ነው፡፡ በጥንት የዚዛ ክወናው ለጀግና እና

አንቱ ለተባሉ ታዋቂ ሰዎች እንጂ ለሴቶች እንኳ እንደማይፈጸም ነው፡፡ (በ10/8/2011ዓ.ም የተተኳሪ ቡድን ውይይት)፡፡

ከዚህ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ምንም እንኳ የዚዛ ክወናው እየተካሄደ ቢሆንም አውዳዊ ነቱን እየለቀቀ ያለ ክወና መኖሩን ነው፡፡

በየም ብሄረሰብ ባህል መሰረት በጊዜ ሞት ወቅት በሟች ቤተሰቦችና በአካባቢው ማህበረሰብ የተሰናዳው ምግብ የሚስተናገደው ከቀብር በፊት ነው፡፡ ይህ የለቅሶ ዕለት መስተንግዶ አካኒ ኡሹ ( በጥሬ ትርጉሙ ውሃ ማጠጫ ወይም የቀብር ዕለት የዕዝን ምግብ) ይባላል፡፡ አካኒ ኡሹ የሚስተናገደው ወደ ቀብር ቀብር ጉዞ ሊደርስ ሲል ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሁሉም ለቀስተኞች ተራ በተራ ጓር ጥላ ወዳለበት የእንሰት ማሳ ውስጥ በአስተናጋጆች አማካይነት ተጠርተው ይሄዱና በመደዳ እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ቆጮ፣ ንፍሮና ቡና፣ውሃም ቀርቦላቸው የቀደሙት ተስተናግደው እየተነሱ ቀጣዮቹ እየተተኩ ይመገባሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ ከበሉ በኋላ የሚመጡ ለቀስተኞች በየመጡበት ቡድን እየተጠሩ ነው የሚስተናገዱት፡፡ በዚህ መልኩ ሁሉም ከተስተናገዱ በኋላ ነው ወደ ቀብር ጉዞ የሚጀመረው፡፡ (ምልከታ በ21/8/2011ዓ.ም ኢዲያ ቀበሌ)

የተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃ እንደሚያስረዳው ከሩቅም ሆነ ከቅርብ የሚመጡ ለቀስተኞች ቡና ሳይስተናገዱ አይሄዱም፡፡ የቀብሩ ዕለት የአካባቢው ሴቶች ጧት ለቅሶ እንደ ደረሱ ወደቤት ተመልሰው ቡና አፍልተው ቤት ያፈራውን አዘጋጅተው በማምጣት ነው በለቅሶ ቤቱ የተዘጋጀው ላይ ጨምረው ለቀስተኞችን የሚያስተናግዱት፡፡ አስክሬን ሳይቀበር ለቀስተኞች የሚስተናገዱበት ምክንያት ቀብር ቦታ ሄደው ማስቀበር የማይችሉት አስክሬኑን እንደሸኙ ወደየቤታቸው ስለሚሄዱና ከሚያስቀብሩትም መካከል ከሩቅ የመጡት ወደ ለቅሶው ቤት ሳይመለሱ በዚያው እንዳስቀበሩ ወደቤታቸው የሚሄዱ ስለሚኖሩ በረሀብ እንዳይጎዱና የሟች ቤተሰቦችም በለቅሶው ላይ ረሀብ ተጨምሮ ለጉዳት እንዳይዳረጉ ነው፡፡ የሟች ቤተሰቦች ደግሞ ለብቻቸው ኩያ[22] (በወፍራሙ የተበጠበጠ በሶ) እና ወተትም ካለ ወተት ይቀርብላቸውና እነሱም በልተው ይነሳሉ፡፡

---

[22] ኩያ ፡-በወፍራሙ ተበጥብጦ ለሟች ቤተሰቦች የሚሰጥ በሶ፡፡



*ፎቶ.8. ለቀስተኞች በአካኒ ኡሹ(የእዝን መስተንግዶ) ላይ፡፡*

*ወደ ቀብር ጉዞ የሚጀመረው ከ6  እስከ 7 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ለቀብር ከቤት መውጫ ሰዓት ላይ ቃሬዛው የሚቀመጥበት የእንሰት ቅጠል ተቆርጦ ይመጣና ከቤቱ በረንዳ ላይ ይነጠፋል፡፡ የቀብር ሰዓቱ ሲደርስ የአካባቢው አዋቂ ወንዶች ቃሬዛውን ለአራት ሆነው በጋቢ ወይም በቡሉኮ አልብሰውት በጓሮ በኩል ዞረው ፊት ለፊት ይዘው ይመጡና ወደ ቤት ውስጥ ሳይገቡ መውጫ በሩ ጋ በጋቢ ሸፍነው  ይቆማሉ፡፡ ከቤት በኩል ደግሞ እንደዚሁ አራት ሰዎች አስክሬኑን ይዘው ቃሬዛው ውስጥ ያስገባሉ፡፡ ከዚያም ወደ ውጭ ያወጡና አስቀድሞ በተነጠፈው የእንሰት ቅጠል ላይ ለአምስት ደቂቃ ያህል ያሳርፉና እንደ አዲስ ከፍተኛ ለቅሶ ይሆናል፡፡ በዚሁ ቀብር ቦታ መሄድ የማይችለው በደንብ አልቅሰው ይሰናበታል፡፡ ከዚያም አራት ሰዎች አስክሬኑን በቃሬዛ ተሸክመው ወደ ቀብር ቦታ ጉዞ ይደረጋል፡፡ በጉዞው ወቅት የሚኖረው ለቅሶ መጠነኛ ሲሆን ባብዛኛው የሟች ቤተሰቦች ናቸው የሚያለቅሱት፡፡ ነገር ግን መንገድ ላይ እያሉ ከቀብር በፊት ያልደረሱ የሟች ዘመድ ቢመጡ አስክሬን የተሸከሙት ትንሽ ቆም ይሉና ከተለቀሰ በኋላ ነው እንደገና ጉዞ የሚጀመረው፡፡*

*ቀብር ቦታ እንደተደረሰ ሴቶች ገለል ብለው ሴት ሀዘንተኛ ቤተሰቦችን ከበው ይቀመጣሉ፡፡ ወንዶች ሀዘንተኛ ቤተሰቦችም ጭምር ግብዓተ መሬቱን ለማስፈጸም ወደ መቃብሩ ይሄዳሉ፡፡ የሟች ወንድ ቤተሰቦች መቃብሩ የተቆፈረበትን ሁኔታ ቀድመው ሄደው ካዩ በኋላ ሌሎች አስክሬኑን ተሸክመው ወደ መቃብሩ አጠገብ ያስቀምጡና ሂደቱ የተጋለጠ እንዳይሆን አራት ሰዎች በቡሉኮ ይከልሉና አስክሬኑን ከቃሬዛው አውጥተው ቀድሞ ተዘጋጅቶ መቃብሩ ውስጥ በተቀመጠው ሳጥን ውስጥ ያስገባሉ፡፡ ከዚያም የሳጥኑ ክዳን*

*በሚስማር ተመቶ ይከደናል፡፡ ይህ የሚስማር ምት ድምጽ ሲሰማ በቤተሰቦቹ ዘንድ ከፍተኛ ለቅሶ እንደገና ይሆናል፡፡በዚህ ሂደት መቃብሩ አፈር ይለብሳል፣ግብዓተ መሬቱ ይፈጸማ ል፡፡*

### 5.1.3.2.ጊዜ ቀብር ስርዓት

ቁልፍ *መረጃ* አቀባዮች ቀደምሲ ለማንኛውም ሰው ሞት የቀብር ስርዓቱን ያስፈጽሙ የነበሩት ቤራዎች ቢሆኑም በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በባህላዊ እምነቱ መሰረት በተለየ የአሟሟት ሁኔታ የሚሞቱትን ካልሆነ በስተቀር የማናቸውንም የቀብር ስርዓት (የአስክሬን ቃሬዛ ማዘጋጀት፣ አስክሬን መሸከም፣ መቃብር መቆፈርና ግብዓተ መሬት) የሚያስፈጽሙት ወንዶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ወንዶችም ሆኑ ሴቶች እስከ ቀብር ቦታ ድረስ አስክሬኑን አጅበው ግብዓተ መሬቱን አስፈጽመው ነው የሚመለሱት፡፡

ከቁልፍ *መረጃ* አቀባዮች አቶ ሳህሌ ዘበን፣ አቶ ወልደማሪያም ያዳ እና በ10/8/2011 ዓ.ም የተካሄደው የተተኳሪ ቡድን ውይይት *መረጃ* እንደሚያመለክተው ቀደም ሲል የመቃብር ቦታ በጎሳ በነበረበት ወቅት እዚያው በየጎሳቸው መቃብር አጠገብ ነው የሚቀብሩት፡፡ አሁን ግን ከአኗኗር ለውጥና የኃይማኖት አስተ ምህሮ ጋር በተያያዘ እንደየማህበረሰቡ እምነት መሰረት በጋራ መቃብር ቦታ ነው የሚቀበረው፡፡

በብሄረሰቡ ዘንድ አስክሬን በሳጥን ውስጥ ገብቶ ከቤት አይወጣም፡፡ እስከቀብር ቦታ የሚወሰደው በቃሬዛ ነው፡፡ ይህ ቃሬዛ ቀደም ብሎ ነው ተዘጋጅቶ የሚቀመጠው፡፡ ቃሬዛው በአስክሬኑ ልክ ከቀርከሃ የአካባቢው ሰዎች ሰርተው አስክሬኑን መያዝ በሚችል መልኩ ዳር ዳሩን በእንሰት ቅጠል ዘንግ ተጠብበው ካሰናዱ በኋላ የስንደዶ ሳር ያነጥፉበታል፡፡ በአሁኑ ወቅት መቃብር የሚቆፈረው በአካባቢው ማህበረሰብ በተዋቀረ አደረጃጀት ነው፡፡ የአስክሬን ሳጥንም በሚች ወላጅ ተዘጋጅቶ ቤት የነበረው ዞዳ (በሀገር በቀል ዕውቀት ከኮርች ወይም ሾላ የተዘጋጀ ጣውላ) ወደ መቃብር ቦታ ተወሰወዶ ነው በአካባቢው አናጺዎች ተጠርቦ የሚገጠመው ፡፡ የአስክሬን ሳጥኑና መቃብሩ ተቆፍሮ ዝግጁ መሆኑን ከቆፋሪዎች አንድ ሰው ወደ ቤት ተልኮ መልዕክት ሲያደርስ ነው አስክሬን ከቤት ወጥቶ ለቀብር የሚወሰደው፡፡ መቃብር አቆፋፈሩም ከአዋቂዎች ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ጥልቀቱ

በአንድ ሰው ቁመት ልክ ሆኖ ስፋቱ አንድ ሜትር ሲሆን ርዝመቱ ደግሞ በሟቹ ቁመት በተዘጋጀው የአስክሬን ሳጥን ልክ ነው፡፡

በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ለአስከሬን የሚዘጋጀው መቃብር ጥልቀቱ በአንድ ሰው ቁመት ልክ ሲሆን ስፋቱ አንድ ሜትር እንዲሁም ርዝመቱ በሟቹ ቁመት ወይም በአስክሬን ሳጥኑ ልክ ነው፡፡ አስክሬኑ ሲቀበርም ራስ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ እንደሚሆን ነው በ10/8/2011 ዓ.ም የተደረገ የተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃ የሚያሳየው፡፡

በጊዜ ቀብር ወቅት የሚፈጸሙ ስርዓቶችን በሟቾች ማንነት ስንመለከት በማህበራዊ ደራጃቸው የንጉስ ቀብር ስነስርዓት ምስጢራዊ ነው፤ በቅርብ የሚያውቁ ሰዎች ካልሆኑ በስተቀር የንጉስ አስክሬን ሲቀበር ሌላ ሰው አያይም፡፡ አስክሬኑ በድብቅ ነው ተውስዶ የሚቀበረው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የነገስታት መቃብር ቦታም ከሌሎቹ የተለየ እንደሆነ ነው መረጃ ሰጪዎቹ የሚገልጹት፡፡

> እያንዳንዱ ጎሳ በየአካባቢው የየራሱ መቃብር ቦታ እንዳለው ሁሉ ነገስታትም የራሳቸው መቃበር ቦታ አላቸው፡፡ የመቃብር ቦታቸው ኢዲያ ቀበሌ ዛክነር የሚባል ቦታ ነው፡፡ በዚህ ቦታ መቃብር ተቆፍሮ እንደተዘጋጀ አስክሬኑን ቤራዎችና አገልየጋዮች ናቸው አስቀድመው በድብቅ ወስደው የሚቀብሩት፡፡ ሲቀብሩም ባረፉበት መቃብር ውስጥ ይጠቀማሉ በሚል እምነት በህይወት እያሉ የሚጠቀሟቸው ጥሩ ጥሩ የተለያዩ መገልገያ ቁሶች አብረው ነው የሚቀበሩት፡፡ አስክረኑ በድብቅ መቀበሩን ማንም ሳያውቅ ሌላ ንጉስ የማንገስ ስርዓት እንደተጠናቀቀ ነው የንጉሱ መሞት ለህዝቡ ይፋ የሚደደረገው፡፡ አዲስ ንጉስ መሰየሙም በዚሁ ጊዜ ነው ለህዝቡ የሚገለጸው፡፡ በቀብሩ ዕለት ግን ሳኦ (ቃሬዛ) ተዘጋጅቶ የእንሰት ኮባ እንደ አስክሬን ታስሮ ነው ተወስዶ የሚቀበረው፡፡ ከተቀበረም በኋላ በመቃብሩ ላይ ሳር እስኪበቅል ድረስ በአገልጋዮች ይጠበቅ ነበር፡፡ (ቃ.መ.በ15/7/2011 ዓ.ም ሳጃ)፡፡

ከላይ በተገጸው መረጃ በብሄረሰቡ ዘንድ ለንጉስ ሞት የቀብር ስርዓቱ በሚስጥር እንዲፈጸም የሚደርጉ ትዕምርታዊ መልዕክቶች መኖራቸውን ነው፡፡ እነዚህም አንደኛው ዋና ዋና የንጉሱ መገልገያ ንብረቶች አብረው ከአስክሬኑ ጋር ሚቀበሩ ሲሆን ሁነተኛው በንጉሱ መቃብር ላይ ሳር እስኪበቅል ድረስ በአገልጋዮች የሚጠበቅ መሆኑ ነው፡፡ እነዚህ

ትዕምርቶችን በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ስንመለከት አምላክ የሚኖረው ዶኖካናም (የላይኛው ተራራ አምላክ) እና ዳካም (የምድር አምላክ) እንደሆነ ነው፡፡ ነፍስ ከስጋ ስትለይ ስጋ አፈር ሲሆን ነፍስ ግን በአካባቢው በስውር ትሰፍራለች ማለትም በላይም በታችም ትገኛለች የሚል እምነት ነው ለው፡፡ ንጉሱ በስጋ ቢሞቱም በመንፈስ ሆነው ስለሚያዩ ከነመገልገያ ቁሶች መቀበራቸው ንጉሱ በአካለ ስጋ እያሉ የሚከበሩትን የክብር መልክ ለአስክሬኑም መስጠትን የሚያሳይ ነው፡፡

ሁለተኛው የንጉሱ መቃብር ላይ ሳር እስኪበቅል ድረስ የሚጠበቀው አስክሬኑን ቆፍረው የሚወስዱ አካላት ስላሉ ይህ እንዳይፈጸም ነው፡፡ በየም ብሄረሰብ ሳር ምኞት ማሳኪያ፣ የርህራሄና የእገዳ ተምሳሌት ነው፡፡ በመሆኑም ብሄረሰቡ ለሳር የሚሰጠው ክብር የተለየ ነው፡፡ሳር ከምግብ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለንጽህና ተምሳሌትነት የሚውለው ከብቶች የሚበሉት ሳር ነው፡፡ ሚበሉ እንስሳት የሚበሉት ሳር ነው፡፡ ይህን ሳር የሚበሉ ከብቶች ናቸው ለምግብነት የሚውሉት፡፡ ሳር በህይወት ኡደት ከሰው ጋር አብሮ የሚኖር ነው፡፡ በብሄረሰቡ ዘንድ የተጣላን ለማስታረቅ እርጥብ ሳር ነው ተይዞ የሚለመነው፡፡ ልጅ ለማጨት እርጥብ ሳር ነው ከእንሰት ቅጠል ጋር ተይዞ የሚኬደው፣ እርጥብ ሳር ከተሰጠ አደራ አይካድም፣ነው የሚሰጠው፣ ከንጽህና ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በሳር የተጠየቀ ነገር ምላሽ አያጣም፡፡ ስለዚህ ሳር እስኪበቅል ድረስ የንጉስ መቃብር መጠበቁ ሳሩ ከበቀለ በኋላ ታገደ በመሆኑ ስለማይነካ ነው፡፡

አቶ ገዛኸኝ ዘርፉ እና አቶ ሳህሌ ዘበን ገለጻ መሰረት ለማግች፣ ለጀግና እና ለተራ ሽማግሌዎች ሞት የሚፈጸመው የጊዜ ቀብር ስርዓት ተመሳሳይ እንደሆነ ነው፡፡ በየም ብሄረሰብ ባህል መሰረት የእድሜ ባለጸጋ ሞት የትውልድን መሰረት የማጠናከርና የባህል እሴትን የማስጠበቅ ስርዓትም የሚፈጸምበት ነው፡፡

> አቶ ኃለማሪያም ዲዱ በሰጡት መረጃ ቀደም ሲል ቤራዎች የሁሉን ሰው የቀብር ስርዓት በሚያስፈጽሙበት ጊዜ የተደበቀ ሚስጥርም በቀብር ላይ ይጋለጥ ነበር፡፡ ከቤራዎች ያለፈ ነገር መፍትሄ የለውም ተብሎ በብሄረሰቡ ዘንድ ስለሚታመን ተጣልተው የነበሩ የሟች ቤተዘመዶችም በዚሁ ዕለት ነው እርቅ እንዲያወርዱ የሚደረገው፡፡ ከሟች ጋር እንኳ የተጣላ ካለ ቤራዎች እዚያው መቃብሩ ላይ ነው ጥፋቱን በሟች ላይ በመፍረድ ጸሎት ያደርግና ከዛሬ ጀምሮ እርቅ ተፈጸሟል ብሎ የሚያስተካክለው፡፡

ሌላው ሟች ቤት የተወለደ ልጅ እንዳለና ከዚያ በፊት እናት ልጅነቷን ለሌላ ሰጥታ ሟችን አግብታ ወንድ ልጅ ተወልዶ የሌላ ነው የሚል ጥርጣሬ ካለ ቤራው ነው በመቃብሩ ላይ የሚያጣራው፡፡ መቃብሩ እንደተጠናቀቀ ቤራው ልጁን ይጠራና መቃብሩን እንዲመለከት‹‹አንተ ልጅ የአባትህ ቤት ጥሩ መሆን አለመሆኑን ናና እይ› ይለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ የሟች ሚስት ልጅነቷን ለሌላ የሰጠችና በብሔረሰቡ ባህል መሰረት የሌላ ሰው ነው የሚል ጭምጭምታ እያለ ልጁ የሟች አባትን መቃብር ሄዶ ቢመለከት ከማግስቱ ጀምሮ መታመም ይጀምራል፣ አመት ሳይደርስ ነው የሚሞተው ፡፡ የሟች ህጋዊ(እውነተኛ) ልጅ ከሆነ ነው የአባቱን መቃብር ሄዶ በመመልከት ሰላም ሊሆን የሚችለው፡፡ (ቃ.መ በ15/7/2011ዓ.ም ሳጃ እና በ16/7/2011ዓ.ም ሳጃ)፡፡

ከላይ ከተገለጸው መረጃ መረዳት የሚቻለው በየም ብሄረሰብ ባህል መሰረት ሞት አስታራቂም ባህልን ጠባቂም በመሆን ባህላዊ እሴትን የመጠበቅ ፋይዳ አለው፡፡

## 5.1.3. 3. ድህረ ቀብር ስርዓቶች

ድህረ ቀብር ስርዓት ግብዓተ መሬት ከተፈጸመ በኋላ የሚከናወኑ ስርዓቶችን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ እንደየእድሜ ደረጃቸው የተለያዩ ስርዓቶች እንደሚፈጸሙ ነው ቁልፍ መረጃ አቀባዮች የሚገልጹት፡፡ የጎሳ መሪዎችና ጀግና የሚባሉት ባልተጠበቀ አደጋ የሞቱ እንደሆነ ምንም እንኳ ዘር የተኩ ቢሆንም ሳያረጁ ድንገት በመሞታቸው የሀዘን ስሜቱ ከፍ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም አስክሬን እንደተቀበረ ለሟች ቅርብ ዝምድና ያለው ሽማግሌ ለቀስተኞች ሰብሰብ እንዲሉ በማድረግ ከዛሬ ጀምሮ እንደዚህ ዓይነት ድንገተኛ የሞት አደጋ በሰፈራችሁ አይከሰት፣ በሰላም ወደየቤታችሁ ሂዱ ይሉና መርቀው ስርዓተ ቀብሩ ያበቃል፡፡ እንደዚሁም የታዳጊዎችና የወጣቶች ሞት ተራውን ያልጠበቀ ሞት ነው ስለሚባል ግብዓተ መሬት ከተፈጸመ በኋላ በተመሳሳይ መልኩ ሁሉም አንድ ላይ እዲሰባሰቡ ይደረግና በሟች ወላጅ የስንብት ምረቃ ይደረጋል፡፡ምረቃውም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

‹ሀዘናችንን ሀዘናችሁ አድርጋችሁ ከኛ ጋር የዋላችሁ ሰላም ይሁንላችሁ››፣

‹‹ምድራችን ይቀዝቅዝ››

‹‹የዛሬው ዓይነት ተራ የሌለው ሞት በሰፈራችሁ እንዳይከሰት››

‹‹ምድራችን እንደዚህ ዓይነት ሞት ከዛሬ ጀምሮ እንዳታስተናግድ››፡፡

‹‹በሰላም ወደየበታችሁ ግቡ›› ብለው ይመርቁና የሩቆቹ ለቀስተኞች ወደየቤታቸው፣ ጎረቤቶችና ቤተዘመድ የሆኑት ደግሞ የሟች ቤተሰብን አጅበው ወደ ሟች ቤት ይመለሳሉ፡፡

ተራውን የጠበቀ ሞት ነው ለሚባለው የሽማግሌ ሞት ግን ግብዓተ መሬቱ ከተፈጸመ በኋላ በባህሉ መሰረት ሴቶችም ከተቀመጡበት ተነስተው ቀብር ሲያስፈጽሙ የነበሩ ወንዶችም ባንድ ላይ ከነጦራቸው እዲሰባሰቡ ይነገርና በሽማግሌዎች የስንብት ምረቃ ይደረጋል፡፡ ምረቃውም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ሀዘናችንን ሀዘናችሁ አድርጋችሁ ከኛ ጋር የዋላችሁ ‹‹ሰላም ይሁንላችሁ››፣ ‹‹ምድራችን ይቀዝቅዝ››፣ ‹‹የዛሬው ተራ ያለው ሞት ነው ሁሉም ነገር በተራው ይሁንልን›› ‹‹ቤታችሁ ሰፈራችሁ ሰላም ይሁን በሰላም ወደየበታችሁ ግቡ›› ብለው ይመርቁና የሩቆቹ ለቀስተኞች ወደየቤታቸው፣ ጎረቤቶችና ቤተዘመድ የሆኑት ደግሞ የሟች ቤተሰብን አጅበው ወደ ቤት ይመለሳሉ፡፡

አስክሬን ወደ ቀብር ሳይሄድ የተመደቡ የሰፈር አስተናጋጆች ከማግስቱ ጀምሮ በሚኖረው የቴሻ (ለቅሶ) ስርዓት ከፈጸሙ በኋለላ ለቀስተኞችና ሀዘንተኞች አረፍ የሚሉበት ቶሻ (የዛፍ ጥላ ወይም ባህላዊ ድንኳን) ከአካባቢው እንደብሳና ሰፋፊ ቅጠል ያላቸው ዛፎችን ቆርጠው በራፍ ላይ ቆፍረው በመትከል ጥላ ሰርተው ነው የሚጠብቁት፡፡ ሀዘንተኞች ከቀብር መልስ እቤት ሲደርሱ ቤተሰቦች የተወሰነ ያለቅሱና ተከልክለው ሁሉም ተቀምጠው እህል እንዲቀምሱ ይደረጋል፡፡ ከቀብር ማግስት ጀምሮ ወንበር ከቤት ውጪ ይወጣና የሟች ቤተሰቦችም ሆኑ ቤተዘመዶች ተቀምጠው በቀብሩ እለት ያልደረሱ ለቀስተኞች ሲመጡ እየተነሱ በቴሻ ስርዓት እያለቀሱ ድንኳን እስከሚነቀልበት ቀን ድረስ በዚሁ ድባብ ይዘልቃሉ፡፡ ለመስተንግዶውም ከቤት የሚዘጋጀው እንደለ ሆኖ ድንኳን እስኪነቀል ድረስ የየእለቱ ተረኛ አስተናጋጆች ይመደባሉ፣ ከአካባቢው ማዕዋ (ለእዝን ከየቤቱ የሚዘጋጅ ምግብ ወይም ምሳና እራት) የሚያቀርቡ በሻኒዎች (በየአካባቢው የተመረጡ የለቅሶ ቤት ምግብ ዝግጅትና አቅርቦት አዛዦች) እየታዘዙ ያቀርባሉ፡፡ መቅርብ

አለመቅረቡን ደግሞ ኦግዲዎች (የለቅሶ ቤት መስተንግዶ ተቆጣጣሪዎች) ይቆጣጠራሉ፡፡ በዚህ መልኩ እስከ ድንኳን መንቀያ ቀን ድርስ ይደርሳል (ምልከታ በቀን 21/8/2011ዓ.ም. ኢ.ዲ.ያ)፡፡

ቁልፍ መረጃ አቀባዮች አቶ ሳህሌ ዘበንና አቶ ወልደማሪያም ያዳ እንደሚገልጹት ሞት ተክስቶ ከተለቀሰበት ቀን ማግስት ጀምሮ ድንኳን እስከሚነቀልበት ጊዜ ድረስ ያለው ቀን ጋምታ (ለሀዘን መቀመጥ ወይም የሀዘን ሳምንት) ይባላል፡፡ ቀደም ባሉት ጊዜያት ጋምታ እስከ 8 ቀን ድረስ ብቻ እንደነበረና ኋላ እስከ 12ኛ ቀን ድረስ እንደዘለቀ ነው መረጃ አቀባዮቹ የተናገሩት፡፡ ጋምታ ሙሉ የሀዘን ሳምንት ነው፡፡ ለቅሶው እንደቀብር እለት አይሆንም እንጂ በቴሻ (ለቅሶ) ይፈጸማል፡፡ የለቅሶ ድባቡ ከቀብሩ ዕለት የሚለየው ለቴሻ የሚመጡ ለቀስተኞች ሲኖሩ ብቻ ነው የሟች ቤተዘመዶች በሙሉ ቆመው የሚያለቅሱት፡፡ በዚህ የጋምታ (የሀዘን) ሳምንት ከርቀት የመጡ ቤተዘመዶችና ለሁለተኛ ጊዜ ቶሎ ለመመለስ የማይችሉት ቢያነስ ከሁለት ቀን በላይ አድረው ሀዘንተኞችን አጫውተው ነው የሚሄዱት፡፡ ጎረቤቶችም ቀን ቀን መጥተው ያጫውታሉ፣ ወጣቶች ውሃ ይቀዳሉ፣ ለቀስተኞችን ያስተናግዳሉ፣ የእዝን ምግብም ከቀብር ዕለት ማግስት ጀምሮ ነው ከየምድብ ምድቡ ቁርስ፣ ምሳ፣እራት የሚመጣው፡፡ ይህ የእዝን ምግብ ‹‹ማዕኖ›› ይባላል፡፡ ከየቤቱ የሚመጣው የእዝን ምግብ ቤት ያፈራው ሲሆን አብዛኛውን ቦታ የሚሸፍነው ቆጮ ነው፡፡ ቆጮ ከማንኛውም ማባያ ጋር ተዘጋጅቶ ሊመጣ ይችላል፡፡ የታዘዘው የእዝን ምግብ መምጣት አለመምጣቱን የሚቆጣጠረው ኦግዲ (የእዝን ምግብ ተቆጣጣሪ) ሳምንቱን ሙሉ ከለቅሶ ቤቱ አይጠፋም፡፡ የጋምታ ጊዜ እስኪያልቅ ድረስ ከአካባቢው ማህበረሰብ የማገዶ እንጨት ከየቤቱ ተፈልጦ ይመጣል፡፡ የሟች ቤተሰቦች ጥልቅ የሀዘን ስሜት ውስጥ እንዳይገቡ ጎረቤቶች በየቀኑ ከለቅሶ ቤት አይጠፉም፡፡ በአካባቢው ያሉ አዛውንቶች ለቅሶ በአካባቢው ቢከሰት እንደመዋያ ይጠቀሙታል፤የትውውቅ አጋጣሚም ነው፡፡ በለቅሶ ቤቱ ታሪክ ይወራል፡፡ አስለቃሽ ሲመጣ ይለቀሳል ፤ አንዴ በጨዋታና ሳቅ ይደራል፣ ተመልሶ ለቀስተኞ ሲመጡ ድባቡ ባንዴ ይቀየራል ፡፡

እንደቁልፍ መረጃ አቀባዮች አቶ ኃይለማሪያም ዲዱ እና አቶ ሳህሌ ዘበን ገለጻ መሰረት ድንኳን መንቀል ‹‹ቶሽኒ ዋራ›› ይባላል፡፡ ይህ ዕለት የቴሻ ለቅሶ ስርዓት የሚያበቃበትና ውርስ የሚረጋገጥበት ነው፡፡ በድሮ ጊዜ ድንኳን የሚነቀለው በስምንተኛው ቀን ሲሆን ከጊዜ በኋላ በአስራ ሁለተኛው ቀን ሆኗል ፡፡ በዚህ ዕለት ጎረቤቶች ቡና አፍልተው ይመጡና ለቅሶ ቤቱን በእበት ይለቀልቃሉ፣ ወንዶች ደግሞ እደጅ ላይ ለጥላ ተብሎ ተተክሎ የነበረውን ቶሻ ነቃቅለው ከበራፍ ራቅ አድርገው ከቤት ተጠርጎ ከወጣው ቆሻሻ ጋር ያቃጥላሉ፡፡

ይህ የለቅሶ ቤት ቆሻሻን ሰብስቦ ማቃጠሉና ቤቱን በእበት መለቅለቁ በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ትዕምርታዊ መልዕክት ያለው ነው፡፡ ቆሻሻን ጠርጎ ማቃጠሉ የሟችን ቤተሰብ የማክበር ሲሆን ለቅሶው ይብቃችሁ፣ እርሱት እዚህ ላይ የሰፈረው መንፈስ ተጠርጎ ወጥቷል፣ የሚል ነው፡፡ ሰውን የሚገድለው ኪታ (የሞት መላክ) ነው ተብሎ ስለሚታመን ይህ ገዳይ መንፈስ ከአካባቢው በጭሱ አማካይነት እንዲሸሽ ነው ጥራጊው የሚቃጠለው፡፡ ጭስ ሲጨስ ሰውም ነፍሳትም ይሸሻሉ፣ እንዲሁ ክፉ መንፈስም ይሸሻል የሚል እምነት አለ፡፡

ለቅሶ ቤቱን በእበት መለቅለቁ ደግሞ ሁሉም ነገር ነጽቷል የሚል መልዕክት ያለው ነው፡፡ እበት በብሄረሰቡ ዘንድ የንጽህና ተምሳሌት ነው፡፡ ከብት በተፈጥሮ ሳር ብቻ የሚበላ ንጹህ እንስሳ ነው ተብሎ ነው የሚታመነው፡፡ በመሆኑም የየም ብሄረሰብ ለምስጋናም ሆነ ለንስሀ መስዋዕትም የሚያቀርበው ከብት ነው፡፡ ስለዚህ በእበት ቤትን መለቅለቅ ቤትን ከማጽዳት ባሻገር መንፈስንም ለማጽዳት የሚወክል ነው፡፡

ሟች ተላላፊ ነው ተብሎ በሚፈራ በሽታ የሞተ እንደሆነ ቶሽኒ ዋራ ዕለት በቤራዎች የሚፈጸም ስርዓት እንዳለ ነው አቶ ኃይለማሪያም የሚገልጹትት

> *ሟች ሆዱ አብጦ የሞተ እንደሆነም ወደ ፊት በሽታው ወደ ሌሎች እንዳይተላለፍ ቤራው በመጸለይ ስርዓቱን ካስፈጸመ በኋላ ነው ቶሻ የሚነቀለው፡፡ ድሮ ለጋምታ ማጠናቀቂያ እለት የሚሆን ቦርዴ ይዘጋጃል፡፡ ለቦርዴው ዝግጅት የሚሆን እህል ራሱ በእጅ ተቆፍሮ የሚዘራ ነበር፡፡ ይህን ቦርዴም ያረጠች ሴት ናት እህሉን ፈጭታ የምትጠምቀው፡፡ በ7ኛው ቀን አልባ /ያልተጣራ የቦርዴ ድፍድፍ / ተለይቶ ይቀመጣል፡፡ ቤራው መጥቶ*

*አልባውን በፋእላና /ከቀንድ በተሰራ ማንኪያ/ በመጭለፍ ከዛሬ ጀምሮ ይህ በሽታ ወደ ሌሎች እንዳይተላለፍ በማለት እርስ በርስ ያቀማምሳል፡፡ ዛሬ ደግሞ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ቢሆን ቄስ ተጠርቶ በሽታው ወደ ሌላ እንዳይተላለፍ በዚህ ይብቃ ተብሎ ጸበል ተረጭቶ ስርዓቱ ይፈጸምልታል፡፡*

*ይህ ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ ከጎረቤትም ከቤትም የተዘጋጀው ቡና ተጠጥቶ እንደየ ሟቹ ሁኔታ ሽማግሌዎች መርቀው ጎረቤቶች ወደየቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦች ደግሞ ከዚህ ዕለት ጀምሮ ውጭ ተቀምጠው ማልቀስና የቴሻ ለቅሶ ስርዓትም ያበቃል፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ የሚመጡ ሰዎች ሀዘናቸውን የሚገልጹት እቤት በመግባት በኦቾ (በማጽናናት) ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ሂደት የሀዘኑ መጠን እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ (ቃ.መ. አቶ ኃማሪያም ዲዱ በ25/7/2011 ዓ.ም ላይኛው ከሸሊ፡፡)*

የውርስ ስርቱን ሂደትም አቶ ኃይለማሪያምና አባ ፊጣ ሲገልጹ፡-

አስቀድሞ ሟች አባት ለማን ምን እንደሚገባ ቤተሰቡን ሰብስቦ ተናዞ ከሆነ የአባትን ኑዛዜ ማንም ሊቀይር አይችልም፡፡ ለንብረት ሲባል በልጆች መካከል ግጭት እንዳይነሳ በሚል የአካባቢው ሽማግሌዎች በዚሁ ድንኳን በሚነቀልበት ዕለት የሟች ቤተሰብን ሰብስበው ያወያያሉ፡፡ ሟች ቀድመው ንብረት አከፋፍለው ከሆነ ሽማግሌዎች የሟችን ኑዛዜ ያጸናሉ እንጂ አይለውጡም፡፡ ሳይናዘዝ በድንገተኛ አደጋ የሞተ እንደሆነ ግን የሟች ዋናው መኖሪያ ቤት፣ ትልልቅ ወንበሮችና ጦር ለታላቅ ልጅ ነው የሚሰጠው፡፡ መሬትና እንስሳትን በተመለከተ ፍትሀዊና ችግር በማያስነሳ መልኩ ሽማግሌዎች ያከፋፍላሉ፡፡

በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ውርስ በሴቶችና በወንዶች መካከል ልዩነት ይደረጋል፡፡ እናት እያለች አባት ቀድሞ ቢሞትና ሌላ ባል አልፈልግም ብላ የምትኖር ከሆነ በእናትነቷ ድርሻ ይኖራታል፡፡ ዋናው ቤት ውስጥ አትኖርም እንጂ በሌላ ቤት ወይም አዲስ ቤት ተሰርቶላት በልጆቿ እንክብካቤ ትኖራለች፡፡ መሬትም ይሰጣታል፣ይታረስላታል፡፡ ማግባት ብትፈልግ ግን በሟች ቤት ውስጥ ፈጽሞ ማግባት አይፈቀድላትም፡፡ እንዲሁም ሴት ልጆች ምናልባት

ያገቡ ዕለት አባታቸው ከሚሰጣቸው ስጦታ ውጭ በውርስ ላይ ድርሻ የላቸውም፡፡ የድርሻቸውን መካፈል የሚችሉት ወንዶች ብቻ ናቸው፡፡ ወንድ ልጅ በሙሉ የንብረትም የመሬትም ወራሽ ነው፡፡ በባህሉ መሰረት ዋናው የአባት ቤት የታላቅ ልጅ ስለሆነ ከመጀመሪያው ወደ ክፍፍል ውስጥ አይገባም፡፡ ቀጥሎ ላሉት ወንዶች ደግሞ የአካባቢው ሽማግሌዎች ከቤተሰብ ጋር በመሆን የድርሻ ድርሻቸውን ያከፋፍላሉ፡፡ በባህሉ መሰረት ሽማግሌዎች የወሰኑትን መሻር አይቻልም፡፡ ሟች ወንድ ልጆች ባይኖሩት እንኳ ወራሾች በተራው መሰረት የሟች ወንድሞች እንጂ ሴት አትወርስም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ወንድ ልጅ የአባቱን ዘር የሚያስቀጥል በመሆኑና ሴት ደግሞ የሌላ ዘር የምታራባ በመሆኑ እንደሆነ ነው፡፡ የብሄረሰቡን ባህል ለመጠበቅ ሲባል አንድ አባ ወራ ቢያንስ ሁለት ቤት ነው የሚኖረው፡፡ አባት ሲሞት  ዋናውን ቤት ወራሽ ታላቅ ልጅ ስለሆነ እናትና ሌሎች ልጆች የሚኖሩበት እንዳያጡ ታሳቢ በማድረግ ከአንድ በላይ ቤት እንደሚሰራ ነው መረጃ ሰጪዎቹ የሚናገሩት ፡፡

ቀደም ሲል ታላቅ ልጅ አባቱ ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ለዓመት ያህል ከሚስቱ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት አይፈጽምም፡፡ በዓመቱ የተለያዩ ስርዓቶችን ፈጽሞ ነው ነጻ ሆኖ እንደማንኛውም ሰው መኖር የሚጀምረው፡፡ ይህ ስርዓት የአባቱን የሀዘን ስርዓት ለመፈጸም በንጽህና መቆየት ይባላል፡፡ በዚህ መልኩ ራሱን በንጽህና ጠብቆ የተቀመጠ የሟች ታላቅ ልጅ የአባቱ መቃብር መሀል ላይ በዓመቱ ጠርዝ ያለው አንድ ድንጋይ የመትከል ስርዓት እንደሚፈጽም ነው በቃ.መ.15/7/2011 ዓ.ም ቁልፍ መረጃ አቀባዩ አቶ ሳህሌ ዘበን የተናገሩት፡፡

ይህ ተግባር መተካትን የሚመለክት ነው ፡፡ ድንጋዩ የመቃብሩ መሀል ላይ መተከሉ በብሄረሰቡ ዘንድ የምሰሶ ተምሳሌት ነው፡፡ ምሰሶ ደግሞ በብሄረሰቡ ባህል መሰረት በወንድ (በአባት) ነው የሚመሰለው፡፡ ታላቅ ልጅ ንጽህናውን ሲያጎድፍ ‹‹ዬቶሲ ኪኒ››[23] (ምሰሶውን አጎደፈ) ነው የሚባለው፡፡ በመሆኑም የመቃብር መሀል ላይ ድንጋይ የመትከሉ ትዕምርት በንጽህና ሆኖ የአባቱን ቦታ (ምሰሶውን) መረከቡን የሚያመላክት ነው፡፡

---

23 ‹‹ዬቶሲ ኪኒ››፡- ቀጥታ ትርጉሙ ምሰሶውን አጎደፈ ማለት ሲሆን አባቱ የሞተበት ታላቅም ሆኑ ቤተሰቦች በባህሉ የማይፈቀድ ተግባር ሲፈጽሙ የሚባል ነው፡፡ ምሰሶን ማቆሸሽ ማለት የአባት ቤት ወይም ቤተመቅደስ እንደማቆሸሽ የሚቆጠር ነው፡፡

አቶ ኃይለማሪያም ዲዱ  በንጽህና ራሱን ጠብቆ ለዓመት የተቀመጠ የሟች ታላቅ ወንድ ልጅ  ምን ዓይነት ስርዓት ፈጽሞ ወደ መደበኛ ኑሮው እንደሚቀላቀል ሲገልጹ፡-

> ታላቅ ልጅ አባቱ ቤት ለመግባት በንጽህና ራሱን ጠብቆ ለአመት ያህል ይቀመጥና በዓመቱ ባትካል[24] ለሚባል መንፈስ ተራራ ላይ ወጥቶ ወይፈን አርዶ የሚቃጠል መስዋዕት ያቀርባል፡፡ ከዚያም እደጅ ላይ ደግሞ አንድ ላም አርዶ ቤተዘመድና ሌሎች ጎረቤቶች ተጠርተው በልተው የተረፈውን ተከፋፍለው ይዘው ይሄዳሉ፡፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ ነው ታላቅ ልጅ በአባቱ ቤት ገብቶ መኖር የሚጀምረው፡፡ ይህንም ስርዓት የሚያስፈጽመው ቤራ(የሽከላ ስራ ሙያተኛ) ነው፡፡ የሟች ታላቅ ልጅ መስዋዕት አቅርቦ ንጹህ መሆኑ ተረጋግጦ ወደ አባቱ ቤት እንዲገባ የሚከናወነውን ስርዓት ጸልየው የሚያስፈጽሙት ቤራዎችና ማጎች ናቸው፡፡ በዚህ ቀን ባቾ (ለተክሳር እንደማለት ነው) ትልቅና ትንሽ ከየእህል አይነቱ ይሰናዳል፡፡ ይህ የሚሰናዳው ምግብ ባንድነት ‹‹ቹኢ›› የሚባል ነው፡፡ የሟች ታላቅ ልጅ፣ እማወራዋን ጨምሮ ማን የት መኖር እንዳለበት ቤራው ነው ምሪት የሚሰጠው፡፡  ቹአው ተዘጋጅቶ ቤራው ጸሎት ካደረገ በኋላ ዘመድ አዝማዱ በተሰባሰበበት ታላቅ ልጅ ንጽህናው የተረጋገጠ ስለሆነ ከዛሬ  ጀምሮ እንደማንኛውም ሰው መኖር ይችላል ተብሎ በቹአው እጅ የማስጠረግ ስርዓት ይከናወናል፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ የሟች ታላቅ ልጅ ከሚስቱ ጋር መደበኛ ኑሮውን መኖር ይጀምራል፡፡ (ቃ.መ.25/7/2011ዓ.ም.)፡፡

በየም ብሄረሰብ ባህል መሰረት የአባት ቤት የቤተመቅደስነት የሚወክል ነው፡፡ ቤተ መቅደስ ለመግባት ንጽህና ይፈልጋል፡፡ በቤተመግደስ ለመግባት በሴትና በወንድ መካከል ልዩነቶች አሉ፡፡ ራሱን ጠብቆ የተቀመጠ ታላቅ ልጅ በዓመቱ ለንጽህናው የምስጋና መስዋዕት በማቅረብ ነው አባቱ ቤት የሚገባው፡፡ ይህ ታላቅ ልጅ በዓመቱ የአባቱ ቤት  ሲገባ ንጽህና ይፈልጋል፡፡ የአባቱ መንፈስ በቅርብ ያያል ተብሎ ስለሚታመን ቃል ኪዳን ገብቶ ጠብቆ መኖሩንና ነገም ይህ ዕድል ለሱ እንዲደርሰው እንዲሁም በአካባቢው ማህበረሰብ ይሄ ልጅ አባቱን ያከበረና ባህላችንን የጠበቀ ነው የሚል ስምና  ዕውቅና ለማግኘት ሲል ከብት አርዶ

[24] ባትካል፡- ለጽድቅም ሆነ ለኩነኔ የሚሰዋ መስዋዕት፡፡

መስዋዕት በማቅረብ ቤተዘመድና የአካባቢው ማህበረሰብ እንዲበላ ያደርጋል፡፡ ይህ መስዋዕት ካቀረበ በኋላ ልጁና ቤተሰቡ ምህረትና ጽድቅ አገኘ ማለት ነው፡፡

ከላይ ከተገለጸው መረጃ መረዳት የሚቻለው የየም ብሄረሰብ ባህላዊ ስርዓት ስሪቱ በቤራዎች መንፈሳዊ ስልጣን ላይ የተመሰረተ ሲሆን የምስጋናም ሆነ የንስሀ መስዋዕት የሚቀርበው በነሱ አማላጅነት እንደሆነ ነው፡፡

በቀን 6/8/2011 ዓ.ም ፎፋ ላይ የተካሄደ የተተኳሪ ቡድን ውይይት መረጃ እንደሚያሳየው በቤራዎች አማካይነት የሚፈጸሙ ባህላዊ ስርዓቶች በጣም በውስን ደረጃሠ ካልሆነ በስተቀር በተላያዩ ኃይማኖቶች አስተምሮና ዘመናዊነት ጋር በተያያዘ በአሁኑ ጊዜ እንደማይፈጸም ነው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት

በዚህ ክፍል የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ምን ይመስላል የሚለው የጥናቱ ሂደት ውጤት የሚገለጽበት ነው፡፡

### 6.1. የጥናቱ ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የየም ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ላይ በማትኮር የተካሄደ ነው፡፡ የጥናቱ ዋንኛ ዓላማ የብሔረሰቡን የለቅሶ ስርዓት ከሞት እስከ ግብዓተ መሬት ፍፃሜው ድረስ ያለውን ሂደት በገለጻ ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ተፈጥሯዊ መቼቶች ላይ በመገኘት ምልከታ በማድረግ፣ ስለ ብሔረሰቡ ባህል ጥልቅ መረጃ ካላቸው የተለያዩ ግለሰቦች ቃለ መጠይቅ እና የቡድን ውይይት በማካሔድ እንዲሁም በመዛግብት ፍተሻ የጽሁፍና የምስል መረጃዎችን በመመልከት በቂ መረጃ ለማግኘት ተችሏል፡፡

በመረጃ ትንተናው የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ምን እንደሚመስል በአግባቡ ለማሳየት ይበጅ ዘንድ በማህበራዊ ደራጃ፣ በዕድሜ፣ በጾታና የአሟሟት ሁኔታን መሰረት በማድረግ ከቅድመ ሞት ዝግጅቶች ጀምሮ እስከ ድህረ ቀብር ድረስ ያሉ ስርዓቶችን ጥናቱ ለማየት ሞክሯል፡፡

ቅድመ ሞት በሚለው እርከን ውስጥ የተመላከቱት ብሔረሰቡ አንድ ቀን ሞት መከሰቱ አይቀርም በሚል የሚያከናውናቸውን ቅድመ ዝግጅቶችን የሚመለከት ሲሆን በጊዜ ሞት ስር የተዳሰሱት ደግሞ አንድ ሰው ህይወቱ ስታልፍ ከመለቀሱ በፊት የሚፈፀሙ ክንውኖችን የሚያሳይ ነው፡፡ በድህረ ሞት እርከን ደግሞ የለቅሶ ስርዓቱና ባጠቃላይ ቅድመ ቀብር፣ ጊዜ ቀብርና ድህረ ቀብር ተግባራት የተተነተኑበት ነው፡፡

በብሄረሰቡ ባህል መሰረት የሚከናወኑ የቅድመ ሞት ዝግጅቶች የአስክሬን ሳጥን መስሪያ ዞዳ (በአካባቢው ዕወቀት በወፍራሙ የሚዘጋጅ ጣውላ)፣ ኪኖ (የከፈን ልብስ)፣ ታላ (አስክሬን መገነዥ የፈትል ክር ወይም ማግ) እና ለዚዛ ክወና የሚያገለግል ሾሮዶ ሞት ሳይከሰት ቀድመው ተዘጋጅተው ሞት የሚጠባበቁ ቁሶች ናቸው ነው፡፡

ከማህበራዊ ደረጃ አንጻር ሟች ንጉስ፣ የጎሳ መሪ፣ በጀግንነት የሚታወቅ ሲሆን ከሌላው ህብረተሰብ ለቅሶ ይልቅ ሰፋ ባለ እና በደመቀ መልኩ  የለቅሶ ስርዓታቸው እንደሚከወን ነው ጥናቱ የሚያመለክተው፡፡ ይሁን እንጂ ዋነኛው የክወናው ስፋትና ድምቀት ልዩነት ሟች ወይም የሟች ቤተሰብ ያላቸው ኢኮኖሚያዊ አቅምና ማህበራዊ ስልጣን መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡  ከእድሜ አንጻር ለታዳጊ ህጻናትና ወጣቶች ሞት ለቅሶውን ይፋ ለማድረግ እንደአዋቂዎቹ  ቅድመዝግጅት የማይደረግ መሆኑና ዚዛ(ሙሾ) የማይከወንላቸው መሆኑ ነው፡፡ የሚኖረው የለቅሶና የሀዘን መጠን ከሌሎች እጅግ መሪር ነው፡፡ ነገር ግን ጊዜውን ያልጠበቀ ሞት ነው ስለሚባል የዚዛ ስርዓት አይከወንላቸውም፣ ኪኖ)ቡሉኮ) ቤት ላይ ተዘርግቶ አይነጠፍላቸውም፡፡ በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ጊዜውን የጠበቀ ሞት የሚባለው ቢያንስ ሟች ዘሩን የተካ ሲሆን ነው፡፡ ከጾታ አንጻር ያለው ልዩነት ግን ከአባወራው ቀድማ እማወራዋ የሞተች እንደሆነ በብሄረሰቡ ዘንድ የታላቅነት ወይም የአዋቂ ሰዎች ሞት ምልክት የሆነው ኪኖ(ቡሉኮ) የሚዘረጋው አጥር ላይ ነው፡፡

በለቅሶ ስርዓቱ የሚስተዋሉ መሰረታዊ ልዩነቶች   በብሄረሰቡ ባህል መሰረት ከእናቱ እቅፍ ያልወረደ ጨቅላ ህጻን በሞት ሲነጠቅ ‹‹ኃጢያት ሳይሰራ እግዚአብሔር ስለመረጠው ነው የወሰደው፡፡›› የሚል  እምነት በብሄረሰቡ ዘንድ ስላለ ለዚህ ህፃን በቴሻ(የለቅሶ) ስርዓት አይከወንም፡፡ ይልቁንም ብዙም ሰው ሳይሰማ ጥቂት ጎረቤቶች ተሰብስበው ወላጆች ብቻ ናቸው እርማቸውን ለማውጣት የሚያለቅሱት፡፡ የሚቀበረውም በወላጆቹ የእንሰት ማሳ ውስጥ ባለ ዛፍ ስር መሆኑ የመረጃ ትንተናው ያሳያል፡፡

በጊዜ ሂደት ከኃይማኖት መስፋፋት ጋር ተያይዞ የመቃብር ቦታ በየእምነቱ አንድ ቦታ ተደረገ እንጂ ከዚያ በፊት የመቃብር ቦታ በየጎሳው እንደነበረም በመረጃ ትንተናው ለማወቅ ተችሏል፡፡

ቀደም ሲል የብሂረሰቡን አባላት አስክሬን ገንዘው፣መቃብር ቆፍረው የሚቀብሩት ቤራዎች (የሸክላ ስራ ሙያተኞች) እንደነበሩና በጊዜ ሂደት ይህ ቀርቶ ዛሬ የሟች ቤተሰቦች አስክሬን እንደሚገንዙና የቀብር ስነስርዓቱም በአካባቢው ማህበረሰብ እንደሚፈጸም ከመረጃ ትንተናው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የአምላክ ቁጣ ነው ተብለው በብሂረሰቡ ዘንድ በሚታመኑ በስጋ ደዌ፣ በሆድ እብጠት ህመምና በመብረቅ አደጋ የሞተን ሰው የመገነዝና የቀብር ስርዓቱን የመፈጸም ተግባር አሁንም ድረስ ፍርሀቱ ባልለቀቃቸው የብሂረሰቡ አባላት ዘንድ በቤራዎች እንደሚፈጸም ነው መረዳት የተቻለው፡፡

የብሔረሰቡ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ አጠቃላይ ሂደት ከስምንት እስከ አስራ ሁለት ቀናት ድረስ የሚቆይ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡

የለቅሶ ስርዓት ክዋኔው የተለያዩ ፎክሎራዊ ጉዳዮችን የያዘ ነው፡፡ የሟችን ክብርና ማንነት፣ የዘር ሀረጉን ለመግለጽ የሚጠቀሙባቸው ሙገሳዎችና ፉከራዎች በስነ ቃል ዘውግ የሚታዩ ሲሆን በቅድመ ሞትም ሆነ በለቅሶ ጊዜ ስርዓቱን ለመፈጸም ጥቅም ላይ የሚውሉ እንደ ጦር፣ ጋሻ፣ ቀንድ፣ የነብርና የአንበሳ ቆዳ፣ ጥሩምባ፣ ሾሮዶ፣ ጉዶ፣ እንስራና ኪሶ(ከዝሆን ጥርስ የሚሰራ አምባር)፣ ለአስክሬን መቅበሪያነት የሚዘጋጀው ጎኑ (ሳጥን)፣ ዞዳ (ጣውላ)፣ የለቀስተኞች መስተንግዶ የሚዘጋጀው ቆጮ፣ ቡና፣ የባቄላ አሹቅ በቁሳዊ ባህል ስር የሚመደቡ ናቸው፡፡ በለቅሶ ስርዓቱ ቤራዎች (ሸክላ ሰራተኞች) አስክሬን እንዲገንዙ መደረጉ፣ አባወራ ቀድሞ ከሞተ እማወራዋ ከኖረችበት ቤት እንድትወጣ የሚደረገው ስርዓት፣ እህል ከሟች ቤት ወጥቶ ደጅ ላይ መበተን፣ እንሰት መቆራረጥና መነቃቀል፣ የተጣላ ካለ በመቃብሩ ላይ በቤራዎች የማስታረቅ ስርዓት፣ ቡሉኮ ቤት ላይ ወይም አጥር ላይ መዘርጋት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ የሚካተቱና የተለያየ ትዕምርት ያላቸው ናቸው፡፡ ለቅሶው በቴሻና በዚዛ ሲከወን የሚታዩት ሙዚቃዎችና ዳንኪራዎች የቂጭት፣ የሙገሳ የውዳሴ ዜማዎች በትውን ጥበባት ዘውግ የሚታይ ሲሆን በአጠቃላይ የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክወና አራቱንም አብይ የፎክሎር ዘውጎች የያዘ ነው፡፡ የእነዚህ ክዋኔዎች ተግባር ሟችን ለማስታወስ፣ የብሂረሰቡን ታሪክ ለተተኪ ትውልድ ለማስተዋወቅና ማህበራዊ ህይወታቸውንና ባህልን ለመጠበቅና ለማጠናከር የሚከወኑ ናቸው፡፡ ይህ ስርዓት ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍበት መንገድ ደግሞ በክዋኔ ነው፡፡ በክዋኔው ወቅት የሚታዩ ስነ ቃሎች፣ ቁሳዊ ባህሎች እና ልማዶች ከክዋኔው ጋር ተጣምረው በጥናቱ ተገልጸዋል፡፡

ሌላው በጥናቱ የተደረሰው የየም ብሔረሰብ ለአዋቂዎች ሞት በቀብሩ ዕለት ለቅሶውን የሚያጅበው "ዚዛ" በተባለ ባህላዊ የዘፈን እና የውዝዋዜ ክወና ነው፡፡ ይህ የዚዛ ክወና የሟችን እና የቤተሰቦቹን መልካም ገፅታዎች የሚያወሱ፣ ጀግንነትን የሚያወድሱ፣ ሞት ለሁሉም የቀረበ ግዴታ መሆኑን የተመለከቱ፣ የሟችን ጎሳ የዘር ሀረግ መነሻና ማንነት የሚተርኩ ግጥሞችን ለቀስተኞቹ እየደረደሩ ‹‹ሾሮዶ››፣ ‹‹ጉዶ›፣ጋሻ፣ጦር፣ ‹ኪሶ›የመሳሰሉ ቁሶችን እንደምት የሙዚቃ መሳሪያ በመጠቀም፣ በአጋዘንና ድኩላ ቀንዶች፣ በነብርና አንበሳ ቆዳ፣ እና ጥሩንባ አጅበው በመከወን የሟችን ቤተሰቦች ሀዘን እንዳይጎዳቸው ከማድረግ በተጨማሪም የተለያዩ መልዕክቶች የሚተላለፉበት ነው፡፡ የብሔረሰቡ ልዩ ልዩ ባህላዊ  እሴቶች የሚገለጡበት፣ የሚፀኑበት እና ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉበት ማእንዲሁም ህበራዊ ትስስሩን ከሚያጠነክርባቸው እና የትውልድ መነሻውን ከሚያስተዋ ውቅባቸው አጋጣሚዎች መካከል "የለቅሶ ስርዓት" ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ ነው፡፡

ስለዚህ የዚዛ ስርዓቱ 1ኛ የብሄረሰቡ ታሪክና ማንነት እንዲቀጥል ቀደምት ታሪክ የሚዘከርበትና ለተተኪ ትውልድ ግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ ነው፡፡ 2ኛ ለቅሶውና በዜማ የሚታጀበው ዳንኪራ (ዚዛው) ትዕምርታዊነት ህይወት ለጊዜው ያበቃለት ቢመስልም እንደገና ወደ ሌላ የሚሸጋገርበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ የሚያመለክተው በየም ብሄረሰብ እምነት መሰረት ሞት የህይወት ፍጻሜ አለመሆኑን እና የማህበረሰቡ ታሪክና ማንነት በአንድ ሰው ሞት የማይቋጭ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡

3ኛ የዚዛ ክወናው የሟቾችን እድሜና ማንነት የሚገልጽ ነው፡፡ ጥሩምባው እየተነፋ፣ ሾሮዶ ከመሬት ጋር እየተጋጨ የሚመታው የከበሮ ድምጽ ከርቀት ስለሚሰማ ባካባቢው ትልቅ ሰው መሞቱን የሚገልጽ ነው፡፡ 4ኛ ጦር፣ የአጋዘንና የድኩላ ቀንዶች፣ የነብርና አንበሳ ቆዳ ለጀግና ሞት የዚዛ ክወናውን የሚያጅቡ ሲሆን የግዳይነትና የምርኮ ምልክት በመሆን ጀግንነቱን የሚያስተዋውቁ ናቸው፡፡ 5ኛ የዚዛ ክወና ስርዓቱ  ሟችን መሸኛ ብቻ ሳይሆን ስለ ህይወትና ሞት ጠቃሚ መልዕክቶች የሚተላለፉበት ነው፡፡ ይህም ሞት የመሸጋገሪያ ስርዓት መሆኑንና በዚህ ስርዓት ማህበረሰቡ ከአካለ ስጋ  በመንፈስ ወደ መኖር የሚሸኝበት  መሆን የሚያሳይ ነው፡፡ 6ኛ በዚዛ ክወናው ጀግንነት፣ መልካምነትና የኑሮ ደረጃ የሚወደስበት በመሆኑ ማህበረሰቡ በዚህ አጋጣሚ ስንፍናን የሚያወግዝበትና ጥንካሬን የሚያበረታታበት ነው፡፡

በንጉስ መተዳደር በብሄረሰቡ ዘንድ ሙሉ በሙሉ ከቀረበት ከ1966 ዓ.ም ወዲህ ለንጉስ ሞት የሚከወን የለቅሶ ስርዓት በአሁኑ ወቅት የለም፡፡ ለሌሎች ትላልቅ ሰዎች በሚፈጸመው የዚዛ ክወና ውስጥም ሂደታዊ ለውጦች መስተዋላቸውን ከቃለመጠይቅ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ቀደም ሲል በዚዛ ክወና ቀንድ፣ ጋሻ፣ የነብርና የአንበሳ ቆዳ ተይዞ የሚከወነው ለአዳኝና የተለያየ የጦር ጀብድ ለፈጸመ ሰው ብቻ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ያለጾታ ልዩነት ለሁሉም ሰዎች እንደሚቀርብ ታወቋል፡፡ ይህም በዚዛ ክወና ስርዓቱ ላይ መዋሀድ (fusion) ተስተውሎ በታል ፡፡

## 5.2. አስተያየት

የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ሟችን አልቅሶ ከመቅበር ባለፈ በውስጡ በርካታ ይዘቶች ያሉት ነው፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረት በተለያዩ ምክንያቶች  ቀደም ሲል የለቅሶ ስርዓቱ ክወና አካል የነበሩ ዛሬ ግን የቀሩ እንዲሁም የተቀላቀሉ በርካታ ጉዳዮችን ማወቅ ተችሏ፡፡

ለምሳሌ ቤራዎች (የሽክላ ስራ ባለሙያዎች) በእያንዳንዱ የየም ብሄረሰብ አባላት መንፈሳዊ ስርዓቶችን የማስፈጸም ስልጣናቸው ሙሉ በሙሉ ወደሚቀርበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በውስን መልኩ ሚናቸው ያለው በመብረቅ አደጋና በስጋ ደዌ ህመም የሚሞቱ ሰዎችን የቀብር ስርዓት ማስፈጸም ላይ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሁሉንም የብሄረሰቡን ጎሳዎች አስክሬን ገንዞ የመቅበር ተግባር አያከናውኑም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የተለያዩ ኃይማኖቶች የነሱን ተግባር መተካታቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከማህበራዊ ደረጃ አንጻር ለንጉስና ለጎሳ መሪዎች ይከወን የነበረው የለቅሶ ስርዓትም ዛሬ እንደዚህ ዓይነት የአስተዳደር ስርዓት ባለመኖሩ ክወናው ቀርቷል፡፡

በዚዛ (ሙሾ) ክወናው ላይም የመቀላቀል ባህሪ ታይቶበታል፡፡ ለምሳሌ ቀደም ሲል የተለያየ ጀብድ የፈጸሙ ጀግኖችን ለመዘከርና ዕውቅና ለመስጠት በዚዛ ክወና ላይ ከሚቀርቡ ቁሶች መካከል ጋሻ፣ የአጋዘንና ድኩላ ቀንድ እና የነብርና የአንበሳ ቆዳ በአሁኑ ጊዜ  ለሁሉም አዋቂ ሟቾች ዚዛ ላይ እንደሚቀርብ ከመረጃዎች ትንተና ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ የዚዛ ክወናውን ያጅቡ የነበሩ ከዚሆን ጥርስ የሚሰራው (ኪሶ) የተሰኘ

የእጅ አማባር፣ ከስንደዶ የሚዘጋጀውና የምት ሙዚቃ መሳሪያ ሆኖ የሚያገለግለው ጉዶ፣ አፉ በቆዳ ታስሮ እንደከበሮ እየተመታ የሚያጅበው እንስራ፣ የመሳሰሉት ቁሶችም ዛሬ ላይ በዚዛ ክወናው ላይ ለማጀቢያነት የማይቀርቡ ናቸው፡፡ እንዲሁም የዚዛ ክወናው በመጠጥ ኃይል ምክንያት ስርዓቱ እየተዛባ መሆኑ በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ በአሁኑ ወቅት የዚዛ ክወናው ለታዳጊዎችና ወጣቶች አለመደረጉ፣ ለአዋቂ ሴቶች አባወራው ቀድሞ ከሞተ ኪኖ (ቡሉኮ) ቤት ላይ የማይነጠፍ መሆኑ ካልሆነ በስተቀር አብዛኛዎቹ የለቅሶ ስርዓት ክወናዎችና የዚዛ ግጥሞች ተቀላቅለዋል ወይም ተዋህደዋል ማለት ይቻላል፡፡ በጥቅሉ ሲታይ በየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት ላይ Mwandayi (2011,96-97) በአንድ የባህል እሴት ላይ የሚታዩ ለውጦች ብለው የዘረዘሯቸው ለምሳሌ በሌላ መተካት (substitution)፣ ፈጽሞ መጥፋት (Loss)፣ መጨመር (Incrimentatio) እና መዋሀድ (Fusion) የሚሉ ክስተቶች ተስተውሎበታል፡፡ ይህ ጥናት ትኩረቱ የነበረው አጠቃላይ የለቅሶ ስርዓት ክወናው (Death ritual) ነው፡፡ በመሆኑም በቀጣይ በለቅሶ ስርዓቱ ላይ ሂደታዊና ንጽጽራዊ እንዲሁም በእያንዳንዱ ዘውግ ላይ በተለያዩ ይዘቶች ጥናት ማድረግና ባግባቡ መሰነድን ይጠይቃል፡፡

## ዋቢዎች


ለማ ንጋቱ፡፡ (1999ዓ.ም.)፣ ‹‹በየም ብሄረሰብ ጸታ ተኮር ተረቶች የወንድና ሴት ‹ምስል›› ትንተና፡፡›› ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

---------------፡፡ (2002 ዓ.ም.)፡፡ ‹‹የፎክሎር ኮርስ መግቢያ ማስተማሪያ መሳሪያ፡፡›› የአማርኛ ቋንቋና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ጅማ ዩኒቨርሲቲ፡፡ ያልታተመ፡፡

ምትኩ ነጋሽ፡፡ (2005 ዓ.ም.)፡፡ የየም ህግ ስርዓት፣ ቁ.1.ፋር ኢስት ትሬዲንግ፣ አዲስ አበባ፡፡

ሰለሞን ተሸመ (2007 ዓ.ም.)፡፡ የፎክሎር ምንነቱና የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ፡፡ ፋር ኢስት ትሬዲንግ፣ አዲስ አበባ፡፡

ሸኡ መጽሔት፡፡ (ቁ.1.2000 ዓ.ም.)፡፡ የም ልዩ ወረዳ ማስታወቂያና ባህል ጽ/ቤት፡፡ የታተመበት ቦታ አልተገለጸም፡፡

ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን፡፡ (2002ዓ.ም.)፣ በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/በደቡብና ደቡብ ምዕራብ በሚገኙ 20 ብሄረሰቦች ኢንታንጀብል ባህላዊ ቅርሶች ላይ የተደረገ ኢንቨንተሪ፡፡ቅጽ 3. አዲስ አበባ፡፡

ቱባ መጽሔት፡፡ቁ.፳፮.(፱፻፲.ዓ.ም.) ማስተር ማተሚያ ቤት፣አዲስ አበባ፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡(2008ዓ.ም.)፡፡ በይነድስፕሊናዊ የስነጽሁፍ ጥበብ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ አዲስ አበባ፡፡

አለቃ ታዬ፡፡(፲፱፻፲፬ ዓ.ም.) የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ፣ ባጭር ቃል የወጣ፡፡ ሚሲአንግ ሱኤድዋ ማተሚያ፣አስመራ

አማርኛ ቋንቋ መዝገበ ቃላት(1993 ዓ.ም.)፡፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ፡፡

አበራች ብርሃኑ፡፡ (2010 ዓ.ም.)፣ ‹‹የቦሮ-ሺናሻ የለቅሶ ስርዓት ክወና የቋንቋ አጠቃቀም ትንተና፡፡›› በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ጂማ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አየሁሽ ቶማ፡፡(2005 ዓ.ም) ፡፡ "የወላይታ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ ጥናት›› በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ወንድማገኝና ሌሎች፡፡ (2004 ዓ.ም.) የየም ብሄረሰብ ታሪክ፣የም ልዩ ልዩ ወረዳ በ/ቱ/መ/ኮ/ጉ/ጽ/ቤት፣ ቼምበር ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፡፡

ውቤ ታደገ፡፡ (2005 ዓ.ም.) "የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ጥናት፡፡" በአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዘላለም ፋንቱ፡፡ (2004 ዓ.ም.) "የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ" በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ ለኤም.ኤ ዲግሪ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡(1992)፡፡ የስነ-ጽሁፍ መሰረታውያን፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ

የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፡፡(1992 ዓ.ም)፣ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡ ባናዊ ማተሚያ ቤት፣ 6ኛ ዕትም፣ አዲስ አበባ፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡(2009)፡፡ የመወርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣Tefera Seyoum Printing Press.

ዮሐንስ ወልደማሪያም፡፡ (1936 ዓ.ም.)፣ የአለም ታሪክ ከጂኦግራፊ ጋር፣ አዲስ አበባ፡፡

ደስታ ወልደመስቀል፡፡ (2006 ዓ.ም)፣ ‹‹የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ››፣ ለኤም.ኤ.ዲገሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ፍፁም ብርሃኑ፡፡ (2006 ዓ.ም.)፣ ‹‹የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ››፣ ለኤም.ኤ. ዲገሪ ማሟያ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

Abbink,J. Funerals as Ritual:An Analisis of Me'en of Mortuary Rites(South west Ethiopia.) L'Africa:I'Oriente,Anno47.No.2(GIGNO1992)PP.221-236.

Alembi, E. (2008*) .*THE ABANYOLE DIRGE: "ESCORTING" THE DEAD WITH SONG AND DANCE. http://www.folklore.ee/folklore/vol38/alembi.pdf/.

Bauman, Richard. (1986.), Story, Performance and Event: Contextual Studies of oral Narrative. Cambridge: Cambridge University Press.

DeborahA.Kapcham,(1995). The Journal of American Folklore, Vol. 108, No.430, Common Ground Keywords for the study of Expressive Culture (Autumn 1995) PP.479-508. American folklore society.

Demeke Gizachew and Fekede Menuta.(2013),Sketch of Yemsa Grammare. Haw asaa.

Dorson, Richard. (1972),M ed. Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London:The University of Chicago Press.

Eva Reimers (*1999).* Death and identity: graves and funerals as cultural Communication. Mortality, Vol. 4, No. 2. Umea University, Sweden

Finnegan, Ruth. 1992. Oral Tradition and the Verbal Arts: A Guide to Research Practices. New York: Thomson Publishing Company.

----------------- et.al. (2005,). Oral traditions and the verbal arts. A guide to research practices. Taylor & Francis e-Library, London.

Gire, J. (2014). How Death Imitates Life: Cultural Influences on Conceptions of Death and Dying.*Online Readings in Psychology and Culture, 6*(2).https://doi.org /10.9707 /2307- 0919.1120

GIVEN M. LISA. (2008) .The SAGE Encyclopedia of QUALITATIVE RESEARCH METHOD S. VOL.1 &2,United States of America.SAGE Publications, Inc.

Hirut Woldemariam,(1993).Word Formation in Yem.Unpublished,Ma.A.thesis,Addis Abeba University.

Mwandayi Canisius (2011). DEATH AND AFTER _LIFE RITUAS IN THE EYES OF THE SHONA. Vol. 6.University of Bamberg Press.

Peter McL. Black . THREE DEFINITIONS OF DEATH .The Monist, Vol. 60, No. 1, Bioethics and Social Responsibility (JANUARY, 1977),pp. 136-146. Oxford University Press.

Sangasubana, N. (2011). How to Conduct Ethnographic Research.*The Qualitative Report*,*16*(2), 567-573. Retrieved fromhttps://nsuworksnova.edu/tqr/vol16/iss2/14

Sims, Martha. and Martine Stephens. (2005), Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Taditions. Ohio: Utah State University Press.

World Book of Encyclopedia. (1978).World book- Child craft International, Inc. Vol,5. USA.

## አባሪ አንድ፡-

## የመረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ. | ስም | ጾታ | ዕድሜ | የት/ት ደረጃ | ስራ | የመኖሪያ አካባቢ | የሰጡት የመረጃ ዓይነት | መረጃው የተሰጠበት ቀን | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ ሳህለ ዘበን ችሮ | ወ | 59 | ድፕሎማ | የመንግስት | ሳጃ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 15/7/2011ዓ.ም | |
| 2 | ወ/ሮ አበበች መጫ | ሴ | 60 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | አዝጊ ዘምዳ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 18/7/2011 ዓ.ም | |
| 3 | አባ ዲጋ ባሻን | ወ | 82 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ሰሙ አዋሾ ቀበሌ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 17/7/2011ዓ.ም | |
| 4 | አቶ ኃይለማሪያም ዲዱ | ወ | 74 | 5ኛ ክፍል | አርሶ አደር | የላይኛው ከሸሊ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 25/7/2011ዓ.ም. | |
| 5 | ወ/ሮ አስናቀች ፊጣ | ሴ | 50 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ሰሙ አዋሾ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 26/7/2011ዓ.ም | |
| 6 | አቶ አየለ ገላን | ወ | 54 | ድግሪ | የመንግስት | ሳጃ | የየም ብሄረሰብ | 16/7/2011ዓ.ም | |
| 7 | ወ/ሮ በቀለች | ሴ | 62 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ኦያ ኤሬቶ | የለቅሶ ስርዓት›› | 03/08/2011ዓ.ም | |
| 8 | አባ ፊጣ ሲመል | ወ | 88 | ፊደል | አርሶ አደር | ሰሙ አዋሾ | የየም ብሄረሰብ | 30/7/2011ዓ.ም | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ያልቆጠሩ | | | የለቅሶ ስርዓት›› | | |
| 9 | ወ/ሮ አበበች ለማ | ሴ | 75 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ሸሞና መተሎ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 02/8/2011ዓ.ም | |
| 10 | ወለተየሱስ ምሬ | ሴ | 50 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ሸሞና መተሎ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 01/8/2011ዓ.ም | |
| 11 | አቶ ገዛኸኝ ዘርፉ | ወ | 52 | ድፕሎማ | የመንግስት | ሳጃ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 16/7/2011 | |
| 12 | ወ/ሮ/ፈለቀች መጫ | ሴ | 70 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ሰሙ አዋሾ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 02/8/2011ዓ.ም | |
| 13 | አቶ ወልደጊዮርጊስ ጊቤ | ወ | 60 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ሸሞና መተሎ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 01/08/2011ዓ.ም. | |
| 14 | አቶ በቀለ ጆቢር | ወ | 91 | 3ኛ | አርሶ አደር | አዝጊ ዘምዳ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 01/08/2011ዓ.ም. | |
| 15 | በየነች ምልኪ | ሴ | 50 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ላይኛው ከሸሊ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 25/7/2011ዓ.ም. | |
| 16 | አቶ ወልደማሪያም ያዳ | ወ | 100 | 3ኛ | አርሶ አደር | ኢዲያ ቀበሌ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 03/08/2011ዓ.ም | |
| 17 | አባ ሶሪ አባ ጆቢር | ወ | 90 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ኦያ ኤረቶ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 03/08/2011ዓ.ም | |
| 18 | አቶ ወልዴ ሸኢ | ወ | 70 | ፊደል | አርሶ አደር | መለካ | የየም ብሄረሰብ | 03/08/2011ዓ.ም. | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ያልቆጠሩ | | ቀበሌ | የለቅሶ ስርዓት | | |
| 19 | ሀብታሙ ዘውዴ | ወ | 44 | ድግሪ | የመንግስት | አዝጊ ዘምዳ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 10/08/2011 | |
| 20 | ፍቃዱ ወ/መስቀል | ወ | 49 | 10ኛ | አርሶ አደር | ኢዲያ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 10/08/2011 | |
| 21 | ኪዳኔ ከበደ | ወ | 40 | ድግሪ | የመንግስት | ሳጃ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 10/08/2011 | |
| 22 | ምስጋና ከበደ | ወ | 30 | ድግሪ | የመንግስት | ኢዲያ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 10/08/2011 | |
| 2 | ወ/ሮ አለሚቱ ኩምሳ | ሴ | 80 | ፊደል ያልቆጠሩ | አርሶ አደር | ደሪ ወንጋቾ | የየም ብሄረሰብ የለቅሶ ስርዓት | 22/08/2011 | |
| | | | | | | | | | |

**አባሪ ሁለት፡-** በቃለ-መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉ መነሻ ጥያቄዎች፡፡

ቃለ-መጠይቁ የተደረገበት ቀን-------------------------------------

የተካሄደበት ቦታ----------------------------------------

የተጀመረበት ሰዓት-------------------------------------

የቃለ-መጠይቁ ሰጪ አጠቃላይ መረጃ፡-

ስም -----------------------------------------

ፆታ -----------------------------------------

ዕድሜ----------------------------------------

የትምህርት ደረጃ----------------------------

ስራ--------------------------------------------

በአካባቢው ቆይታ ጊዜ--------------------------

የትዳር ሁኔታ -------------------------------

የየምን ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ ለማጥናት የተዘጋጀ የቃለ መጠይቅ መነሻ ጥያቄዎች፡-

1. የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ምን ይመስላል?
2. በየም ብሄረሰብ ዘንድ ስለሞት ምን የሚባል ነገር አለ?
3. በየም አስተሳሰብ ሰው ከሞተ በኋላ ዕጣ ፈንታው ምንድነው
4. የአስክሬን ግነዛ ስርዓቱና የቀብር አፈጻጸሙ ምን ይመስላል?
5. በየም ብሔረሰብ ዘንድ ሰው ሲሞት ሀዘን የሚገለጸው እንዴት ነው?
6. ከጨቅላ ህጻን እስከ ሽማግሌ ድረስ ለሚከሰት ሞት የሚፈጸመው የለቅሶ ስርዓት ምን ይመስላልል?
7. ሰው ሊሞት መሆኑን እንዴት ይታወቃል?
8. ሰው ሲሞት ለወዳጅ ዘመድ መልዕክት የሚደርሰው በምን መንገድ ነው?
9. በቀብሩ ዕለት ያልደረሰ ወዳጅ ዘመድ ሀዘኑን የሚገልጸው በምን መልኩ ነው?
10. ሰው ከሞተ በኋላ ምን ምን ተግባራት ተከናውነው ነው ለቅሶ የሚጀመረው?

11. የለቅሶ ስርዓቱ ምን ያህል ጊዜ ይቆያል? ምን ምን ተግባራት ይከወናሉ?

12. አስክሬን ወደ ቀብር እስኪወሰድ ድረስ በምን መልኩ ይቆያል?

13. አስክሬን የሚገንዘው ማን ነው? ለምን?

14. የቀብር ቦታ እንዴት ይመረጣል?

15. አስክሬኑን ወደ መቃብር ቦታ የሚወሰደው በምን መለኩ ነው?

16. አስክሬን ወደ መቃብር የሚወሰድበት የተለየ ሰዓት አለው? ለምን?

17. ለእያንዳንዱ የለቅሶ ስርዓት ምን ምን ዝግጂቶች ይከናወናሉ? ምክንያታቸውስ?

18. ማን ሲሞት ምን ዓይነት የለቅሶ መጠን ይኖራል? ለምን? ምን ምን እየተባለ ይለቀሳል?

19. ሐዘን የማይበዛው በየትኛው የእድሜ ክልል ውስጥ ያለ ሰው ሲሞት ነው? ለምን?

20. ዚዛ የሚከወነው ማን ሲሞት ነው?

21.የዚዛ ክወና እንዴት ይካሄዳል?

21. ከቀብር በኋላ ሀዘን እስከ ስንት ቀን ይቆያል? ምን ምን ክንውኖች ይፈጸማሉ?

22. ባጠቃላይ የየም ብሄረሰብ የለቅሶና ዚዛ ስርዓት ያለበት ሁኔታ ምን ይመስላል?

23. መጠየቅ ነበረብህ ብለው የሚያስቡት ሌላ ጥያቄ ካለ ቢገልጹልኝ?

24.በአንድ ቤት ለቅሶ ቢከሰት ለለቅሶው የሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች ምን ምንድናቸው?

25. ለቅሶ ስለመከሰቱ ለዘመድ መልዕክት አድራሽ በምን መልኩ ነው የሚላከው

26. ምን ዓይነት ሰው ነው ? ምን ዓይነት ሰው ነው የሚመረጠው?

27.በየም ብሄረሰብ ባህል በአንድ አካባቢ ሞት ሲከሰት የአካባቢው ማህበረሰብ /ጎረቤት/ የሚያከናውኑት የስራ ድርሻ ምን ምንድነው?

28. በየም ብሄረሰብ ታዳጊ ህጻናትና ወጣቶች፣ጀግኖች፣ንጉስና የንጉስ እንዲሁም ማንኛውም ሽማግሌ ሲሞት ምን ምን እየተባለ ነው የሚለቀሰው?

29.በወንዶች የቴሻ ስርዓት ስንት ጊዜ ነው ሄድ መለስ ተብሎ የሚወደቀው? ምክንያቱ ምንድነው?

30.በየም ብሄረሰብ ፈረስ በለቅሶ ስርዓት ላይ ይቀርባል ወይ በምን ዓይነት ለቅሶ?

31.ስንት ዓይነት የካብጉኒ ማማ(ቡሉኮ) ዓይነቶች አሉ? ለማን ምን ዓይነት ቡሉኮ ይገነዛል?

32.ለሴት ልጆች ተቆርጦ የሚሰጠው ካሮ(የከፈን ቁራጭ) መጠኑ ምን ያህል ነው?እስከ መቼ ነው የሚለበሰው? ካሮ ዬት ዬት ይለበሳል?

33.ዚዛው የሚጀመረው በምን መልኩ ነው?

34.ለዚዛው የሚቀርበው ቀንድ ከዬት ነው የሚመጣው?

35.ቀንድ ባይኖር ዚዛ የሚከወነው በምን መልኩ ነው?

36.አንድ ሰው ብቻውን ቴሻ ለማካሄድ አስቀድሞ ምን ምን መልመድ አለበት?

37.በዚዛው የሴቶች ብቻ እንዲሁም የወንዶች ብቻ ተግባራት ምን ምንድናቸው?

38.ወንድ ልጅ ባይኖር የአባት ቤት የሚወርሰው ማን ነው?

39.በየም ብሄረሰብ ባህል መሰረት የመቃብር ጥልቀትና ስፋት ምን ያህል ነው? ወዴት አቅጣጫ ነው የሚቀበረው? ለምን?

40.በድሮ ጊዜ አስክሬን የሚቀብሩት ቤራዎች የሆኑበት ምክንያት ምንድነው?

41.ቤራዎች አስክሬኑን ከገነዙ በኋላ በምን መልኩ ነው ወደ መቃብር የሚወስዱት?

42.ስንት ዓይነት የዚዛ ስርዓት  አለ? ምን ምንድናቸው ?

## አባሪ ሶስት፡-ከቁልፍ መረጃ አቀባዮች ጥቂቶቹ











# አባሪ አራት፡- የቴሻ (ለቅሶ) ግጥሞች

| በመገኛ ቋንቋ | የማርኛ አቻው |
|---|---|
| ዌውዋ ቴጋና ኬስዋ | አንተ እገሌ ልጥራህና ውጣ |
| ካቡዋ ፣ካቡዋ… | ተነስልኝ፣ተነስልኝ.. |
| ጉዳማዋ፣አራማዋ፣ካሳማዋ.. | ጉዳማሳ፣አራማሳ፣ካሳማሳ(የደረባ ስሞች) |
| ካቡዋ ካቢን አምኒዋ | እባክህ ተነስና እንሂድ |
| ያንዋ ካቢን አምኒዋ | መጥቻለሁ ተነስና እንሂድ |
| ጉዙዋ አፋዕቴቶሶ? | ንቃ እንጂ አንቀላፍተሀል ወይ? |
| አዞዞ አኔ ግዕተፌዋ አቴሶ | ሌላ ቀን አታኮርፍም ነበር ምን ሆነሀል |
| አቴሶ ካቡዋ | ምነካህ ተነስ እንጂ |
| ካሳዬፋን ማኮንዋ | ቀና በልና ልንገርህ |
| ኬሳ ኡጳዋ አፌኖሶ ? | ውጣና ላግኝህ የለህም ወይ? |

## 2.ሟች ጀግናና የዕድሜ ባለጸጋ ከሆነ

| | |
|---|---|
| ኦይ አባኒሶ ቤዚሶ | ወይኔ አባታችን ጀግናችን |
| ገዴውኒሶ ካሹምኒሶ | ወይኔ ዝግባችን ዋርካችን |
| ዎላባሶ ኬጹኒኛ | ኬላዎችን ይቆጣጠሩልን |
| ሽምርዋ ሽምርዋ | ሽምር ነው ሽምር ነው(የቦታ ስም)፡፡ |

3.ሟች በተለያዩ ጦርነቶች ተሳታፊ ከሆነ

| በመገኛ ቋንቋ | በአማሪኛ |
|---|---|
| አውኔዋ፣ አውነዋ፣አውኔዋ | ወይኔ፣ወይኔ፣ወይኔ |
| አምባንሶ አግሪ አማባንሶ ኡጬሪ | ምን ሆነህል፣ምን አገኘህ |
| አኙን ኔቦክ አምኒዋ | ና ለውጊያ እንሂድ |
| ካማድርኖን፣አደድርኖን፣ዲፐሳኖን | ካማድርኖን፣አደድርኖ፣ዲፐሳኖን(የቦታ ስም) |
| ካቢን አምኒዋ ካምቤልዋ | ተነሳና እንሂድ ካምቤል(የቦታ ስም) ነው |
| አውኔዋ ዞሞታሶ ቴጋና ከስዋ | ወይኔ ጓደኛዬ ልጥራህና ውጣ |
| አኙን አምኒዋ ኦታና አማናሶ | ናና እንሂድ ከማን ጋር ልሂድ |
| ጋቹኔ ኦቸፒፋንዋ | በሬዎችህ ይዳከሙ |
| ዞሞኔ ፒፋዎዋ | ጓደኞችህ ይዳካሙ |
| ቤዝኒሶ ያዲዋ፣ያዲዋ | ጀግናችን ያዲ ነው፣ያዲ ነው(የቦታ ስም) |
| ዲፐሳዋ፣ካምቤልዋ | ዲፐሳ ነው፣ካምቤል ነው (የቦታ ስሞች) |
| ካቡዋ፣ካቡዋ፣ኦፒቶሶ | እረ ተነስ፣ እረ ተነስ ደከመህ ወይ |
| ካቡዋ፣ኦፒቶሶ ዞሞታሶ | ተነስ እንጂ ጓደኛዬ ደክሞህል ወይ |
| ዞሞኔሳ ኀዳ ኦፒፋንዋ | የጓደኛህ አቅም ይዳከም |
| ዞሞኔሳ ታላ ካተፋንዋ | የጓደኛህ ቋንጃ ይቆረጥና |
| የረፋይዋ ካቡዋ | አይዞህ ተነስ እንጂ |

| | |
|---|---|
| ዛጳሶ ዎልጉዋ፣ዛጳኔሶ ኦጳ ያንዋ | ጦርህን መልስ፣ጦርህን ይገፎ መጥታቻለሁ |
| ዛጳኔሶ ኦጳ ያዲፋንዋ | ጦርህን ይገፎ እየመጣሁ ነው፡፡ |
| አኔ ካሰፊ፣ ዛጳሶ ኦጳ ያድፋንዋ ዎልጉዋ | አብረን የምንጫወተውን ጦር ይገፎ መጥቻለሁ |
| ኬሳ አን ኔቦሲ ዎልጉዋ | ወጥተህ ይሄን ጦር መልስ |
| ዛጳሶ ዎልጉዋ | ዘንጉን መልስ ፡፡ |

## 4.ሚች በመልካምነቱ የሚታወቅ ትልቅ ሰው ከሆነ፡-

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አውኔን ኒኔን ኮኢኛ | ከዛሬ ጀምሮ ሁሉም ነገር በእርሶ አበቃ |
| አቤንዮይ፣አቤንዮይ | ምን እናድርግ ምን እናድርግ |
| ዙታሾኖ፣ዙቲቦኖ አቤኒዮይ | ሰብሳቢ አለቃችን፣ሰብሳቢያችን ምን ይሻለናል |
| አይን አማንሪ፣አይን አማንሪ | የት ነው የምንሄደው የት ነው የምንሄደው |
| አውኔዋ አውጌሻኖ አባኒሶ | ወይኔ ትልቁ ጎሻችን አባታችን |
| ማንጉ ሜያሲን ፉኦኒኛ | ከክፉ ፍላጻ ያድኑኝ |
| ታን ኮሩንኛ | ዋስ ይሁኑኝ |
| ማንጊና ዎኖ ንኪቱ ዮናኛ | ሲካፋኝ እርሶ ጋር ነው የምመጣው |
| ኮርራቱ ፉኦኒኛ | ዋስ ሁነው ነው የሚያድኑኝ |
| ማንግፋን ያናና | ከፍቶኝ  መጥቻለሁ |
| ኬሩክ አፌኒኖይ | ከቤት የሉም ወይ …፡፡ |

## አባሪ  አምስት፡- የዚዛ (ሙሾ) አዝማች ቅኝት  ዓይነቶች

### ቅኝት1. ‹‹አኼያ››

በመገኛ ቋንቋ፡-     አኼያ ዬያ አሂ…አሂ ዬሃ…ዬሃ

በአማርኛ ፡-     አኼያ ዬያ አሂ…አሂ ዬሃ…ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-     ኤኪባሪ…አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-     እነዲህ ቢያደርግ አሂ ዬሃ…ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-     ቴሱናይ አሳኖይ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-     የመጀመሪያም አዲስም አይደለም አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-     ኮችባሪ ካላ ኮችባሪ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-     ይምራ ቀንዱ ይምራ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-     ዞሞባሶ ቡሴዲፌ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-     ጓደኞቹ እየመከሩ ነው አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-     ዞሞባሳ ኀዳ ሻካና አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-     የጓደኛው አቅም ይድከምና አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-     ሚያ ኢሽኮሶን ኡሽባሪ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-     ከብቶች ኢሽኮን ቢጠጡ  አሂ  አሂ  የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡-     ኤቶ ዛዋሶ ቡኚኛ   አሂ ፣አሂ ፣ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡-     አንበሳው ሆራውን አደፈረሰ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ሚያስ ሚኮኒ ማባሪ አሂ ፣አሂ፣ የሃ፣ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ከብቶቹ ከሚኮ ጋር ቢበሉ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ፋዝኒስኔን ዖሊኒዮይ አሂ ፣አሂ ፣ የሃ፣ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ከነፈረስዎ ተመለሱ ወይ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ዖልግሬ ዖሊዮይ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- መልሰው ከበብዎት ወይ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ሚያ ኮቹና ፋዛ ኮቹና አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ከብቶችዎ ይዝለሉ ፈረስዎም ይዝለልአሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ሽምር ኬማ ባዛኖይ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ሽምር ምሽጉ ባዶ ነው ወይ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- አው ጌሻሶቴ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- አውራው ጎሻችን አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- አውራ ጋይማቴ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- አውራና ታላቁ ሰው አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- የጆን ኬማ ባዛኖይ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- የዬጆ ምሽግ ባዶ ነው ወይ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ሚያሶ ዋእያስታ ዋዕባሪ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ከብቶቹን ባቴ ላይ ቢፍቃቸው አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ኤቶኖቴ ሜውኖቴ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- አወይ አንበሳው አወይ ነብሩ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- አካግቴዎይ ቤዚሶቴ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- እንዴት አደረጉ ጀግናው አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- አቤኒዮይ አርዋኒ አርዋሶቴ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ወይኔ አውራው አውራችን አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ኬሞኛ ኬር ጎቶኛ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ያግድና ቤት ያምጣ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ፋዛ ታኞኔ ፌሽባሪ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ፈረሱ እንደተለጎመ ይዋል አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ዞሞባሶ ዋሴዲፌ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ጓደኞቹ እያለቀሱ ነው አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ዎሪ ኪታ ሲባሲክ ዎርፋውና አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ገዳዩ ሞት ባፍጢሙ ይውደቅ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ኤቶኖቴ ሜውኖቴ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- አወይ አንበሳው አወይ ነብሩ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ኦይ ኮሪሬ ኮቶኛ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ወይኔ ዋስ ሁነው ያስፈቱ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ኦይ ቶኔይሶ ቶቶኛ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- ወይኔ የሚወስዱትን ይውሰዱ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በመገኛ ቋንቋ፡- ሳማኖቴ አጢኖቴ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

በአማርኛ ፡- አቶ ሳማኖ፣አቶ አጢኖ አሂ አሂ የሃ ዬሃ

| | |
|---|---|
| በመገኛ ቋንቋ፡- | ገዴውኒ አባኖ ኦሮምኒ አባኖ አሂ አሂ የሃ ዬሃ |
| በአማርኛ ፡- | የዝግባው አባት የኦሮማው አባት አሂ አሂ የሃ ዬሃ |
| በመገኛ ቋንቋ፡- | አውማኬኒ ቤዚሶቴ አሂ አሂ የሃ ዬሃ |
| በአማርኛ ፡- | አወይ ጀግናችን ምናልን አሂ አሂ የሃ ዬሃ |

**ቅኝት 2. አርፋኝሳ /ሚያ/**

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አውራጅ፡- ዎሪፋ ኪታሴ ጋውኔ | ገዳዩ ኪታ በየገደሉ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ቤዛ ቤትዋ ቤዚሶ | ገድለህ ተሰደድ አንተ ጀግና |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡-ዌውኖ ፋዛ ታኞኔ | የአቶ እገሌ ፈረስ እንደተለጎመ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡-ዛዋሲ አባኒ ዎናፊወ ኦጲ | የሆራውን ጌታ መብረቅ መታው |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ካሲ አውኒክ ፋሲሬ | ለወፍ አውራ አስመርምሮ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ኮናኪ ማናሶ ሚሲሬ | የኮናን ሸክላ ሰብሮ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ካሹምኒ ማከቶ ዋሪሬ | እንደዋርካ ሰፍቶ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |

| | |
|---|---|
| አውራጅ፡- ዱማሲ ማቶ ዱዲሬ | እንደ ድኩላ በርትቶ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ካሞባሴ….. | ሴት ዘመዶቹ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አፐኩሎኒ እሜ ካሞባ | ጬኸት አሰሙኝ ዘመዶቹ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ኤቶሳ ማቶ ቡሪሬ | እንደ አንበሳ የሚያገሳ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- የሬ ዞባሳ ዛጳናዌ | የቆሙ ገንደኞቹን የጦር ዘንግ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አርዋ ፋዛሲ አርዋናኛ | አውራው ፈረስ በአውራነቱ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ሼሼና ሼሾዬ | አስፈሪው ሼሾ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ቴጋ ኬባስታ ጌያሶ | ከፍ ባለው ቤቱ ላይ እሳቱን |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ቴጋ ኬባስታ ናፍቶሶ | ከፍ ባለው ቤቱ ላይ ፈንጂውን |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ሜውሳ ማቶ ባከሬ | እንደነብር ጭሮ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |

| | |
|---|---|
| አውራጅ፡- ጌሻሳ ማከቶ ካበሬ | እንደጎሽ ታግሎ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ዬክትኒ ፋዛ ታኞኔ | የዬክቶዎች ፈረስ እንደተለጎመ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- -ሼሾኪ ማናሶ ሜሲሬ | የሼሾን ሽክላ ሰብሮ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ኮናኪ ማናሶ ሜሲሬ | የኮናውን ሽክላ ሰብሮ |
| ተቀባይ፡-ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- በድኒ ሀኦኒን ፋድሲሬ | የአመድ አምላክን አስመርምሮ |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ኬስባውኒ ጌሪባ | ከፍ ብሎ ይሰማ ሸለላው |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ኪኡኒ ሀኦኒ ፋድሲሬ | የቁጫጭን አምላክ አስጠይቆ |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ኩሎኒ ሀኦኒ ፋድሲሬ | የግብረ ጉንዳንን አምላክ ስጠይቆ |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አቤኒዮይ ቤዝኒሶ | ወይኔ ለግናችን |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ቤዛ ቤትዋ ቤዚሶ | ጀግነ ተሰደድ ጀግናው |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |

| | | |
|---|---|---|
| አውራጅ፡- | አቤኒዮይ ጋይማኖ | ወይኔ ትልቁ ሰው |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- | ጋይማናዋ ካሽምኔ | ትልቅ ሰውና ዋርካ |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- | አፕኩሌሮሶ ፍዞኛ | አይጮሁም እኮ ፍየል ናቸው |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- | ጌብኒን መሬ ጌሻና | ጋሻን ያሸነፈ ጎሽ ነው |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- | ኪታሲ አፋኖ ጋሮና | የኪታውን(የገዳዩን) ዓይን ቆንጥር |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- | ሜው ካሞቴና ካሞዌ | ነብር የጮኸው ጩኸት ነው |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- | ኤቶ ካሞቴና ካሞዌ | የአንበሳ ግሳት ነው |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- | አቴድ አማይሶን ሻዋክዌ | አምልጦ የሄደውን በመሞቻ ስፍራው |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- | ኬስባራምሴ ጌራርባ | ሽለላው ድምጹቱ |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- | ና ሴሉዌ ሴላባ | ልጁ ኃይለኛ ነው ሴለባው |
| ተቀባይ፡- | ዬሃሃ | ዬሃሃ |

| | |
|---|---|
| አውራጅ፡- አውኔዋ ጋይማኖ | አወይ ትልቁ ሰው |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አውኔዋ ኤቶኖ | አወይ አንበሳው ሰው |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አውዛኖኔ ፋውዛ | አቶ እገሌን የሚመስል ነገር |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አፐኩሎዌ ካሞባ | ጩሁ እንጂ ካሞዎቹቹ |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ካሻሲ ማቶ ካነሬ | እንደዋርካ የሚገነደስ |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ዎጃሲ ማቶ ዎሊሬ | እንደጭልፊት ዘምቶ |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አፐኩሎዌ ሶሳሴ | ጩሁ እንጂ ካሞዎቹ |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አውኔዋ ኔቦኖ | አወይ ጦረኞችን |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አውኔዋ ጋይማኖ | አወይ ትልቁ ሰው |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውጪ፡-ኮኡሲ ማሲሬ ድችይሶ | አይጦችን መግቦ አሳዳጊ |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |

| | |
|---|---|
| አውራጅ፡- ካሳሶ ማሲሬ ዲችሶ | ወፎችን መግቦ አሳዳጊ |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- ቡሩሶ ቱግሬ ኤክሲይሶ | ጫካውን ገፍቶ ያስጠጋው ጀግናችን |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |
| አውራጅ፡- አውኔዋ ቤዚሶ | አወይ ጀግናችን |
| ተቀባይ፡- ዬሃሃ | ዬሃሃ |

**ቅኝት 3. አሴ፡-**

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| ከጀሬ ከስናይሶ ጌያ ኮእሳው | አድኖ የወጣውን እሳት ይፍጀው |
| ነበሬ ከስናይሶ ጌያ ኮእሳው | ተዋግቶ የወጣውን |
| ቴጋ ኬንቲሶ ጌያ ኮእሳው | ከፍ ያለ ቤትዎን |
| ፈሽቴ ገሮሶ ጌያ ኮእሳው | መዋያ ቦታዎን እሳት |
| ሳሳካዎኖን ጌያ ኮእሳው | ማዘውተሪያዎን |
| ተሬ ከስናይሶ ዎጃ ኮእሳው | ተቀብሎ የወጣውን ጭልፊት ይፍጀው |
| ባነሬ ከስናይሶ ዎጃ ኮእሳው | ተካፍሎ የወጣውን ጭልፊት ይፍጀው |
| ታጋ ኬባስታ ጌያ ኮእሳው | ሰፊ ቤቱን እሳት ይፍጀው |
| ኤተና ዳባሶን ጌያ ኮእሳው | የውጊያ ሜዳው እሳት ይፍጀው |
| ከጀሬ ከስቴይሶ ጌያ ኮእሳው | ወግተው የወጡትን እሳት ይፍጀው |
| ታጋ ፊታሮ ጌያ ኮእሳው | ሰፊውን ፊታር እሳት ይፍጀው |

| | |
|---|---|
| ታጋ ዋቤዎ ጌያ ኮእሳው | ሰፊውን ዋቤ እሳት ይፍጀው |
| ዎላጎዎ ጌያ ኮእሳው | ዎላጎን እሳት ይፍጀው |
| ኤትኒ ፋዝንቲሶ ጌያ ኮእሳው | የውጊያ ፈረስዎን እሳት ይፍጀው |
| ታሬራ ከስቲ ገብንቲሶ ጌያ ኮእሳው | አንግበው የወጡትን ጋሻ እሳት ይፍጀው |
| ዎላጎ ከማሶ ጌያስ ኮእሳው | የወላጎን ምሽግ እሳት ይፍጀው |
| ኤዞ ከማሶን ጌያስ ኮእሳው | የኤዞን ምሽግ እሳት ይፍጀው |
| ጋርኪ ቱናሶን ጌያስ ኮእሳው | የጋርን ምሽግ እሳት ይፍጀው |

### ቅኝት 4. አውማኬኒ

| | በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|---|
| አውራጅ፡- | ኤቶኖቴ ሜውኖቴ | አቶ አንበሳው አቶ ነብሮ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ቴሱናይ አሳኖይ | ጅማሬም አዲስም አይደለም |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ፋዛ ታኞኔ ፌሽባሪ | ፈረስዎ እንደተለጎመ ይዋል |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ኤኪዮይ ኤኪዮይ | ወይኔ እንዲህ አደረገዎት ወይ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ሶሞባሶ ዋሴድፌ | ጓደኖቹ እያለቀሱ ነው |
| ተቀባይ- | አማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ዞሞባሳ ከእሲዋ | በጓደኞቹ ጉልበት ስር |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ሲባሲክ ዎርፋዎኛ | በአፍጢሙ ይውደቅ |

| | | |
|---|---|---|
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ዎሪ ኪታ ሲባሲክ ዎርፉዎኛ | ገዳዩ ኬታ ባፍጠሙ ይውደቅ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ኤቶኖቴ ሜወኖቴ | አንበሳውና ነብሩ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | አይ ኮሪፌ ኮቶኛ | ወይኔ ዋስ ሆነው ያስፈቱ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | አይ ቶኔይሶ ቶቶኛ | ወይኔ የሚወስዱትን ይውሰዱ |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | አይ አኔንትሮ በይቶኛ | የወደፊቱን ይተው |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ኤቶ ዛዋሶ ቡኚኛ | አንበሳው ሆራውን አደፍርሷል |
| ተቀባይ- | አውማኬኒ | ምን እንበል |
| አውራጅ፡- | ዞሞባሳ ጎዳ ሻኪኛ | የጓደኞቹ ጉልበት ደክሟል |

## ቅኝት 5. ማግኖቲና ማግኖ

| በመገኛ ቋንቋ | | በአማርኛ |
|---|---|---|
| አውራጅ፡- | ማግኖቲና ማግኖ | ማግኖ ብዙ ናቸው ማግኖ |
| ተቀባይ- | ማግኖቲና ማግኖ | ማግኖ ብዙ ናቸው ማግኖ |
| አውራጅ፡- | ቲር አውኖቴ ማግኖቴ | የብዙዎች መሪ ማግኖ |
| ተቀባይ- | ማግኖቲና ማግኖ | ማግኖ ብዙ ናቸው ማግኖ |
| አውራጅ፡- | አውኒ አውኖቴ ማግኖ | የትልልቆቹ አውራ ማግኖ |
| ተቀባይ- | ማግኖቲና ማግኖ | ማግኖ ብዙ ናቸው ማግኖ |

## ቅኝት 6. ጋኛኖቲኛ

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አዝማች፡- ጋኛኖቲኛ | ጋኛኖቲኛ |
| ስንኝ፡- አውኔን ጋኛንቲ ኬሲኛ | ከዛሬ ጀምሮ ስልጣንዎ ቀርቷል |
| አዝማች፡ ጋኛኖቲኛ | ጋኛኖቲኛ |
| ስንኝ፡-ሚያ እጉኖይ ጌልሙስ ኡሽባሪ | ከብቶች ያለስጋት ወንዙን ይጠጣሉ |
| አዝማች፡ጋኛኖቲኛ | ኛኖቲኛ |
| ስንኝ፡- አውኔን ጋኛንቲ ከሲኛ | ከዛሬ ጀምሮ ስልጣንዎ ወጥቷል |
| አዝማች፡ ጋኛኖቲኛ | ጋኛኖቲኛ |

## ቅኝት ሰባት.ዳምኖቲና ዳምኖ ፡-

| በመገኛ ቋንቋ | በአማርኛ |
|---|---|
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |
| አውራጅ፡-ኤኪዮ ዳምታሮ | እንዲህ አደረገዎት ወይ ጌታዬ |
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |
| አውራጅ፡-አይ ኤካኖይ ዳምታሮ | ወይኔ እንዲህ ነው ወይ ጌታዬ |
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |
| አውራጅ፡-ኤቶ ዛዋሶ ቡኚኛ ዳምታሮ | አንበሳው ሆራው አደፈረሰው ጌታዬ |
| አውራጅ፡-ዳምታሮ ዳምታኛ | ጌታዬ ጌታዬ |
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |
| አውራጅ፡-አይ ፋዛ ታኞኔ ፌሽባሪ | ፈረሱ እንደተለጎመ ይዋል |
| አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ | አዝማች፡ ዳምኖቲና ዳምኖ |

## ቅኝት 8. ማኖቲና ማኖ፡-

ለሴቶች ብቻ የሚከወን ነው፡፡ በጾታ ልዩነት ምክንያት የአዝማቹ ቃልና ዜማው ተለየ እንጂ ከቅኝት 7. ጋር ተመሳሳይ የዚዛ ክወና ምት ያለው ነው፡፡

# አባሪ ስድስት፡- የትብብር ደብዳቤዎችና የጥናቱ አካባቢ ካርታ

ቁጥር፡ኢ/ቋ/ሥ/ጽ/አማ/66/11

Ref.No.

ቀን፡ 16/05/2011 ዓ.ም.

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም (IES) ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት

አዲስ አበባ

**ጉዳዩ፡- ትብብር ስለመጠየቅ ይመለከታል**

መ/ር **ደመቀ ጀንበሬ** በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል መደበኛ ድኅረ ምረቃ ዕጩ ተመራቂ ተማሪ ሲሆን፣" **የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ሙሾ (ዚዛ) ስርዓት ክወና ትንተና"** በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሁፍ ለመስራት መረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም መ/ር **ደመቀ ጀንበሬ** ከጥናታዊ ጽሁፉ ጋር በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ በቤተመጻህፍታችሁ እንዲገለገል መልካም ፈቃዳችሁን እየጠየቅን፣ ለሚደረግለት ትብብርም ምስጋናችን ላቅ ያለ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

ጅማ ዩኒቨርሲቲ
Department of Amharic

ከሰላምታ ጋር

አማ/ኛ ትምህርት ክፍል ኃላፊ

Tel + 251 0471120534

JIMMA UNIVERSITY
ጅማ ዩኒቨርሲቲ
We are in the Community

ቁጥር፡ኢ/ቋ/ሥ/ጽ/አማ/67/11

Ref.No.

ቀን፡16/05/2011 ዓ.ም.

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም (ILS) ቤተ መጻሕፍት አገልግሎት

<u>አዲስ አበባ</u>

**ጉዳዩ፡- <u>ትብብር ስለመጠየቅ ይመለከታል</u>**

መ/ር **ደመቀ ጀንበሬ** በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል መደበኛ ድኅረ ምረቃ ዕጩ ተመራቂ ተማሪ ሲሆን፣" **<u>የየም ብሔረሰብ የለቅሶ ሙሾ (ዚዛ) ስርዓት ክወና ትንተና</u>"** በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሁፍ ለመስራት መረጃዎችን በማሰባሰብ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም መ/ር **ደመቀ ጀንበሬ** ከጥናታዊ ጽሁፉ ጋር በተያያዘ መረጃ ለመሰብሰብ በቤተመጻህፍታችሁ እንዲገለገል መልካም ፈቃዳችሁን እየጠየቅን፤ ለሚደረግለት ትብብርም ምስጋናችን ላቅ ያለ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

ጅማ ዩኒቨርሲቲ
አማርኛ ትምህርት ክፍል
Department of Amharic
University

ከሰላምታ ጋር

ሁብታሙ እንግዳው
አማረኛ ትምህርት ክፍል ኃላፊ

Tel + 251 0471120534

... Woreda
...ulture Tourism and Sport Office

ቁጥር [illegible]

ቀን 24/7/2011

ለየም ልዩ ወረዳ [illegible] ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት

**ጉዳዩ:- ትብብርን ይመለከታል**


ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረዉ አቶ ደመቀ ጀንበሬ በየም ብሔረሰብ የልቅሶ ሥርዓት ክዋና ላይ ጥናት እያደረጉ እንደሆነ ከጂማ ዩኒቨርሲቲ በቀን 16/05/2011 ዓ/ም በቁጥር ኢ/ቋ/ሥ/ጽ/አማ/68/11 በተጻፈ ደብዳቤ መሠረት ትብብር እንዲናደርግ ጠይቀዋል፡፡በመሆኑም በቀበሌዉ በሚያደርጉት የሥራ እንቅስቃሴ አስፈላጊዉን ትብብር እንዲታደርጉ እንገልጻለን፡፡

YEM SPECIAL WOREDA CULTURE TOURISM AND SPORT OFFICE

// ከሠላምታ ጋር//

ተካልኝ ኃይሉ ጃላ
Tekalign Hailu Jalla
የየም ልዩ ወረዳ ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ጽ/ቤት ኃላፊ


yem Special Woreda Map
KONER
OROMIYA Region
SOKORU Woreda
ASHE
SAJA LAFITEN
SAJA TOWN
TIGIR
Guraghe Zone
DERI TEGU
DERI KEPHO
JIMMA To Addis
Abeba Road
SAE MAFO
ASHER
OYA KEPHO
WENIGECHO
OYA ERETO
OROMIYA Region
GESI
EDIYA
OYA DEN
KEREWA
NUBA
GORUMINA HANIGERI
AZIGI ZEMIDA
FOFA TOWN
KESHELI
KESHELU
HAdiya Zone
SHEMONA METELO
MELEKA
BORI DEN
SHOSHERINA ALIMAMA
SOMU AWASHO
SHOSHO
KERIZIDOYO
EZO ZETA
WEGERO AZEGN
KELECHI
WEYURA KULAZE
FAIYA
Legend
JIMMA To Addis
Abeba Road
SAJA To Fola &
Fola To Toba Road
Fola To Gilgele
Gibe No 2 Road
SORUGUN
Scale
6000
0
6000
12000


THE Geographical Location Of
Yem special Wereda in SNNPRS
ETHIOPIA
N
Oromia
Hadiya
1:400 000
Legend
Town.
Earth Truck
Boundaries.
Regional boundary
Zonal boundary
woreda boundary
Road's Types
Asphalt
All weather
Dry weather
Peasant Association